



# ሌቱም አይነጋልኝ

ከስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

Meysor Bro
t.me/BooksandYou

©መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።
©All Rights Reserved.

የመጀመሪያ እትም (ፎርማት የተደረገበት) 1993
ሁለተኛ " (እንደመረያ) 1999 ሚያዝያ
ሦስተኛ " 1999 ሰኔ

አሳታሚ - ቃልኪዳን ታደሰ
የውስጥ ዲዛይን የገጽ ቅንብር - ሌትሮንስ ፕሮሰሲንግ
ከቨር ዲዛይን - ሄኖክ ማሞ
letumrep02@yahoo.com
P.O.Box - 17125

# ምስጋና

- እንደ ሸማኔ መወርወሪያ በፍጥነት እየተረረሙ ከአንድ ሰው በላይ አስተዋፅኦ ላበረከተው ለሄኖክ ማሞ
- ብዙ ላበረታታኝና ለረዳኝ ለአጋዤ ከሆነው ከፍሬ
- ለኢማኑኤል ግርማ ወንድሙ ፈለቀ፣ ሁሉና ወዳጄ
- የገፁ ቅንብሩንና ትየባውን በትጋት ለሠራችልን ለምስጋወርቅ ወርቁ
- ለሁሉም ሐሳቢ ጓደኞ ምክርንና

  እንዲሁም
- እያወቁና ሳያውቁ
- እየፈለጉና እያልፈለጉ
- እያወቅናቸውና እያላወቅናቸው

  ይህ መጽሐፍ እንዲሳካልን ዘንድ

  ይደርስ ዘንድ

  አስተዋፅኦ ዘንድ ላደረጉ
- አጣፊንታቸው ሳይመናቀዱ አስተዋፅኦ ላያደርጉ ቢቀሩም ሊያደርጉ ፈቃደኛ ለመሆን ይችሉ ለነበሩ
- ከዚህ በተጨማሪም

  ወዳጆቻችን ከኛ ጋር ይደሰቱ ዘንድ

  ጠላቶቻችን ከኛ ርቀው ይበሳጩልን ዘንድ!

እነሆ
ገበ በረከት
ከቃላት በስግነት ባሰፉ ነቱ ዜገኙ!

ይህ መጽሐፍ ዕድሜያቸው ከ17 ዓመት
በታች ለሆኑ ሕጻናት የተከለከለ ነው

ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሀዱ አምላክ አሜን

ይህ መፅሐፍ ታሪካዊ ልቦለድ ሳይሆን፣ እውነታዊ ልቦለድ ነው። ከዛሬ አርባ ሁለት አመት በፊት ("ጊዜው እንደሄደ ይሮጣል እንጂ አይቆምም!") በሀይ-ስኩል ትምህርትና ሀገ-ሰርኮት አመቴ ውብ በርሀ ከታዘብኩት፣ እየተደሰትኩኝ እየተገረምኩ፣ ያየሁትንና የሰማሁትን በተከታታይ ደብተር ውስጥ መዘገብኩት።

ያለመታደል፣ በዚያ ጊዜ ሳገኝ አስፈቅጄ የሚል ነበር። የተለያዩ እንቅፋቶች ውብ ሊቃናው ሆነና በየጊዜው ለማሳር- ቼኝ ለረጅም አገር ተመሰደኩ።

እዚህ በቀር ገንዘብና ጊዜ ሳገኝ ያደረግኩትን እውነታ እንደ ወረደ ፃፍኩት። የሰዎቹን ስምና መልክ ለውጬ፣ ሲኖሩት እንደሚያውቃቸው (ሚስጥም ምንጭም ሳይ- ለውጥ) ታሪካቸውን አስቀርኩት

ለቅርብ ወዳጆቼ አነብላቸው፣ እንደዚያ ስንቅ ነበሩ ለጥንቃቄ ባታዩሩው ኖሮ፣ ደግ የምትታትን መፍቶ በቀረ ነበር። ሰንደ አበበ መስጠት ምክርና ሲደንቁት ነው — ደጆች ያስጉኙ!

እኔ ና ያደረብኝ ለዘመናቱ ለዝብ ዛር በበቂ ደረጃና "ትርና ሰጤት" እያመለሸከሸ ለሳቢያቸን ጽፌው፣ እኛም ለተቶም አሌተቶም ደጅታ አስቀርቼም።

ሲታተም ምስ ግልፅ ግን አልቀረም፣ ከታተመ በኋላ በልጆች ዘመን ሊሆናል። ያ ጊዜ ሲደርስ ደግ ታሪኩ ሀቀኛ የሰው ልጆች መከረኛ ህይወት ዘገባ ለሌሎች እየዳረኝ እንዳያስታዉ ያስደስታል

# ምስራፍ ስንድ

# ሰቆቃው ምናሴ
## እሀዱ
## «ተይ'ኮ ተይ'ኮ»

መማት አለበው ናልኝ
አደናግሙ ናልኝ
ሴቱም አደነጋልኝ።
(ምግርኛ ዘፈን)

በሰው አብ መወለድ መሣገል ትናል ... ቝጥቁ ውስጥ ሰቆቃው ምናሴ ዘበሌረ ውብ በረሀ ዜታዎቱ ገየርጊስ ሰማዕት ... አልተንኘንም በሰድሳ አሙታቸው፤ ወደ ትላንትና ዞረው ተከፍው

ተይ'ኮ ተይ'ኮ ተይ'ኮ ተይ'ኮ
እኔ ሰሙንኛ ቆሬዬ ነኝ 'ኮ
ተይ'ኮ ተይ'ኮ

እያሉ በናፍቆት መሰንቆቸው
መማትንቴን አስተመሰኝ
ሳይተስትሱኝ ምን ቸገረኝ?
ሙብ መማትንቱ ጀደች
እየተንጋፈፈች
ያመማት የጊዜ ወንዝ ወሰፋት
እንግዲህ
ቀስ በቀስ
ሳይታወቀኝ
ግምባሬ እየገፋ
በራዬ እየሰፋ
ሽበቴ እየበዛ
እድሜዬ እየገፋ ሄደ



[illegible]

አልፈልግም እምቢ!
ማርጀት አልፈልግም
መሞት አልፈልግም
እምቢ አልፈልግም
እምቢ! እምቢ! እምቢ!

የወንዞች ወንዝ የሆነው የጊዜ ወንዝ ግን፣ ትፈቅዳለህ ወይ ሳይለኝ ዝም ብሎ ይወስደኛል። በተስታ. . . እያረሳሳ. . . እያንሳፈፈ ይወስደኛል. . . እንዳመጣኝ ይወስደኛል

ወደ ምዕራብ በሃይ
ወደ ምስራቅ ጥላ
አልብሽኝ ብልኮ
ከሞት የሚያጣላ

አምላክ ሆይ፣ የኛን ያቸንጉሊቶችህን ልመና ትሰማለህን? ወይስ ታንቀላፋለህን? ወይስ ወንዙ አንተንም እያንሳፈፈ ይወስድሃልን?. . .

ቆራቢ ነኝ'ኮ
እንዲያው ዝም—ዝም! ዝም—ዝም!
ነይኮ ነይኮ ልበልሽ እንኮኮ
ተይ'ኮ ተይ'ኮ
አትበይኝ እንኮኮ
ተይ'ኮ ተይ'ኮ

ልጅነቴ የልጆች አሊሆይ አላሊሆይ ጠፍቷት
ብትረ ሙሴ
በበረሀ
ከላይ ማና
ከታች ውሀ
ሙሴ ሙሴ
'ያለች ነብሴ
ሙሴ ሙሴ
የት ነህ ሙሴ?

የሙሴ ጀላኪስ ልጅ ሞተ አሉ
ዋይ—ዋይ! ዋይ—ዋይ!
አገሩ ማንም የለበት
አልቦው ላይ አልቦ ተቆልሉበት
ባዶ ላይ ባዶ ተደራርቦበት. . .



ነይኮ ነይኮ ልበልሽ እንኮኮ
ተይኮ ተይኮ አትኩኒ ችኮ
ወደ ምዕራብ በሃይ
ወደ ምስራቅ ጥላ
በመካከላቸው
ተደብቋል እምና

እንማቱሳላ
እንአብርሃም
ጠጡ ሁቲሁላ
እድሜ የሚያረዝም
ምስጢሩን ለማንም
አልተናገሩም
ጠጥተው ዝም ዝም
ሞተው ዝም ዝም

ወደ መስታወት ሮጥኩ
እፊቴ ቆምኩ
ከፍርሃት ጋር ተፋጠጥኩ
ከእብደት ጋር ተዋወቅኩ
በአይኔ መስኮት ገባሁ
ወደ ውስጤ አየሁ
እኔን አጣሁ

ኧረ ነብሴ ው! ብዬ ጮህኩ
ኧረ ነብሴ ው! ብላ ጮኸች

የባዶ ማሚቶ
ኧረ ነብሴ ው!
ኧረ ነብሴ ው!
ነብሴ ው!
ሴ ው!
ሰው!
ውው!
ው!

አባ ቄሱ
ወደ ውስጥዎ እንዳይገቡ
ባዶ ባዶ እንዳይሆኑ

# ክልኤቱ

## «ፀፀት»

Qu'as-tu fait, ô toi, que voilà, pleurant sans césse,
Dis,qu'as-tu fait de ta jeunesse?*

Paul Varlaine

ኀልማሳውም አነበነበ እንዲህ ሲል. . . . አንተ መስታወት ውስጥ ያለኸው ግራኝ ሰውዬ፣ ከድሮ ጀምሬ አይሀለሁ:: ዛሬ ግን በጣም ተለውጠሀል . . ግምባርህን ጊዜ የሚባለው ችኮ ዶሮ ጭሮበታል፣ ፀጉርህን ከድሮ ይበልጥ ሽበት ዘርቶበታል፣ ስትመለከተኝ አይንህ ውስጥ ሀዘን ይታየኛል፣ ሳትህ የእንባ አገር መልስክተኛ ይመስለኛል:: ምን ሆነሀል?

ምናሲ፣ ምናሴ፣ ምን አጠፋሁና ታዝንብኛለህ? ምን ወንጀል ሰራሁና ዳኛ በሌለበት ትከሰኛለህ? ምናሲ፣ ምን በድልኩህና በፊትህ ፈገግታ ታሰትስብኛለህ? ወጣትነትህን አባከንኩብህ?

ወጣትነቴ! እንደምስጥ ውስጥ ውስጡን ይበላኛል:: ያለፈው ጊዜ፣ ጥሎኝ የሄደው ጊዜ፣ የማይመልሰው ጊዜ ይናፍቀኛል::

ወጣትነቱን እንደ አቧራ ንፋስ ውስጥ ለበተነ ሰው ምን ይቅርታ ይደርግለታል? ማንስ ደፍሮ «አይዞህ ግድ የለም» ይለዋል? ወይኔ ወጣትነቴ!

የማውቃቸው ወጣቶች ነበሩ

አንዶቹ፣ ቤተስኪያን ሄዱ፤ ከግዜር ተዛመዱ፤ መንፈሳዊ ሀብትን ዘሩ፤ ሰሙነኛ ሆኑ

ሁለቶቹ፣ በእውቀት ለመበልፀግ፤ ወደፊት ለማደግ፤ ወዳጅ አገር በረሩ ዘመናዊ ሆኑ

ሶስቶቹ፣ በወጣትነቴ እሳት አለምን ሳቃጥላት፤ ብለው ተነስተው እንዳያፍሩ ሰከሩ፣ እንዳይፈሩ ፎከሩ፣ ሽርሙጣ አቅፈው አደሩ

ሌሎቹ፣ ልጃገረድ ከነፈሩ፣ የሰው ሚስት አነጣጠሩ፣ አንድዋን ሳቁ አንድዋን መቱ

የኔ ግን ወጣትነት፣ ዋ! ይኔ ወጣትነት!
በውቢ በረሀ በሽርሙጦች ሰፈር
ወጣቱ ሲንጋጋ እልጋ ላይ ለመስፈር
ሴቶቹን ለማረስ ባንድ ስንዝር ሞፈር
የወንዱ ሀጢአት ባስር ብር ሲሰፈር

*ምን ሰራህበት፣ አንተ ያለማቋረጥ የምታለቅሰው ተናገር፣ በወጣትነትህ ምን ሰራህበት?



በሴትየዋ «እሀ» ሌሊቱ ሲመተር
ከስር ከስር
ቀይ ብር አስር
በውቢ በረሀ በሽርሙጦች መንደር
ውብ ወጣትነቴን እየሁ ስትሻገር
ሳልጠጣ ሳልደንስ
ሽርሙጣ ሳልዳስስ
ቆንጆ ሴት ሳልጠቅስ
ልጃገረድ ሳልልስ
ዘኬ ሳልከሰክስ
አንዴም ሳላስተድስ
አክስፎርድም ሳልደርስ
እንዲሁ እንደ ነገሩ
አለሁ ስሳሴዎች ይመስገኑ
አንቺ የውቢ በረሀ ሴት
የሌሊት ልፋት ቀጋሽን አግኙ
በማለዳው ኩታ ተሸፋፍነሽ
በታኮ ጫማሽ ተራምደሽ
እስክትደርሺ ከመጠጥ ቤትሽ
መንገድሽ ላይ ማን ማንን አገኘሽ?
የወጣትነቴን ጥላዋን እየሽ?
ጭምጭምታዋንስ ሰማሽ?
ኩኩሉ ኅህ ቀደደ
ያጣም ጠላ ያገኘም ወደደ
አንቺ ወጣት የነብር ጣት
በዚያ በማለዳ በዚያ በጧት
ልጅነቴን እንዴም አላየሻት
መንገድ ዳር ስትጫወት?
አንቺ ከቤት ደጃፍ
ተደፍተሽ የምታንጎራጉሪ
እኔንም አስታውሺ
አንቺ ከሞት አፋፍ ተዘቅዝቀሽ 'ምታለቅሺ
ተንሰቅስቀሽ ለኔም ትንሽ እንባ አፍስሺ
እኔ ለራሴ ማልቀስ አልችልምና

## ሰለስቱ

## «ፍልስፍና»

ማልቀስ ስለማፍለቅ መለፍለፍ መፈላሰፍ ልጀምር ነው። አፍህን ዝጋ! ጆሮህን ክፈት እና ስነግርህ ዝም ብለህ ስማኝ።

ትንሽ ቢታሰብበት መብላት እጅግ የሚያሳፍር ተግባር ነው። ቆራ ውረድና አንድ በሬት ያህል አስተውል። በሬውን እንጉሩን ከጠገበው ሲያርዱት፣ ቆዳውን ሲገፉት፣ ብልቱን ሲለያዩት፣ ፈርሱን ሲያስጉሉት ተመልከት። ሆቴል ግባና አይንህን ጨፍነህ ህዝቡ ሲያኝክ፣ አጥንት ሲቆረጥም ስማ። አክ! ምን አይነት መጨማለቅ! ይሄ ሁሉ ያችን የግማት ስልቻ ለመሙላት! ቀበቶህን ባጠበቅክ ቁጥር ፈርስ እንደምትጨፈልቅ አስጠዘብተሃል? ልክ የነሰጉሉትን የበሬውን ፈርስ የሚመስል። ለመሆኑ፣ በሬውን ሲያርዱት በስመአብ ብለው ሲጀምሩ አይገርምህም? እኔ በበኩሌ ይህን በስመአብ ብሎ ማረድ የጀመረው ቀልደኛ ቄስ ነው እላለሁ። ቀልድ ካልሆነ፣ እንዴት የአብን ፍጡር በአብ ስም ትገድለዋለህ?

ማራት መቻስ አንድ ትልቅ ውርደት ነው። አፍንጫህንና አይንህን እንዲሁም ጆሮህን ብትጠይቅ ይህን ያረጋግጡልሃል። ቂጥህን በጠረግክ ቁጥር አይቀፍህም? ምግብ በልቶ አር የሚወልድ ሁሉ እንዴት በእፍረት አይሞትም? ይሄ ሁሉ ሲሆን «አር ሲቀብጥ የንግሳል ይወድቃል» ግን የእስተያየት ጉዳይ ነው። ማለቴ፣ አሩ የእንግሳል የሚወድቀው ሲቀብጥ ነው ወይስ ሲዘንጥ ነው? ሲቀልድ እንደሆንስ? ወይስ ጅምናስቲክ መስራቱ ይሆን? የሆነ ሆኖ፣ አሩን አፍንጫችንን ይዘን እንለፈው

ውብ ወጣትነቴ
ኸት ልጅነቴ.
ከሩቅ እያየችኝ
እየናፈቀችኝ
እንዲህ ስላት ሰማችኝ
 ነይ'ኮ ነይልኝ
 እያልሽ እጥፍ ዘርጋ
 እምጨልኝ ሰዊልኝ
 የአይንሽን እንባ



በይ'ኮ ነይልኝ
ብለሽ እንደምነ
በለሰለስ እንድሪኝ
የጡትሽን እቦባ
ተይ'ኮ ተይልኝ
መሸበት ወደቁ
ገና'ለጠገበኩትም
የዛለትሽን ጡቱ
እንግቱባ
እንእብርህም
ምን በሉ ምን ጠጡ
እርግጥ የሚያረክም
ምን እፎ ምን ስሙ
እርግጥ የሚያረክም፣
ምስጢሩን ለማንም አልተናገሩም
እለቱ ዝም ዝም
ተኙ ዝም ዝም
የህይወትን ምስጢር
ሰይጣን ከግዜር ሰርቆ
ደብቆት እንደሆን
በትንዝር ሸለቆ
እናገኘው እንደሁ
ጭንገር መሀል ወድቆ
ከቲንተር ተናንቆ
ወይ እምስ ውስጥ ተጣብቆ
እንፈልገው እስቲ
 እሺም አላልኪት እምቢም አላልኪት
 ምንም አላልኪት እንዲያው ዝም አልኪት
ተይ'ኮ ተይ'ኮ
ሂድሽ 'ኮ ሸሸሽ'ኮ
ራቅሽ'ኮ ባከንሽ'ኮ

የተጠሩ ብዙ ናቸውና፤ የተመረጡ ግን ጥቂት ናቸው

በአሊሆይ አላሊሆይ ግልቢያ

-ሲጀራ እጠግለሁ ላንተ ስል ላንተ ስል

በየወረቀቱ እገኝህ ይመስል»

ሲጋራና መጠጥ፣ ከስዉ ትንፋሽና ላብ፣ ከሴቶቹ ሽቶና ከሰንደል ጢስ ጋር ሲቀላቀል የውቤ በረሀን ሽታ ይሰጣል። ማታ ባንድና ባራት ሰአት ላይ የእጣንና የቡና ሽታ ይጨመርበታል

ይህን የማወራልህ እኔ ምናሴ ነኝ፤ ምናሴ ቤተ ማርያም ዘብሄረ ውቤ በረሀ፡ ውታቦቱ ውእቱ ጊዮርጊስ ሰማእት። ስንግርህ ዝም ብለህ ስማኝ

-ኢትዮጵያ ታብዕህ እደዊሀ ሀበ ወዳጅ ሀገር» አለ ክንፈ

ፈረንጆች ኢትዮጵያን ማሰልጠን ስለፈለጉ፤ የኤሌትሪክ መብራትን፣ ሽርሙጥናን፣ ቂጥኝን ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ጋር ስጡዋት ሾሰጦታ ፈረስ ጥርሱ አይታይም/

ሚስዮንም አለ።

የአሜሪካ ተራድኦ፣ ሲኒማ፣ ኮካ ኮላና ሮክ'ንሮል አለምን አጨማለቀ። የኛ ወታደሮች በዋሽንግተን ትዕዛዝ ኮሪያ ዘምተው ሲመለሱ -ጋዶምሺት አይዘንሀወር» እና «ሾርት ታይም» የሚባል ንግግር ከነክር ማዶ ይዘው መጥተው በየጣሳ ቤቱ ነዙት፣ ቀስ ብሎ ውቤ በረሀ ደረሰ

ማሚት እሹሩሩ ቤት ትርሲትና ብርሀኑ ይዋደዳሉ። ጠንፍየለሽና ጴጥሮስስ?

ጥላሁን ማሚት እሹሩሩ ቤት ብቻ ሳይሆን መላው ውቤ በረሀ ውስጥ ይረብሻል። ይስክራል ይደባደባል፣ ይታረቃል

እኔ

ሁሉን ትቼ

ማታ ማሚት እሹሩሩ ቤት በቀይ መብራት ሰፋ ላይ ተቀምጬ ስለወዳጆች መለያየት፣ ስለወጣቶች ማርጀት፣ ስለኑሮ ማጠር ተከዝኩ ስለወጣትነቴ ማለፍ አዘንኩ

ተይ'ኮ ተይ'ኮ
አመለጥሽኝ'ኮ
ነይ'ኮ ነይ'ኮ
ባዶ ቀረሁ'ኮ



ቦታው፤ ማሚት እሹሩሩ ቤት

ጊዜው፤ ማታ ማታ

ሰዎቹ፤ ትርሲትና ብርሀኑ እንተኔኒ

ሁለቱ ፍቅር ይዟቸዋል። ወጣት ፍቅር፣ ቆንጆ ፍቅር በሙዚቃው ጨኸትና በስዉ ጫጫታ ውስጥ ይተያየሉ ይሳሳቃሉ ተተቃቅፈው እየተንሾካሾኩ ይደንሳሉ። ለሌላ ሰው ወይም ለሌላ ነገር አይን የላቸውም የትርሲት ቀጠን ብሎ ረዘም ማለት፣ ጠይም ፊቷ ላይ ዘወትር የሚታየው የፈገግታ ብርሀን፣ ትከሻዋ ላይ የሚፈሰው ጥቁር ዞማ ፀጉር፣ ይሄ ሁሉ የወንዶቹን አይን ይስባል። ዘወትር የሚለብሰው ንጹህ ወዝዋዛው አረማመዱ የወንዶቹን ምኞት ይጠራል ብዙ ወንዶች በዙ ገንዘብ እንስጥሽ ይሏታል። እሷ ግን እሺ አትላቸውም ከብርሀኑ ጋር ፍቅር ይዟታልና።

ጠንፍየለሽና ጴጥሮስስ? ይዋደዳሉ ወይስ ምንድን ነው?

ጥላሁን ጠብ ፍለጋ ውቤ በረሀን ይዞራታል።

ማሚትና ክንፈ። እሷ መልክ መልካም ወጣቶችን እያተያየረች ትደሰታለች፣ እሱ እንደ አውሬ ዶሮ ከቤት ቤት ይዞላል በመጨረሻ ሁለቱ ሊተቃቀፉ ሊቃለሉ

እጠገቢ በሌላ ሰፋ

ጋሼ እልተገናኘንም ተቆልለዋል እንደ ተራራ

ሙሉ ጭናቸው ላይ ትንሳፈፋለች እንደ ዳመና

እነዛ በመስንቆ

እንባ በገቢያ አይሸጥም 'ኮ

ተይ'ኮ ተይ'ኮ

አሉ ጋሼ አልተገናኘንም

ወንዙ ላይ እየተንሳፈፈች ሙብ ወጣትነቴ፣ እንደ እናት በሳግዋ እረፍት የሚሰጡ እጆቿን ዘርግታ ትጠራኝ ነበር

«ና'ኔ ልቀፍህ
ጊዜ ሳይደገህ
ሳይጨባብጥህ
ሙብ ወጣትነቴ
የገደል አበባ ንፁህ ፊቷ

የማለዳ ምንጭ ቀዝቃዛ ጉንጪ
እንደናት ምቹ ደረቷ
«የህይወት ተጋድሎ ያተኮሰውን ግምባርህን
በጉንጩ ሳተገዝትገዝልህ
የሥነ ሸክም ያደከመውን ራስህን
ደረቷ ላይ ሳንተርስልህ
እረፍት ልስጥህ እለችኝ
እሺም አላልኳት እምቢም አላልኳት
እንዲያው ዝም አልኳት
እንቺ ቆንጆ ወጣት
ወጣትነቴ የተበረከበት
ከወጣትነትሽ ቢጎትፍ ምን አለበት?
ጥሩ ወደ ምስራት
ህይወት ወደ ምእራብ
ፀሀይ ወደ ምስራት
በመካከላቸው ታጣ ትላንትና
ወደ ሰማይ ነዘዘ
ወደ መሬት ጨዓ
ሂደች ራቀችብኝ
ሸሸች እንደዋ።

What is the price of the priceless youth we wasted when we were young?



ቦታው. . . ማሚት እሹሩሩ ቤት
ጊዜው. . . ማታ ማታ
ሰዎቹ. . . ጥላሁንና መሳቂያው

ጥላሁን ጥል አሁን፡፡ ጥላሁን ረብሻ የሚጣላው ሰው ቢያጣ ትልት መስታወት ገዝቶ ከምስሉ ጋር ለመጣላት ሳይሞክር እያተርም «የማረገውን አታርግ ብዬሀለሁ፣ ዋ ፈረስኸውሁ» ይለዋል

ከንፈ ማሚትን በሙሉ ነብሱ ይወዳታል፡፡ ግን ነብሱ ቂላው ሜፍ ላይ ነው፣ ፊታውራሪ ይሙት!

ትርሲትና ብርሀኑ እንዲህ ሲዋደዱ ልጅ ቢወልዱ ልጃቸው ምንኛ ያምር ይሆን?

ጠንፍየለሹና ጺዋርቢ ወልደው ቢሆን ናር ልጃቸው ጅብ ይሆን ነበር? ወይስ ባልቾኛ? ወይስ ድንክ? ወይስ ጉድ? ምን አይነት?

እኔ
እዝጌ
ተስፋ ቆርጬ
ሁሉን ትቼ

ማታ ማሚት እሹሩሩ ቤት በቀይ መብራት ተቁር ስር ላይ ተቀምጬ፣ ወጣቶቹ ቤቶቹን ይቀባበሉዋቸዋል
/ቤቶቹ ወንዶቹን የሚያጭበረብሩ ይመስላቸዋል/

የኔን ግን ወጣትነት
ችላ አልኩዋት አላሰፍኩዋት
ባይሆን እስቲ በሌለችበት ላንሳት
በበገና ላሞጋግሳት ላወዳድሳት
በቃላት ተረት ልካሳት

«እስቲ እሳት ልሙት»
እሱ እማማ ሰንበቴ
ቤት እዳሪ የነበሩቴ
አቃጣሪ የሆኑቴ
እንቺ ወጣት የነብር ጣት
ልጅነቴን ምንጭ ዳር ስትሣወት አገኘሻት?
እና ምን አልሻት?
መነሻዬ የአባይ ዳር እንባ
መድረሻዬ የከንአን ኩምታ

ባርባ አመት ሰፋት ምድረ በጻ
ቢያዘው ዱላ ውሀ ሚቶዳ ሙሴ
ሙሴ ጀላጅያን ነው
ወይስ ሙሴ ሙዛኪስ?

ሙሴ ባሰኘው ቁጥር በዱላ
አለቱን እየመታ
ይባላል ያፈልቅ ነበር ውሀ

ውሀ ውሀ
የግዜር ውሀ
ቅንዝር አይኔን ዱሊዋ ላይ ተክዬ ቃላት ልሰንዝርልሀና

«ጉልበትም ሀብትም እውቀትም ባዶ ናቸው፣ እንደሊላው ሁሉ:: ጉልበተኛውም ከጊዜ ጋር አይታገልም:: አምስት መቶ ኪሎ የሚመዝን አለሎ አንሳሀ ተብሎ ደስ አለሀ:: እሺ፣ ታድያ ምን ይጠበስ? ብዬ ብጠይቅህ ግን፣ የጉልበትህ ዋጋቢስነት ይታይሀል:: ከንቱ!» አሉ ሽባው ሰውዬ፣ አይኖቻቸው እንደወፍ እየበረሩ

ዳኛው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የተፃፈውን የሰው ልጅ አቤቱታ ካነበቡ በኋላ

«ይህን ጥያቄ ደጋግመን ሰምተናል:: ግን መልሱን የሰማነው አይመስለኝም:: ጥያቄ ቢበዛ ስንቅ አይሆንም»

ጠበቃው:- «ጌታዬ፤ እዚህ ጎረቤት አልምጥ የሆነች የገደል ማሚቶ አለች፣ እምና የጠየቅነውን ጥያቄ እየሰበሰበች ባመት ባመቱ ትወረውርብናለች»

ዳኛው:- «ማስጠንቀቂያ ይሰማት»

ጠበቃው:- «ተይኮ ተይኮ ተብለሻል»

የገደል ማሚቶ

«ተይ'ኮ ተይ'ኮ ተይኝ ልተኛበት
ቁላዬ ነው ዳገት ቆለጤ ቁልቁለት
ተይ'ኮ ተይ'ኮ
አትበይኝ እንኮኮ
ነይ'ኮ ነይ'ኮ ልበልሽ እንኮኮ
ቁላዬ እምስሽ ፊት ሰግዶ ተምበርክኮ
ታስታውሺኛለሽ የያሪኮን ምርኮ

በሀፊ:- ቀኑን በመቼ ላድርገው ጌታዬ?



ዳኛው:- ዘለአለም፤ ሰባት ዘመናት፤ እልፍ እም አእላፍ አመተ ውድመት በለው:: ደብዳቤው ከዘለአለም አርባ አራት ዘመናት በፊት እንዲላክ:: በሬኮማንዴ

ክስ:- ምድረ በጻ ውስጥ ለብቻህ
በተስያት በበጋ
ፀሀይ እሳት ስትተፋ
ንፋስ ደክሞት ሲያንቀላፋ
ሲና በረሀ ውስጥ ለብቻህ
ፀሀይ ከላይ ስትከካህ
አሸዋ ከታች ሲጠብስህ
አየሩ ከዙሪያህ ሲያበስልህ
ውሀ ጥም ሲያጠወልግህ
የሙሴ በትር ሳይኖርህ
አለቱን ማን ያንኳኳልህ?
አባይን ብታገኘው ጠጥተህ
የምትጨርሰው ሲመስልህ
ታዲያ. . .
ኩዳ
ውሀ
በትንሽ ኩዳ
ጥቂት ውሀ
ብትኖርህ
ያችን ኩዳ ከፍተህ
በንቀት ቀስ ብለህ
ያችን ጥቂት ውሀ
ብታፈስ
እያወቅክ እንደማትታፈስ
በህሊናህ ፊት የለብህም ወይ ክስ?

ወይኔ ወጣትነቴ!
ከሰሰኝ ሽበቴ
ማነኝ ብሎ?

ሙት እንተገ
እኑ ምናቤ ንጉስ በረሀ
ጠባሀታዊ በውቤ በረሀ
የምፈልገ ጠብታ ውሀ
ጠብ
ጠብ
ጠብ
ያችን ውሀ ደፍተህ
ጥቂት ጠብታ ብቻ ስትቀርህ
ወይኔ ውሀዬ
ወየው ውሀዬ
ፈሰሰ ውሀዬ
እንቺ ጠብታዬ ጠብታዬ
ናፈቀኝ እንባ ጨው ውሀዬ
ብለህ በማልቀስህ
ሰላም በመንሳትህ
በህይወት ጠበቃ በሀሊና ዳኛ የለብህም ወይ ክስ?
አዬ እንዴት ያረጉታል?
ዖይ ዋይ ኧረ ወየው
አዬ ያልተኖረን ኑሮ
ዋይ ዋይ!
አዬ እንዲህ ይቀብሩታል
ዋይ ዋይ!
አዬ እንደ ሌላው ኑሮ
ዋይ ዋይ!
ኧረ ወየው ብሎ
ዋይ ዋይ!



# አርባእቱ

## «ሰላም ለኪ»

ከሀ ግእዝ እስከ ሆ ሳብእ በሰብእቱ ሆህያተ ፊደል ግእዛዊ ግጥም እቡነ ክንፈኤል እንደደረሱት

መልከአ በረሀ

ሀ — ግእዝ ሀ፤ ሰላምታ
ሰላም ለኪ
ቤተ ዊስኪ
ያስከረኪ ገንዘባችን
ያመልከኪ ትንገዶችን
ወይቆፍረኪ ቁላችን
የሁላችን

ሁ — ካእብ ሁ፣ ባጭሩ
እንቺ የሌሊት ሴት
ዊስኪ ቢራ ቤት
የገንዘብ ገረድ
የቁላ እመቤት
ያምና ልጃገረድ
የከርሞ ባልቴት
እማጊት የሊት ሴት
የሀበቴ ቤት

ሂ — ሳልስ ሂ፣ ተዘጋጂ
ብርሀንን ሊቀብሩ
ጨለማን ሊጠሩ
ወፎች ሲዘምሩ
ፀሀይ ስትሸሽ
ቀኑ ሲመሽ
ግብር ውሀ ወጥተሽ
ፊትሽን ተኳኩለሽ

በካርታ ጠንቁለሽ
ትጠብቂኛለሽ
ትጠብቂናለሽ

### ሃ — ራብእ ሃ፤ አንቺ ነሻ

አንች መልክሽ «ፑድር»
በሀይሽ ቀይ አምፑል
ባልሽ የብድር
ፍቅርሽ ያስር ብር
አንቺ አታሳይ
ሳቅሽ ካንገት በላይ
ባሎችሽ ብዙ
አንች አጭበርባሪ
የሰው ኪስ ቆፋሪ
ጆሎችሽ ብዙ
ፊትሽን ማሳመር በፑደር በኩል
ጭንሽን መክፈት ለሁሉም እኩሌ
መበዳት አታፍሪ
መውለድ ስትፈሪ
ኑሮሽ መዘዙ
በምንም በኩል
ሀይወትሽ አጉል

### ሄ — ሀምስ ሄ፤ እኔ ራሴ

አንቺን አምኚ
ቂጥኝ ዘግኚ
ጎርጊስን ለምኚ
ፔኒሲሊን ውጪ
ከቂጥኝሽ ድኚ
ከጨብጥሽ አምልጪ
አንቺን አምኚ
ቀረሁ ባክኚ
ቀረሁ መሀኚ



እምቧ
አለች ላሟ
ምን ማለቷ?
መውለዷ
መቀለዷ
ቀልድ ነው ''ንጂ
እንግዲያማ?
እኔ'ንጂ
አንቺን አምኚ
ቀረሁ መሀኚ

### ህ — ሳድስ ሀ፤ ቁሳ ነህ

ውጥርጥር ግትርትር
አጭር ክርክር ብትር
ዘወትር ትርትር
በጻሊሽ ውርውር
በቂንጥርሽ ሙልጭ
በብልትሽ ንክር
ፉጭ-ፉጭ
ፉጭ-ፉጭ
ኢጭ
ሬጭቶ ሲጠወልግ
በጨርቅ ጥርግ
አርገሽ ብድግ
አሁንም ኢጭ
ለስንት ብር?
ስራሽ ስልችትችት
ኑሮሽ ብስጭትጭት
እድልሽ እጣሽ እንደኔ ስንኩል
በምንም በኩል ህይወትሽ አጉል
ብሬን ቁጭ
ፉጭ-ፉጭ
እይ ኑሮ

መች እንዲህ ነበር
ያሰብነው ዱሮ?

ሆ — ሳብአ ሆ፣ ያው ነን'ኮ

አይዞሽ የኔ እህት ቻይው እጣሽን
አይዞሽ የኔ እህት ቻይው ጣጣሽን
ብትሆኚም ለኛ አሻንጉሊታችን
አሻንጉሊት ነን እኛም ፊሳችን
ሳንፈቅድላቸው እየፈጠሩን
በጨለማ ውስጥ የወረወሩን
ስንደናቀፍ የሚስቁብን
እኔ
ድንገት ነቅቼ
እንቺን አይቼ
ደንግጬ
ውበትሽን ፈርቼ
ከማንነትሽ ሸምጥጬ
አምልጬ
ብልቴን አድክሜ
ነብሴን አሳምሜ
ትኩሳቴን አዳፍኜ አጥፍቼ
ተኛሁ ተመልሼ
አሁንም ባንኜ
ነብሴን አውልቄ አጥቤ
አስጥቼ አድርቄ
አጥፌ ጠቅልዬ
አምጥቼ ላንቺ ሰጥቼ
እጠብቃለሁ
እፀልያለሁ
ተይ'ኮ ተይ'ኮ
ነይ'ኮ ነይ'ኮ



ተይ'ኮ ነይ'ኮ
ነይ'ኮ ተይ'ኮ
ልበልሽ እንኮኮ
ግን ጻሩ ግን
ግን ነገር ግን
እባ ቁሱ
ባለ ነብሱ
እየጠሙ
እየከሱ
እየሰጡ
እየነሱ
ቡራኬ
ዘለሳኤ
ለሲጋዬ
ለነብሴ
ድንገት ወደ ውስጥዎ እንዳየዩ
እንደኔ እንዳይበረግጉ
እልቦ በእልቦ ውስጥ
ባዶ በባዶ ውስጥ እንዳይሆኑ

ደጃች ውቤ ሰፈር፣ ማሚት እሹሩሩ ቤት ሙሉ የምትባል ሸርሙጣ አለች

ላሁን ደርሶ መልስ ሶስት ብር
ላዳር አስር ብር
እንዤር ያለ አለት
መናፍቅ ደብተራ በዜማ፡
«ማርያም መግደላዊት በጊዜዋ ስለነበረች አመንዝራ
ሙሉ በረሀዊት በልጅነትዋ ስላልነበረች ሸርሙጣ
ያችንስ ማን አወጣ ይችንስ ማን አመጣ?
ልበ ንፁህዋን ትንሽ ልጅ ወደ እርኩስ ሸርሙጣ የሚለውጣት ማን ነው?»

የሙሉ ድምፅ በቴፕ ሪኮርደር፦ «ኧረ ጎሺ! የእስላሙንም የክርስቲያኑንም ሀጢአት ጠርጌ የማድር ሰው ነኝ:: ማንንም አልለማመጥም:: ሆ!»

አምላክ ሆይ መቼ በደልንህ? አንተ በደልከን እንጂ

ሸርሙጣዋን ማርያም ቅድስት ያደረጋት ማን ነው?

ተይ'ኮ ተይ'ኮ ተይ'ኮ ተይ'ኮ

እኔማ ወዳጅሽ ቶራቢ ነኝ'ኮ

ተይ'ኮ ተይ ችኮ

ስንግርህ እህ ብለህ ስማኝ

መሄዳት መቸስ ትልቅ ነውር ውርደት ነው:: ሴትየዋ ላይ ወተህ፣ ስታስከልክ ቆይተህ፣ ሀጢአትህን ስትረጭ ሳለህ «ምን ማድረጊ ነው?» ብለህ ራስህን ጠይቀት አስተ:: ወይም ቱሳህ ቃቄ በሊብህ ከበሮ እስከስታ ወርዶ ወርዶ፣ ገብቶ ወጥቶ ገብቶ ተፍቶ «አሁን ልትጠወልግ ምን አስለበለበህ?» ብለህ ጠይቀውማ:: ከንቱ ተጠጣህ!

ከሴሉ'ን ልጆች ጋር ተልቦሽና ኩኩሉ ስትጫወት የነበረችውን ትንሿን ሙሉ፣ አሁን ከሊሉ'ፕ ቤቶች ጋር እንድትሸረሙጥ ያደረጋት ማን ነው? ኧረንሺ ነሣ

እንደ ማታ ማማጊት እፉኑሩ ቤት እንጻርጋቸው ሰካራሙ እንደሊማዱ ሰክሮ፣ እፍንጫውን ይዞ «እፍ! እነዚህ ሸርሙጦች እምላቸው ይገማል ጃል! ማዘጋጃ ቤት ውሀ ከለከለ? ለምን ግብር ውሀ አይወጡም?» አለና

በዘመን ቁልቁለት

ስምቹ ሳቁለት

ይህ አይነቱ ንግግር በየቀኑ ይሰማል

ከነሳቱ:: ሳቱ

ሳቱ ሳያውቁ

እንባዶ ሳቱ

አምላክ ሆይ መቼ በደልንህ

አንተ በደልከን እንጂ

«ይፍቱኝ አባቴ»

ካንድም ሁለቴ፣ ሁሁ

ተይ'ኮ ካእቤ

ልንገርሽ አስቤ

«ይፍቱኝ አባቴ»



መፅሀፊ ፅዳት

እንቺ ቆሻሻ ሻሽ

ቅማላም ብላሽ

ንፁህ እያለሽ

የጠመጠመሽ ይፍታሽ

አሁን ቆሽሽሽ እንደምን ልንካሽ?

ሁሁ

ኢሮ አለ አውራ ዶሮ

እድሜውን ጥሮ

ጥሮ ግሮ

ሀልሙን ከምሮ

ቅዝቃዙን ጭሮ

ያሮጊቶች እሮሮ

አይ ኑሮ!

በጊዜ ከበሮ

እምና ጨፍሮ

ሞሞት ዘንድሮ

ይኸው ነዋ ኑሮ

እግዚኦ!

«ይፍቱኝ አባቴ»

ካንድም ሰለስቴ፣ ሂ ሂ ሂ

ተይኮ ሳልሴ

ፈጠሩሽ ስላሴ

አራት ዘሁልቱ

አትብሉ ያለው ሙሴ በኦሪት

እንቁራሪት እንሽላሊት ሽረሪት

በመሳሰለ ተበድተሽ ሊሊት

ራስሽ ረክሰሽ

ሰው አርክሰሽ

በኪሩቤል

በሱራፌል

የገዘተሽ ይፍታሽ

ሂ ሂ ሂ

እግዜር የጊዜ ክብሪቱን ጭሮ
እቃጠለነ እንደ ጭራሮ
ዞሮ ዞሮ
መገጊያው ጭራሮ
በሀይ ስትቆነን
ጨለማ ሲጀነን
ሸሸች ኑሮ
ሾልካ በጎሮ
ዋ'ያለች ዋለች ዋኔዋ
ምን ሆና ይሆን?
«ይፍቱኝ አባቴ»
ሃ ራብእ ሃ፣ መፅሀፈ ደንቃራ
በስመ ቃኤል
ወሳጥናኤል
ደንቃራ ያዞረብሽ
ድግምት የደገመብሽ
ይፍታሽ
ሃ ሃ ሃ
እውውው
አለ ጅቡ
ምን ማለቱ?
እንትን ማለቱ
እንትን እንትን
ለምናምን
መጣቶቹ በሩን ቆለፉ
ተዋደዱ ተቃቀፉ ተጣደፉ
እንቀላፉ
ኩኩሉ!
ሌሊቱን ለብሶ እርጅና ደረሰ
ቀኝ እጁን ሰደደ
ውብ ጡት ዳሰሰ



ወጣቶቹ ጣወለጉ
ጠወለጉ ጠወለጉ
ሲነጋ ተያዩ
እለቀሱ እለቀሱ
እሜት መሬት ያለ ቅሬት
ሳታላምጥ ዋጥ ስልቅጥ!
ዋይ ዋይ
ዋይ ዋይ
«ይፍቱኝ አባቴ»
ሂ - ሂ ሀምሴ፣ ካንድም አምስቴ
ተማሪ ከሙሴ
«ይፍቱኝ አባቴ»
መፅሀፈ ሙታን
እንቺ ሞተሽ
በኪሩቤል
በሱራፌል
በንፁህ ሻሽ የገነዘሽ ይፍታሽ
ሂ ሂ ሂ
ሙሴ ሙሴ
በበረሀ
ከላይ ማና
ከታች ውሀ
ተይ'ኮ ተይ'ኮ
ዳዊት እደግማለሁ
አትበይኝ እንኮኮ
ነይ'ኮ ነይ'ኮ
አረጀሁ በረደኝ
አልብሺኝ ብልኮ
በይ'ኮ በይ'ኮ
ሽበቴ ከበደኝ
አንተርሺኝ ብልኮ

እምቢ! ማርጀት እምቢ!
መሞት እምቢ!
ወደ ሰማይ ኮከብ
ወደ መሬት ጨዋ
አልብሺኝ ፍቅርሽን
ሀይወት እንድገባ
እምንቷ የቦ ምንጭ እንዷት ደቂቅ ፈሳ
በአልቦ እሸዋ ተቋጠች መልሳ
«እኔና እንትኔ የምናቀው ቅኔ»
እሉ አለታ ገብረሀና
ዳዊታቸውን ደገሙና
አሁን እትመኚኝ አልፈልግምና
ተረት ተረት
የመኪና ጋራዥ
አንዲት ቢትዮ ነበረች
ስትኖር ስትኖር ሞተች
ተቀበረች. . .
ይህ የሁላችንም ታሪክ ነው
እንዴት ያረጉታል ያልተኖረን ኑሮ?
እንዲህ ይቀብሩታል እንደሌላው ኑሮ
እምላክ ሆይ መቼ በደልንህ
አንተ በደልከን እንጂ
አንቺ ቆይ
ዝም በይ
ፍጡር ቢንጫጫ
በሞት ሙቀጫ
ዝም ዝም
ዝም በይ
እብሾ መበጥበጥ
ድግምትን ማላመጥ
በዕርጋ በእብራደስጥ



መጣፍ መገላለጥ
ይጠቅም ይሆን ወይ
እንሞክር ይሆን ወይ
አለችኝ ውብ ወጣትነቴ
ገነት ልጅነቴ
ወገዙ ላይ እየተንጎላፈች
እሺም አላለኪት
እምቢም አላለኪት
እንዲያው ዝም አለኪት
ውዴ ሆዴ
ሂድሽ 'ንዴ
ራትሽ 'ገዴ
ባከንሽ 'ንዴ
እኔ 'ምስቀው
ሳገባ ብቻ ነው
ሃ ሃ! እያረረች ሳተ
የህይወት ማሽላ
ደሞ የማገባው
እንዴ ብቻ ነው
የምንኖረው
ብዙ ሳስብ ነው
ሂ ሂ ሂ! ትካዜ
ለዚሀ'ኮ ነው
'ምንከተከተው
ሆሆሆ!
ሲቆዩ ሰቆ
ጥላዬ ጠልቆ
እንደዚህ ስስት ብቻይው ሙስጤን
በመሀረቤ ጠቅልዬ ንፍጤን
ቲ ቲ ቲ ት!

ተይ'ኮ ተይ'ኮ
አትበይኝ እንኮኮ
ቂንጥሬ ይታያል
በቆለጥሽ ሾልኮ
/ውስጡን ለቄስ/

«ይፍቱኝ አባቴ»
ሊያንከራትትሽ
ካፈር የፈጠረሽ
በረሀብ ያጠረሽ
በምኞት የወጠረሽ
በእጦት የቋጠረሽ
ፈጣሪሽ ይፍታሽ

አሁንስ ሳቁ ለቀቀኝ
እንባው ተናነቀኝ
ዋ'ያለች ዋለች ዋኔዋ
እኔም እንደሷ
ምን ሆነን ይሆን?

«ይፍቱኝ አባቴ»
ካንድም ስድስቴ፣ ሀ ሀ ሀ!
ተይ'ኮ ሳድሴ
ላንቺ ነው ውዳሴ
«ይፍቱኝ አባቴ»
መፅሀፈ ፍትህ ብሂር
አንቺ በልቃጣ
ሽርሙጣ

በህግ ተከሰሽ
ያሰረሽ ይፍታሽ
ሀ ሀ ሀ!

ያዋቂ እሮሮ
የልጅ እንጉርጉሮ



ሸሸች ኑሮ
ሾልካ በጓሮ
እግዚኦ
ዋ'ያለች ዋለች ዋኔዋ
ምን ሆና ይሆን?

«ይፍቱኝ አባቴ»
ካንድም ሰባቴ፣ ሆሆሆ!
እንግባ ሰባኢ
«ይፍቱኝ አባቴ»
መፅሀፈ ፍትሀት
አንቺ ባለቲንተር
ነሚሄ ፍጡር
አንቺ ታላቅ ሚስጥር
የተመረመርሽ ይፍታሽ
ሆሆ

ይኸውልሽ
ከ ሀ ግእዝ
እስከ ሆ ሳብእ
በፊደሉ
በሙሉ
አሳሳቅ
አስማሁሽ
በስምና ወርቅ
አለባበስኩሽ
በውስጠ ወይራ
ወጋጋሁሽ

«እኔና እንትኑ
የምናቀው ቅኔ»
አሉ አለቃ ገብረሀና
ቂላቸውን አቆሙና

«ይፍቱኝ አባቴ»
ተይኝ አቦጊዳ
ደሞ ልጅ ሆንሽ?
ዲማም ብልቴን
በልቶብኝ ቡዳ
መቼ ወለድኩሽ?
ቂቂቂቅ!

አሁን ደሞ
ባዲሱ ሞ
ድ አሳሳት
እስቲ ልሳት
ቲቲቲት!

ሽርሙጣና ውሻ ሁለቱ አንድ ናቸው
ቤተክሲያን አይገቡ ቄስ አይባርካቸው
ሙብዳትን የመሰለ መላጣ ውርደት የት አ.
እያሉ ሲሰብኩ ስልቡ ባህታዊ
ካድማስ ወዲያ ርቀት
ካልማዝ ወድያ ድምቀት
ከሳት ወድያ ሙቀት
ከሲት ወዲያ ውበት
ከእምስ ወድያ ጥልቀት
ከሞት ወዲያ ህይወት
ይገኝ እንደሆነስ?

አለችኝ ውብ ወጣትነቴ ግንት ልጅነቴ፣ ወንዙ ላይ እየተንሳፈፈች የወንዞች ወንዝ የሆነው የጊዜ ወንዝም ከምንም ሳይቆጥረን መድረሻ የለሽ ጉዞውን ይቀጥላል ይቀጥላል ይቀጥላል

ውብ ወጣትነቴ
እንደቡሃ ማታ የሚያበሩ ሊታዊ አይኖቿ
እንደማር ወለላ የሚያስጎመጁ ከናፍሯ



ና አፍህን አፌ ላይ ደትን
የኑሮን ምሬት ላጣፍጥልህ
ጊዜ ሳይመጠኝ
ሳይጨራምተኝ
ቅደመው ሳመኝ
ተደሰትብኝ
ተጠቀምብኝ
ከፈለግክም ተጫወትብኝ
ብቻ እንዲሁ አትተወኝ
ከንቱ አታስተረኝ» አለችኝ
እሺም እላልኳት እምቢም አላልኳት እንዲያው ዝም አልኳት

## ምዕራፍ ሁለት

# እ ሹ ሩ ሩ ቤ ት

«እኛም እየነው ሁሉንም
እንዳንቺ ዓይነት አዳራሽ የለም»
/ያማርኛ ቅኔ/

ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ይሆናል። ቅዳሜ ማታ ማሚት እሹሩሩ ቤት። አሻሻጮቹ ሁሉም የጥለቱ ስፋት ስንዝር የሚያህል የሀበሻ ልብስ ለብሰዋል። ግን በቀዩ መብራት ምክንያት የጥለቱ ቀለም ምን እንደሆነ ለመለየት አይቻልም። ሁሉም ነገር ደም ውስጥ የተነከረ ይመስላል።

የሚደንሱትን ሰዎች እንዳልገፉ እየተጠነቀቅኩ ወደ ውስጠኛው ክፍል አመራሁ። የውጪው ክፍል አምስት ሰአት እስኪሆን ድረስ ምንም አይታይበትም። ያው የተለመደው ቀይ መብራት፣ የተለመደው ጩኸታም ሙዚቃ፣ የተለመደው ዳንስ እና የተለመደው ጉራ ብቻ ነው። ከአምስት ሰዓት በፊት አዲስ ነገር ቢገኝ እውስጠኛው፣ የማይደነስበት፣ እንጂያው ቁጭ ብሉ የሚጠጣበት ክፍል ውስጥ ነው። አዲስ ነገር ባይኖርም ጋሼ አልተገናኘንም ይኖራሉ።

ይኸዋ! እንደ ልማዳቸው ጥግ ሶፋቸው ላይ እንደ ተራራ ተቆልለዋል። አሁን የውስኪ ብርጭቆ ይዛ ጭናቸው ላይ እንደ ነጭ ጉም የምትንሳፈፈው ዕጌ ናት። አጠገባቸው ያለው ሶፋ ላይ ተቀመጥኩ። እዩኝ፣ ተሳሳትን በአንገት እጅ ተነሳሳን፣ በቃ። ማሚት እሹሩሩ ቤት ስንተያይ ይኸው ሶስት ዓመት ሆነን። ታዲያ ተነጋግረን አናውቅም።

ዙሪያውን በየሶፋው ላይ አንድ ስድስት የሚሆኑ ሰዎች መጠጥና ወሬ ይዘዋል። ከአንዱ ጋር ማሚት እሹሩሩ ታወራለች። እንደ አሻሻጮቹ የሀበሻ ልብስ ለብሳለች። ከነውፍረቷ ከነቅላቷ ሲያምርባት! አብሯት ያለውን ሰውዬ አየሁት። ጠይም፣ ኩሩ ቢጤ፣ መልከ መልካም ወጣት። ጥቂት ቆይታ እንግዲህ ወደ ጠንፍየለሽ መኝታ ትወስደዋለች። የታደለ ሰውዬ! ማሚት ወጣቶችን ስታስደስት ጠንፈየለሽ መኝታ ቤት እያስገባች ነው። የራሷ መኝታ ለሷና ለከንፈ ብቻ ነው። ሌላ ወንድ አይገባበትም።

እኔ ብዙ ጊዜ ገብቼበታለሁ፣ ግን ከከንፈ ጋር ሆኜ ነው።



ዛሬ እውጪው ክፍል ዳንስ፣ ጩኸትና ቀይ መብራት አለ። እጠገቤ ጋሼ አልተገናኘንም ዕጌን በጆሮዋ አንድ ነገር አሏት። ትንሽ በመንቀሳቀስ ሰውነቷን ጭናቸው ላይ አመቻቸችና በሽክሽክታ «አሁንስ?» አለቻቸው። ስትቀመጥባቸው ሽንቷን እንደምትሸና ዓይነት ቀሚሷን ገልባ ስለሆነ ቀሚሱ ዙሪያውን ኩፍ ብሎ ቦርጫቸውን አልብሶታል። አሁንም በጆሮዋ ምናምን አሏት። «ትር-ትር ሲል ይታወቀኛል» አለቻቸው። ሙስታሻቸውን እየደባበሱ «ወማጂ! ባሌጊ!» አሉዋትና በእጃቸው የብብቷን ፀጉር መደባበስ ጀመሩ። የተቀመጠ ቻባቸውን ሴት ብብት ሁልጊዜ እንደደባበሱ ነው። እና ሙስታሻቸውን የሚያሹ እየመሰሉ ቤትየዋ ብብት ውስጥ ሲታጠን የቆየውን ጣታቸውን ያሸታሉ። ዕጌ በተስታ «ሂ!ሂ!ሂ! እኮ እያኮርኮሩኝ» ትላቸዋለች።

እኔ እንሱን እማላይ እማልሰማ መስዬ ወደ ያቸውን ክፍል እመለከታለሁ። ሰዎቹ ካሊፕሶ ሲደንሱ ይታዩኛል፤ ግን ለማየት የምችለው የበሩን ስፋት ያህል ብቻ ስለሆነ፣ ደናሾቹ ብቅ ይሉና እንደ አምስቴ ረግጠው ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ በኩል ጥፍት ይላሉ። ጠፉ ብዬ ሌሎቹን ደናሾች ስመለከት ብቅ ይላሉ። እንዚህ ደሞ ተራቸውን ይጠፋሉ።

ትርሲት ከአንድ አጭር ሰውዬ ጋር እየደነሰች ብቅ አለች። ወደ ግራ ወደ ቀኝ ስትወዛወዝ የደስ ደስ አላት። ንፋስ እንደሚያወዛውዛት ወጣት ዛፍ። ሙዚቃው ሀዘንና ውበት ሞልቶበታል፣ በተለይ ለዓ የሚዘፍን ይመስላል። ወደ ግራ ወደ ቀኝ ወዛወዝ - ወዛወዝ - ጠፋች። አጭሩ ሰውዬ ወደ ጠፋችበት በኩል ዞሮ ብቻውን ይደንሳል። እያትበትም። እሱም ተራውን ጠፋ። ግራ ጫማው ብቻ ይታየኛል። እነ አስቴር እንብዙንሽ ይደንሳሉ። ከሙዚቃው ጋር ትግግርና ሳት ይሰማል። ብቅ አለች ትርሲት። ወዛወዝ - ወዛወዝ። ረጅም ፀጉሯ ጠይም ፊቷን ከቦታል፣ ተትረፍርፎ ትከሻዋ ላይ ተጋደሟል። ረዘም ቀጠን ያለች፣ ጠይም ውበት የተጉናፀፈች ወጣት.. እየኋት፣ ፊቷ ብርሃን ለብሷል፣ ሳት አለች። ሆዴ ውስጥ እንደ ሙቀት ዓይነት ነገር ተፈጠረ። ፈገግታዋን ባየሁ ቁጥር እንደዚህ ነው።

ዳንሱ ሲያልቅ ቢራ ይዛልኝ መጣች። ወደ ጾር ሆንኩላትና ሶፋው ላይ ተቀመጠች። አተፍኳት። ራሷን ትከሻዬ ላይ አሳረፈች፣ ሀይሏን ዘጋች። ፀጉሯን ነካሁት። ሀር፣ ሕይወት ያለው ሀር፣ ከሴት ውስጥ የበቀለ ሀር። ማሚት እሹሩሩ ቤት የምመጣበት አንዱ ምክንያት የትርሲትን ፀጉር ለመዳሰስ ነው።

አንድ ወፍራም ሰውዬ ከወዲያ ያየናል። ፊልጓት መሰለኝ። በሃሳቤ «ሁለት ሳምንት ታገስ» አልኩት። ከትከሻዬ ላይ ቀና አለች። ተያየን። ውብ ጠይም ሳቂታ ፊቷን ስጋት ወሮታል። ከዚህ ቀደም ሰላሳ አርባ

ጊዜ የተነጋገርንበትን ጉዳይ እንደገና እንደ አዲስ ልንነጋገርበት፣ ልንስቀይበት ሆነ፡፡ መስቀየት በሸፈነው ድምፅ «መቼ ነው 'ሚሄደው?» አለችኝ፡፡ ከብርሃኑ ጋር ፍቅር ይዟታል፤ ብርሃኑ ለሥራ ተልኮ ጀኔቫ መሔዱ ነው፡፡

«ከአንድ ሁለት ሣምንት በኋላ» አልኳት

በግራ በኩል የከናፍሯ መገናኛ ይንቀጠቀጥ ጀመር፡፡ ዐይኖቿን አስር ጊዜ ትጨፍናን ትከፍተዋለች፡፡ እንባዋን እንዳይወርድ ለመከልከል አቃታት፡፡ ሰው እንዳያያት ቶሎ ብላ ፊቷን አንገቴ ስር ደፋች፡፡ ራሷን በእጄ እተፍክኩት፡፡ ሙቅ እንባ አንገቴን ነካኝ፡፡ ፀጉሯን እየዳበስኩ «አይዞሽ ትርሲትዬ፣ አይዞሽ» አልኳት፡፡ ምንም ላረጋጋት አልችልም፣ ስትሰቃይ እያየሁ ማዘን ብቻ ነው፡፡ ብዙ ሰንባ ከፈሰሰች በኋላ፣ እንደልማዷ መሃረብ ከደረት ኪሴ አወጣች፡፡ እንደተደፋች እንባዋን አደረቀች፡፡ አየችኝ፡፡ ሳቅ ለማለት ሞከረች፡፡ አቃታት፡፡ ተመልሳ አንገቴ ሥር ገባች፡፡ የማረጋው ጨነቀኝ፡፡

ወዲያኛው ክፍል ውስጥ ዳንስ፣ እዚህኛው ክፍል ውስጥ ወሬ ስላለ፣ ማለት ሰው ሁሉ የየራሱን ደስታ ስለሚያሳድድ፣ የዚችን ልጅ ስቃይ ማንም አላስተዋለም፡፡ ወፍራሙ ሰውዬ ብቻ ያየናል፡፡ እሱም የገባው አይመስለኝም፡፡ አሁን የሚያያት በምኞት ነው እንጂ በፍቅር አይደለም፡፡

ዕጊ ጋሼ አልተገናኘንም ጭን ላይ እንደተቀመጠች «ውስኪ ልድገም?» ስትላቸው ተሰማኝ «አያስፈልግሽም» አሉዋት

«እንዴት ውስኪ ብቻ?»

«የለም»

«እንግዲህ ተነስቼ እሄድልሃለሁ» ቀልድ ነው

«ሂጂያ!»

«ካንክለሁን ማን ያሞቅልኋል?»

«ቂጥ ያለሽ አንቺ ብቻ ነሽ?»

«የኔን ያህል ወፍራም ቂጥ ከየት ታመጣለሁ?»

«ሞልቶ!»

«እንደኔ ካንክለሁን የሚያሞቅልሁ?»

«እንጃፈር!»

«እንደኔ ትርትር የሚያደርግልሁ?» ሳቀችባቸው

«አልተገናኘንም ልጄ! ባንገናኝ ነው» አሉዋት

«እኛም አልተገናኘንም» ተነሳችና ቀሚሷን አስተካከለች፡፡ ወደ



ዳንሱ ክፍል ስትራመድ ወንዶቹ ሁላችንም የቂጧን ከፍ ዝቅ ማለት በቃላዋጭ ዐይን ተከተልነው፡፡

ትርሲት ከትከሻዬ ቀና ብላ አየችኝ፡፡ ሀዘን ለቅሶውን ለማሸነፍ የታጠቀች ትንሽ ፈገግታ እያሳየች

«መሀረብህን አበላሸሁብህ፣ ምናስዬ?» አለችኝ

«የልጅ ነገር፣ ሁሌ ማልቀስ» አልኳት

«ምን ላርግ ምናስዬ? እወድሃለሁኮ»

«እሱም ይወድሻል»

«ታዲያ ለምን ትቶኝ ይሔዳል?»

«መሔድ አለበት፡፡ ደግሞ ከአራት ወር በኋላ ይመለሳል'ኮ»

«አውቃለሁ»

እንባቷን ደፍታ መሀረቤን እያጣጠፈች ትንሽ አሰበች፡፡ የምታለቅሰው ለአራት ወር ከብርሃኑ መለየት ስላቃታት ብቻ አይደለም፡፡ ዋናው ምክንያት «ሲመለስ ቢተወኝስ?» ብላ ስለምትሰጋ ነው፡፡ መድረሻ በሚጣድ ውቢ በረሃ ገባች እንጂ፣ መሸርሞጥ የምትወድ ዓይነት አይደለችም፡፡ ብርሃኑ ከሷ ጋር እስካለ ድረስ መሸርሞጥ የለባትም፡፡ ቀና ብላ

«ሁለተኛ አላለቅስም፡፡ ምናስዬ ሙት-ሙት እውነቴን ነው» መሀረቤን ወደ ኪሴ እየመለሰች «ብርሃኑ ሲሄድ እየመጣህ ታጫውተኝ የለ?»

«አዎን»

«ሙት?»

«ሙች»

«ምናስዬ ሙት?»

«ትርሲትዬ ሙች!» በትራሴ ዜማ «ትርሲትየ! ተራትሽ ይነካሬኝ ውነቴን ኖ፡፡ አዋሽ ይብራኝ!» አልኳት

እየሳቀች «እንግዲያው አላለቅስም» አለች፡፡ ሳቋ በጣም ደስ ይላል፡፡ አሁን ግን ከሀዘን ጋር ተቀላቅሏል፡፡ አንጀቴን በላኝ፡፡ በሁለት እጄ ለስላሳ ጉንጮቿን ያዝኳቸው፡፡

«አውራልኝ» አለችኝ

«ምን ላውራልሽ?»

«ቀፈለከውን፡፡ የቻርሊን አውራልኝ»

«ትላንት አላወራሁልሽም?»

ቻርሊ ቻፕሊን የሠራቸውን ፊልሞች ሁሉ ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ነግሬያታለሁ፡፡ ግን እንደዚህ ባዘነች ቁጥር እንደገና እንድነግራት

ትፈልጋለች። በነገርኳት ቁጥር እንደ አዲስ ነገር ያስቃታል። ይልቁንም ቻርሊ ጦርነት ሔዶ አስራሶስት ወይም አስራአራት የጀርመን ወታደሮች ብቻውን ማርኮ እየነዳ ሲያመጣ አለቃው «ጎበዝ! እንዴት ማረካቸው?» ሲለው፣ ቻርሊ «ከበብኳቸው» ይለዋል፣ ብዬ በነገርኳት ቁጥር በሳቅ እየተንከተከተች፣

«አይ ቻርሊ! አስራ አራቱን ከበባቸው? ብቻውን?» ትልና ደስ የሚለኝ ሳቋን በረጅሙ ትስቃለች። ዛሬ ግን ቻርሊ እንዳይሰለቻት ብዬ ሌላ ወሬ ጀመርኩላት። ክንፈና ጥላሁን ለዕረፍት አስመራ ሄደው ነበር አልኳት፣

«እንግዲህ የአስመራ ጋሪዎች ማታም ይሠራሉ። ታዲያ ክንፈና ጥላሁን ማታ ጥምብዝ ብለው ሰክሩና ባለጋሪውን ጠርተው፣ ማማጊት እሹሩሩ ቤት አሉት።

ባለጋሪው «እንታይሉ ሀብዚሉ ማማጊት እሹሩሩ?» አላቸው። ማማጊት እሹሩሩ ቤት ደሞ የት ነው? ማለቱ ነው

«ደጃች ውቤ ሰፈር» አሉት

«እንታይሉ ደጃች ውቤ?» አላቸው

«ደሀ ባለጋሪ ደጃች ውቤ ሰፈርን እንዴት አያውቅም?» በማለት ትግሬዎችን በሙሉ ናቁ። «ይኼ ሕዝብ ተስፋ የለውም» ተባባሉ። «ደጃች ውቤ ሰፈርን የማያውቅ ሕዝብ እንዴት ተስፋ ይኖረዋል?» ብለው ተስማሙ። ባለጋሪው ይጠብቃል።

«አዲስ አበባ» አሉት

በሃይል ተናደደ «ቧ! እንታይሉ አብ አስመራ አብ አዲስ አበባ ቢጋሪ?» ከአስመራ ወደ አዲስ አበባ በጋሪ ይኬዳል አሏችሁ እንዴ? ቧ! ሰክራም እንታይ ይመጽእ? ቧ! አዲስ አበባ ንፈልጥ ሀብዚሉ! ቧ! ዲስግራሲያቶ!» እያለ እየተመናጨቀ ፈረሱን እየገረፈ ሄደ።

ትርሲት ለጊዜው ሀዘኗን እየረሳች ሄደች፣ ፊቷ ላይ ሳቅ መታየት ጀመረ።

ክንፈና ጥላሁን «ያልከውን እንከፍላለን» አሉት። ባለጋሪው አልሰማቸውም። «ምን ይሻላል?» ተባባሉ። ክንፈ «እኔ ዛሬ ማማጊትን ካላየሁ እሞታለሁ» አለ። ጥላሁን «እኔም አስናቅቹን ማየት አለብኝ» አለ። «ከጋሪ ፈረስ እኩል በእግራችን መሄድ ያቅተናል ወይ?» አሉና በፉጫ ወደ አዲስ አበባ አመሩ። ትንሽ እንደሮጡ ቆሙ። «አዲስ አበባ በዚህ በኩል እንዳልሆነስ?» ተባባሉ። በዚያውም ደክሟቸው ስለነበረ፣ ለድካም መድኃኒት ብለው መጠጥ ቤት ገብተው ሁለት ውስኪ አዘዙ። ሲጠጡ ሳለ ክንፈ «ከማማጊት ተለይቼ ሳድር አሳሳዝንም?» አለ። ጥላሁን «ታሳዝናለህ። በጣም ታሳዝናለህ!» አለው። አዝነው



ቆሞ አሉ። ትንሽ ቆይቶ ክንፈ «ላልቅስ? እሪ ብዬ ላልቅስ?» አለ። ጥላሁን «ተወው። ምን ያረግልሃል?» አለው። ክንፈ «እውነትክን ነው። ምን ያረጋል? ይኸኔ'ኮ እኛ ለነሱ እንዲህ ስንጠወልግ እነሱ እኛን ጨርሰው ረስተው እንዳንድ ወንድ ይዘው ይሉታል» አለ። «እውነትክን'ኮ ነው። ይሉታል! ሴትን ያመነ ውሃን የዘገነ» ጥላሁን «ታዲያ እኛም ለምን አንለውም?» አለ «እንበለው» ተባባሉና ሴት ቤት ሄደው አደሩ፣ አልሻለሁ።

ያንን ውብ ሳቋን መሳት ጀመረች። እኔም መሳት ጀመርኩ። ትርሲት ስትስቅ ሳቅ አገር ውስጥ እንደገባሁ ይሰማኛል። ሳቁ ከየት እንደሚመጣ እንጃ፣ ብቻ ይመጣል፣ እንስቃለን። ቀጠልኩላት።

አንድ ቀን ደግሞ ሌሊት ዘጠኝ ሰዓት ላይ ክንፈ፣ ብርሃኑ፣ እኔ፣ ጥላሁን ከፓርቲ እንመለሳለን። ሃሳታችንም ሞቅ ብሎናል። ጥላሁን ግን ብሙ ብሎ ሰክሯል። በስድስት ኪሎ ስናልፍ ቆመና ሀውልቱን አየየ

«ታውቃላችሁ? እኔና ይኼ ሀውልት በጭራሽ አንስማማም» አለን። ዝም አልነው። «አልወደውም ነውኮ ምላችሁ! የቂም ሀውልት ነው። እግዜር ጠላቶቻችሁን መርቁ ይላል፣ እዚህ ግርሻል ቲቶ የቂም ድንጋይ አምጥቶ ይቆልላል። አሁን የኛ ሕዝብ የፋሺስትንና የጣልያንን ልዩነት አያውቅም። ታዲያ ፋሽስት ለሠራው ግፍ ጣልያንን ይተነማል። ይህ ሃውልት መፍረስ አለበት። ኑ እናፍርሰው» አለና እጅጌውን መሰብሰብ ጀመረ። «አይቻልም ማፍረስ» አልነው። «እውነታችሁን ነው፣ ማፍረስ አይቻልም፣ እራችንን እንረብት» አለ። የለም አይሆንም ብንለው፣ እናንተ ባትፈልጉ ተዉት፣ እኔ ግን እራብታለሁ አለ። ምን ያደርጋል? ብንለው፣ ስሜቴን መግለጽ አለብኝ። ይህ ሀውልት እር መሆኑን ለሀገሬ ሕዝብ መግለጽ አለብኝ» አለ። ብንከራከር ብንለምን ብንለማመጥ እምቢ አለ። በመጨረሻ ክንፈ «አንተ ብቻህን ከምታረብት ሁላችንም ብንሸናበት ይሻላል» አለው ጥላሁን «እውነትክን ነው» አለ። እራታችንም ሀውልቱ ሥር ሸናንና መንገዳችንን ቀጠልን።

ዐይኗ ያበራል፣ ጥርሷ እንደዔም አይከደንም። እንደ ትንሽ ልጅ ናት፣ ከእንባ ወደ ሳቅ በቀላሉ ትሻገራለች። ሳሽጋግራት ኩራት ይሰማኛል።

«አንድ ሌሊት ደሞ ብርሃኑና ጴጥሮስ አንቺንና ጠንፍየለሽን ሲያበስሉ አምሽተው ወደ ኮሊጅ ይመለሳሉ። ክረምት ነው። መንገድ ላይ እንግዲህ እልፎ እልፎ የውሃ ጥርቃሚዎች የሉም፣ ጫማ የሚያበስብሱ ከ'ነዚህ ውሃዎች አንዷ የመንገድ መብራት ሥር ወለል ብላ ትታያለች። በስፋት አንድ እርምጃ ትሆናለች። ብርሃኑ ታዲያ ሰክሮ ነበር። እዚች ውሃዋጋ ሲደርስ ተሻግሯት እንደማለፍ፣ ድንገት

ቆመና ኩቱን አውልቆ ለጴጥሮስ አቀበለው:: ጴጥሮስ ግራ ገብቶት «ምነው?» አለው «ኩቴን ይዘህልኝ በወዲያ በኩል አለፍ» አለው «አንተስ?» «ዋኘቼ እጾርጣለሁ»

ሙዚቃ መስጣት ጀመረች:: እኔም አብሬያት እስቃለሁ:: ሰዎች ዘወር ብለው ያዩንና ወደየወሬያቸው፣ ወደየሃሳባቸው፣ ወደየመጠጣቸው ይመለሳሉ:: ትርሲት ጠይም ፊት ላይ የሚጨፍረው ሳቅና ደስታ! ጉልህ ዐይኖቿን እንባ ሞልቷቸዋል:: አሁን ግን የሳቅ እንባ ነው፤ በጣም ያምርባታል:: እንዲህ እያወራን ለአርባ አምስት ደቂቃ ያህል ከሳቅን በኋላ በልዝብ ድምጽ

«አይ ምናስዬ! አንተ ባትኖረኝ ምን ይውጠኝ ነበር?» አለችኝ:: ልቤ በደስታ ፈነደቀ:: እቀፋት እቀፋት አለኝ::

«አሁን ሒጂና ትንሽ ደንሰሽ ተመለሺ:: እሹሩሩ እንዳትቀየምሽ»

«እሺ»

«ቆይ'ስቲ!» እምባው ኩሏን አበላሽቶት ነበር፣ በመሀረቤ አስተካከልኩላት:: ወደዚያኛው ክፍል ስትራመድ እግሮቿ ታዩኝ:: ከዘበኛ ቀሚሷ በታች ባቷ፣ ቁርጭምጭሚቷ፣ ተረከዟ፣ መላው እግሯ ከእርዝመቱ እንዴት ደስ ይላል! የኔ ብትሆን እግሯን ሁልጊዜ በሳምኩ::

ብርሃኑ ምንኛ ታድሏል! ሁለት ዓመት ሙሉ ከዚች ጋራ!

ዘወር ብዬ ያለሁበትን ክፍል ተመለከትኩ:: ከቅድሞቹ ሰዎች አንድም የለ:: በየሶፋው ላይ ሌሎች ሰዎች ተቀምጠው ሌላ መጠጥ ሌላ ሃሳብ ሌላ ወሬ ይዘዋል:: አሁን ጋሼ አልተገናኘንም ጭን ላይ ቢራ ይዛ የተቀመጠችው ወስንዬለሽ ናት:: እሷንስ ለምን እንደሚያስቀምጧት አይገባኝም:: ቲሟ ይህን ያህልም ትልቅ አይደለም:: ኧረ ትንሽ ነው:: እንዷውም ቲጥ የላትም:: ግን የብብቷ - ብቻ የራሳቸው ጉዳይ ነው::

እዚያኛው ክፍል ውስጥ ጥቁር የለበሱት ወንዶችና የሀበሻ ቀሚስ የለበሱት ሴቶች በፍጥነት ውር-ውር ሲሉ ይታዩኛል፣ ሮክንሮል ይደንሳሉ:: ቢል ሄሊና ኮመትስ የተባሉት የሮክንሮል ጓዶቹ

"We gonna rock' we gonna" rock

Around the clock tonight"

የሚለውን ውድ ዘፈናቸውን ይዘፍናሉ:: ታምቡሩ - ፍጥነቱ - ጊታሩ ያሳብዳል:: ሰዎቹ ነሽጧቸው እየጨበጨቡ «ኤድያ! . . . ጋዴማት! . . .» ሲሉ ይሰማል:: ወደ ሴቶቹ መኝታ ቤት የሚወስደው በር ተከፈተ:: ማሚት እሹሩሩ ከጠይሙ መልከ መልካም ወጣት ጋር ገባች:: ከጠንፈለሽ መኝታ ቤት መመለሳቸው ነው:: እሱ ወደ ዳንሱ ክፍል ሄደ:: እሷ ግን አንድ ቁጭ ያለ ሰውዬ አይታ፣ በወፍራም



ልዝብ ድምጿ «ውይ! አለን! ከየት መጣህ?» ብላ ሳመችውና አብራው ተቀመጠች:: እሱም መልከ መልካም ነው:: በጣም ቀይ:: ሃያ አምስት ዓመት ሰፈር:: የትልቅ ሰው ዘር ይመስላል:: እሱም እንግዲህ ትንሽ ቆይቶ ማሚትን ወደ ጠንፍየለሽ መኝታ ቤት ይከተላታል:: መልከ መልካም ወጣት በሆንኩ! ማሚት ወደ ጠንፍየለሽ መኝታ ቤት ትወስደኝ ነበር:: አሁን ግን በዐይኔ እያየሁ መጎምጀት ብቻ ነው:: ይልቁንም ስትራመድ፣ ከቀጭን ወገቧ በታች ያበጠው ዳሌዋ ወዲያ ወዲህ ሲማታ

ከዳንሱ ክፍል መጥቶ በሩ ላይ ቆመ አሥራት:: አሥራት ዕንቁ ይሉታል:: የአባቱ ስም ዕንቁ ሥላሴ ነው:: እነሱ ግን እንቁራሪት ማለታቸው ነው:: ደግሞ እውነታቸውን ነው:: በፈጠጠ ዐይኑ እያየህ፣ ቃላቱን በሰፊ አፉ እያሳመጠ፣ በወፍራም ሸካራ ድምፁ ሲያናግርህ፣ ከእንቁራሪት ጋር ያለህ ይመስልሃል:: አዲስ ሰማያዊ ልብስ ለብሶ፣ ነጭ ከራቫት አስሮ፣ ነጭ ጫማ አድርጎ፣ እንደ ከንፈ ለመልበስ ይሞክራል:: በግራ እጁ የተለኮሰ ሲጋራና የውስኪ ብርጭቆ ይዞ በሩ ላይ ቆሟል:: በረሃ ውስጥ ሩቅ ለማየት የሚፈልግ ሰው የፀሐይዋ ጨረር ዐይኑን እንዳይወጋው ለዐይኑ ጥላ ለማጥላት ሲል እጁን ግንባሩ ላይ ያደርጋል:: አሥራት ቀኝ እጁን ግንባሩ ላይ አደረገ:: ዙሪያውን ተመለከተ:: ከቀኝ - ወደ ግራ - ከግራ ወደ ቀኝ አየ:: የሚፈልገውን አገኘ? እንቁራሪት ዐይኑ እኔ ላይ አረፈ:: ሩቅ ሩቅ እንዳለሁና፣ እኔ መሆኔን እርግጠኛ እንዳልሆነ አስመስሎ አትኩሮ ተመለከተኝ:: እና እጁን ግንባሩ ላይ እንዳደረገ ወደኔ ተራመደ:: ትንሽ ትንሽ ይንገዳገዳል:: አጠገቤ ተቀመጠ::

«አፎ ወአልከ» አለኝ:: ድሮ አብረን ግዕዝ እንማር ነበር

«ይሰባህ እግዚአብሔር:: አፎ ወአልከ» አልኩት:: መልሶ

«ይሰባህ እግዚአብሔር:: አፎ ወአልከ» አለኝ

«አፎ ወአልከ እያልን ልናድር ነው?» አልኩት

«Brilliant idea! እንዴት መጣልህ ባክህ? አፎ ወአልከ» አለኝ:: ዝም አልኩት:: ትንሽ ቆይቶ «ጠጋ በል፣ እንግረክ ዝንቱ ታላቅ ምሥጢር:: አ አምላከ እስራኤል፣ ተአምራት ውእቱ ግብረከ፣ ዘትፈጥር ወብእሲት ወአባብ ወአፀ በለስ፣ ወዘትፈጥር ጌሾ ወብቅል ወአልኮል ወገ ትስጥዎ ለአሥራት እንዲሰላሴ:: ሰክሬያለሁ:: Honestly I am drunk I am drunk, because I drank some drink which makes you drunk and so on and so forth. ወዘተርፈ:: ምናልባት የረሳሁ እንደሆን አስታውሰኝ እ?»

«ምኑን?»

«የመጣሁት ገንዘብ እንድታስቀምጥልኝ ልሠጥህ ነው»

«ለምን አሁኑኑ አትሰጠኝም?»

«Brilliant idea, brain wave! አሁኑኑ ለምን አልሰጥህም? አሁኑኑ! right now! now or never, better now than never' and so on and so forth መዘተርፌ» እጁን ደረት ኪሱ ከተተ «ሙሉ መብት ያለኝ ኢትዮጵያዊ ስሆን with all the piss and the privilege attached thereunto ገንዘቤን አሁኑኑ ለምን . . . » ድምፁ ሞተ፤ እጁ ኪሱ ውስጥ ቀረ። አየሁት። ፊጣጣ አይኑ የባሰውን ፈጦ ይመለከታል። አይኑን ተከተልኩ። ማሚት እሹሩሩ ቀዩ ሰውዬ የተቀመጠበት ሰፋ እጅ መደገፊያ ላይ ቁጭ ብላ የሰውየውን አንገት አቅፋለች። አስራት በመገረም «እ-የ-ሀ-ል-ኝ ወይ ያ-ን ን ቂጥ!» አለ። ቂጧን የሶፋው እጅ ከሥሬ ገፍቶ ወደ ውጭ አስብጦታል፤ ፍጥጥ ብሎ በጣም ያንጓል። ቀዩ ሰውዬ ወገቧን አቀፋት።

አስራት «አ!» አለ

በዚች ትንሽ «አ!» ውስጥ ስንት ምኞት፣ ስንት ተስፋ የለሽ ምኞት፣ ስንት ያልተሟላ ምኞት ተቋጥሯል!! የማሚት ምሥጢራዊ ጭኖች ለመልከ መልካም ወጣቶች ብቻ ነው የሚከፈቱት። ግን እኛም ብዝሆን ያበጠ ዳሌዋን ማየታችን መመኘታችን አልቀረም - እንዲያውም ልናገኘው ስለማንችል የበለጠውን ያምረናል ያንገበግበናል። እኔና አሥራት እንዳፈጠጥን ቀረን።

ይህን ግሩም ትርጂን እያየሁ፣ ትድም ከጠንፍየለሽ መኝታ አብሯት የተመለሰውን እድለኛ ኅረምሳ አስታወስኩ። ያንን ወገብ አቅፏል፣ ያንን ቂጥ አሻሽቷል፣ ጭኖቿ መሀል ተጋድሟል፤ ላጭር ጊዜ መንግሥተ ሰማያት ገብቷል። ከንፈ - ከንፈሟ ሌሊቱን ሙሉ መንግስተ ሰማያት ውስጥ ነው የሚያድረው፣ ኅረምሶቹም የሚደርሳቸው ከሱ የተረፈው ነው። ብቻ እሱ ሌላ ታሪክ ነው. . . ግን ከማሚት ጋር ማደር እንዴት ያደርግ ይሆን?

ቀይ ሰፊ ጥለት ያለው የሀበሻ ልብስ ፊቴ ድቅን አለ። ቀና ስል ትርሲት አጠገቤ ቆማለች። ፈገግታዋን አየሁና ሁሉን ረሳሁ፣ የአሥራትንም እንቁራሪትነት፣ የማሚትንም ቂጥ፣ የራሴንም ምኞት። ትርሲት ጉልበቴ ላይ ተቀመጠች።

«ምን ይምጣልሽ?» አልኳት

«ምንም። ስንት ሰዓት ነው?»

«ለአምስት ሩብ ጉዳይ»

«ገና? መደነስ ደከመኝ። እዚህ ካንተ ጋር ትንሽ ልቆይ?» ከጉልበቴ ላይ ተነስታ በቀኜ ተቀመጠች፣ አቀፍኳት ትከሻዬን ተንተርሳ አይኗን ዘጋች። ፀጉሯን እየዳበስኩ ዙሪያውን አየሁ። አሥራት ከማሚት ቂጥ ላይ አይኑን አልነቀለም። በምኞትና በንዴት ታችኛ ከንፈሩን ነክሷል።



እሷ ከቀዩ ሰውዬ ጋር ጨዋታ ይዛለች፣ አንድ ቦርጫምና አንድ በጣም ጥቁር ሰውዬ አብረዋቸው ያወራሉ። ሌሎቹ ሰዎች እንደኛው ዝም ብለው የግል ሃሳባቸውን ያስባሉ። ጥቂቶቹ ሲጋራ ያጨሳሉ። እዛኛው ክፍል ሙዚቃ፣ የዳንስ እርግጫ፣ ሳቅ ይሰማል።

ወሰንየለሽ ከጋሼ አልተገናኘንም ጭን ላይ ተነስታ ሄዳለች፣ ብቻቸውን ቁጭ ብለዋል። እኚህ ጋሼ አልተገናኘንም ሳያቸው ያስቁኛል። በጣም ግዙፍ ናቸው። ምናልባት መቶ ኪሎ ይመዝናሉ ። ሰደርያቸውን ውጥር አድርጎ የተነፋ ስልቻ የሚያስመስል ትልቅ ቦርጭ ተሸክመው፣ በተጨማሪ እዚህም እዚያም ብዙ ሥጋ አንጠልጥለዋል። ከአገጫቸው በታች ሌላ አገጭ አንጠልጥለዋል። ይህ አገጭ ወደፊት እንዳይመዘገናቸው በማለት ማጅራታቸው ላይ ሁለት ወፋፍራም እጥፋት ለድፈዋል። አንገታቸው ዙሪያ ባለከራቫት ሸሚዛቸው ጨምቆ ያወጣው ሥጋ ተንጠልጥሏል። ይኼ ሁሉ ሥጋ ትንሽ በተንቀሳቀሱ፣ በሳቁ፣ በሳሉ፣ በተናገሩ ቁጥር ይንቀጠቀጣል። በዚህ ሁሉ ሥጋ ተከበው ዐይኖቻቸው ሲያበሩና መላጣቸው ስታብለጨልጭ ሳያቸው ሳቁ ይመጣል። ግን ደግሞ ያሳዝኑኛል። ሴቶቹ እንደነገሩኝ የጋሼ አልተገናኘንም ብልት የእህያ ስለሚያክል ደፍራ አብራቸው የምትተኛ ሴት የለችም። ብቻ በወሬያቸው ስለሚያስቁና ቢራና ውስኪ እንደልብ ስለሚገዙ ሴቶቹ ጭናቸው ላይ ይቀመጡላቸዋል። ብዙ ሰው የሌለ ጊዜ ሴቶቹ ቀሚሳቸውን ገልበው ይቀመጡባቸዋል። ማንም ሰው ከሌለና ጋሼ አልተገናኘንም ሞቅ ካላቸው ደግሞ እሳቸው የሱሪያቸውን ቁልፍ ፈትተው ብልታቸውን ያወጡና ሴቶቹ ልብሳቸውን ገልበው ይቀመጡባቸዋል።

እነተዋበች እነፅጌ ሲነግሩኝ፣ ሙሉ ከወንድ ጋር ካደረች ሁለት ቀን አልፏት ከሆነ፣ ጋሼ አልተገናኘንም ብልታቸውን ሲያወጡ፣ እሷ ሙታንታዋን አውልቃ ኪሳቸው ታስቀምጥና ቀሚሷን ገልባ ትቀመጥባቸዋለች። እየተቁነጠነጠች፣ ትንሽ ትንሽ እያንቋለለች ስታስደስታቸው ከቆዩ በኋላ፣ አላስችል ይላትና ተነስታ «ኑ'ንግባ» ብላ እጃቸውን ይዛ መኝታ ቤቷ ትወስዳቸዋለች። በሩን ትቆልፋለች። እዚያ ውስጥ ምን እንደሚያደርጉ ማንም አያውቅም።

ትርሲት «ይባዳሉዋ! ሌላ ምን አለና?» ትላለች። እነፅጌ ግን «ያስጠቡዋት እንደሆን እንጂ ቢበዱዋት ይደባልቋታል» ይላሉ። በመጠራጠርና በመገረም ድምፅ «እዬዬ! . . .» ስላቸው «አትጠባም ብለህ ነው?» ይሉኛል «ሙሉ ቁላ አግኝታ፣ እንኳን መጥባት ከትፋ ትበላዋለች» ከዛ እንግዲህ ስለ ሙሉ ማውራት ይጀምራሉ። የሚከተለውን ቢያንስ አምስት ጊዜ ነግረውኛል።

አንድ ቀን ማታ ወደ ስድስት ሰዓት ላይ ካሳ ከነሎፍሮቹ መጣ። ሰባት ነበሩ። እና ዮሐንስ የድሮ ወዳጅ ስለሆነች ሙሉን አዳር እንሂድ

አላት፡፡ እሺ ብላ ቤቱ ሄደች፡፡ ተኙ፡፡ በድቷት ሲጨርስ መጣሁ አለና መጣ፡፡ በሱ ፋንታ ሉልሰገድ መጣ፡፡ ከፍታ ሰጠችው፡፡ ሲጨርስ «ዮሐንስ ሳይደርስብኝ» አለና ሄደ፡፡ ሒብቴ ተተካ፡፡ ሰረራትና ሔደ፡፡ ኤልያስ ቀጠለ፡፡ ከሱ በኋላ ብሩ፡፡ ከዚያ ታደሰ፡፡ ታደሰ ሞልቷት ከሄደ በኋላ፣ ካሁን አሁን ካሳ መጥቶ ይከትብኛል ብላ ከፍታ ስትጠብቅ ሳይመጣ ቀረ፡፡ ኩም አለች፡፡ ካሳ ውቤ በረሃ ውስጥ ሴት ተኝቶ አያውቅም ይባላል፡፡ ስለዚህ ሴቶቹ ሁሉ ይፈልጉታል አሉ፡፡ ግን በረሀ የሚመጣው ከጭፍሮቹ ጋር ለመጠጣት፣ ለመደነስ፣ ለመረበሽ፣ ነው፡፡.

ስለዚህ ስለ ሙሉ ጉዳይ አንድ ቀን ኤልያስን ጠየቅኩት፣ ነገረኝ

አየህ፣ ስድስታችንም ሰክረን ነበር (አለ ኤልያስ ሲነግረኝ) አይፈረድብንም፡፡ ሰክረናል፡፡ ቆሞብናል፡፡ ካሳም ቆሞበታል፣ ግን ታውቃለህ እሱ ሸርሙጣ አይበዳም Anyway በካሳ ላንድሮቨር ሙሉን ይዘን ወደ ጆኒ ቤት ስንመጣ በሃይል አግረችን፡፡ አይፈረድብንም፣ ምክንያቱም እሷም በጉሯን ተሰርታ ነበር፡፡ እኛም ሰክረን ነበር፡፡ ስለዚህ እሷ እንዳትሰማን በእንግሊዝኛ ተማክረን Ideaውን ያመጣው ሉልሰገድ ብልጠ ነበር፡፡ አይ እሱ የሚያመጣው Idea! Genius እኮ ነው፡፡ ተራ በተራ ሁላችንም ይድረሰን አለ፡፡

«ምክንያቱም» አለን ብሩ መሊጥ ደሞ «እሷም በጉሯን ተሠርታለች፣ እኔም በጉሬ ተመልጧል፡፡ እኛም ቆሞብናል፣ እምሱም ቢቆፍሩት የሚልጫል እንጂ አያልቅም፡፡ ስለዚህ ጆኒ ሆይ፣ አትንገብገብ፡፡ ደሞስ ኮሚኒስትነትህ ለዛሬ ያልሆነ ለመቼ ነው?» አለው፡፡ መጀመሪያ ጆኒ እምቢ አለ፡፡ በኋላ ግን አምስት መሆናችንን አስቦ፣ ባይፈቅድልንም በጉልበት እንደምንበዳት አየ፡፡ እሺ አለ፡፡

ጆኒ ሲሞላት በጭለማ በሩ ጋ ተጣብቀን እንሰማለን. . . ቆመብን፡፡ ምክንያቱም አልጋው በሩ አጠገብ በመሆኑ የሚሠሩት ሁሉ ይሰማናል፡፡ ታዲያ ትንፋሽ እየጠራቸው «እህ! እህ!» ማለት ሲጀምሩ ሀብቴ «ሊጨርስ ነው» አለ፡፡ ሉልሰገድ ብልጠ «ብቀጥል» አለ፡፡ ተቀበልንና አራታችንም አንድ ላይ «ብቀጥል – ብቀጥላት» አልን፡፡ በሹክሹክታ ነው 'ምናወራው አስታውስ፡፡ ሉልሰገድ «ቀድሜያችኋለሁ» አለ፡፡ የተቀረነው አራታችን እንግዲህ ክርክር ጀመርን፡፡ ብሩ መሊጥ «በዕድሜ ነው፡፡ ታላቅ ይቅደም» አለ፡፡ ሦስታችንም «አይሆንም» አልን፡፡

ካሳ እየሳቀ «መብራት አብራ» አለ፡፡ ማብሪያው አጠገቤ ነበር፣ አበራሁ፡፡ እንግዳ ቤት ውስጥ ነን፡፡ ካሳ ሶፋ ላይ ቁጭ ብሏል፡፡ ከኪስ ደብተሩ አንድ ቅጠል ወረቀት አውጥቶ አራት ቦታ ቀደዳት፡፡ የያንዳንዳችንን ስም እያንዳንዱ ቁራጭ ላይ ጽፎ፣ ቁራጮቹን አጣጠፋቸው፡፡ አራታችንም ከበነዋል፣ ሉልሰገድ ግን ጆሮውን በሩ ላይ ለጥፎ



እቃን ከፍቶ ይሰማል፡፡ ታዲያ በድንገት ወደ እኛ ዘወር ብሎ እጁን እያመናጨቀ «ኤጭ! እናቱን» አለ፡፡ በጣም ተናዷል «ምነው?» ብንለው «ገብጋባ የሸርሙጣ ልጅ! እንደገና ጀመረ» አለ፡፡ ሁላችንም በሽቀን እኛ እዚህ ለአንዴ እንሻማለን እሱ እዛ ድጋሚ ይሞላል» እርር አልን፡፡ ገብተን ልናስወጣው ነበር፣ ካሳ ከለከለን «ምን መሆናችሁ ነው? የራሱ ነች'ኮ» አለን፡፡

ወረቀቶች የያዘ እጁን ወደ ሉልሰገድ ዘረጋና «አውጣ» አለው

«ምንድን ነው 'ማወጣው?»

«እጣ»

«የምን እጣ? »

«ማን እንደሚቀጥል»

«እናታችሁን! እኔ ነኝ 'ምቀጥለው»

«አንተማ ነህ፡፡ ካንተ ቀጥሎ ኸረ»

«ኦ!እሱ'ኳ ይሻላል» አለና ዕጣውን ሊያወጣ እጁን ሲዘረጋ

«ቆይ!» አለ ብሩ መሊጥ፡፡ ሁላችንም አየነው

«ዕጣው ከመውጣቱ በፊት ትንሽ ፀሎት ብናደርግ ምን ይመስላችኋል?» አለ

«ኤድ! ኪድ! Shit!» አካለብነው፡፡

በመጀመሪያ የኔ ስም ወጣ፡፡ ሁሉም ጨበጡኝ «Congratula-tions» አሉኝ፡፡ ብሩ መሊጥ ሲጨብጠኝ «ኤሊ፣ አደራሽን እንዳትደግሚ» አለኝ፡፡ ሌሎቹ «አዎን አዎን! መድገም የለም» አሉ፡፡ ዕጣ ማውጣቱ ቀጠለ፡፡ ከኔ በኋላ የሀብቱ ስም ወጣ፡፡ ቀጥሎ ታደሰ፡፡ በመጨረሻ ብሩ መሊጥ፡፡ መሊጥን ጨበጥነው «Congratulations» አልነው «ምናባታችሁንስ! ፀሎት እናድርግ ስላችሁ እምቢ ብላችሁ ውራ አስወጣችሁኝ» አለን

ካሳ መቼስ ደስ ብሎታል ይስቅብናል፡፡ እሱ ብቻ ነው ያልሰከረው፡፡ ብሩ መሊጥ ሉልሰገድን «ሉ» አለው «ምነው?» «ነይ'ማ ልንገርሽ» ለብቻው ወሰደውና አንገቱን አቅፎ በሹክሹክታ ምናምን ነገረው፡፡ ሉ «እናትሽን!» እያለ ወደ'ኛ መጣ፡፡ አየነው «ተራህን በሦስት ብር ሽጥልኝ ይለኛል?» አለ፡፡ ሳቅንበት፡፡ ታደሰ፣ የመጨረሻ ሁለተኛው «ብሩ፣ የኔን ልሸጥልህ» አለው

በዚህ ስንስቅ ዮሐንስ ፒጃማውን ለብሶ በነጠላ ጫማ ወጣ፡፡ በንዴት «ምን ያስጮሃችኋል? ቀስ ብላችሁ አታወሩም? እጣ my ass!» አለ፡፡ መድገሙን ለማረሳሳት ያለው ነው፡፡ እኛ ግን ገብቶናል፣ አኮረፍነው፡፡ ቁጭ አለና Time Magazine ማንበብ ጀመረ፡፡

ሉልሰገድ ሊሞላት ገባ:: እጣ ባወጣነው መሠረት ሁላችንም ደረስን:: ታዲያ የመጨረሻ ብሩ መሊጥ ገብቶ ሳለ ሉልሰገድ ራሱን እያከከ «ልጆች፣ እቺ ሲትዮ በጣም ጣፈጠችኝ» አለ «መልካም ፈቃዳችሁ ሆኖ እንዴ ብደግም ምን ይመስላችኋል?» ተያየን:: በኃይል ሳቅን:: ሁላችንም በተራ ደገምን::

ይሄ ሁሉ መቸስ ሙሉ ጥምብዝ ብላ ባትሰክር ኖሮ አይቻልም ነበር:: ድጋሚ ስሞላት መሳቅ ጀመረች:: «ምን ያስቅሻል?» ስላት ምን አለችኝ መሰለህ «አንተ ሰውዬ፣ ስንቴ ነው ምትሸናው? ፊኛህ አይቋጥርም? ደሞ ሽንተህ በተመለሰከ ቁጥር ቁላህ ይለወጥብኛል» አለችኝ:: ሁላችንም ጅኒ ሳንመስላት አልቀረንም» አለ ኤልያስ ሲነግረኝ::

ትርሲትን አቅፌ ሐር ፀጉሯን እየዳበስኩ ስለሙሉ፣ ስለካሳ ጭፍሮች፣ ስለጋሼ አልተገናኘንም ሳስብ፣ አሥራት በእንቁራሪት ድምፁ

«እንካ'ንጂ» ሲል ተሰማኝ:: በእጁ ብዙ የአሥር የአምስትና የአንድ ብር ኖቶች ጨብጧል፤ ከቆሻሻ መጣያ ቅርጫት አፍሶ ያመጣቸው ይመስላል:: በግራ እጄ ተቀበልኩትና አስተካክላ ቆጥራ እንድትሰጠኝ ለትርሲት ሰጠኋት:: እጄን ከፀጉሯ እንዳላወጣ ብዬ ነው:: አሥራትን «ስንት ነው?» አልኩት

«እንጃ ሠላሳ ወይ አርባ ይሆናል»

«አብደሀል? ቢያንስ ሁለት መቶ አይሆንም?»

«እሱን ለማወቅ እንግዲህ ቀያዩን ወስደህ ባሥር ታባዛለህ:: ቢጫዎቹን በአምስት ታባዛለህ:: አረንጓዴዎቹን በአንድ ታባዛለህ:: በኋላ ሁሉን ትደምራለህ:: በኋላ ደሞ» ኪሱን ዳበሰና አሁንም እንደቅድሙ ዘግኖ አውጥቶ «ውጤቱን ከዚህ ጋር ትደምረዋለህ. . .» አለኝ:: እንደቅድሙ ተቀብዬ ለትርሲት ሰጠኋት::

«ለምንድን ነው ይህን ሁሉ ተሸክመህ 'ምትዞረው?» አልኩት

«እኔ'ንጃ:: ጠዋት ይገፎው እንደወጣሁ ነው» አለኝና፣ ተነስቶ ትንሽ ትንሽ እየተንገዳገደ ሔደ:: ወደመደነሻው ክፍል አንድ እግሩን ካስገባ በኋላ ተመልሶ እየተንገዳገደ ወደ'ኔ መጥቶ በሹክሹክታ «በኋላ ደግሞ በመቶ ታባዛዋለህ:: ወይም ሁለት ዜሮ ትጨምርበታለህ» አለኝ

«ምኑን?»

«ገንዘቡን:: ስንት ሳንቲም እንዳለኝ ማወቅ ከፈለግክ ማለቴ ነው» አለኝና እየተንገዳገደ ወደ መደነሻው ክፍል ገባ::

ከማሚት ጋር የነበረው ቀይ መልከ መልካም ወጣት ተነስቶ ከኋላ ኪሱ ቦርሳውን እየመዘዘ ወደ ዳንስ ቤቱ ገባ:: ክፍሉ ሊሔድ ነው:: ትርሲት «አራት መቶ አስራ ስድስት» ብላ የአሥራትን ገንዘብ ጠቅልላ



ሰጠችኝ:: ማሚት እሹሩሩ ተነሲታ ውብ ዳሌዋን እያወዛወዘች ወደ ሴቶቹ መኝታ ቤቶች በኩል ተራመደች:: ቀዩን ወጣት በጓሮ በር ና ብላዋለች ማለት ነው::

የመደነሻው ክፍል ጨኸት ሰውን ወደዚህኛው ክፍል ሲተፋው ያለንበት ክፍል እየሞላ ሄዶ ሶፋው ሁሉ ተይዞ፣ ደረት ወንበሩ ሁሉ ተይዞ፣ እንዳንዱ ሶፋ ላይ ሁለት ጓደኛሞች ተጣበው ተቀምጠዋል:: በግራዬ በኩል የመጠጥ ጠርሙሶችና ብርጭቆዎች የተሸከመች አንዲት ትንሽ ክብ ጠረጴዛ ዙሪያ የተቀመጡ አምስት ሰዎች ሲጋራና ሁለት የበራ ክብሪት ይቀባበላሉ:: ፊት ለፊቴ ወዲያ ግድግዳው ሥር ሁለት ሰዎች ቆመው አንዱ የለቀቀውን ደረቅ ወንበር ይገባበዛሉ:: አንድ ረዥም ልጅ መጥቶ ከበላዬ ቆሞ አሥራት እንቁ የነበረበትን ቦታ በእጁ አመለከተኝ:: ተይዟል ወይ? ማለቱ ነው:: በእጄ ቁጭ በል አልኩት:: ከተቀመጠ በኋላ የቫይስሮይ ፓኮ ወደ እኔ ዘረጋ . . . በእጄና በአንገቴ አሳጨስም እግዜር ይስጥልኝ አልኩት:: ለራሱ አንድ አውጥቶ በማኪኒታ አቀጣጠለ:: የሌባ ጣቱ ጫፍ በፋሻ ተጠምጥሟል:: <ጣትክን ምን ሆንክ> ሲሉት <እምስ ነክሰኝ> ብሎ እነማሚትን ያሳቃቸው ወጣት ይሄ ይሆን? ብዬ አሰብኩ:: ጋሼ አልተገናኘንም ብቻቸውን ሶፋው ላይ ተቆልለዋል:: አምስት ሰዓት ከሩብ:: ከትርሲት ጋር ተያይዘን ወደ መደነሻው ክፍል አመራን::

የመደነሻው ክፍል ጢቅ ብሏል:: ሦስቱ ጥቁር ሶፋ ተይዞ፣ በየግድግዳው ሥር ያለው ደረቅ ወንበር ሁሉ ተይዞ፣ የመጠጥ መቅጃው ባንኮኒ ዙሪያ ሰዎች ተደራርበው ቁመው፣ ከዛም ተርፎ መግቢያው በር ዙሪያ አንድ ስምንት ሰዎች ቆመው፣ ወደ ውስጠኛው ክፍል የሚያስገባው በር ዙሪያ አንድ አስር ሰዎች ቆመዋል:: አብዛኞቹ የመጠጥ ብርጭቆ ወይም የቢራ ጠርሙስና የተቀጣጠለ ሲጋራ ይዘው ያወራሉ:: ሰው ከመብዛቱ የተነሳ መንቀሳቀስ በጣም ያስቸግራል:: መተላለፊያ ቀርቶ መቆሚያ ችግር ስለሆነ፣ መተላለፍ የፈለገ ሰው አንዱ ዳንስ እስኪያበቃ መጠበቅና ሌላው ዳንስ ሳይጀምር በቶሎ መሔድ አለበት:: ለዛውም መራመድ የሚቻለው እየተጋፉ «ይቅርታ - sorry» እያሉ ነው:: ግን ይቅርታ የሚሉት አዲስ መጭዎች ናቸው:: ከመጡ ሩብ ሰዓት ካለፈ ወዲያ፣ ብዙ ጊዜ ከመጋጨት የተነሳ ለምደውት፣ ተጋጭተው ዝም ነው::

አብዛኞቹ ወንዶች ጥቁር ስለለበሱና ነጭ ያልሆነውን ሁሉ ቀለማት ቀዩ መብራት ጥቁር ቢጤ ደም ስለሚያለብሰው፣ ሴቶቹ ነጭ የሀበሻ ልብሳቸውን እንደለበሱ በወንዶቹ መሃል ውር-ውር ሲሉ ዐይን ይስባሉ:: አልፎ አልፎ ነጭ- እንደ ወጣት ሰው ሽበት:: ቤቱ በጣም ይወብቃል:: የሰው ትንፋሽና የሲጋራው ጭስ በቀዩ መብራት ጉም መሳይ ነገር ሠርቷል፣ መጥቶ ፊትህ ላይ እንደ እርጥብ ጨርቅ ይለጠፍብሃል፣

ይታከክሃል፣ ዐይንህን ያቃጥልሃል፣ ስትተነፍስ ጉሮሮህን ይፍትሃል::

ንግግር በብዛትና በጩኸት ነው:: ወጣቶቹ አማርኛና እንግሊዝኛ እየቀላቀሉ ያወራሉ:: አልፎ አልፎ የትግርኛና የጣልያንኛ ቅልቅል ይሰማል፣ አንዳንዴ ደግሞ የኦሮምኛና የአማርኛ የእንግሊዝኛ ቅልቅል ይነገራል፣ አንዳንዴም የአረብኛ ስድብ «ኢአል አቡክ! ኩስ ኡምሽ . . .» አለ:: «ማሚት እሹሩሩን ጥሪያት'ማ. . . Hello, Johnny, where are you diSappear? Goddamit! one hell of a punch ሰጠሁትና. . .ኦ! መስሪያ ቤቱን እንዴት ያደርገዋል? Disgrazziato! so you tink I afraid? ኢሌ Tesstata ቷሕ እንተብልኩዎ. . . ማን ከማን ያንሳል. . .አታም አቤ! ደብዳቤ . . . ኩስ ዑምሽ! የቂንጥራም ዘር. . . Shit. . . እኔ'ምልህ Twenty dollars a month ምን እንዳይነዳህ ነው?. . . Gotta a match buddy?. . . ቂንጥሯ ሲቆም ቀሚሷ ድንኳን ይሰራል:: እግዞምላክን! . . . ታዲያስ፣ ተጋበዝ. . . የለም፣ እኔኮ ከቁላና ከቆለጥ የቱ ይበልጥ ይናፍቅሻል ነው ያልኩሽ»

ሙዚቃው ከሰው ጩኸት በላይ ይጮሃል:: ሲደንሱ ቡጊ፣ ሮክ ወይም ቻቻ ከሆነ እየተጋጩ ነው እንጂ እግር ለማንሳት በቂ ቦታ የለም:: የዝግታ ዳንስ ከሆነ ደግሞ ተቃቅፈው ቆመው መወዛወዝ ነው:: ጠንጋራዋ አስገዳችና ኮሳሳው ዳኛቸው ግን በሰዎቹ መሃል «ይቅርታ - ይቅርታ» እያሉ መጠጥ ወይንም ገንዘብ ይዘው በቀላሉ ይሹለከለካሉ:: ለምደውታል:: እኔና ትርሲት ከውስጠኛው ክፍል እንደመጣን በሩ ጋ ከሌሎች ሰዎች ጋር ቆመናል:: አንድ ትልቅ የጢስ ቁራጭ እንደ ደመና አፍንጫዬ ስር ተደቀነ:: በእጄ አራግቢ አባረርኩት

«ይቅርታ አድርግልኝ ወንድሜ! Excuse me very much» አለኝ አንድ ቀይ ባለ ትልቅ ጆሮ ሰውዬ:: በቀኜ በኩል ቆሟል «በእውነት አውቄ አይደለም»

«ምንም አይደለም» አልኩት

«እንዴት ምንም አይደለም ትለኛለህ? ጭስ እኮ ነው» አለ:: ሰክሯል:: ትንፋሹም የቃላቱም መጎተት ያስታውቃል «ሰማህ ወንድሜ ልጅ ምናሴ» የት ይሆን የሚያውቀኝ? «የሲጃራ ጭስ ምንም አይደለም ካልክማ፣ እኛ ሲጃራ የምናጨስ ሰዎች ምንም አናጨስም ማለት ነዋ፣ ውሸታችንን ነዋ:: እቺን የሸጠልኝ ጉራጌ እንዲያው ነዋ ገንዘቤን የበላኝ:: ከሰባራ መርፌም አልፎ በሌለ ሲጃራ አታለለኝ በለኛ:: If smoke is noing zen life is a dream! እና እኔ ነኝ አንተ ሕልም ውስጥ ያለሁት፣ ወይስ አንተ ነህ እኔ ህልም ውስጥ ያለኸው እ? እቺን መልስልኛ! ኦ-ኦ! ይቅርታ አድርግልኝ ረስቼ:: ሞት ይርሳኝ እንቅልፍም ይርሳኝ:: ሕልምም ይርሳኝ» ከኪሱ የላኪ ስትራይክ ፓኮ



አውጥቶ ሲጃራ ጋበዘኝ:: ፓኮው ባዶውን ነው::

«አሀ ረስቼ! ለካ ጨርሻለሁ:: አዚች ቆየኝ ገዝቼ እመጣለሁ:: Wait me here my dear brozer» ግን ወደ ውጭ እንደመሔድ በሩን ተሳስቶ ወደ ውስጠኛው ክፍል ገባ:: ማን ይሆን? ከዚህ በፊት አውቀው ይሆን? አይመስለኝም:: ያንን የሚያህል ጆሮ እንዴት ይረሳል? ያንን የመሰለ አነጋገርስ?

«እንደንስ?» አለችኝ ትርሲት

መጫወት የጀመረው የኔና የሷ ሙዚቃ ነው Green Eyes Rhumba:: አጠገባችን ብዙ ታምቡሮችና አንድ ከበሮ ይጎሰማል፣ ትንሽ ረቶ ብሉ ቫዮሊኖች ተሰብስበው ይንሰቀሰቃሉ፣ ከመዲያ ከሩቅ አንዲት ጥሩምባ ብቻዋን እሪ ብላ ታለቅሳለች:: Green Eyes Rhumba እኔና ትርሲት ስንደንስ፣ ከማሚት እሹሩሩ ቤት ወጥተን ውቤ በረሃን ለቀን ከዓለም አምልጠን፣ ሙዚቃው ውስጥ ገብተን፣ መሳሳሙ ውስጥ መንሰቅሰቁ ውስጥ - እሪ ብሎ ማልቀሱ ውስጥ ገብተን ተቀላቀልነው:: እንደንሳለን:: ቀጭን ሽንጧን አቅፌ፣ ሃር በጉሯ ውስጥ ፊቴን ደብቄ ራሷን ደረቴ ላይ አንተርሳ - ዐይኗን ዘግታ - ሰውነቷን ከሰውነቴ ጋር አጣምራ እንወዛወዛለን:: ከታምቡሮች ከከበሮው እኩል እግራችን ይንቀሳቀሳል፣ ከቫዮሊኖቹ ጋር መዋደዳችን ይንሰቀሰቃል - ከጡሩምባይቱ ጋር ልባችን እሪ ብሎ ያለቅሳል:: እንደንስ - እንወዛወዝ እንተቃቀፋለን:: ከበሮው ይጎስምልናል፣ ቫዮሊኖቹ ይንሰቀሰቁልናል፣ ጥሩምባይቱ ከሩቅ አገር - ከውበት አገር - ከሀዘን ሀገር - ከዋይ ዋይታ አገር ትጠራናለች፣ ትሰብከናለች፣ ትወስደናለች፣ እንወዛወዛለን:: ጥሩምባይቱ ሀዘን እስከሯት ኡይ! ስትል፣ ኡኡታዋን እንደበፊት ማቆም አትችት አይ! ስትል፣ ታምቡሮቹ ከበሮውና ቫዮሊኖቹ (ተማክረው ይሆን?) አንድ ላይ ዝም!! ሲሉዋት ኡኡታዋ ቁርጥ ይላል:: ዝም፡ ፀጥ፡ ሞት:: የሞት አገር ከኡኡታ አገር አልፎ ይሆን? የሞት አገር ከናፍቆት አገር እኩል ያምር ይሆን? የሞትን አገር የእንባ ወንዝ ያቋርጠው ይሆን? የናፍቆት መርከብ በእንባ ወንዝ ስትንሳፈፍ የሞትን በረሃ ታልፈው ይሆን? ወደ ዘለአለም ውቅያኖስ:: ጥሩምባይቱ ሞተች:: የሰው ጩኸት እንደገና ይሰማኝ ጀመር::

ከትርሲት ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን ከሰው እየተጋጨን «ይቅርታ - ይቅርታ» እያልን ወደ ቦታችን ተመልሰን በሩ አጠገብ ቆምን:: ሰው በሰው ላይ ተደራርቦ ቤቱ በጣም ይጠብቃል፣ ግን መስኮቶቹ ዝግ ናቸው:: መስኮት በተከፈተ ቁጥር አጠገቡ ያሉት ሰዎች «ኩራንዲር አስመትታችሁ ሳምባ በሽታ ልታስይዙን ነው?» ብለው ይዘጉታል:: ስለዚህ የሲጋራውን የትንፋሹንና የላቡን ሽታ ለመሸፈን የተለኮሱ ሰንደሎች በየግድግዳው ተሰክተው ይጨሳሉ:: ከበላያቸው የተለጠፉትን

የሆሊውድ ተዋናዮች ለማስደሰት የሚጨስ ቅዱስ ዕጣን ይመስላሉ። ሠላምታው፣ ሳቁ፣ ንግግሩ፣ ጨኸቱ ፈጽሞ አልተቀነሰም። እንዱ ትርሲትን ለዳንስ ወሰዳት። ወዲህ ወዲያ እየተመለካከትኩ የማውቃቸውን ሰዎች ከሩቅ ሠላምታ ሰጠኋቸው። ከቆምኩበት ቡታ አንድ ስምንት ያህል ሰው አልፎ እነ አለማየሁ አንድ ላይ ቆመዋል። እንደነካሳ ዓይነት ማህበር ናቸው፣ ግን እንደነካሳ አይረብሹም፣ ሠላማዊ ሰዎች ናቸው። ደሞ እንደነካሳ ያለ አለቃ የላቸውም፣ ሁሉም እኩል ናቸው። ጥሩ ልጆች ናቸው፣ ሰው አይነኩም። ሳቅ ጨዋታ ብቻ።

አለማየሁ አየኝና ለሌሎቹ አሳያቸው። ዛሬ አምስት ናቸው። ሠላም ካሉኝ በኋላ በእጅ ምልክት ና አሉኝ። በመሃላችን ያሉትን ሰዎች እያሳየሁ «እንዴት አድርጌ?!» ለማለት ያህል ትከሻዬን ብድግ አረኩና እጆቼን በትንሹ ዘረጋሁ። በደንብ ለመንቀሳቀስ አልችልም። አለማየሁ በመነጽሩ እያየኝ በተዘረጋ እጁ ጥምዝምዝ ያለ የአባብ ትርጽ አመለከተኝ። ሹልክልክ ብለህ ና ማለቱ ነው። ተክለሃይማኖት ሁለት እጆቹን አገናኝቶ ሲያበቃ መጋረጃ እንደሚከፍት ሰው አለያያቸው። በሰዎቹ መሀል መንገድ ክፍተህ ና ማለቱ ነው። አብርሃም እጃቸውን መትቶ ዝም አሰኛቸውና፣ በሁለት እጁ ዝብርቅርቅ ያለ ምልክት ይሰጠኝ ጀመር። ጣቶቹን ያገናኛል ያላቅቃል፣ ግንባሩን መታ ያደርጋል፣ ሁለት ጣቱን ወጣ ያደርግና በሌላው እጁ ይሸፍናቸዋል፣ በጣቱ ጆሮውን ይደፍናል። ይኸ ሁሉ ሲሆን የምንተያየው እየተንጠራራን፣ መሀላችን ባሉት ሰዎች አንዱ ሲከልለን ዘወር እያልን አንገታችንን እየዘረጋን «አየሁህ» እንደሚሉት የሕፃን ጨዋታ ዓይነት ሆነ በመጨረሻ «ይቅርታ – ይቅርታ» እያልኩ በሰዎቹ መሐል እየሾለኩ እነሱ ጋ ደረስኩ።

ከጨበጥኳቸው በኋላ አብርሃምን «ምንድነው ያ ሁሉ ዝብርቅርቅ ምልክት?» አልኩት ሁለት ጆሮውን ደፈነና ዐይኑን ጭፍን – ክፍት እያደረገ «ባ-ባ» አለኝ። ዘወር ብዬ ዳርጌ ዱቤን «በግ መሆኑ ነው?» አልኩት። አብርሃም – አለማየሁ – ተክለሃይማኖት አንድ ላይ «Is not- is ዱዳ!» አሉኝ። ሳቅ ተጀመረ ማለት ነው። እነሱ እንግዲህ በዱዳ ቋንቋ መነጋገር ጀመሩ። አንዱ የሌላው ምልክት አልገባ ሲለው «ምን ማለትህ ነው?» ይለዋል። እንዲህ እንዲህ ማለቴ ነው ብሎ ሲመልስለት፣ ታዲያ እንዲህ ዓይነት ምልክት ነው የሚሰጠው? ይለዋል። ይኼኛው፣ ታዲያስ ምን ልትል ነው? ይለዋል፣ ይጨቃጨቃሉ። አብርሃምን ለዳኝነት ይጠሩታል። ሲዳኝ አንዱ ልክ ነው ካለ ሌላው «ኤድ ባክህ! አንተ ምን ታውቃለህ?» ይለዋል። አብርሃም ትንንሽ ዐይኖቹ እንደኮከብ እያበሩ፣ ረዥም ሹል አፍንጫውን፣ ረዥም ሹል አገጩንና ረዥም ቀጭን ጣቱን እምቢተኛው



ፊት ላይ እየጠነቆለ «ዱዳ እኅት አለሁ?» ይለዋል።

«የሉኝም»

«ዱዳ የአክስት ልጅ አለሀ?»

«የለኝም»

«ዱዳ ሞግዚት ነች ያሳደገችሀ?»

«አይደለችም ባክህ!»

«እንግዲያውስ ምን ትዘባርቃለሀ?» ይላል አብርሃም «እኔ አንድ ዱዳ እኅትና አንድ ዱዳ የአክስት ልጅ አሉኝ። ያሳደገችኝ ሞግዚት ዱዳ ናት – ነበረች ማለቴ፣ ነብሷን ይማረውና!» ያማትባል «ደሞ አያቴ ዱዳ፣ ነበሩ ብቻ ሳልወለድ ሞቱ እንጂ፣ ነብሳቸውን ይማረውና) (አሁንም ያማትባል) ከዚህም በላይ ዱዳ girl friend ነበረችኝ። ታዲያስ፣ ስለዱዳ ምን ታውቃለህ በለኛ! Why you ignorant shit, I had my first kiss deaf and dumb style!» ሳቃችን እየበዛ ይሄዳል። የዱዳ ንግግሩ ይቀጥላል። ያው ትንሽ ቆይተው ይጨቃጨቁና አብርሃምን ዳኝነት ይጠይቁታል። ዳኝነቱን አልቀበል ሲሉት «ዱዳ መንታ ወንድም አለህ? ወይም ዳዊት ያስተማሩህ ቄስ ዱዳ ነበሩ?» እያለ አፋቸውን ያስይዛቸዋል።

እነአለማየሁ በየጊዜው አንድ ዓይነት ቀልድ ይጀምራሉ። ያ ቀልድ አንድ ሦስት ሳምንት ያህል ካሳቃቸው በኋላ፣ ይሰለቻቸውና ሌላ ቀልድ ይፈጥራሉ። የበፊቱ ቀልድ አርጅቶ ሲሞትና አዲሱ ቀልድ ተወልዶ ሲያድግ ለአንድ ሳምንት ያህል ሁለቱም በመፈራረቅ ያገለግላሉ።

ዳርጌ ዱቤ «አሎ!» አለ

አለማየሁ የቢራ ጠርሙሱን ወደ ጆሮው አስጠግቶ «አሎ! . . . » አለው

ዳርጌ «American embassy?»

አለማየሁ «Is not »

ዳርጌ « Marilyn Monroe?»

አለማየሁ «እናትክን Is not!»

ዳርጌ «Is!»

አለማየሁ «Is not I say you! ችጋራም ጥሊያን! ዝገት!»

ይህን የቴሌፎን ቀልድ ያመጣው ተሾመ ነበር። እንግዲህ የተሾመ የመሥሪያ ቤት ባልደረባ የሆነ አንድ ኅረምሳ አለ። ውሽማ አለችው። ወጣት ናት፣ ባሏ ግን ሀብታም ሽማግሌ ናቸው። የድሮ ሰው ናቸው። ቤታቸው ስልክ አለ። አንድ ቀን ኅረምሳው ውሽማ እንደልማዱ ባል

በሌሊቱብት ሰዓት ደወለላት:: ታዲያ አንድ ወፍራም ቦርጫም ድምፅ «ሄሎ» አለው:: ባልየው ናቸው:: «ሄሎ» አላቸው:: ደንግጧል:: መልሰው «ሄሎ» አሉት:: በአሜሪካን አነጋገር «Hello, American embassy? አላቸው:: «Is not» አሉት:: እንደመዘንጋት ታዲያ በንዴት «Is !» አላቸው «Is not, I say you! ችጋራም ጥልያን!» አሉና ዝግት አደረጉበት::

አለማየሁ «ሄሎ» አለ

አብርሃም «ሄሎ» አለው

አለማየሁ «ሄሎ! Brigite Bardot?»

አብርሃም «Is can be never not should be . . . » እዚህ ላይ አሥራት ሰንቱ መሐላችን ገባ:: ጥምብዝ ብሎ ሰክሯል:: ደም በለበሱ ፈጣጣ ዓይኖቹ እያየን፣ በእንቱራሪት ድምፁ «አንድ ጊዜ ቀልዳችሁን አቁሙ:: የምጠይቃችሁ ቁምነገር አለኝ» አለን:: ዝም ብለን አየነው::

«ምናሴ፣ ገንዘቤ አንተጋ ነው?» አለኝ:: በጭንቅላቴ አዎን አልኩት

«እሱን ሁሉ ብሰጣት ማሚት አንዴ አትስጠኝም?» አለኝ

«አትስጥህም» አልኩት

«አንዴ ብቻ? በድብቅ?» አለ:: በጣም አሳዘነኝ

«የለም» አልኩት

«ታዳላለች በለኛ»

ዝም አልነው::

«ታዳላለች ማለት ነው:: በቃ ታዳላለች:: እግዜርም ያዳላል፣ ማሚትም ታዳላለች፣ ሁሉም ያዳላል:: እንግዲህ ምን ይሻላል?»

ያው የተለመደው ነዋ:: አሥራት የኡመር ካያምን ግጥሞች በቃሉ እየወጣ ሙትት እስኪል ይሰክራል:: ሙሉ ወስዳ አልጋዋ ላይ ታስተኛዋለች::

የሙሉና የአሥራት ሰንቱ ግንኙነት ልዩ ዓይነት ነው:: እሱ በእንቱራሪት መልኩ ምክንያት ብዙ ካልከፈለ ሴት አያገኝም:: ሲያገኝም በገንዘብ ብርታት ብቻ እንደሆነ ያውቃል ስለዚህ ለፍቅር ይራባል:: እሷም ወንዶች ሲቆምባቸውና ሌላ ሴት ሲያጡ ብቻ ማብረጃ ያደርጉዋታል:: እሷም እምቢ ማለት አትችልም:: ግን እሺ ስትል ለምን እንደፈለጉዋት በደንብ እያወቀች ነው:: እሷም በበኩሏ ለፍቅር ትዃዃለች:: እና በሙሉና በአሥራት መካከል አንድ ዓይነት ጥሩ ስሜት ተፈጥሯል:: ሁለቱም የተናቁ በመሆናቸው፣ ብስጭታቸውን ያለ ቃላት በመተቃቀፍ ይወያያሉ:: ከመግባባትና ከመተዛዘንም ፍቅር



ይወለዳል:: በእንዲህ የሚታጠብ ንፁህ ፍቅር::

አሥራት ለሁለተኛ ጊዜ «ታዲያ ምን ይሻላል?» አለኝ:: የሚወዳትን የኡመር ካያምን ግጥም ጀመርኩለት "Come, fill the cup, and in the fire of spring" በእንቱራሪት ድምፁ ተቀበለኝ " The winter garment of reprentance fling. The bird of life has but a little way to fly. And lo! the bird is on the wing!"

እጁን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጎ እያፈጠጠብኝ

«አይ ምናሴ ጀግናው! ምን ላርግህ? ኡመር ካያምና ዊስኪ ይኑሩ እንጂ የማሚት እምስ ቢቀር ምን አለ? right?» አለኝ

«Right» አልኩት

«ሌላ ጀምርልኝ» አለኝ:: ጀመርኩለት

"Indead the Idols I have loved so long."

ተቀበለኝና "Have done my credit in men's eye much werong. Have drawned my honour in a shallow cup. And sold my reputation for a song." እያለ እየተንገዳገደ ሰዎቹን እየገጨ ከኛ ራቅ ብሎ ባንኮኒውን እየመታ

«አንድ ዊስኪ - ዲፕሮ! » አለ:: ሁላችንም አሳዝኖናል፣ ግን ደግሞ ሳቃችን መጥቷል:: አሥራት እንቱ በጣም ቢያሳዝንህም እያዘንክለት ትስቅበታለህ:: ሲፈጥረው እንዲህ አድርጎ ነው «ያዳላል»

አለማየሁ መነጽሩን እያወለቀ «ልጂ - መነጽሬን ሳወልቅ ሁላችሁም ማሪሊን ሞንሮን ትመስሉኛላችሁ Is Right?» አለ

በአሥራት ሰንቱ ምክንያት የተጠራቀመውን ሳቃችንን ለመሳቅ ሰበብ አገኘን «Is not right! Is ውሸት! Is ቲንጥር!» እያልን ስቀን ወደ ቅድም ቀልዳችን ከተመለስን በኋላ፣ አብርሃምን

«ይህን Is-is not የሚለውን ወደ ዱዳ ቋንቋ እንዴት ትለውጠዋለህ?» አልኩት

ሲተረጉም፣ ሌሎቹ አይደለም ሲሉት፣ ሲከራከሩ ሲጨቃጨቁ፣ ምክንያት ሲሰጥ፣ አይሆንም ሲሉት፣ ሞግዚታችሁ በዱዳ ቋንቋ እሹሩሩ ትላችሁ ነበር ወይ? ሲላቸው፣ እሹሩሩን እዚህ ምን አመጣው? ሲሉት፣ ቤቷ አይደለም ወይ? ሲላቸው፣ አለቃ ገብረሃናን መሆንህ ነው ወይ ሲሉት «እኔና ወሰኔ የምናውቀው ቅኔ» አሉ አለቃ ገብረሃና፣ ዱዳ ነበሩ ይህን አታውቁም ወይ? ሲላቸው፣ ኤድ! ሲሉት፣ ጠስ በጤስ ጠስ ያርገኝ ብሎ በወላይትኛ ሲምልላቸው፣ እስኪ እንግዲያው ከአለቃ ገብረሃና ንግግሮች አንዱን መርጠህ ከሙቶ በማይንስ ከሀምሳ በማይበልጥ የእጅ የአፍና የቂጥ ማንቀሳቀስ ወደ ዱዳ ቋንቋ ለውጥ ሲሉት፣ እዚህ

ላይ ዕርዳታ ያስፈልገኛል፣ ለምን? በሉኝ። እኔ ወንድማችሁ አላሳፍራችሁም፣ አጥጋቢ መልስ እሰጣችኋለሁ፣ ይኸውም፣ አንድ አይነድ - አንድ አይፈርድ - አንድ አይቀድ- አንድ አይበድ - አንድ አይበቃ - አንድ አይወቃ - አንድ አይነቃ - ሲል፣ ኡፉ! ሲሉት፣ አንድ አይነፋ - አንድ አይሰፋ - አንድ አይገፋ - ሲል፣ እናትክን ሲሉት፣ እናቱን - እናትክን - እናትሽን - እናቷን - እናታችንን - እናታችሁን - የሁላችሁን እናታችሁን - የብቻችሁን እናታችሁን - የግላችሁን እናታችሁን. . . አብርሃም እንደዚህ እየቀለደ ስንስቅ ስንጫወት ብዙ ከቆየን በኋላ፣ እኔን መኪና ከሌለህና እምስ ካላገኘህ አሰገደች አላምረው ቤት ወይም ታየች ቤት ወይም ፈትለወርቅ ቤት ወይም ፀሐይ ቤት ታገኘናለህ፣ ወይም እዚሁ ቆየንና በኋላ መጥተን እንወስድሃለን፣ አሉኝና ሂሳባቸውን ከፍለው ሄዱ።

ሲሔዱ ጊዜ ጭር አለኝ። በዐይኔ ትርሲትን ሰው መሃል ፈለግኳት

Meysor Bro
t.me/BooksandYou



# ምዕራፍ ሦስት

## ገድለ ጥላሁን

«እያ በለው በለው
እያ በለው በለው
እያ በለው በለው»
/ያማርኛ ዘፈን/

. . . ታድያ ዐይናችን አገልጋያችን ነው ትለኛለህ? አገልጋያችን ከሆነ ለምን ትርሲትን ፈልግ ስለው ሄዶ ኃይለሚካኤል ላይ ያርፋል?

ኃይለሚካኤል አንድ የውቤ በረሃ ጀግና ነው። ሰውነቱ ግዙፍ፣ መልኩ ቀይ፤ አፍንጫው ደፍጣጣ፤ ፀጉሩ በጣም ሉጫና በቅባት የሚያብለጨልጭ፤ በጡንቻው የታወቀ ነው። አሁንም ሳየው ሮዛን እጇን ጠምዞ የቀልድ እያስመሰለ ቂጧን በጥፊ ይመታታል። ሮዛ እንዳትስቅ አመማት፣ እንዳታመር የባሰውን እንዳይደበድባት ፈራች። ስለዚህ በውሸት ሳቅና በእውነት ንዴት መሃል «ኃሺ ኃይልዬ! እባክህን ተወኝ ያማል!» ትላለች። አልተዋትም። ውቤ በረሀ የሚመጣው ሴቶቹን ለመደብደብ ወይም ወንዶቹን ለመገላመጥ ነው።

አንድ ማታ ለምሳሌ ከአንድ ፈረንጅ ጋር ዝናሽ ቤት መጣ። ይኼ ፈረንጅ ፀሐይን ሁለት ውስኪ ጋበዛትና እንሂድ አላት። ሰው አለኝ አለችው። ኃይለሚካኤል ታዲያ ብድግ አለና «የኔን እንግዳ? እንቺ ቂንጥራም!» እያለ በጥፊ - በእርግጫ - በክርን - በጡጫ ሲያጣድፋት ጊዜ አፍንጫዋ ደማ፣ ዐይኗ አበጠ። አምስት ቀን ተኝታ ስትተነፍስ ጎኗን እያመማት ብዙ ተሰቃየች። እስከ ዛሬ በደንብ አልዳነችም፣ ስትስል ወይም ስትስቅ ጎኗን ያማታል። የኃይለሚካኤል ጡንቻ ነው። ተኝታ ሳለ ልጠይቃት ገብቼ ስናወራ «ለምን አትከሺውም?» አልኳት «አንተ ደሞ! ከመቼ ወዲህ ነው ሽርሙጣ ተረግጥኩ ብሎ ’ሚከሰው?» አለችና ማልቀስ ጀመረች «ደሞ ብከሰውም እኔ ነኝ ምታሰረው። ወንድሙ የፖሊስ ሻለቃ ነው»

ኃይለሚካኤል ሲያጠቃ ሴቶችን ብቻ አይደለም። ወንዶችንም ነው። አህዝ ሲነግረኝ (አህዝም ራሱ ጉልበተኛ ነው፣ ብቻ ሴቶቹን አይነካም) አንድ ማታ ሁለቱም አብረው መርካቶ ሾፌሮች ቡና ቤት ገቡ። እዚያ አንድ ጠብዚራ ክብር ዘበኛ ነበር። ስክር ብሎ መጠጥ መቅጃው ባንኮኒ ዘንድ ቆሞ ስለኮሪያ ዘመቻ - ስለቶኪዮ ይለፈልፋል። ኃይለሚካኤል አህዝን «አቦ ይኼ ቡፋ ምን ጡሩንባውን ይነፋብናል?» አለው·

«ካማረህ ገዛም አታስገኘውም?» አለ አህዝ። ኃይለሚካኤል «ተመልከት እንግዲህ» አለውና ሙክ ብሎ

«አቦ እዚህ ጨርኸት በዛ!» አለ። ክብር ዘበኛው «ታዲያ ጆሮህን አትዘጋም?» አለው ኃይለሚካኤል «አንተ አፍህን አትዘጋም?» አለና እጆቹን ጨብጦ ቀረብ አለው

«ጆሮሽን ነው በጥፊ ብዬ 'ምደፍንልሽ»

ሀይለሚካኤል ጠጋ ብሎ ፊቱን ለጥፊ አመቻችቶ ሰጠውና «እስቲ?» አለው

ክብር ዘበኛው «እንቺ!» አለና አንዴ በጥፊ ወለወለው።

ኃይለሚካኤል ፊቱን እያሻሸ «ታዲያ ይኼ የሚገባ ነገር ነው?» አለውና፣ ወንበር ፈልጎ ለብቻው ቁጭ አለ። አህዝን አኮረፈው።

ታዲያ ቅድም እንዳልኩት፣ ማሚት እሹሩሩ ቤት ውስጥ ኃይለሚካኤል ሮዛን የቀልድ ሲያጎሳቁላት ከቆየ በኋላ፣ ድንገት እርግፍ አድርጎ ተዋትና፣ ሰዎች መሀል መንገድ እየከፈተ ወደ በሩ በኩል ሔዶ ጥላሁንን ጨበጠው።

ጥላሁን በውቤ በረሃ የታወቀ ረብሸኛ እንደመሆኑ መጠን፣ ልክ ሲገባ እንዳየኸው ሔደህ ካልጨበጥከውና «እንደምነህ ጥላሁን? የት ጠፋህ ባክህን?» ካላልከው ኮራህ ብሎ ይቀየምሀል፣ ትንሽ የጠጣ ጊዜ ነገር ይፈልግሀል። ሱሪውን በክንዶቹ ከጎንና ከጎኑ ከፍ እያደረገ፣ መፋቂያውን አፉ ውስጥ በግራ ወደ ቀኝ እያዘዋወረ፣ ደም የለበሱ ትልልቅ ዐይኖቹን እያፈጠጠ፣ በሚያስፈራ ድምጽ «ፈረሰኛውን!» እያለ ይመጣብሃል። ስለዚህ ኃይለሚካኤልና ሌሎችም የበረሃ ጀግኖች መጥተው ጨበጡት፣ አንገቱን አቀፉት፣ ጀርባውን መታ አደረጉት። በውቤ በረሃ ሥነ ሥርዓት ገበሩለት። አሁን ከኃይለሚካኤል ጋር አብረው እየተሽቀጠቀጡ ጥላሁንን ሠላምታ የሰጡት ጀግኖች፣ ምናልባት ከጥቂት ደቂቃ በፊት ኃይለሚካኤልን ራሱን እየተሽቆጠቆጡ ሠላምታ ሰጥተውታል. . .

ውቤ በረሀ እንዲያው መጥቶ ደንሶ ገንዘብ ከፍሎ ሴት ተኝቶ የሚኬድበት ቦታ አይደለም። ወንዶች የተሰበሰቡበት ማንኛውም ቦታ ውስጥ አንዱ ከሁሉም መብለጡ መታወቅ አለበት። ከብቶችም መሀል፣ ውሾችም መሀል፣ ሰዎችም መሀል፣ አብዛኛው በማህበር የሚኖር ፍጡር መሀል እንደዚህ ነው። የተፈጥሮ ሕግ ሳይሆን አይቀርም። በዶሮ፣ በዝንጀሮና በሌሎችም አንዳንድ ፍጥረቶች መሀል ይህ ህግ ከመጠን በላይ ይሠራል። አንድ ወንድ ከሌሎቹ ሁሉ በላይ መሆኑ እንዳይበቃው፣ ሌሎቹን ሁሉ ወንዶች ልጅነታቸውን ጨርሰው ሴቶቹን ማሽተት ሲጀምሩ ቢገድላቸው ይፈቅዳል። አንዳንዱማ በሕፃንነታቸው



ይገድላቸዋል። እናቶቻቸው አንዳንዶቹን እንደ ሙሴ ደብቀው ያሳድጓቸዋል። ሲያድጉ መጥተው አውራውን ገድለው (አውን ሽምግሏል) ቦታውን ይወስዳሉ። ተራቸውን እስኪገደሉ ድረስ ይነግሳሉ።

ለምንድን ነው? ያልክ እንደሆን፣ ለሴቶቹ ነው። እኔ ግን ለሴቶቹ ብዬ አይደለም፣ ለወንድነቱ ነው ትላለህ። ራስህን አታለልክ። ወንድ ስትል ከጎኑ ሴት ውስጠ ታዋቂ ነው። ስለዚህ ስማ፣ ውቤ በረሃ መጥተህ ስትጣላ ስትደባደብ የፍጥረትን ሕግ መከተልህ ነው። በሕጉ መሠረት እንዳሸናፊነትህ መጠን ሴትህን ወይም ሴቶችህን ትመርጣለህ። ካንተ ቀጥሎ ከሌሎቹ የሚበልጠው ከቀሩት ሴቶች ውስጥ ይመርጣል። መጨረሻ የቀረው ወንድ መጨረሻ ይመርጣል፣ ወይም የቀረችውን አንዲት ይወስዳል፣ ምንም ሴት ካልተረፈ ቀረበት። ምናልባት አንተን ተደብቆ ይከተልህና ሴትህን ከጠገብካት በኋላ ለጥቂት ጊዜ ትተሃት አደን ስትሄድ በስርቆሽ ይተኛታል። ግን ዘርህን ቀድመኸው ዘርተሃልና፣ የሚወለደው ልጅ ያንተ ነው፣ ጉልበት የሌለው ዘር ሳይተው ይሞታል። ይህ የፍጥረት ሕግ ነው፣ ብርቱውን ማባዛት፣ ደካማውን ማጥፋት። ክርስቶስም ብሎታል «ላለው ይጨመርለታል፣ የሌለው ግን ያ ያለውም ይወሰድበታል»

የሰው ሥልጣኔ ይህን የጉልበት ሕግ ጥሶታል። ግን ላይ ላዩን ነው እንጂ ውስጥ ውስጡን ይህ ሕግ አሁንም ይሠራል። እዚህ በረሀ ውስጥ ብታስተውል ጉልበተኛው ነው የፈለጋትን ሴት የሚያገኘ። አንዳንዴ ባለ ገንዘቡ ነው። ለምን? ሕገ-ወጥ የሆነው የሰው ሥልጣኔ በጉልበትህ እንዳትጠቀምበት ይከለክልሃል። ግን አሁንም ላይ ላዩን ነው እንጂ ውስጡን ብትመለከት እንዴት ነው? ገንዘቡ ከጉልበትህ የበለጠ ጉልበት ነው። የሚገዛውን ጠበቃ፣ የሚያስከትለውን እሥራት አስብ - ይኼ ጉልበት አይደለም?

አንድ ማታ ማሚት እሹሩሩ ቤት እኔ፣ ክንፈ፣ እሥራት ዕንቁ እና ጥላሁን ባንከኒው ዙሪያ ቆመን ስናወራ፣ ጥላሁን እየሳቀ «ለመሆኑ ለምንድን ነው እዚህ በረሀ ጥል የሚበዛው?» ብሎ ጠየቀና፣ ይህን የፍጥረት ሕግ ከዘበዘብኩለት በኋላ፣ በቁጣ ዓይነት ድምፅ

«እንግድያው አንተ ለምን እንደ ሕጉ መሠረት አትደባደብም?» አለኝ። እየሳቅኩ «እኔ ወንድ መቼ ሆንኩ?» አልኩት። ሌሎቹም ከኔ ጋር ሳቁ። ጥላሁን ግን አፈጠጠብኝ። ስሜት ይጎድልሃል፣ ሰው አይደለህም ብሎ ሁልጊዜ እንደነቀፈኝ ነው። አሁን ግን የተቀየመኝ ክልቡ የጠ የቀኙን ጥያቄ ወደ ቀልድ ስላዞርኩበት ነው።

ወደ መደነሻው ወለል እያመለከተ፣ አፉ ውስጥ መፋቂያውን ከግራ ወደ ቀኝ እያዛወረ «ትርሲትንና ብርሃኑን ተመልከት» አለኝ። የሱ ሁላችንም አየናቸው። ጥብቅ ብለው ተቃቅፈው ታንጎ ይደንሳሉ። የሱ

ፀጉር (በአባቶቹ የወረሰው ሪዝም ሉጫ ፀጉር) ከግንባሩ በኩል ወድቆ ከሪዝ ፀጉር ጋር ተደባልቋል።

«ብርሃኑ እንደምታየው ከሳሳ ቢጤ ነው» አለ ጥላሁን «በጉልበትም ቢሆን እዚህ የሚመጡት ወንዶች ብዙዎቹ ያሸንፉታል። በገንዘብም ቢሆን ብዙዎቹ ይበልጡታል። ግን ማንም ቢሆን ትርሲትን ሊወስድበት አይችልም። እውነቴን ነው? You agree?»

«አዎን»

«ታዲያ የዳርዊን Natural Law የምትለው የታል የሚሠራው?»

ሬታው ብሎ ደስ ብሎታል። በቆንጆ ነጭ ጥርሶቹ ፈገግታ አሳየኝ

«እንድያውም እዚህ ላይ ነው በግልጽ የሚሠራው» አልኩት

«እንዴት?»

«እዚህ ቤት ከሚመጡት ወንዶች ሁሉ ከእያንዳንዳቸው ጋር ቢመዘን፣ የብርሃኑ ወንድነት እጥፍ ወይም አሥር እጅ ነው»

«ኤድ - !» አለኝ። «የማነህ ቀርፋፋ?!» እንደሚባለት ያህል «ድ» ላይ ድምጹን ጫን ብሎ ነተተው። ሌሎቹ ደስ ብሏቸው ዝም ብለው ያዳምጣሉ። ጥላሁን መጨረሻ ላይ እንደሚቆጣኝ ያውቃሉ።

«አስብ እንግዲህ» አልኩት «ከብርሃኑ ሌላ ማን ወንድ ነው ደፍሮ ሸርሙጣ ይዞ ፒያሳ መሀል የሚንሸራሸር? ማነው በየቡና ቤቱ ይዟት የሚገባ? ሌሎቻችን እንዲያው እዚህ ስንሆን ቂጣቸውን እየላስን፣ ውጪ ስናገኛቸው እንደማናውቃቸው እናልፋቸዋለን። ማን ነው ሸርሙጣ ወዳጁ ስትታመም ራሱ በቀን ውቢ በረሃ መጥቶ ሀኪም ቤት የሚወስዳት? ገንዘብ መክፈሉንስ ምናልባት የሚከፍል አይጠፋም እንበል። ማነው በየቀኑ እየሄደ አብሯት የሚውል? ማነው የአስታማሚ ፈቃድ አስወጥቶ አልጋዋ አጠገብ ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ የሚያድር? ከብርሃኑ ሌላ ማን ነበዝ ነው ፓርቲ በተደረገ ቁጥር ያችኑ ሸርሙጣ ይዞ ሔዶ ልክ እንደ ልጃገረድ የሚያከብራት? ደሞ «ይህን የሚያደርገው ትርሲት ልዩ ስለሆነች ነው፣ በሌዶችበት እንደ ሸርሙጣ ሳይሆን እንደጨዋ ሴት ስለምትሆንለት ነው እንዳትለኝ፣ እንደ ሸርሙጣ መሆን ትታ እንደ ሴት ወይዘር የምትሆንበት ምክንያት ብርሃኑ ሸርሙጣነቷን ስለሚያስረሳት ነው። ሸርሙጥናን እንደ ዕድፍ ወይም እንደ ብረት ልብስ ብንቆጥረው፣ ካንዲት ሸርሙጣ ላይ ዕድፏን ለማጠብ ወይም የብረት ልብሱን ቀድዶ ለመጣል ምን ያህል ወንድነት የሚጠይቅ ይመስልሃል? ታውቃለህ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲተኛት ገንዘብ አልከፈላትም። እስካሁንም ቢሆን ሊተኛት ሲል ወይም ከተኛት በኋላ ገንዘብ ሰጥቷት አያውቅም»

ጥላሁን «ኧረ ባክህን?» አለኝ። አሁን ከርከራችንን ረስቷል።



የትርሲትና የብርሃኑ ነገር ደግ ትን ልቡን ነክቶታል።

«በፍጹም ከፍሏት አያውቅም» አልኩት «ልብስ ሲያስፈልጋት ሲያምራት ግለቱ ፡ የጨርቁንና የስፌውን ዋጋ ትነግረዋለች። ይሰጣታል። እሱ ተውልስ፣ የፍቅር ስጦታ ነው እንጂ የእምስ ዋጋ አይደለም። አንዳንዴ ለምን እንደሚጨቃጨቁ ልንገርህ? እሱ ገንዘብ ሲሰጣት እሷ አልፈልግም ስለምትለው ነው። ወይም ትንሽ ወስዳ ከዛ በላይ አያስፈልገኝም ስትለው። ለምሳሌ ለፀጉር መሠሪያ ስትጠይቀው አሥር ብር ነው 'ሚሰጣት። እሷ አምስት ብር ይበቃኛል ትለዋለች። ወረፋ ስትጠብቂ ኬክና ጀላቲ ያስፈልግሻል ይላታል። እንግድያው ስድስት ብር ይበቃኛል ትለዋለች። እንግዲህ አትጨቅጭቀኝ ይልና አሥሩን ብር በግድ ይሰጣታል»

ትርሲትና ብርሃኑ ፊንሳቸውን አብተተው አንድ ሶፋ ላይ ተቃቅፈው ቁጭ ብለው እየተሳሳቁ ያወራሉ። ጥላሁን እንደ እናት ደስታና ፍቅር በሞላው ገጽ ይመለከታቸዋል። እኔ ዝም ስል ጊዜ ክርክራችንን አስታወሰና «መጀመሪያ'ኮ ወንድነት አላልከም ጉልበት ነው ያልከው» አለኝ

«ጉልበትስ ቢሆን፣ ጥላሁን? እንደዚህ ተመልከተው እስቲ፤ አሁን አንድ ጉልበተኛ ጠብ ፈሪ መጥቶ በጥፊ ብሎት ትርሲትን ቢቀማው አንተ ዝም ብለህ ታያለህ?» አልኩት። ሱሪውን በሁለት ከንዶቹ ከፍ እያደረገና የወይራ መፋቂያውን አፉ ውስጥ ከግራ ወደ ቀኝ እያዛወረ «አይሆንም!» አለ። ሰጠብ ሲዘጋጅ ነው።

በሳቃችን መሀል «ይኸውልህ፣ ብርሃኑ የራሱ ጉልበትና ያንተ ጉልበት አንድ ላይ አለው ማለት ነው። የሌሎችም» አልኩት

«እኔ ምልህ፣ የነዚህ ልጆች ፍቅር እውነተኛ ፍቅር ነው በለኝ» አለ

«እንዲህ አይምሰልህ!» አልኩና ለምሳሌ ያህል የሚከተለውን አጫወትኩት

አንድ ሰኞ ማታ ወደ ሁለት ሰዓት ላይ ወንዶች ገና መምጣት ስላልጀመሩ ቤቱ ባዶውን ነበር። ብርሃኑ እዚያ ጥግ ሶፋ ላይ ብቻውን ቁጭ ብሎ ሲጋራ ያጨሳል። እዚህ ጋ ትርሲት፣ ከበቡሽ፣ አስቴርና ምስጢ ካንድ ሰውዬ ጋር ቁጭ ብለው ስለ በረሀ ፍቅር ያወራሉ። (ሌላ ማንም ሰው የለም፣ ሌሎቹ ሴቶች እውስጥ እራታቸውን ይበላሉ) በወሬያቸው መሀል፣ ሰውዬው እንንቱን ወደ ብርሃኑ በኩል ጣል እያደረገ

«ያ ክልስ ከማንኛችሁ ጋር ነው ፍቅር የያዘው? በመጣ ቁጥር . . .» በረፍተ ነገሩን ሳይጨርስ አፉን እንደከፈተ ቀረ። ትርሲት የቢራ ጠርሙስ ይዛ ከላዩ ቆማ እንደ ቁጣ አምላክ ትገላምጠዋለች።

«ያንቺ ነው እምዬ?» አላት ደንግጦ። ስትናደድ እያረ ያስፈራል። ሳትርመህ፣ ግን በቁጣ «አንተ የውሻ ክልስ! ውጣ!» አለችው። የጠርሙሱን አንገት የጨበጠው እጇ ይንቀጠቀጣል። ሰውዬው ፈርቶ ብድግ አለ።

ግን ሲነሳ ጊዜ ትንሽ ሆነችበት። እሱ ቁጭ እንዳለ እሷ ወደ ታች ስታፈጥበት ደነገጠ እንጂ፣ አሁን እሱ ከላይ ሆኖ ወደ ታች ሲያያት ፍርሐቱ ለቀቀው። ተራውን እየገላመጣት በሚያንቋሽሽ ድምፅ «ምን ሆንሽል? ግም ሽርሙጣ!» አላት። ደግነቱ ይህን ጊዜ ብርሃኑ ከኋላዋ መጥቶ ያዛት። ዐይን ዐይኗን በቀጥታ እያየ ጠርሙሱን ቀስ አድርጎ ከእጇ ነጥቆ ለከበቡሽ እያቀበለ፣

«ምንድን ነው?» አላት

«ምንም» አለችው። ገባው፣ ፊቱ ደም ለበሰ። ለማረጋገጥ ያህል ሰውዬውንና እነከበቡሽን እያየ «ምንድን ነው?» አለ

ከበቡሽ «ሽሪ የለም፣ እዚህ እኔና አስቴር. . .»

«ውሸታም!» አላት ለመሳቅ እየሞከረ። ወደ ነጭነት የሚያደላ ፊቱ አሁን ሳምባ መስሏል። ሰውዬውን «ክልስ አልከኝ መሰለኝ» አለው። ሰውዬው ግዙፍ፣ ኩፉ ቢጤ ነው። ብርሃኑን በንቀት እያየ

«እ. . . በእውነቱ ወንድም»

«ወንድምህ አይደለሁም። ክልስ ብለኸኛል?»

«ብልህስ?»

«ትችላለህ። ግን እሷን ግም ሽርሙጣ ስትላት የሰማሁህ መሰለኝ»

«ብላትስ?»

«አትችልም። እሷን እንዳንተ ያለ ግም አቃጣሪ አይሰድባትም»

አስቴር «ብርሃኑ» ብላ ልትይዘው ስትል መነጨቀና ወደዚያ ገፋት። ከበቡሽ ደንግጣ አፈገፈገች። ትርሲት እንደቆመች ቀረች። ሌሎቹ ሴቶች እውስጥ እራታቸውን ይበላሉ። ማንም ሌላ ሰው የለም። ሙዚቃው ይዘፍናል።

ሰውየው «ንፍጣም ክልስ! ሴቶቹ ያግዙልኛል ብለህ ነው መቼስ እንዲህ ሰው 'ምትደፍረው» አለው

ብርሃኑ «ለምን ሴቶች የሌሉበት አንሄድም?» አለው

«ማን ቀድሞ ይውጣ?» አለ ሰውዬው

«እኔ»

«ሽንታም ክልስ! ልትፈተለኪ ፈልገሽ ነው?»

እሺ አንተ ቀድመህ ውጣ»

«ትዘናም ነሁ! በጓሮ ልትሸሺ! እግሬ አውጪኝ ልትይ? መች አጣንሽ?»

እ-ምህ! እሺ አብረን እንውጣ»

ሴቶቹ አይፈትዱልሽም!»



ብርሃኑ ቃል ሳይጨምር ወደ በሩ ሔደና መጋረጃውን ከፍቶ ጠበቀው። አብረው ወጡ። ብርሃኑ እዚችው አጥር ግቢ ውስጥ ያለችውን ትንሽ ሜዳ እያሳየ «እዚህ ትፈልጋለህ?» አለው

«ሴቶቹ መጥተው እንዲያግዙልሽ ነው?»

ካጥር ጊቢው ወጡና ባቡር መንገድ ሲደርሱ ብርሃኑ «እዚህስ?» አለው

«ገላጋይ አይጠፋም። ወይ የማሚት እሹሩሩ ዘበኞች ተልከው ይመጡና ያግዙልሻል»

ብርሃኑ ተበሳጨ። ሊያለቅስ ምንም አልቀረው።

«ታዲያ የት እንሂድ?»

«እንጃልህ!» አለው ሰውዬው

«ጊዮርጊስ ጓሮ እንሂድ?»

«እሺ ምን ከፋኝ?»

ወደ ጊዮርጊስ በኩል ትንሽ እንደተራመዱ ሰውየው ቆመ። «አሀ! ገባኝ ለካ! . . .» አለ

«ምኑ?» አለ ብርሃኑ

«ጊዮርጊስ ጓሮ ወስደህ በማጅራት መቺ ልታስመታኝ አቅደህ ነው። እኔ ግን እንደዚህ በቀላሉ አልታለልም። መላኩ ይጠብቀኛል!»

ብርሃኑ ስልችት አለው። «እንዲዋጋልን ትፈልጋለህ ወይስ አትፈልግም?» አለው

«አልፈልግም»

ብርሃኑ በመገረም «ለምን?» አለ

«ንፁህ አየር ሲመታኝ ጊዜ ሴጣኔ አለፈልኝ»

ብርሃኑ ዝም አለ።

«ሴጣናም ጎንደሬ ነኝ ልንገርህ። ሴጣኔ ሲመጣ የሚመልሰኝ የለም። አምስት ስድስቱን ከመሬት ጋር ደባልቄ ቤቴ የምገባበት ጊዜ አለ። ታዲያ ሴጣኔ ሲያልፍልኝ የሠራሁት ሥራ ይቆጨኛል። የገዛ ሀገሬን ልጆች፣ የገዛ ወንድሞቼን መደብደቤ ኃይለኛ ፀፀት ያሳድርብኛል። አንተ ግን እድለኛ ነህ። ሴጣኔ ቶሎ ለቀቀኝ»

«ሴጣንህ ክልስ ሲያይ ይፈራል እ?»

«ይቅርታ አድርግልኝ ወንድሜ። በውነቱ ለክፉ ያልኩት አልነበረም»

ብርሃኑ ይሄ ሰውዬ ሌሎችንም ክልሶች እንደሚያስቸግር ታየው። ስለዚህ እንደ አብዛኛዎቹ ጉረኞች ፈሪ መሆኑን እውቆ እንዲህ አለው

«በግዛ ወንድም፣ ለወደፊቱ ክልሶችን ለማቀድት ባትሞክር ይሻልሃል። ምክንያቱም የምታየው ክልል ሁሉ በኔ ጭምር) ነፍ ክልሎችንቱ ጀምር እንዳንተ ያሉ ደደቦች «ክልል እህ መልስ እየገፉ አሉቅሱ እያሉ ሲያጠባዉትን እየተደረደበ ያደገ በለሆን ዋል እንደሆነ ነው። ፍቅ ብንሕድ እኔን ተመልከት። ብትፈልግ እንመራረድና! እለቢትር ወርቀን! እንዳንተ ያሉ ሌሎች ሁለት ጨምረህ! ምክታችሁ ልብሽቆ «ልን። አፈር አለመሻገኛለሁ። አስተውል! ንልበት በሳለኝ አደደሬም። ክልል በመሆኑ መደበደብ በንጹታ ስለተማርኩ ነው። ገባህ? ስል እልን እንመልሰና ልጅቷን ይቅርታ ለምናት»

«እ... በግዛ ወንድም፣ ምንስ ቢሆን. . .»

«ወይም ይምጣልን»

«ምንስ ብባትት፣ ራሴው በደፍ ሰው አስቀደሚ ይቅርታ ባልጠይቅ የምሔድ ሰው እመስልሀሁ 'ጎዴ?»

ከዚያ ተመለሰና በውዬው ትርሲትን ይቅርታ አድርጊልኝ ብሎ ቢራ ጋባዛት። ብርሃኑንም ቢራ ጋበዙት፣ ሲያወራላቸው እምሽቶ ሄደ እለሃለሁ። ከዚያች ማታ ወዲያ እዚህ በመጣ ቁጥር ትርሲትን መርቶ «እሳተ ጥሙራይቱ፣ ዛሬ ምን ልጋብዝሽ?» ብሎ አንድ ቢራ ሳይጋብዛት አይደድም።

ያን ለለት ማታ ጥላሁን ማሚት እሹሩሩን እስፈቶዶ ወይም እስንድደ ትርሲትንና ብርሃኑን ተ ሀ ስ ቲያትር ናይት ክለብ ወሰዳቸው። እና ብርሃኑ «ከትርሲት ጋር ደንስ» አለው

«የለም፣ እናንተ ስትደንሱ ደስ ይለኛል። የሚዋደዱ ሰዎች ሳይ! እንደ'ናንተ ያለ እውነተኛ ፍቅር ሳይ ልቤ በደስታ ይሞቃል - ይመታል ማለቴ» አለና የሁለቱንም እጅ ይዞ ሳመ። ስከፎል «ደስ ትሉኛላችሁ» አለ።

ትርሲት «ደስ ካልንህ ከኛ ጋር ለምን አትደንስም?» አለችና አስነሳችው። ሲደንስ ጠጋ አደረጋት። ሲቆምበት ተሰማት። አፈረች። እሱም አፈረ። የበለጠውን እያስጠጋት

«ትርሲትዬ ይቅርታ አድርጊልኝ» አላት «ስክሬያለሁ። ፀጉርሽ ብቻ ሳይሆን ወገብሽም ጭምር ደስ ይለኛል። ስለዚህ ይቅርታ ካላረግሽልኝ ሰላይ እገባለሁ። አንቺ ጥሩ ልጅ ነሽ። እኔ ግን ውሻ ነኝ። ከስከርኩ ከእህቴም ጋር ብደንስ ይቆምብኛል። ብቻ እህት የለኝም። እህቴ አንቺ ነሽ። ግን ልቤ ንፁህ ነው። ቁላፉ ያልተቆነጠጠ ባለጌ ሆኖ ነው'ንጂ! እኔስ እንደ እህቴ ነው የማይሽ። ተቀየምሽኝ?»

«የለም»

«ጥሩ ልጅ ነሽ። እኔ'ኮ 'ሚቆምብኝ የድሮው ትዝ እያለኝ ነው።

አደራ ለብርሃኑ እንዳትነግሪው»

«አልነግረውም»

ቤርይት ክለቡ ሲወጡ በጣም ሰክሮ ስለነበረ ትርሲትና እንዳደረሰቻቸው አስቶም አደራ ላይ እንዳይደርሱ ብርሃኑ ጋር ሄደ እሉት።

«ከናንተ ጋር ባድር ደስ ይለኛል። ከናንተ ጋር ባድር ከልቴ ይሰማኛል። ከናንተ ጋር ባድር ከፍቅር ጋር እንዳደርኩ ይሰማኛል። ከናንተ ጋር ባድር ከናንተ ከመጣቴ ጋር አደራለሁ። ከናንተ ጋር ባድር» አላቸው

ቤት ሲደርሱ መሀላቸው ደግፈውት እንዲተኛው አድጊ ላይ ሁቀራ ትንሚቸውን እያላመ

«በጣም በጣም ነው 'ምወዳችሁ፣ እዚች ላይም ላይ እንደ'ናንተ 'ምወደው የለም። መቼ ይሆናል?» እያለ ወደ ቤት ገባ። ትርሲትን መሀል አርገዋት ተኙ።

ሩብ ሰዓት ካለፈ በኋላ ብርሃኑ ቀስ ብሎ «ትግሉን» አለ። መልስ የለም። ጥላሁን ተኝቷል ማለት ነው። ቀስ ብሎ ሙቀቱን መዝጋት ጀመሩ።

«ትርሲትዬ!»

«ጠዬ የኔ ብርሃን!»

«ፃሽሽን አውልቂልኝ»

«እምቢዬ!»

«እባክሽን!»

«ቆንጆ አርገህ ሳመኝና» ሲባባሉ

«ቆ!» አለና ድንገት መብራቱ በራ። ጥላሁን ማብሪያውን እንደቀደ ሲጋራ በጣቶቹ መሀል ይዞ፣ ደም የለበሱ ንልሁ ዐይኖቹን ከፍቶ ነው እያደረገ

«እኔ ምላችሁ» አለ «እንደዚህ ዞናችሁ ፍቅራችሁን ከትግል ቀላችሁና እምባችሁ የቱ የማን እንደሆነ ይታወቃችኋል?» መናቴን ሬሳቱው ስለነበር ከመደንገጣቸው የተነሳ እንደተቀቀቀ ትንፋሻቸውን እንደዋጡ ቀሩ።

«ማለቴ፣ ከመዋደዳችሁ የተነሳ ቁላው የማንኛችሁ እምባል የማንኛችሁ እንደሆን አይጠፋችሁም ወይ?»

«ምን ማለትህ ነው?» አለ ብርሃኑ

«እየህ ብርሃኑ፣ እንደዚህ ነው። እኔ ፍቅር ፍለጋ ነደ ነው ያለሁት።

የፍቅር አጻኝ ይሉሃል ማን ነው? ጥልዬ ነው፡፡ ሌላ መልስ የለውም፡፡ ፍቅር ማለት እንግዲህ ምንድን ነው? አንድ መሆን ነው፡፡ አንድ ታውቃ የለ? ሁለት መሆን ቀርቶ አንድ ትሆናላችሁ፡፡ አንድ፡፡ የምትተቃቀፉት ለዚህ ነው፡፡ አንድ ስትሆኑ እንግዲህ ቁላውም የሁለታችሁ ነው፤ እምሱም የሁለታችሁ ነው፡፡ ገባህ?»

ብርሃኑ ዝም ሲል ጊዜ

«እኔ 'ምፈልገው ፍቅር ነው፡፡ ፍቅር፡፡ እስናቶችን ስበዳት በጣም ጣፍጧት በሀይል ስታቅፈኝ «ምንድነው ሚገባብሽ?» ስላት «መርዘኛው ቁላህ ነዋ ጥልዬ!» ትለኛለች፡፡ እበሽቃለሁ፡፡ እኔ የምፈልገው «ቁላችን ነዋ!» እንድትለኝ ነበር፡፡ «ይሄ እምስ የማን ነው?» ስላት «ያንተ ነዋ!» ትለኛለች «የኛ ነዋ!» እንደማለት፡፡ ገባህ? ጸሩ ምን ይገባሃል? ቁላ ሲነሳ እንኳል ይተኛል፡፡

«ትርሲትዬ፤ ይቅርታ አርጊልኝ ስላቋረጥኳችሁ አለ፡፡ ቀጥሉ

«መፋቂያዬን ጣልኳት ወይስ አስቀመጥኳት? ያለ 'ኳ ምን ዘመድ አለኝ?» አለና መብራቱን አጥፍቶ ተኛ፡፡

አንድ ቅዳሜ ሌሊት እኔአለየማሁ በጥላሁን ምክንያት የደረሰባቸውን ጣጣ አለማየሁ አጫወተኝ፡፡ አለማየሁ መነጽሩን እንደሰካ፤ ዳርጌ ዱቢ ሲጋራውን እንደለኮሰ፤ ቶኒ እጁን ኪሱ እንደከተተ፤ አብርሃም አፍንጫውንና አገጩን እንዳሾለ ከጠባብ አፉ ኩምክናውን እያንጠባጠበ፤ ሁሉም እየቀለዱ Goddamit, the dragon ማለት በመጥረጊያ ግራ ጎኔን ያደማኛል I fuck you in the dragon ማለት በግራ ጎኔ ተቀይሚሻለሁ፤ እያሉ እየሳቁ ከጋዲሴ ቤት ወጥተው ወደ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ማሚት አሹሩሩ ቤት ሄዱ፡፡

እዚያ ጥላሁን ሰክሮ ሲረብሽ ቆይቶ ኖሮ፤ እንደገቡ ማሚት ቶሎ ብላ «እባካችሁን ውሰዱት ይገሉታል» አለቻቸው

በቀኝ በኩል ሦስት ይሆኑ አራት አብረው ቆመዋል፡፡ ለጠብ የተዘጋጁ ይመስላሉ፡፡ አንድ ስድስት የሚሆኑ ሰዎች ከበዋቸዋል፡፡ «ተው 'ንጂ ምን መሆናችሁ ነው? 'ሰክሮ እያያችሁት?» ይሏቸዋል

በግራ በኩል ጥላሁን በአምስት ሰዎች ተይዞ «ልቀቁኝ አረግጣቸዋለሁ!» እያለ ይፍጨረጨራል፡፡ አብዛኛዎቹ ሰዎች በየወንበራቸው ፊት ቆመዋል፡፡ ግማሾቹ በድንጋጤ፤ ግማሾቹ ጠብ ለማየት በመቻኮል እንደተነሱ ቆመው ቀርተዋል፡፡ ሶስት ሴቶች ረብሻውን ሸሽተው መጠጥ መቅጃውን ባንኮኒ የሙጥኝ ብለው ከኋላው ቆመዋል፡፡

ሙዚቃው አይጫወትም፡፡ በአምቧጓሮው ምክንያት ተቋርጧል፡፡

ጥላሁን «እንኳን አራት አርባ ብትሆኑ ግድ የለኝም፡፡ ልቀቁኝማ!» አለና፤ ተመናጨቀ



ከሰዎቹ አንዱ «አራት እያደለንም ባነህ? ምን ጉራ ትነዛለህ? ብቻየን ነኝ፡፡ ልቀቁት እስኪ!» አለና ወደፊት አንድ እርምጃ እግሩ ገና መሬት ሳይነካ ጓደኞቹ ወደ ኋላ ጎተቱት፡፡ «ተው ባክህ! ጠብ ምን ያረጋል? ትዕግስት መራራ ናት፤ ፍሬዋ ግን ጣፋጭ ነው» አሉት

«ምን ላርግ ብላችሁ ነው ወንድሞቼ?» አላቸው «እያያችሁት፤ አርፌ በተቀመጥኩበት ነገር እየፈለገኝ? የመላጣ ልጅ እያለኝ?»

እኔአለማየሁ ግልግሉን ጭቅጭቁን ትንሽ እይተው ነገሩ ከገባቸው በኋላ፤ ለካ ከነዚያኞቹ ሰዎች ጋር በመጠኑ ይተዋወቁ ኖሮ «ለኛ ስትሉ ታገሱት፡፡ ሰክሮ ነው እንጂ ጥሩ ልጅ ነው፤ ታያላችሁ፤ ስካሩ ሲያልፍለት መጥቶ ይቅርታ ይጠይቃችኋል» ብለው ሰዎቹን ለምነው አስታገሱዋቸውና፤ ማሚት ደሞ በበኩልዋ «እባካችሁ ለኔ ስትሉ ወንድሞቼ፤ ቤቴን አትረብሹብኝ በቁልቢው» እያለች ውብ ፊትግታዋን [illegible] በኋላ፤ ከፍለው ሊወጡ ሲሉ «ግድ የለም እያስፈልግም፤ መቼ ተደስታችሁና ትከፍላላችሁ?» እያለች «የለም እንከፍላለን» ብለው ገንዘቡን ሲሰጧት «አይ የናንተ ነገር፤ እምቢ ካላችሁ መቼስ» ብላ ገንዘቡን ተቀብላ በለዘበ ድምፅ እየተለማመጠች፤ በምርጥ ቃላት ማር እየቀባባች፤ በለስላሳ እጇ ትከሻቸውን እየነካካች ወደ በሩ አድርሳቸው ስታበቃ፤ ሦስቱ ወጥተው አራተኛው ሊወጣ የበሩን መጋረጃ በተዘረጋ እጁ ሲይዝ፤ ጥላሁን ሆዬ ሱሪውን በአንዱ ከፍ እያደረገ

«አክ እንትፍ፤ ትዘናም የመላጣ ልጅ ሁሉ! ባሬ ብትሸሹ ነገ አገኛችኋለሁ» አላቸው፡፡ ተመለሱ፡፡ ማለት ጥል የፈለገው ሰውዬ ተመለሰ፡፡ ጓደኞቹ ባንድ በኩል ተው ሊሉት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ምናልባት ጥላሁንን የሚያግዝ ቢኖር እነሱም ጓደኛቸውን ሊያግዙ ተመልሰው ገቡ፡፡ እንደገና ጭቅጭቅ፤ ግልግል፤ ስድብ፤ ልምምጥ፡፡ በመጨረሻ በስንት መከራ ማሚት አስወጣቻቸው፡፡ ሰዉ ተነፈሰ፤ በየወንበሩ ተቀመጠ፡፡ ጥላሁን ዘወር ብሎ (አሁን ጓደኞቹ ለተውታል) መጠጥ ቤቱ ያሉትን ሰዎች «ይቅርታ አድርጉልኝ ወንድሞቼ ጨዋታችሁን ስላቋረጥኩባችሁ፡፡ You are my brozers and country men, or razer, if I may say so, my compatriots. We belong to ze same country and ze same category. I am ready to give you satisfaction አስደስታችኋለሁ፡፡ I am a man of peace እውነቴን ነው፡፡ ሠላማዊ ሰው ነኝ፡፡ ካልነኩኝ አልነካም» አላቸውና፤ ዘወር ብሎ ደም የለበሱ ዐይኖቹን እያፈጠጠ አንዱን አጭር ጠይም ሰውዬ

«አንተ ነህ እኔ ላይ 'ምትስቀው?»

«የለም ጌታ፤ ከሱ ጋር ነው!» አለ ሰውዬው፤ አጠገቡ ያለውን ተደ ባለቆብ ሰውዬ እያመለከተ

«ታዲያ ከሱ ጋር ብትሆን አፈራሀለሁ? ትልቅ ሁለታችሁም፡፡

ሶስቱማም እንዳላችሁ ጨምሩና ኑ፡፡ ኑ»

ዝም

«ኑ 'ንጂ ትዘናም ድንዝ ዙሉ፡» እንአለማየሁ ያዙትና ተው አሉት፡፡ «Sorry my dear broзers, but ሰው ሲሰትብኝ አልወድም I can't stand it!» ትንሽ ተዝቶዝ አለ፡፡

ሙዚቃው መዝፈን ጀመረ፡፡ ዳንስ፣ ቀልድ፣ ሳቅ፣ ጨዋታ፡፡ ጥቂት ሰዎች ከፍለው ወጡ፡፡ ሌሉች ሰዎች መጥተው ተተኩ፡፡

አለማየሁ፣ አብርሃም፣ ቶኒ፣ ዳርጌ ዱቢ አንድ ላይ ቆመው እያወሩ እየሳቁ «Goddamit broomstick! ማለት በመጥረጊያ ይደበድቡኛል፡፡ Testa di casso! ማለት ራሴን ይከብክቡኛል» እያሉ ሲቀልዱ ትንሽ ከቆዩ በኋላ፣ ዳርጌ ዱቢ ሲጋራውን እንደለኮሰ ስለወይዘሮ ብርቱ አንድ ሁለት ነገር አጫወታቸው፡፡ ስለቢች ስለወይዘሮ ብርቱ ማውራት ከጀመረ ሁለት ወር ያልፈዋል፡፡ አንድ ቀን ስለመልኳ ያወራል በሰል ያለች ቆይ ሴትዮ ነች፡፡ አንገቷ ላይ ንቅሳትና ሀብል ከሰመንት መስቀል ይታያል፡፡ እጇ ላይ አምባር፣ ከመዳፏ ጀርባ የመስቀል ንቅሳት አለ፡፡ ብዙ ምን ልበላችሁ፣ ይምበኛ ክርስቲያን ሴት ወይዘሮ ናት ናቸው ማለቴ» ሌላ ቀን ስለትርጂ ያወራል «Shapeዋ ወደመበላሸት ሊዘጅል ምንም ያህል ቀረው ለማለት የሚያስደፍር ባይሆንም፣ ደስ የሚል Shape ነው» አንዴ ስለ ሥራዋ ይነግራቸዋል «እይ ሥራ፣ እኔ'ኮ መንቀሳቀስም የለብኝ፣ ተጋድሜ ተመቻችቼ ቲቪ'ን ማቆም ብቻ ነው» በዚያው አከታትሎ «እቃዋን ያደንቃል ጉቤት ሰቃ እሷ እንደማርጀት አለች እንጂ እቃዋ'ኮ ኘኖ ኘኖ ሕገ ነው፡፡ ስትሞት ለልጅ ልጇ ብታወርሰው አራት አምስት ትውልድ ያገለግላል፡፡ ከርቶ ያገለግላል፡፡ እይ ሲማሩ፣ የፍንድድ ስትሰጥማ አ!

አንዳንድ ጊዜ ስለፍቅሯ ያወራቸዋል «እይ ፍቅር፣ እውነተኛ ተንዞላሟ ዘበኛዬ ፍቅር'ኮ ነው፡፡ ከሥራን በኋላ ሲቸራፉን ታተማቲልለኛለች፡፡ «ትራስ ልለውጥልህ፣ ዱብዬ? ክንዴን ላንተርስህ? ትለኛለች፡፡ ሟት እንቁላል ልጥበስልህ ወይስ ፕንፍልፍል ይሻላሀል?» እዛላለሁ ሌላ ቀን ደግሞ ስለሁቶኛነቷ ይነግራቸዋል «Honestly ያለው ወይዘሮ ብርቱ ቤት ነው፣ ልንገራችሁ አንዳንዴ ምትለኝን ታውቃላችሁ? «አደራ ደህና አድርገህ ብዳኝ ዱብዬ፣ ከአንድ ሁለት ዓመት በኋላ የሚበዳኝ አላገኝም» ትለኛለች

ዳርጌ ዱቢ ስለወይዘሮ ብርቱ ይህን ያህል ሲያወራ እነ አለማየሁ ሊተዋወቋት ይፈልጉ ነበር፡፡ ግን ቤቷ ውስጥ ቢሉት እምቢ አለ፡፡ እሺ አትውሰደን፡፡ ቤቷን አሳየንና እኛ ራሳችን እንሄዳለን አሉት፡፡



«እምቢ ትበዱብኛላችሁ» አላቸው፡፡ ማሉለት «አላምናችሁም» አላቸው፡፡ ነገሩ በዚሁ ቆመ፡፡

«ብዙ ጊዜ ጠፍቼ ቆይቼ» አለ ዳርጌ ዱቢ «ከትላንት ወዲያ ወይዘሮ ብርቱ ቤት ብቅ አልኩ፣ እደር አለችኝ፡፡ አልጋ ውስጥ እንደገባን

«እንሶላዬን ወይም ጭገሬን ሳታቃጥልብኝ ሲጃራህን አጥፋ» አለችኝና፣ አጥፍቼ እሷም መብራቱን አጥፍታ አንዴ ከሞላኋት በኋላ፣ እንደገና መብራቱን አብርታ፣ ሲጋራዬን አቀጣጠለችልኝ፡፡

«ሰሞኑን ጠፋህ ምነው እምዬ?» አለችኝ

«ገንዘብ አጠረኝ እባክሽን»

«ታዲያ ቢያጥርህ ምን አለ? እኔ ሁልጊዜ ገንዘብ እምጣ አልልም'ኮ፡፡ ሲገኝ አስር ብር፣ ሲገኝ አምስት ብር እየሰጠኸኝ ብታድር ደስ ይለኛል፡፡ እሱ ከጠፋ ደግሞ አንድ ሁለት ጥፌ ይበቃኛል»

«ጥፌ?»

«አዎን»

«ጥፌ ጥፌ?»

«አዎን ጥፌ ጥፌ! የፍቅር ምልክት»

«የፍቅር ምልክት?»

«አዎን፡፡ የዛሬ ልጆች ስለ ፍቅር ምንም አታውቁም፡፡ አንዳንዴ ጥፌ ካላቀመስከኝማ ምኑን ወደድከኝ?»

«ታዲያ አሁን አንድ ቃሪያ ጥፌ ባልስሽ?»

«አቡማ የት ተገኝቶ ልጄ?» አለችኝ፡፡ «ግን ልመታት አልቻልኩም፡፡ እሷን የመሰለች ሴት ወይዘሮ እንዴት አድርጌ ልምታ?»

«እንግዲያው ስናደድ መጥቼ እጠፈጥፍሻለሁ» አልኩና ሳም ሳም አሸት አሸት አድርጌ አቆምኩባት፡፡ እሷም በሃይል አቆመችብኝ፡፡ ሰሞኑን አልበዳሁም ነበር Next thing I know የፍንድድ ልሞላት ጀምሬያለሁ፡፡ ታዲያ ብቅ ጥልቅ ሲል በጣም fascinate አድርጎኝ ዐይኔን ከቲሟ መንቀል አልቻልኩም፡፡ እስከ መጨረሻው ሲገባ ሲወጣ ማየት ፈልጌ ነበር፣ ግን እሷ

«ሲኒማው እንዳይደለችህ እምዬ!» አለችና «እፍ!» ብላ መብራቱን አጠፋችው፡፡

አብርሃም ከት ብሎ መሳቅ ጀመረ፡፡ ሌሎቹ አዩት፡፡ እየሳቀ በጣቱ ወደ ዳርጌ እየጠቆመ «ኩራዝ!» አለ

ዳርጌ ዱቢ «እናትክን! ዝም በል!»

አብርሃም «እንዴት ብላ ነው ያጠፋችው?»

ዳርጌ ዱቤ «እናትክን?»

አብርሃም «ለካ ኩራዝ ተራ ስለሆነች ነው ቢቷን አላሳይም ያልከን» ሁሉም ሳቁበት፣ ተንከተከቱ፡ መሳቅ ጀመረ።

«ያፍ ወለምታ ምንም ቢያሳፍር በቅቤ አይታሽም» አለ። የባሰውን ሳቁበት። ጮኸው ከት ብለው ሲስቁ ሳቃቸው ድንገት ተቋረጠ። ጥላሁን ከወዲያ ጠረጴዛውን በኃይል መታና «አይሆንም!» እያለ ተነሳ። አብሮት ይጠጣ የነበረው ቀይ ደቃቃ ሰውዬ ብድግ አለ። ሰው ሁሉ ጸጥ አለ። የሚደንሱት ሰዎች ተቃቅፈው ቆመው ቀሩ። ሙዚቃው ብቻውን ይዘፍናል።

ጥላሁን «እንግዲያው እኔ የአንድ ቢራ ዋጋ ቸግሮኝ ነዋ ትላንት የጋበዝከኝ» አለ

«እንደሱ አይደለም ጥላሁን» አለ ሰውዬው ቀስ ብሎ። በጭራሽ የደነገጠ አይመስልም።

«እንግዲያው ለምን ተራዬን ልጋብዝህ ስል ገንዘብ ይገርለሁ ትላለህ?»

«ኧረ ባክህን እንደሱ ማለቴ አልነበረም»

«ታዲያስ?»

«እሺ ጋብዘኝ» አለ እየሳቀ። ቁጭ አሉ። ሰዉ ተነፈሰ። ግን ያኔውኑ ጥላሁን ብድግ አለና እነ አለማየሁ ባንኮኒው አጠገብ ወደ ቆሙበት በኩል ደም የለበሱ ዐይኖቹን እያፈጠጠ «አንተ፣ ምናባክ ያስቅሃል?» አለ። ከኋላቸው አንድ ወጠምሻ ባለሉጫ ፀጉር ሰውዬ (ኃይለ ሚካኤል) ቆሞ ወደ ጥላሁን በኩል ይመለከታል።

«ኧረ አበት ብላ አባክ፤ በጥርስህ ሳቅኩ?» አለ። ጥላሁን «ጥርስህን ነው 'ማስለቅምህ፤ አዲ'ንክ!» እያለ ሱሪውን በክንዶቹ ከፍ እያደረገ፣ መፋቂያውን በኃይል እየነከሰ፣ ወደ ኃይለሚካኤል መራመድ ሲጀምር፣ አብሮት የነበረው ቀይ ሰውዬና አንድ ሌላ ሰውዬ ከግራና ከቀኝ ያዙት።

«Shit! እኔ ደሞ መፋቂያሽን ነው 'ማስውጥሽ፤ አቡክ!» እነ አለማየሁ ኃይለ ሚካኤልን ያዙት። ዝግ ብለው «እባክህን ወንድም፣ ታገሰው ሰክሯል» አሉት። እሱ ግን ጮክ ብሎ «Shit! ታዲያ ቢሰክር ሌዶ አይተኛም? ምን እዚህ ሰው ያስቸግራል? አሸዋለሁ!» ሁለቱም እንደተያዙ «ልቀቁኝማ! ልቀቁኝማ!»እያሉ መፍጨርጨር ሆነ። እንደገና ሰው ሁሉ ጸጥ አለ። ሙዚቃውም ቆመ።

ብዙ ከተሰዳደቡ በኋላ ውጭ ይዋጣልን ተባባሉና፣ ጥላሁን የያዙትን ሰዎች «እንግዲህ ልቀቁኝ ልውጣበት እ? ነገር አትፈልጉኝ» ብሎ



አመናጭቆ አምልጧቸው ሲያበቃ «ውጭ እጠብቅሻለሁ!» ብሎት ወጣ።

ኃይለ ሚካኤል «በዛው እንዳትሸሺ ብቻ!» አለው። እነ አለማየሁ ቶሎ ተማከሩ። ዳርጌና ቶኒ ጥላሁንን ሊይዙት ወጡ። አለማየሁና አብርሃም ኃይለ ሚካኤል ሂሳቡን ከፍሎ እስኪወጣ ጠብቀው አብረውት ወጡ። እንግዲህ ውጪ ባቡር መንገዱ ላይ ሁለቱ ጥላሁንን፣ ሁለቱ ኃይለሚካኤልን ያዙ።

ጥላሁን «ኩስ ዑመክ! ነይ እንግዲህ አፈር ባስበላሽ» አለው

«Shit! አንቺ ነይ እንጂ ላናፍጥሽ»

«እኔማ ተይገርለሁ!»

«እኔም ተይገርለሁዋ!» ትንሽ ተፍጨረጨሩ። ማምለጥ አቃታቸው። ጥላሁን «ኩስ ኡክትሽ!» አለው

«ጢገ! አቡሽ!»

ጥላሁን «አይ! አሁን ገና የምሬን ተናደድኩ» ሲለው

ኃይለ ሚካኤል «ምን ሆንሽ?» አለው

«ጢገ! አቡሽ! ሲሉኝ አልወድም ል'ባርግ» አለ ጥላሁን ድምፁ ያስፈራል።

«ታዲያ ምን ላርግሽ?»

«ስድብ ለውጪ»

«ኢነዐል ስሊበክ!»

«ኢነዐል በጣጢስክ!» አሁንም ተፍጨረጨሩ። ማምለጥ አልቻሉም። ማምለጥ የፈለጉም አይመስሉም።

ኃይለ ሚካኤል «ግን ያሳዝናል» አለ «እነዚህ ወንድሞቻችን ባይይዙን ኖሮ ለካ እኔና አንተ ልንጣላ ኖሯል። እኔና አንተ፤ ድሬዳዋ ሆነን እንደዛ አብረን እነ ማሚቴ ዞላ ቤት እንጻልጠጣን፣ ከዚራን በሞላ እንጻልረበሽነው ሁሉ!»

«አህ! የድሬዳዋ ልጅ ነህ'ንዴ?» አለ ጥላሁን

«ታዲያስ!»

«አቦ ለምን በፊት አልነገርከኝም?»

«መች ጠየከኝ? የሳቅኩትም ባንተ ላይ አልነበረም'ኮ። ድሮ ድሬዳዋ የምትረብሸው ትዝ ብሎኝ ነው» እነ አለማየሁ እፎይ ብለው ለቀቁዋቸው

«አቦ ጨብጪኝ፣ የድሬዳዋ ልጅ ሳይ ደስ ነው 'ሚለኝ» አለ ጥላሁን

«እኔም» ተጨባበጡ

«የጥንቱ ትገ ይለኛል»

«እኔም ይኸውልህ:: አይ ጥላሁን ረብሻ!» ወደነአለማየሁ እያየ «ስሙን ጥላሁን ረብሻ ነበር የምንለው:: ጥላሁን፣ ያ ሁልጊዜ 'ማይለይህ ረዥም ሱማሌ ጓደኛህ ማን ነበር ስሙ?»

«ሐሰን»

«አ-ዎን! ሐሰን:: ቅዳሜ ማታ ሁለታችሁ የረብሻ ልብሳችሁን ለብሳችሁ መጋሳ ብቅ ስትሉ ሰው ሁሉ ሲርበተበት ትገ ይልሃል?» ወደነአለማየሁ ዞሮ «ሁለቱ መቼስ ድሬዳዋን ሁለት ዓመት ሙሉ አንቀጥቅጠው ገዝተዋታል:: ፖሊሶች ሳይቀሩ ይፈሩዋቸው ነበር:: ሰዓት እላፊ መንገድ ላይ ሲያገኙዋቸው እንኳን ሊያስሯቸው ይቅርና ሠላምታ ሰጥተው ነበር የሚያሳልፏቸው:: ጥላሁንን

«አሁን ግን ቅዳሜ ቅዳሜ የረብሻ ልብስህን አትለብስም» አለ

«ትቼው! ውስጥ ገብተን ለምን አንጫወትም? ነይ አንድ ሁለት ቢራ ሳስተምስሽ»

«የለም እኔ ነኝ የምጋብዝ»

«ኡምሽ! ቀድሜያለሁ»

«ኡክትሽ! እንግዲያው እንዳትረሳ ሌላ ቀን እኔ ነኝ 'ምጋብዝህ»

«ok እንግባ» ተቃቅፈው ስለድሬዳዋ እየተወያዩ ወደ ማሚት እሹሩሩ ቤት ተመልሰው ገቡ::

ጥላሁን ድሬዳዋ ሳለ ለቅዳሜ ረብሻ ብሉ የገዛትን ልብስ፣ ሰማያዊ ቆብ፣ ካኪ ዓይነት ጅንስ ሱሪ፣ ካኪ ሸሚዝ እና ብረት ቦክስ አሁንም አንዳንድ ቀን «ልዩ ጉዳይ» ሲያጋጥመው ይለብሳታል:: ውቤ በረሃ ውስጥ (አንዳንድ ጊዜም አራት ኪሎ፣ መርካቶ፣ ወይም ሌላ ቦታ) ደስ የምትለው ሴት ያየ እንደሆነ፣ በአንድ ሳምንት ውስጥ አንድ ሦስት ጊዜ አከታትሎ አዳር ይወስዳታል:: ከተስማማችው በሁለተኛው ሳምንት እሷ ቤት ማደር ይጀምራል:: መስማማቱ አሁንም ከቀጠለ፣ በአራተኛው ወይም በአምስተኛው ሳምንት አንድ ማታ የረብሻ ልብሱን በጋዜጣው ጠቅልሎ ያመጣና ሴትየዋ ቁም ሳጥን ውስጥ ይሰቅላል:: ከዚያ በኋላ ፍቅራቸው እስኪያልቅ ድረስ ጥላሁን ሌላ ሴት አይተኛም፣ ሴትየዋም በበኩሏ ጥላሁን የረብሻ ልብሱን ከተሰቀለበት ቁምሳጥን አውርዶ በጋዜጣ ጠቅሎ እስኪወስድ ድረስ ሌላ ወንድ ጋ መሄድ የለባትም:: ይህ የጥላሁን ሕግ ነው::

«ሸርሙጣ ነኝ፣ ገንዘቤን ከፍዬ እተኛታለሁ» የሚል /ማለት የጥላሁንን ሕግ አፈርሳለሁ የሚል/ ወይም ቂል መሆን አለበት/ ለምሳሌ ፈረንጅ ሊሆን ይችላል/ ወይም በእውነት ሱሪ ታጥቋል፤ ወይም ደሞ



የሚተማመንባቸው ጓደኞች አሉት ማለት ነው::

ሴትየዋን የሚፈልጋት ሰውዬ ደፍሮ ብቻውን መጥቶ ጥላሁን እዚያው እያለ ሊወስዳት የሞከረ እንደሆነ፣ ጥላሁን በሰላም መንገድ ይሞክረዋል «ስማኝ ወንድሜ፣ እኔ ከዚች ልጅ ጋር የሚያከሳ ፍቅር ይዞኛል:: ላንተ ግን እንዲሁ ደስ ያለችህ ሴት ነች:: እና አዲስ አበባ ሴት ሞልቶ ተርፏል:: ስለዚህ በወንድምነት እቺን ትተህልኝ የፈለካትን ሴት ብትመርጥ ምናለበት?» ይለዋል:: አንዳንድ ጊዜ ሰውየው እሺ ይላል:: ጥላሁን መጠጥ ጋብዞ ይሰደዋል፣ ሌላ ጊዜ ከሰው ጋር ሲጣላ ያገኘው እንደሆነ ያግዘለታል::

አንዳንድ ጊዜ ግን ሰውየው ፈሪ ያገኘ መስሎት ጥላሁንን ማመናጨት ይጀምራል:: ጥላሁን «ወሰን የሌለው ትዕግሥቱን» ያሳያል:: ማለት ሁለት ደቂቃ ያህል መፋቂያውን በኃይል እየነከሰ ዝም ይላል:: ቀጥሎ ጥፊ - ቦክስ - ቴስታ . . . ሰውየው ሌላ ቀን ወደ ጥላሁን እማላጅ ካልላከ ጥላሁን ባገኘው ቁጥር ይደበድበዋል::

ሴትየዋን ለመውሰድ ሁለት ወይም ሦስት ሆነው የመጡ እንደሆን ጥላሁን ቶሎ ብሎ ነገር ይፈልጋቸዋል:: መጀመሪያ ዘሎ የአንዱን ደረት በእርግጫ ያፈርሰዋል:: ቀጥሎ ቦክስ - ቴስታ - ትግል:: ምናልባት አንዳቸው ጩቤ ከመዘዘ ጥላሁን የቢራ ጠርሙስ ሰብሮ ይይዝና እንደተናካሽ አውሬ ነጭ ጥርሱን እያሳየ «ነይ እንግዲህ ልክተፍሽ እንደምንቸት አብሽ!» ይላል:: እስከዛ እንግዲህ ገላጋዮች ይይዙዋቸዋል::

አራት አምስት ስድስት ሆነው ከመጡ ግን ጥላሁን በጭራሽ ነገር አይፈልጋቸውም:: እነሱ ነገር እስኪፈልጉት ይጠብቃል:: ያን ጊዜ እንግዲህ «ወሰን የሌለው ትዕግስቱን» ሳይሆን «አርአያ የሚሆን ትህትናውን» ያሳያል:: ማለት «ወንድሞቼ፣ እኔና እናንተ ምን የሚያጣላን ነገር አለ? ሁላችንም ኢትዮጵያውያን አይደለንም? ያገር ልጆች አይደለንም? ስለዚህ መፋቀር እንጂ መጣላት ተግባራችን አይደለም:: አጥፍቼ 'ንደሆነ፣ ሳላውቅ እናንተን ወንድሞቼን አስቀይሜ 'ንደሆን ትልቅ ይቅርታ እለምናለሁ» ብሎ፣ አንድ በአንድ ጨብጧቸው ሒሳቡን ከፍሎ ይወጣል::

ሰዎቹ ይሳሳቁና መጠጣት - መጫወት - መደነሳቸውን ይቀጥላሉ:: ከአንድ ሦስት ደቂቃ በኋላ አንድ እነስ ያለ ሰውዬ፣ ሰማያዊ ቆብ፣ ካኪ ሸሚዝ፣ ካኪ ጅንስ ሱሪ ለብሶ ይገባና፣ ቀስ ብሎ መውጫውን በር ይዘጋል::

ጮክ ብሎ «ወንድሞቼ! የፊት በር ተዘግቷል:: በጓሮ በር የሚወጣ ደሞ ፈሪ ነው:: እንግዲህ ምን ትሆኑ?» ይልና ቆቡን ወደ ላይ ይወረውራታል:: ሰዎቹ ገና አልገባቸውም፣ በዐይናቸው ቆቧ ጣራውን

መታ መሬት ሳትነካ እስኪከተሏት ዘሎ ተወርውሮ ያንዱን ደረት በርግጫ ደልቆ፣ ሌላውን በብረት ቦክስ አጋድሞ፣ ሦስተኛውን ሊገጥመው ይጀምራል:: ረብሻው ቢበዛ አንድ ደቂቃ ቢፈጅ ነው:: ወይም ገላጋዮች ሁሉንም ይይዙዋቸዋል፣ ወይም ሰዎቹ መሸሽ ይጀምራሉ. . . ጥላሁንም ወጥቶ ይሄዳል:: ከአምስት ደቂቃ በኋላ የበፊት ልብሱን ለብሶ ይመለስና ቢራ ያዛል:: ግን ይሄን የረብሻ ልብሱን የሚጠይቅ ልዩ ጉዳይ ጥላሁንን ብዙ ጊዜ አያጋጥመውም:: ወሬው በየሴቱ ቤት ስለሚነዛ ብዙ የሚደፍሩ ሰዎች የሉም::

አንድ ሰሞን መርካቶ አንዲት ሴት ነበረችው:: አንድ ሌሊት ሦስት ጓደኞቹን የረብሻ ልብስ ሳይለብስ እንደዚሁ ደብድቦ አባሮ ሲያበቃ፣ ከዚች ከሚስቱ ጋር ተኝቷል:: ወደ ዘጠኝ ሰዓት ላይ (ሰዓት ሲያበቃ፣ ከዚች ከሚስቱ ጋር ተኝቷል:: ወደ ዘጠኝ ሰዓት ላይ (ሰዓት እላፊ የሚሉት ነገር ከተረ በኋላ ነው) በሩ በኃይል ብርግድ ሲል ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው:: ዐይኑን ሲከፍት ኃይለኛ ባትሪ ፊቱ ላይ በርቷል:: ምንም አይታየውም፣ ብቻ ባትሪው ዐይኑን ይወጋዋል:: ዐይኑን እየጨፈነ «ማን ነው?» አለ:: ጓደኞቹ ሰክረው ሊረብሹት የመጡ መስሎታል::

«ማናባክ ቢሆን ትወዳለህ?» አለው አንድ የወንድ ድምጽ:: ኮረንቲው መብራት ሲበራ ያኔውኑ ቁጥራቸው የማይታወቅ ሰዎች ራቁቱን አልጋ ውስጥ እንዳለ ላዩ ላይ ወደቁበት:: እጆቹን ያዙት:: ሌላ ሰውነቱንና እግሮቹን አንሶላ ብርድልብስ አስሮታል:: ልክ ቅዥት ውስጥ ያለ ይመስል መንቀሳቀስ ተሳነው:: ሴትየዋ ኡ ኡ! ድረሱ! ብላ መጮህ ብትጀምር በጥፊ ብለው ዝም አሰኟት:: ከዚያ ጥላሁንን በጥፊ፣ በቦክስ፣ በከርን፣ በእርግጫ ወረዱበት:: እሱ ሁለመናው ታስሮ በአፉ ብቻ «ሴቶች! አገኛችኋለሁ:: ቅዘናሞች! እስቲ ልነሳና ግጠሙኝ! ፈሳሞች! የቊለማ ልጆች!» ይላቸዋል:: ለዚያውም ለአንድ ቃል ሁለት ሦስት ቦክስና እርግጫ ስለሚያቀምሱት፣ ጥቂት ከሰደባቸው በኋላ ብሾ አለበት:: መሳደቡን ተወ:: ፍዝዝ አለ:: የሚመቱት ሁሉ አያመውም «ብቻ መፋቂያዬን እንዳይወስዱብኝ» ብሎ አሰበ:: በሃሳቡ ገረመው:: ቀስ ብሎ ጨለማ ዋጠው::

ዐይኑን ሲከፍት ሴትየዋ ብቻዋን ቆማ የሚታጠብ ሰው ያመስል እጆቿን እያሻሸች «ሞቶ! ምን ተረፈ? ሞቶ! ምን ተረፈ?» እያለች ትደጋግማለች::

«ደሊት ሐጂና ውሃ አምጭልኝ» አላት:: ደም በደም ሆኗል:: በነጋታው ተኝቶ መዋል ግድ ሆነበት:: ግራ ዐይኑ አብጦ ሶስት ቀን ሙሉ በጭራሽ አላያለት አለ:: ጥላሁን እንዲህ ዓይነት ነገር አልፎ አልፎ ያጋጥመዋል:: ግን ስለዚህ መስማት ከፈገከ እሱ ራሱ ይነግርሃል:: ምክንያቱም የረብሻ ወሬ በተነሳ ቁጥር ሰዎች ስለሰሩት ጀብዱ ሲያወሩ፣ እሱ ይቀበልና እንዴት እንደደበደቡት፣ እንዴት ጉድ እንደተሰራ፣



እንዴት ፍዳውን እንዳስጨረሱት፣ እንዴት እንደ ትራሳ እንዳለፋት በሰፊው ያወራል:: ብቻ አስታውሶ ባያወራልህ ነው እንጂ ከደበደቡት ወይም እንደ ኳስ በቦክስ ከተቀባበሉት በኋላ መርካቶና በረሃ መምጣት በጭራሽ ካላቆመ በቀር አንድ በአንድ አድኖ ይወድቀዋቸዋል:: ዓመትም ሁለት ዓመትም ይፍጅ እንጂ በተሉን መጠጣቱ አይቀርም:: ብቻ የረብሻ ወሬ ለጊዜው ይብቃን:: የሠላም ወሬ እናምጣ::

ቢሾፍቱ ውስጥ ትንሽ ባለሁለት ክፍል ቤት ተከራይተው የሚኖሩ አንዲት አሮጊት ያሉ ሴትዮ አሉ:: ኪራዩንና የገረዳቸውን ደመወዝ፣ እንደዚሁም ለኑሮዋቸው የሚያስፈልገውን ገንዘብ የሚችልላቸው አዲስ አበባ የሚኖር ልጃቸው ነው:: ልጃቸው እሱ ብቻ ነው:: እሁድ እሁድ እየመጣ አብሯቸው ይውላል:: ዓመት በዓል ሲሆን እሱ በግ ያርድና እላቸው ዱለት ሠርተው፣ ጠላም ጠምቀው በደንበ መሠረት በዓሉን እናትና ልጅ አብረው በሠላም ያሳልፋሉ:: ከምሳ በኋላ ጎረቤት ሁሉ ለቡና ወይም ለጠላ ይጠራል:: ይሄ ልጃቸው እላቸው ሳያውቁ በየወሩ ባንክ ሀምሳ ብር ያስቀምጣል:: አሁን ሁለት ሺ ሦስት መቶ ብር ሞልቶለታል:: ሦስት ሺ ብር ሲሞላለት እናቱ የሚኖሩበትን ቤት ከነመሬቱ ገዝቶ ይሰጣቸዋል:: ከባለቤትየው ጋር ውል አለው:: በሦስት ሺ ብር ከዚያች የበለጠ ቤት ለመሥራት እንደሚችል ያውቃል:: ግን እናቱ ይቺን ቤት በጣም ይወዷታል:: ብዙ ጊዜ ኖረውባታል «ደግሞ እማማ በዚህ ዕድሜዋ ጎረቤት ስትለቀውጥ ምን መጣባት?» ይላል:: በዚህ ላይ የሕይወት ዋስትና አለው:: ድንገት የሞተ እንደሆነ አስር ሺ ብር ያገኛሉ:: እንደ ብዙዎቻችን የአዲስ አበባ ጎረምሶች ደህ ወጣት ደጃች ውቤ ሰፈርን ያዘወትራል:: ሰዎች እንደሚሉትም ደሞዙን በሙሉ በየሴቱ ቤት ነው የሚያጠፋው:: ደኼ ብቻ ሳይሆን ስለሱ ሲያወሩ «ጥላሁን ረብሻ! ውሃ ቀጠነ ብሎ ይጣላሀል» ይላሉ::

ጥላሁን አንድ ቀን በሕማማት ሰሞን አግኝቶኝ «ሁሌ ብቻኛ መሆን ጥሩ አይደለም» ብሎ ፋሲካውን ከሱና ከናቱ ጋር እንዳሳልፍ ወደ ቢሾፍቱ ወሰደኝና ሦስት ቀን ከእናቱ ጋር አሳልፈን ወደ አዲስ አበባ ስንመለስ፣

«እናት እንዳለህ አላውቅም ነበር» አልኩት

«ማንም አያውቅም» አለኝ

«ለምን?»

በፊጠኑ በተቆራረጠ አነጋገር እንዲህ አለኝ «በጣም ነው 'ምወዳት እማማን:: እሷ ብቻ ነች ያለችኝ:: ለሷም እኔ ብቻ ነኝ ያለኋት:: ድሮ ጅማ የቡና ርስት ነበረን:: በጣም ሀብታም አልነበርንም፣ ግን ደህና ነበርን:: አባቴ ሲሞት ራስ ወልደአማኑኤል (የኳሳ አባት) ርስታችንን ነጠቁን:: ያኔ የአምስት ዓመት ልጅ ነበርኩ:: እማማ ይዛኝ አዲስ አበባ

መጣች:: እቤት አለች:: ፍርድ ቤት ተንቀዋለለች:: ተንከራተተች፣ ወገን ስለሌላት፣ ቤት ስለሆንች እና ስላልተማረች እንለፈው እሱን:: እማማ ስለሱ ባወራች ቁጥር እንዳለቀሰች እድ... የሆን ሆኖ፣ ጅማ መመለስ አልፈለገችም:: እዚሁ አዲሳባ ቀረች፣ እንጨት እየለቀመች፣ ልብስ እያጠበች፣ በየፈረንጅ ቤት ገረድ እየተቀጠረች አሳደገችኝ - አስተማረችኝ - ሰው አደረገችኝ:: ሁለተኛ ደረጃ ስጨርስ አዳሪ ትምህርት ቤት ገባሁ:: ችግር ትንሽ ተቀነሰ...

«High school እንደጨረስኩ ድሬዳዋ ሥራ አገኘሁ:: ደሞዜን በቅድሚያ ተቀበልኩና ቆንጆ የሀበሻ ቀሚስ አስፋሁላት:: ውሬ ከመልበስ ወጣች:: አባቴ ከሞተ ጀምሮ አዲስ ልብስ ስትለብስ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነበር:: አቀፈችኝና አለቀሰች:: እኔም አለቀስኩ... ለከፍተኛ ትምህርት ኮሌጅ መግባት በጣም ፈልጌ ነበር፣ ለማማ ስል ተውኩት:: ወድጄ ነው የተውኩት ታውቃለህ? ግን እንዳን... ይቆጨኛል:: በተለይ G.C.E ያቦንንኳቸው ሁሉ ኮሌጅ ጨርሰው እሚ... ሲሄዱ ሳይ በጣም ነው'ሚቆጨኝ:: ግን ለማማ ስል እንኳን እሚ... መንግሥት ስማያት ቢቀርብኝ ግድ የለኝም::

«ካንተ በቀር ማንም ሰው የማማን መኖር አያውቅም:: እሙቶዬ... ለምን እንደሆነ? ሀበሻ ምቀኛ ነው፣ እየሀ:: ልጅሽ ሰካራም ነው... ሸርሙጣ ቤት ነው መኖሪያው፣ አሁን በጨቤ ወግተው ይገሉታል... እያሉ ያስቃዩብኛል:: አሁን ግን ደስ ብሏት ነው 'ምትኖረው እየተዝ...

«በጣም እድለኛ ነህ» አልኩት

«አውቃለሁ:: እማማ ሌላ ሴት ብትሆን ኖሮ ኩሊ ወይም የመርካቶ ማጅራት መቺ ሆኜ ነበር:: አንተ ግን - ለምን ሁልጊዜ ብቻ... ትሆናለህ? እሁድ ወይም እመት በአል ሲሆን አንዳንድ ቀን እየመጣ... ከኛ ጋር ብትውል ምን አለበት?»

ተመልከት እንግዲህ:: ከፒያሳ ወደ ደጃች ውቤ ሰፈር ስትወ... በንርጊስ በኩል ታልፋለህ:: ዳግማዊ ምኒሊክ አደባባይ:: መሃሉ ላ... በአትክልት የተከበበ ሀውልት:: አጤ ምኒሊክ ጋሻ ጦራቸውን ይዘው የክብር ልብሳቸውን ለብሰው ዘውዳቸውን ደፍተው በፈረስ ወደ እንጦ... በኩል ሲጋልቡ:: ወደ ግራቸው በኩል ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያ... ከግንቡና ከዛፎቹ ኋላ ተደብቆ ድብልብል ራሱን ብቅ አድርጎ አ... ምኒሊክን ያያቸዋል:: ወደ ቀኛቸው በኩል የዶሮ ማነቂያ እር... ቆርቆሮዎች ተዝረከርከዋል:: ቀኛቸው ጋ፣ እዚያው አጠገባቸው አውቶቡስ ማቆሚያው የደከመ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ለብሶ ይጠብቃል:: አንድ ሁለትና ሦስት ቁጥር አውቶቡሶች ቢጫና ቀይ ልብሳቸውን ለብሰው እያቃሰቱ ከፒያሳ በኩል ይመጡና የሀውልቱን የብረት አጥ...



ዞረው ፊታቸውን ወደ ፒያሳ በኩል መልሰው ሲያበቁ፣ በግራ ጎናቸው ጥቂት ሰው ይተፋሉ፣ ጥቂት ሌላ ሰው ያነሳሉ:: እዚህ ቦታ አውቶቢስ ተሳፋሪዎች፣ ሊስትሮዎች፣ ሥራ ፈቶች ሲንተረፈፉ ታያለህ - ቀን የሆነ እንደሆነ:: ማታ ግን!

የምታየው ሌላ ትርኢት ነው:: በግምት ከሦስት እስከ ስድስት ሰዓት ላይ ቁጥራቸው ከሦስት እስከ ስምንት የሚሆኑ ሴት ልጆች እዚህ ቦታ ላይ በኮረንቲ መብራት ይንጎማለላሉ፣ ይላፋሉ፣ ይሯሯጣሉ፣ ወይም ቆመው እያወሩ ያስካካሉ:: ዕድሜያቸው ከአሥራ ሦስት እስከ አሥራ ዘጠኝ ይሆናል:: ልጆች ናቸው:: ለዚህ ነው 'ሚንጎማለሉት፣ 'ሚላፉት፣ 'ሚሯሯጡት በበጋ:: በክረምት ግን ጭቃው፣ ዝናቡ፣ ብርዱ የልጅነት መንፈሳቸውን ስለሚያፍነው እዚያ 'ሚገኙት ቤቶች ግድግዳ ሥር ይቆማሉ:: ቆርቆሮው ከዝናብ ያስጠልላቸዋል — ወጨፎ ከሌለ:: አንዳንድ ቀን እየረመሉ ይስቃሉ:: አብዛኛውን ጊዜ ግን ተከናንበው ሁለት ሁለት እየሆኑ ዝም ብለው ይቆማሉ - በክረምት::

በጋም ሆነ ክረምት እነዚህ ልጆች አላፊ አግዳሚውን በዐይናቸው ይቃኛሉ:: ምንድን ናቸው? እምስ ናቸው:: ወጣት እምስ፣ ርካሽ እምስ:: እነሱን መብዳት ልዩ ልዩ ጥቅም አለው:: ጥቅሙንም ከረዥሙ ባጭሩ፣ ከብዙ በጥቂቱ፣ ከሰፊው በጠባቡ፣ ከደረቁ በእርጥቡ እንገልጸዋለን፣ እንደሚከተለው

ሀ/ ወንድነትህ በግልጽ እንዲሰማህ ብትፈልግ እነዚህ ልጆች ገና ቁላ ስላለመዱ መጀመሪያ ላይ ድንገት በኃይል የከተትክባቸው እንደሆን ከመጠን በላይ ስለሚያማቸው «እህ» ብለው ኩምትር ሲሉ ይታወቅሃል:: ለራስህ «እኮማተርኳት፣ እንዲህ ነኝ እኔ የነውዬው ልጅ!» ትላለህ:: ደሞ እውነትክን ነው:: አባቶቻችን ማይጨው ላይ ከዚህ የበለጠ ጀብዱ ሰሩ ለማለት የሚያስደፍር አለመሆኑን ለማረጋገጥ ያህል ብቻ ሳይሆን፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ጉልማሶች ያልበሰሉ ልጆች እምስ ለመብዳት፣ ሀሩርና ሜዳ ውስጥ ሦስት ሺ ዓመታት ሙሉ አባቶቻችን ያቆዩልንን ቁላ እንደ ነፃነት ሐውልት አውጥተን፣ ለጀብዱ ተዘጋጅቶ ያለ እንዳች ፍርሃት ትርትር እያለ እየፎከረ እየሸለለ ተንደርድሮ፣ ያለ እንዳች ቅሬታ ትንሽ ልጅ እምስ ውስጥ ገብቶ ደሙን አፍስሶ አጥንቱን ከስክሶ፣ ግራኝን በደፈሩ ፋሽስትን ባበረሩ ጥንታዊያን አባቶቻችን ምሳሌ አርአያና አብነት እየተመራን፣ እግዚአብሔርን ፈርተን ሰይጣንን ሸሽተን ከመኖራችንም በላይ፣ በሥራ ላይ ለገመን አፋችንን ለጉመን ጻዊታችንን ደግመን . . . አንድ ሀሳብ ለመግለጽ ነበር የተነሳሁት፣ ግን ሀረፍተ ነገሩን መጨረስ አልቻልኩም:: ስለዚህ ወደ ሁለተኛው ጥቅም መሻገሬ ነው::

ለ/ የቁላ ሳይሆን የመንፈስ ወንድነት እንዲሰማህ ከፈለግክ፣ ደሞ

«የሕዝቡ ግብረገብ ትንሽ ልጅን በግብረ ሥጋ አትገናኝ ቢል ግድ አለኝ? ሰው አይጠተው እንጂ፣ ካሰኘኝ እንኳን ያስራ አራት ዓመትና ያሬት ዓመትም እምስ እበዳለሁ። እኔ የሰውዬው ልጅ!» ትላለህ

ሐ/ ሕሊናህን ማስቃየት ደስ ይልህ እንደሆነ፣ ከሁሉ ትንሽ የሆነችውን ልጅ መርጠህ ስትበዳት «ስንት አመትሽ ነው?» በላት «አስራ ሦስት» ስትልህ ለራስህ እንዲህ በል «አቤት የጊዮርጊስ ያለህ! እንዴት ተበላሽቻለሁ! የአሥራ ሦስት ዓመት ህፃን ስበዳ!» ከዚህ በኋላ «አፈንድጅ!» በላት። በዕፍረት እየተቁነጠነጠች በትንሽ ልጅ ድምጽ «እንዴ! ምንድነው?» ስትልህ «ሁለት ብር እጨምርልሻለሁ» በላት። ታፈንድዳለች። ስትከትባት ለራስህ «ወይ አንቺ እምዬ ማርያም! የአስራ ሦስት ዓመት ልጅ አስፈንድጄ ስበዳ እናቴ ቢያዩኝ ምን ይሉኛ?» በል። ከዚያ ቀጥለህ ይሄኔ እንዳልደነግጥና እንዳልተዋት ገንዘቡ እንዳይቀርባት ፈርታ ነው እንጂ ገና አስራ ሁለት ወይ አስራ አንድ ዓመቷ ነው» በል ሕሊናህን እንደልብህ ታሰቃየዋለህ። ከፈለግህም በድተሃት ስታበቃ ሳትከፍላት ሂድ። ወይም እየበዳሃት ለራስህ እንዲህ በል «ይቺማ የእህቴ የአልማዝ እኩያ ናት። ይቺን አሁን እንደምከትባት አንዱ ደሞ አልማዝዬን ቢከትባትስ? አስፈንድዶ? አልማዝዬን? ውይ! እግዚአብሔር አያርገው!» ሦስት ሺ ዘመን እናቶቻችንን የጠበቀ እግዚአብሔር እህትህን አልማዝንም ከእንዲህ ዓይነቱ ኑሮ ይጠብቃታል። ብቻ እማን ... ሜና - መጋረጃ ስጠው። እለዛ አይጠብቅልህም ዋ! እሱም ጉቦ እየማመው ሂዷል ይባላል። ዳኞቻችንን - ፖሊሶቻችንን - ሹማምንቶቻችንን እያየ፣ የጉቦን ጣዕም እየተገነዘበ አልሔደም ብንል ከስህተት ይቆጥርብን ይሆናል ብለን ባለማመናችን አለመሆኑን ለማሳሰብ መሆኑ ለማንም የተሰወረ አለመሆኑ ቢታወቅም ቅሉ፣ መንግሥትን ለማጥት ... ቡራኬን ለሲም - ዕድሜን ለማቱሳላ - መዝሙርን ለያሬድ የሰጠ፣ ሰማይን ያለ ባላ ምድርን ያለ ካስማ የዘረጋ፣ ሁሉም የማይሳነው፣ ምንም የማይስማው አንዳችም የማይታየው ... ተሳሳትኩ መሰለኝ ጃል! እሁንም ሀረፍተ ነገሩን ለመጨረስ አልቻልኩም። ግን ጥሩ ጀ'መሬ ነበር። አንድ ትልቅ ሹም በሬዲዮ ሲናገር የሰማህ አልመሰለህም? ብቻ ትንሽ ልጅ ከመብዳት ራት ሳንል ቀረን ለማለት አያስደፍርም። ስለዚህ እንመለስ ወደ እምሳችን። እሱ ነው 'ሚያዋጣን።

መ/ አሁን እንግዲህ ወደ ዋናው ጥትም መጣን። ይኸውም ገና ብዙ ቱላ ያላሰፋው ያላጨማለቀው ወጣት ጠባብ እምስ ባንዲት ብር ብቻ መብዳት ነው። እስታውስ፣ ውቤ በረሃ ውስጥ አንድ ጊዜ ለመብዳት የመጠጡና የእምሱ ዋጋ ተደምሮ ከአምስት እስከ አሥር ብር መክፈል ያስፈልጋል።



የሆን ሆኖ፣ አንድ ማታ ከፒያሳ ወደ ውቤ በረሃ ለመሔድ እነዚህ ሕፃናት ሽርሙጦች አራት ሆነው በቆሙበት በኩል ሳልፍ አንዷ፣

«ስንት ሰዓት ነው ጋሼ?» አለችኝ

«አምስት ከሩብ» ብዬ ሳልፍ ስል፣ በሹክሹክታ

«ጠይቂ. . . አንቺ ጠይቂ. . . እፈራለሁ. . .» ሲባባሉ ሰማሁ

«ጋሼ ባ'ክን ይቅርታ አይቆጡ» አቋረጠች። ቆምኩ «ምንድን ነው?» አልኳቸው። አራቱም ነጠላ ተከናንበው፣ የፈረንጅ ቀሚስ ለብሰው፣ የሱማሌ የሚባለውን ነጠላ ጫማ አድርገዋል።

«ጠይቂያቸው» አለች አንድዋ ሌላዋን እየገፋፋቻት። ድፍረት ለመስጠት ያለችው ነው።

«ጋሼ ጥላሁን የት ጠፋ?» አለች ከሁሉም አጠር ያለችው

«ምን?» አልኳት! በሀሳቤ «ጥላሁን እዚህ እየመጣ ይበዳ ይሆን እንዴ? አንዷ የሱ ፍቅር ይዟት ይሆን የምታስጠይቀው?» አልኩ። ግን ነገሩ ሌላ ነበር።

ለካስ አንዳንድ ማታ ጥላሁን ወደ ውቤ በረሃ ሲሄድ ወይም እዚያ አምሽቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ በነዚህ ልጆች በኩል ሲያልፍ፣ ልክ እምስ ፍለጋ እንደመጣ ሰው ዓይነት አንዷን ጠርቶ፣

«አንቺ፣ ባንድ ሌሊት ስንት ታገኚያለሽ?» ይላታል

«ሁለት ወይ ሦስት ብር» ስትለው

ከኪሱ ሦስት ብር አውጥቶ ይሰጣትና «በይ ሂጂ ተኚ» ብሏት መንገዱን ይቀጥላል። እንዲህ ሲል፣ ዛሬ ለአንዷ ሶስት ብር ሲሰጥ፣ ተነገ ወዲያ ለሌላዋ ሁለት ብር ሲሰጥ፣ ቀጥሎ ለአንዷ አራት ብር ሲሰጥ. . . ቀስ በቀስ ተለማምደው፣ ስማቸውን ነግረውት ስሙን ነግሯቸው . . ከጊዜ ብዛት ተዋውቋቸው. . . ብዙ ገንዘብ የሌለው ጊዜ ከረሜላ - ማስቲካ ገዝቶ እያካፈላቸው. . . ሲል ሲል ጓደኛ ሆኗቸው፣ ሲጣሉ እያስታረቀ፣ ሲታመሙ መድኃኒት ገዝቶ እየሰጠ. . . እንደ ወንድም ሆኗቸው።

በኋላማ ገንዘብ ሲሰጣቸው እምቢ ማለት ጀመሩ። እሱም ገባውና ገንዘብ መስጠቱን ተወ። ሲታመሙ ብቻ መድሃኒት ይገዛላቸዋል። ዓመት በዓል ሲሆን ሐገር ፍቅር ሔደው ቲያትር እንዲያዩ ለያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ብር ይሰጣቸዋል። እና ቀጥሎ በሚመጣበት ቀን ያዩትን ቲያትር እየተሻሙ ወይም ሁሉም በአንድ ላይ እየተናገሩ ያወሩለታል፣ አብረው ይስቃሉ፣ እንዳንዱን ዘፈን ይዘፍኑታል። አብሯቸው ይዘፍናል። እንዴት እንደሆነ እንጃ፣ እሱም እነሱም ሳያውቁ አንድ ቀንጆ ፕሮግራም አወጡ፣ ቅዳሜ ቅዳሜ ማታ ወደ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ ሻይ እፍልተው



Meysor Bro
t.me/BooksandYou

ይጠብቁታል። እሱ ከኪንግ ጆርጅ ባር በየዓይነቱ ኬክ ገዝቶ ይመጣል። እስከ ሦስት ሰዓት ድረስ ሻይ እየጠጡ ኬክ እየበሉ ካርታ እየተጫወቱ ያመሻሉ። አንዳንዴ በሲኒማ ያየውን የጉብዝና፣ የቦክስ፣ የተኩስ፣ የፍቅር ታሪክ ያጫውታቸዋል። ወይም አቶ ከበደ ሚካኤል የተረጎሙትን የሼክስፒርን «ሮሜዮና ጁሊየት»ን ያነብላቸዋል። ወይም ደሞ በአረብኛ ያነበበውን አስደናቂ የጂኒ፣ የኢፍሪት፣ የጠንቋይ፣ የፍቅር ታሪክ ሲያወራላቸው ቃል ሳይተነፍሱ አፋቸውን ከፍተው ይሰሙታል። ሦስት ሰዓት ሲሆን ደህና እደሩ ብሏቸው ይሄዳል።

አሁን ግን ካዩት ይኸው ሁለት ሳምንት አለፈ። ለዚህ ነው እኔን ሳልፍ አስቁመው የጠየቁኝ

«የት ጠፋ? ታመመ? ጓደኛው ኖት ብለን ነው የጠየቅኖት. . . በዚህ አብራችሁ ስታልፉ ሁሌ እናያችኋለን። ደህና ነው? ውጭ አገር ሄደ'ንዴ? ምነው ጠፋ?» ይህን ሁሉ ጥያቄ አንድ ላይ ወረወሩብኝ።

«እኔም እንደናንተው ነኝ። ካየሁት ሦስት ሳምንት ሆኖኛል» አልኩና ደህና እደሩ ብያቸው መንገዴን ቀጠልኩ።

ያን ሰሞን ጥላሁን በጨቤ ተወግቶ ሐኪም ቤት ተኝቶ ነበር። ሄድኩና፣ «ጎርጊስ አውቶብስ ማቆሚያው አጠገብ የሚሰሩት ትንንሽ እህቶችህ ብዙ ሠላምታ ያቀርባሉ» አልኩት

«የምን እህቶች?» አለኝ። ከንፈሩ በፈገግታ መወለድና መጥፋት መሀል ይርበተበታል

«እሱን ተወው! የት ጠፋ ብለው ሰግተዋል» አልኩት

እየሳቀ «አንተ በቃ ስራህ እየዞሩ የሰው ጉዳይ ማሽተት ሆነ?» አለኝ ታሪኩን አጫወተኝና ሲያበቃ «ነገሩን ማወቅህ ካልቀረ ሒደህ አስራ አምስት ብር ስጥልኝና አገር ፍቅር መሔጃ ነው በላቸው። ድኜ ስነሳ እከፍልሃለሁ» አለኝ።

ያለኝን ገንዘብ ለልጆቹ ልሰጥለት ስሄድ ከሁለት ዓመት በፊት ማሚት እሹሩሩ ቤት ያየሁት ነገር ትዝ አለኝ. . .

አስታውሳለሁ፣ ቀኝ እግሬን ወለም ብሎኝ ያን ሰሞን ከዘራ እየተመረኮዝኩ ነበር 'ምዞረው። እያነከስኩ ማሚት እሹሩሩ ቤት እንደገባሁ ባንኮኒው ጋ ቆምኩ። ሙዚቃው የሱዳን ዘፈን ነው። አንድ አራት የሚሆኑ ወንዶች ከሴቶቹ ጋር እርስ በርሳቸው እየተሳሳቁ ቫልስ ይደንሳሉ። አረብኛና አማርኛ እያደባለቁ ጮክ ብለው ያወራሉ፣ ሴቶች ይዘው የተቀመጡትም ሦስት ወይ አራት ሰዎች ከሚደንሱት ጋር ይጫጫሃሉ። ሁሉም በአንድነት የመጡ ይመስላሉ። ቤቱ ውስጥ ሁለት ሌሎች ሰዎች ብቻ አሉ፣ ከነሱ ጋር የሚተዋወቁ አይመስሉም።



አንዱ ካሳ ወልደአማኑኤል ነው «ዛሬ ጭፍሮቹ የት ሒደው ይሆን?» ብዬ እያሰብኩ ከሩቅ ሠላምታ ሰጠሁት። ሌላው ሰውዬ ግን እንደሆን እንጃ፣ ነጭ የሳር ባርኔጣ አድርጎ፣ ባፉ መፋቂያ ሰክቶ እንደኔው ባንኮኒው ጋ ቆሟል። በቁመቱም በውፍረቱም መጠነኛ ነው። ጠይም ዐይኖቹ ንፁህ ሆነው በጣም ያምራሉ። አንዲት ጠይም ሴትዮ ከባንኮኒው በስተጓላ ቆማ ከሱ ጋር በለስላሳ ድምፅ ታወራለች። ፊቷ በጣም ደስ ይላል፣ ደግ የደግ መጨረሻ ትመስላለች። እንደገባሁ ደስ በሚል ለስላሳ ድምጽ «ምን ልቅዳልዎት?» አለችኝ። «መሎቲ»

ሰዎቹ ይጮሃሉ፣ ይስቃሉ፣ ቫልስ ይደንሳሉ፣ ዳንሱ መሀል ሴት ይለዋውጣሉ፣ የሴቶችን ቂጥ በእጃቸው መታ ያደርጋሉ. . . «ኢንአል አቡሽ! የቂጤን አደጋ ይስጥህ!» አረብኛ በብዙ ይናገራሉ፣ ግን ግማሾቹ ሀበሾች ናቸው የሱዳኑን ቫልስ አምስት ጊዜ ያህል «ቢስ» እያሉ አስደገሙት። አንድ ስድስት ሴቶች አብረዋቸው እየጠጡ እየደነሱ ያስካካሉ «ሂድ! ኢንአል ዑምሽ!» ይላሉ «አንቺ ደሞ ትርጉሙን ሳታውቂ ዝም ብለሽ!» ይባባላሉ። እንዲህ ሲጫወቱ ሲደሰቱ ስመለከታቸው፣ የቀልድ አንዷን ሴትዮ ወንዶቹ ለሁለት ያዙና ሁለት እጆዋን ጠምዝዘው አስጎነበሷት።

«ልቀቁኝ እንግዲህ!» አለች። አምርራለች። እነሱ ግን ይስቃሉ። አንደኛው «ወይዘሮ ሙሉ ደሞ ምን ሆኑ?» እያለ እጁን ቀሚሷ ውስጥ ከተተና ቂጧን አሻሻት።

«ልቀቁኝ?!» አለችና ጮኸች። ሰውየው እጁን ከቀሚሷ ስር አወጣና አሽተተው።


«እፍ! ይገማል» አለ እየሳቀ።

«ቆሻሻ አረብ!» አለችው። ተናደደ። ቆጭ ካሉት ሰዎች አንዱን ጠራና በአረብኛ ምናምን ነገረው። ሰውየው መጣና የተጠመዘዘ እጇን ተቀብሎ ያዘላት። እሷ ትፍጨረጨራለች። ሙዚቃው ይዘፍናል። ሰዎቹ እየደነሱ ይመለከታሉ። የያዝዋትን ሁለት ጓደኞቹን አንድ ነገር አላቸው። ሴትየዋን በደንብ አስጎነበሷት። ቂጧን ገልቦ ሙታንታዋን ዝቅ አደረገ»

«ወይዘሮ ሙሉ እንግዲህ የኔና የርሶ ነገር አበቃ። እኔ ልሙት! ሁለተኛ አላናግሮትም» አለና «እክ!» ብሎ ቂጧ ውስጥ ተፋ።

እየሳቁ ለቀቋዋት። ሽምቅቅ አለች። ወለሉ ላይ ወድቃ ፊቷን ደብቃ እዛው ቀረች። ሴቶቹ ፀጥ አሉ። ሙዚቃው ይዘፍናል። ወንዶቹ ይስቃሉ።

«እናትክን አረብ! እናትክን! እናትክን!» አለ ካጠገቤ። ዘወር ስል ባለመፋቂያው ሰውዬ ሳር ባርኔጣውን በኃይል ወረወረና የተፋውን



እንደ ወረደ
Meysor Bro
t.me/BooksandYou
② ከ 75–151
ከስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

ይጠብቁታል። እሱ ከኪንግ ጆርጅ ባር በየዓይነቱ ኬክ ገዝቶ ይመጣል። እስከ ሦስት ሰዓት ድረስ ሻይ እየጠጡ ኬክ እየበሉ ካርታ እየተጫወቱ ያመሻሉ። አንዳንዴ በሲኒማ ያየውን የጉብዝናና፣ የቦክስ፣ የተኩስ፣ የፍቅር ታሪክ ያጫውታቸዋል። ወይም አቶ ከበደ ሚካኤል የተረጎሙትን የሼክስፒርን «ሮሚዮና ጁሊየት»ን ያነብላቸዋል። ወይም ደሞ በአረብኛ ያነበበውን አስደናቂ የጂኒ፣ የኢፍሪት፣ የጠንቋይ፣ የፍቅር ታሪክ ሲያወራላቸው ቃል ሳይተነፍሱ አፋቸውን ከፍተው ይሰሙታል። ሦስት ሰዓት ሲሆን ደህና እደሩ ብሏቸው ይሄዳል።

አሁን ግን ካዩት ይኸው ሁለት ሳምንት አለፈ። ለዚህ ነው እኔን ሳልፍ አስቁመው የጠየቁኝ

«የት ጠፋ? ታመመ? ጓደኛው ኖት ብለን ነው የጠየቅኖት. . . በዚህ አብራችሁ ስታልፉ ሁሌ እናያችኋለን። ደህና ነው? ውጭ አገር ሄደ'ንዴ? ምነው ጠፋ?» ይህን ሁሉ ጥያቄ አንድ ላይ ወረወሩብኝ።

«እኔም እንደናንተው ነኝ። ካየሁት ሦስት ሳምንት ሆኖኛል» አልኩና ደህና እደሩ ብያቸው መንገዴን ቀጠልኩ።

ያን ሰሞን ጥሳሁን በጨጨብሬ ተወግቶ ሐኪም ቤት ተኝቶ ነበር። ሄድኩና፣ «ጎርጊስ አውቶብስ ማቆሚያው አጠገብ የሚሰሩት ትንንሽ እህቶችህ ብዙ ሠላምታ ያቀርባሉ» አልኩት

«የምን እህቶች?» አለኝ። ከንፈሩ በፈገግታ መወለድና መጥፋት መሀል ይርበተበታል

«እሱን ተወው! የት ጠፋ ብለው ሰግተዋል» አልኩት

እየሳቀ «አንተ በቃ ስራህ እየዞሩ የሰው ጉዳይ ማሽተት ሆነ?» አለኝ ታሪኩን አጫወተኝና ሲያበቃ «ነገሩን ማወቅህ ካልቀረ ሒደህ አስራ አምስት ብር ስጥልኝና አገር ፍቅር መሔጃ ነው በላቸው። ድኜ ስነሳ እከፍልሃለሁ» አለኝ።

ያለኝን ገንዘብ ለልጆቹ ልሰጥለት ስሄድ ከሁለት ዓመት በፊት ማሚት አሹሩሩ ቤት ያየሁት ነገር ትዝ አለኝ. . .

አስታውሳለሁ፣ ቀኝ እግሬን ወለም ብሎኝ ያን ሰሞን ከዘራ እየተመረኮዝኩ ነበር 'ምዞረው። እያነከስኩ ማሚት አሹሩሩ ቤት እንደገባሁ ባንኮኒው ጋ ቆምኩ። ሙዚቃው የሱዳን ዘፈን ነው። አንድ አራት የሚሆኑ ወንዶች ከሴቶቹ ጋር እርስ በርሳቸው እየተሳሳቁ ቫልስ ይደንሳሉ። አረብኛና አማርኛ እያደባለቁ ጮክ ብለው ያወራሉ፣ ሴቶች ይዘው የተቀመጡትም ሦስት ወይ አራት ሰዎች ከሚደንሱት ጋር ይጯጯሃሉ። ሁሉም በአንድነት የመጡ ይመስላሉ። ቤቱ ውስጥ ሁለት ሌሎች ሰዎች ብቻ አሉ፣ ከነሱ ጋር የሚተዋወቁ አይመስሉም።



አንዱ ካሳ ወልደአማኑኤል ነው «ዛሬ ጭፍሮቹ የት ሔደው ይሆን?» ብዬ እያሰብኩ ከሩቅ ሠላምታ ሰጠሁት። ሌላው ሰውዬ ግን እንደሆነ እንጃ፣ ነጭ የሳር ባርኔጣ አድርጎ፣ ባፉ መፋቂያ ሰክቶ እንደኔው ባንኮኒው ጋ ቆሟል። በቁመቱም በውፍረቱም መጠነኛ ነው። ጠይም ዐይኖቹ ንፁህ ሆነው በጣም ያምራሉ። አንዲት ጠይም ሴትዮ ከባንኮኒው በስተኋላ ቆማ ከሱ ጋር በለስላሳ ድምፅ ታወራለች። ፊቷ በጣም ደስ ይላል፣ ደግ የደግ መጨረሻ ትመስላለች። እንደገባሁ ደስ በሚል ለስላሳ ድምጽ «ምን ልቅዳልዎት?» አለችኝ። «መሎቲ»

ሰዎቹ ይጮሃሉ፣ ይስቃሉ፣ ቫልስ ይደንሳሉ፣ ዳንሱ መሀል ሴት ይለዋውጣሉ፣ የሴቶችን ቂጥ በእጃቸው መታ ያደርጋሉ. . . «ኢነአል አቡሽ! የቂጤን እደጋ ይስጥህ!» አረብኛ በብዙ ይናገራሉ፣ ግን ግማሾቹ ሀበሾች ናቸው የሱዳኑን ቫልስ አምስት ጊዜ ያህል «ቢስ» እያሉ አስደገሙት። አንድ ስድስት ሴቶች አብረዋቸው እየጠጡ እየደነሱ ያስካካሉ «ሂድ! ኢንአል ዑምሽ!» ይላሉ «አንቺ ደሞ ትርጉሙን ሳታውቂ ዝም ብለሽ!» ይባባላሉ። እንዲህ ሲጫወቱ ሲደሰቱ ስመለከታቸው፣ የቀልድ አንዷን ሴትዮ ወንዶቹ ለሁለት ያዙና ሁለት እጅዋን ጠምዝዘው አስጎነበሷት።

«ልቀቁኝ እንግዲህ!» አለች። አምርራለች። እነሱ ግን ይስቃሉ። አንደኛው «ወይዘሮ ሙሉ ደሞ ምን ሆኑ?» እያለ እጁን ቀሚሷ ውስጥ ከተተና ቂጧን አሻሻት።

«ልቀቁኝ?!» አለችና ጮኸች። ሰውየው እጁን ከቀሚሷ ስር አወጣና አሸተተው።

«እፍ! ይገማል» አለ እየሳቀ።

«ቆሻሻ አረብ!» አለችው። ተናደደ። ቆሞ ካሉት ሰዎች አንዱን ጠራና በአረብኛ ምናምን ነገረው። ሰውየው መጣና የተጠማዘዘ እጇን ተቀብሎ ያዘለት። እሷ ትፍጨረጨራለች። ሙዚቃው ይዘፍናል። ሰዎቹ እየደነሱ ይመለከታሉ። የያዝዋትን ሁለት ጓደኞቹን አንድ ነገር አላቸው። ሴትየዋን በደንብ አስጎነበሷት። ቂጧን ገልቦ ሙታንታዋን ዝቅ አደረገ»

«ወይዘሮ ሙሉ እንግዲህ የኔና የርሶ ነገር አበቃ። እኔ ልሙት! ሁለተኛ አላናግሮትም» አለና «እክ!» ብሎ ቂጧ ውስጥ ተፋ።

እየሳቁ ለቀቁዋት። ሽምቅቅ አለች። ወለሉ ላይ ወድቃ ፊቷን ደብቃ እዛው ቀረች። ሴቶቹ ፀጥ አሉ። ሙዚቃው ይዘፍናል። ወንዶቹ ይስቃሉ።

«እናትክን አረብ! እናትክን! እናትክን!» አለ ካጠገቤ። ዘወር ስል ባለመፋቂያው ሰውዬ ሳር ባርኔጣውን በኃይል ወረወረና የተፋውን

ሰውዬ ስቶ አንዱን የተቀመጠ ሰውዬ መታ:: ከዚያ በኋላ የሆነውን እንግዲህ በደንብ ልከታተለው አልቻልኩም ከመፍጠኑ የተነሳ::

ጥላሁን ከመቼው ሰዎቹ ጋ እንደደረሰ እንጃ፣ ዘሎ የተፋውን ሰውዬ ደረቱን በእርግጫ ብሎ ጣለውና ዘወር ብሎ አንዱን በቦክስ አገጩ ላይ መቶ ከግድግዳው ጋር አጋጨው:: ያን ጊዜውኑ ከአንዱ ጋር ትግል ተያያዙ:: ትግል መስሉኝ ነበር፣ ግን ያኔውኑ የሰውዬው አፍንጫና አፍ ደም በደም ሆነ፣ ጥላሁን በጭንቅላቱ ቴስታ መትቶት ኖሯል:: ሲለቀው ጊዜ ፍስስ ብሎ ወደቀ:: እስከረብሻው መጨረሻ አልተነሳም:: ሰባት ስምንት ሆነው ጥላሁንን ከበቡት:: ዘሎ ተወርውሮ መሃላቸው ሲገባ ታየኝ. . . ካሳ:: ከዚያ እጆች፣ እግሮች፣ ጭንቅላቶች፣ ክራባቶች፣ ትርምስምስ:: ወንበር ሲወድቅ፣ ብርጭቆ ጠርሙስ ከሽ ብሎ ሲሰበር፣ ሰዎቹ ሲግቱ ሲያቃስቱ ይሰማል:: ሴቶቹ በድንጋጤ ግድግዳውን ተጠግተው በጀርባቸው ይገፉታል - ተከፍቶ እንዲያወጣቸው እንዲሸሽጋቸው::

ካሳ አንዱን አንስቶ መሬት ላይ ፈጠፈጠውና ዘሎ ሆዱን ወደታች ረገጠው «ህእ!» አለ:: ጥላሁን ተወርውሮ መጥቶ ከቆምኩበት አጠገብ ወደቀ:: ሁለት ሆነው በላዩ ላይ ወደቁበት:: አንደኛው ጩቤ መዞና ጥላሁንን ሊወጋው ሲል እጁን በከዘራዬ መታሁት:: አየኝና ወደ እኔ ዘለለ በከዘራዬ ጭንቅላቱን መታሁት:: ልደግመው ስቃጣ ወደኋላ ተወረወረ:: ይህን ጊዜ ጥላሁን አንደኛውን «ትግል» ይዞት ኖሮ ሲለቀው ታየኝ:: ሰውዬው አፍንጫው እየደማ ፍስስ ብሎ ወደቀ:: እዛው ቀረ:: ጥላሁን ካሳ ወደተከበበበት ዘሎ ገባ::

እጆች፣ እግሮች፣ ጭንቅላቶች፣ ክራቫቶች ድብልቅልቅ:: ጩቤ ብልጭ ሲል ታየኝ:: ያኔውኑ ሽጉጥ ተተኮሰ:: ሰዎቹ ሁሉ ባሉበት ደርቀው ቀሩ:: እንደ ሉጥ ሚስት:: ሙሉ ፀጥታ

«ጩቤህን ጣል!» ሁለት ጩቤ ወለሉ ላይ ወደቀ:: ሦስት ሰዎች ወለሉ ላይ ተዘርረዋል:: ካሳ ሽጉጡን በግራ እጁ እንደያዘ ወደኋላው በተስታ እየተራመደ ከሰዎቹ መሀል ወጣ:: ጥላሁንም ወደ ኋላው እየተራመደ ተከተለው:: ይህን ጊዜ ነበር ከበሩ በኩል የሴት ድምጽ «ፖሊስ መጣ!» ሲል የተሰማን:: ሰዎቹ የወደቁትን ጓደኞቻቸውን ቶሎ ብለው ማንሳት ጀመሩ:: ካሳን በሹክሹክታ «ሽጉጥህን አምጣ» አልኩና ተቀበልኩት:: ጥላሁንን «አንተም መሣሪያ እንዳለህ ስጠኝ» አልኩት:: በኃይል እየተነፈሰ «የለኝም» አለኝ::

በጓሮ በር ወጣሁ:: ከቤቱ ኋላ አጥር ግቢው ውስጥ ሦስት ኮባ በቅሏል:: የካሳን ሽጉጥ አንዱ ኮባ ውስጥ ደበቅኩት:: አጥሩን ዘልዬ ከግቢው ወጣሁ:: ዞሬ በፊተኛው በር በኩል መጣሁ:: መንገዱ ላይ



የካሳ ላንድሮቨርና ሁለት ፊያት መኪናዎች ቆመዋል:: የፖሊስ መኪና የሚሉት የለም:: የውጭ በሩን ስሻገር ቡጊ ሲጫወት ሰማሁ:: ወለምታዬ ያመኝ ጀመር:: ማንከስ ጀመርኩ:: ከዘራዬ ከኔ ጋር እንዳልሆነ አስተዋልኩ::

መጋረጃውን ከፍቼ ገባሁ:: ሰዎቹ በየቦታቸው ተቀምጠዋል:: አያወሩም:: ጥላሁን እንደቅድሙ ባርኒጣውን አርጎ ባንኮኒው ዘንድ ቆሟል:: እግሩ አጠገብ ከዘራዬ ወድቋል:: አነሳሁት:: ካሳ ሶፋው ላይ ቁጭ ብሎ ያየኛል:: በጭንቅላቴ «የለም» አልኩት:: ተነስቶ ወደ'ኔ መጣ:: ሦስታችን ሂሳባችንን ከፍለን ልንወጣ በሩ ጋ ስንደርስ፣ የተተፋባት ሴትዮ ተንደርድራ ተንበረከከችና የጥላሁንን ጉልበት ሳመች:: ቀስ አድርጎ ትከሻዋን ይዞ አስነሳት:: ንዴቱ እንደገና ገነፈለ:: ወደ ሰዎቹ ሊራመድ ሲል ካሳ ያዘው::

«እስኪወጡ ብንቆይ ጥሩ ነው» አለ ካሳ:: ተመልሰን ባንኮኒው ጋ ቆምን:: ቆየን:: ወሬ የለም:: ሙዚቃው ሳምባ ይጫወታል:: ዝም ብሎ መፋጠጥ፣ ዝም ብሎ ግድግዳ ወለሉን፣ ጠረጴዛ ወንበሩን ማየቱ እየከበደን ሔደ:: በመጨረሻ ጥላሁን ሰዎቹን በአረብኛ አንድ ነገር አላቸው:: በኋላ «ክፈሉና ሂዱ» ማለቱን ነገረን:: ሰዎቹ ማመንታት ጀመሩ:: በኋላ ግን ወጥተው ሄዱ:: አሁን እንግዲህ ሴቶቹ አፍ አውጥተው ሁሉም አንድ ላይ መናገር ጀመሩ:: ትተናቸው ወጣን:: የተፋባት ሴትዮ ወጥታ በዐይኗ ተከተለችን:: ጥላሁን ሁለታችንን ካልጋበዝኳችሁ ብሎ አስገደኝ አላምረው ቤት ወሰደን::

ስንጠጣ ካሳ «By the way, የተፋባት ሰውዬ አረብ አይደለም ሀበሻ ነው» አለው

«አውቄያለሁ» አለ ጥላሁን

«እናትክን አረብ ለምን አልከው ታዲያ?» አልኩት

«እኔ'ንጃ»

ያን ዕለት ማታ ሦስታችን አብረን ስንዞር አመሸን:: ከዚያች ሌሊት በኋላ ጥላሁንና ካሳ ሲገናኙ ወይም እጅ ይነሳሳሉ ወይም ይጨባበጣሉ:: ግን አይነጋገሩም:: እንደሚከባበሩና እንደሚዋደዱ፣ በመሀላቸው ጓደኝነት እንዳለ በፊታቸውና ባኳኋናቸው ያስታውቃል:: ከዚያም በላይ ብዙ ጊዜ በአንድነት ትልልቅ ረብሻ ውስጥ ገብተዋል:: ታዲያ አይነጋገሩም::

አንድ ቀን ጥላሁን ሲያስረዳኝ «እናቴ በሕይወቷ እያለች የራስ ወልደአማኑኤልን ልጅ ሳነጋግር አልችልም:: ሀሊናዬ አይፈቅድልኝም» አለኝ::

«የርስቱ ጭቅጭቅ ጊዜ አንተም ካሳም ሕፃናት ነበራችሁ። ይኼኒ እሱ ስለዚህ ርስት ጉዳይ እንዲያውም ምንም አያውቅም»

«እውነት ነው»

«እንግዲያው ለምን አታነጋግረውም?»

«እማማ ብትሰማስ? እንዴት እንደምታዝን ይታይሃል?»

አንድ ሰሞን ጥላሁን በኪሱ ቾክ ይዞ መዞር አምጥቶ ነበር። በረሃ ውስጥ አንድ ሰው ነገር የፈለገው 'ንደሆነ፣ ወይም እሱ ራሱ ሰክሮ ነገር ሲፈልግ ሰውየው ያልተለማመጠው እንደሆነ፣ ቾኳን ከኪሱ መዘዝ አድርጎ ወለሉ ላይ በሱና በሰውየው መሀል መስመር ይሰርዝና ሲያበቃ፣ ሱሪውን ከቀበቶው ዘንድ በክንዶቹ ከፍ እያደረገ በውስኪ ደም የተነከሩ ትልልቅ ዐይኖቹን እያገላበጠ፣ መፋቂያውን በኃይል እየነከሰ፣

«ወንድ ከሆንክ እቺን መስመር ተሻገር» ይለዋል። ጥቂቶቹ ይሻገራሉ። ቦክስ፣ ትግል፣ ቴስታ፣ ደም። አብዛኞዎቹ ግን «ብሻገር ምን ልትሆን ነው? ማነው አንተን ፈቃጅና ከልካይ ያደረገህ?» እያሉ ገላጋዮች መሀል እስኪገቡላቸው ድረስ ይከራከራሉ። ገላጋዮች ከያዙዋቸው በኋላ ከጥላሁን እኩል እየተፍጨረጨሩ «ልቀቁኝማ! አሳየዋለሁ!» ይላሉ

አንድ እሁድ ማታ ማሚት እሹሩሩ ቤት ጥላሁን ባንኮኒው ዘንድ ቆሞ መፋቂያውን እያኘከ ኮካኮላ እየጠጣ፣ የሞክሼውን የጥላሁን ገሠሠን ዘፈኖች ያዳምጣል። ዐይኖቹ ንፁህ ነጭ ናቸው። ምንም አልኮል አልጠጣም ማለት ነው። ዛሬ እንኳን ነገር ሲፈልግ፣ ቢፈልጉትም ይታገሳል። ይህን አስተውሎ ነው መሰለኝ፣ አንድ ትንሽ መላጣ ሰውዬ ነገር ይፈልገው ጀመር። እንግዲህ ጥላሁን በጣም ካልሰከረ በስተቀር በግዙፍነት ከሱ የሚያንሱትን ሰዎች ብቻቸውን ከሆኑ አይጣላቸውም። ግን ይኼ ሰውዬ በጣም አበዛው። አንዴ ጥላሁንን ትንሽ ገፋ አድርጎት ይቅርታ ሳይለምነው ያልፋል። አንዴ አጠገቡ መጥቶ ይቆምና ገላምጦት ይሄዳል። አንዴ «ረብሸኛው ሁሉ ዛሬ ምነው ጭጭ አለ?» ይላል። በመጨረሻ «እንደ ወንድ ውስኪ እንደመጠጣት እንደ በሽተኛና እንደ ልጃገረድ እየተሽኮረመሙ ኮካኮላ ፉት ይላሉ» አለ

ጥላሁን መታገስ ሰለቸውና «ዞር በል ከዚህ - አንተ መላጣ ድንክ!» አለው።

ሰውዬውም ጮሆ «እኔስ ምናልኩ?» አለው

«እንደ ሴት ኮካኮላ ማጣጣም ብቻ ሳይሆን ስድብም ታውቂያለሽ!»

«ተይ ስድብ ብቻ አይደለም ጥፊም አጠጣሻለሁ» መጠጥ ቤቱን የሞሉት ሰዎች አብዛኞቹ ጥላሁንን ስለሚያውቁት፣ ማንም ደፍሮ እንዲህ አይሰድበውም በማለት፣ ይሄ ሰውዬ ወይም እብድ ነው ወይም ነገሩ



የቀለድ ነው ብለው፣ ግማሾቹ እየደነሱ ሌሎቹ እየሳቁ ጭቅጭቁን ይመለከታሉ።

ሰውየው የውሸት ሳቅ እየሳቀ «ጥፊ? እ?» አለ «አንቺ እኔን በጥፊ ብትመቺኝ ሰው ጉድ አይልም?»

ጥላሁን ያቺን ቾኩን ከኪሱ መዘዘና ትንሽ እልፍ ብሎ ወለሉ ላይ መስመር ሰረዘ። በጣቱ መስመሯን እያመለከተ «ወንድ ከሆንክ እቺን መስመር ተሻገራት» አለው

«አንተ ተሻገራት» አለ ሰውዬው

ጥላሁን ቦክስ ጨብጦ ተሻገራትና «ታዲያስ?» አለው

«ታዲያስ ምን?» አለ ሰውየው

«መስመሯን ተሻገርኩ'ኮ»

«ታዲያ ምን ላርግህ?»

«ምታኛ»

«አንተ ራስህ የሰረዝከውን መስመር በተሻገርክ እኔ ለምን እመታሀለሁ? እብድ ነኝ? ወይስ ደካማውን የሚጠቃ ጭቦኛ ነኝ?»

ጥላሁን ቾኩን ሰጠው። ሰውዬው ቾኩን እየተቀበለ «ምንድን ነው?» አለ

«አንተ መስመር ሥራ» ሰውየው ወለሉ ላይ ሌላ መስመር ሰረዘ።

ጥላሁን አሁንም ቦክስ ጨብጦ መስመሯን ተሻገረ። ሰውየው አሁንም ዝም አለ።

ጥላሁን «ታዲያስ?» አለው

«ታዲያስ ምን?»

«ተሻገርኩዋታ!»

«ታዲያ እኔ መች አትሻገር አልኩህ? ለኔ ብለህ እንደሆነ መቶ መስመር ለምን አትሻገርም?»

ጥላሁን ቾኩዋን ቀማው፣ መላጣ ግምባሩ ላይ መስቀል ሣረበት። ሰውዬው ዝም አለ

ጥላሁን «ቅዘናም ለፍላፊ!» አለውና ትቶት ወደ ኮካኮላው ሊመለስ ዘወር ሲል

ሰውየው «እንደ ትንሽ ልጅ በቾክ እየሰረዙ መጫወት ይብቃንና የወንድ ሥራ ሳላይሽ። ውጪ እጠብቅሻለሁ። ብቻሽን ነይ» ብሎት ወጣ።

ጥላሁን ሂሳቡን ከፍሎ ተከተለው። ውጭ ቢመለከት ሰውየው የለም። ጥላሁን ግራ ገብቶት «ይቺ ድንክ ከመቼው እልም ብላ

ጠፋችን እፀ-መሰውር አላት ይሆን?» ብሎ ጭንቅላቱን እያከከ ወደ መጠጥ ቤቱ ተመልሶ ሊገባ በሩ ጋ ሲደርስ

«ሳታየኝ እንዲህ ማፈግፈግ የጀመርከው ብታየኝ ትፈረጥጣለህ። በል መጣሁልህ አንተ በሩ! ፈርጥጥ!» አለው።

ጥላሁን ዘወር ብሎ ቢያይ፣ ትንሽ እልፍ ብሎ አንድ መኪና አጠገብ ሰውየው በሁለት እጆቹ ወገቡን ይዞ ቆሟል። ከመኪናው ኋላ ተደብቆ ኖሯል።

ጥላሁን «ምን ዓይነት ሰው ነው ይሄ?» ብሎ ተገርሞ ዝም ብሎ ሲያየው ሰውየው

«ምን ትጠብቃለህ?» አለው «ፈርጥጥ እንጂ። ያለዛ መጣሁልህ ጥ!» በመሀላቸው አንድ አስር እርምጃ ያህል አለ። ጥላሁን የባሰውን እየተገረመ ስለሄደ በከረንቲው መብራት ዝም ብሎ ሰውዬውን ያየዋል። ምንድነው ይሄ? ሰው ነው ወይስ የሚለፈልፍ መኪና ነው?

ሰውየው «አሁን'ኮ ብትሸሽ ምንም አይደለም። ማንም አያይህም። ቢያይህም ማንም አይፈርድብህም። ነብር ሲያዩ መሸሽ ያባት ነው። በል ልቁጠርልህና ሽሽ። አንድ. . . » ጥላሁን ልክ ህልም ውስጥ ያለ ሊመስለው ጀምሯል።

ሰውየው መቁጠሩን ቀጠለ «ሁለት. . . አስታውስ ዋ! በበባት መሮጥ፣ መፈርጠጥ! መሽምጠጥ ካልጀመርክ መጥቼ ነው የተወለድክበትን ቀን 'ማስረግምህ በል!. . . ? አሁንም ዝም ብለህ ቆመሃል? ትክሻውን እየነቀነቀ «እኔ ግድ አለኝ? ለኔ ብለህ እንደሆን ተገትረህ እደር» አለውና ዘወር ብሎ ወደ ጊዮርጊስ በኩል መራመድ ጀመረ። በግራ እግሩ ያነክሳል።

ጥላሁን «ደቺ ሰውዬ አሁን ካልኮረኮምኩዋት ሌላ ቀንም ታስቸግረኛለች» ብሎ አስቦ፣ ሮጦ ሄዶ በጥፊ ሊለው ፈለገ። ግን አልቻለም። ልክ እንደ ህልም ሁኔታ እግሮቹ አልንቀሳቀስ አሉት። ሰውየው እያነከሰ ሀውልቱ ጋ ደርሶ ወደ ግራ ተጠምዞ እስኪጠፋ ድረስ በአይኑ ተከተለው። ከዚያ ራሱን እየነቀነቀ ወደ መጠጥ ቤቱ ተመልሶ ገባና አራት ውስኪ አከታትሎ ጠጣ።

ከዚያ ወድያ ጥላሁን በኪሱ ቾክ ይዞ መዞር ተወ።



# ምዕራፍ ስድት

## ተአምረ ክንፈ

ሰውነቷ፣ ሰውነቷ
እንዲያው ሰውነቷ!
/ያማርኛ እንጉርጉሮ/

አንድ ቀን ማታ ማሚት እሹሩሩ ቤት እኔና ብርሃኑ ባንኮኒው ዘንድ ቆመን ስናወራ ጥላሁን የበሩን መጋረጃ በጥፊ ከፍቶ ገባ። ቤቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ላይ ተራ በተራ አፈጠጠባቸው። ከዚያ ወደኛ መጣ። ሠላምታ 'ንኳ ሳይሰጠን፣ በቁጣ ድምጽ

«ክንፈን አይታችሁታል?» አለን

«አላየነውም» አልነው

ደም የለበሱ ትልልቅ ዐይኖቹን እያጉላበጠ «እልጋችሁ ውስጥ ቁህን ብታገኙ ምን ታረጉታላችሁ?» አለን

«እንቆቅልሽ ነው?» አልኩት

መፋቂያውን ነከሰብኝ። «ምን ታደርገዋለህ?» አለኝ። የፈለገውን መልስ አውቄዋለሁ፣ ግን ጥላሁንን ማብሸቅ ደስ ይለኛል። ደሞ ዛሬ ምን እንዳናደደው ስለገባኝ ለራሴ ፈርቻለሁ።

«ማንን?» አልኩት

«ማንን ይለኛል። ቁህኑን! ምን ታረገዋለህ?»

«አንት የቁህን ዘር! ሰው አልጋ ውስጥ ምናባክ ትሠራለህ?» ብዬ አካልበውና፣ ልክ ልኩን ነግሬ አሳፍሬው ሳበቃ፣ በመጨረሻ በፖሊስ አሳስረዋለሁ»

ገላመጠኝና «ማን አንተን ጠየቀህ?» ብሎ ወደ ብርሃኑ ዞረ። ብርሃኑ ቁህኑን ምን እንደሚያደርገው በእጁ እያሳየ «ጭፍልቅ!» አለ። ጥላሁን በመልሱ ተደሰተ። ግን ንዴቱ አልለቀቀውም

«እኔም ያንን ልክስክስ ቁህን ሳገኘው ብቻ። ጭፍልቅ!» አለ

«ማንን?» አለ ብርሃኑ

«ክንፈን። ክንፉን ነው ምሰብርለት። እቺ ልክስክስ የእንሽላሊት ዘር! አልምራትም! ፈረሰኛውን!»

«ምን አደረገህ?»

የባሰውን ተናደደ «ከየትም ቆፍሬ ጎትቼ አመጣውና ምን እንዳደረገኝ እሱ ራሱ ይንገራችኋል:: ይሄ ልክስክስ ቱሀን!» አለና ሱሪውን በክንዶቹ ከፍ እያደረገ ሊሄድ ሲል፣ ያዝነው::

«ምን በየመጠጥ ቤቱ አስሮጠህ? ራሱ እዚህ ይመጣልህ የለ?» አልነው::

«እውነታችሁን'ኮ ነው:: የማሚትን እምስ ሳይሳለም አያድር! እዚችው ልጠብቀው» ብሎ ቢራ አዘዘ::

እኛ ግን እዚህ ቆይ ያልነው ክንፈን ለብቻው አግኝቶት ከሚደበድበው እኛ ብንገላግለው ይሻላል፣ በአንድ ሁለት ኩርኩም ያልፍለታል ብለን ነው::

«እስቲ እግዜር ያሳያችሁ» አለን ጥላሁን በጣቶቹ ላይ እየቆጠረ «ውሽታም፣ አጭበርባሪ፣ ለካራም፣ ፈሪ፣ እምስ አምላኩ፣ አለሌ ሰራሪ መሆኑን እያወኩ፤ አዝኜለት ጓደኛ ሆንኩት:: ስንትና ስንት ጊዜ ሊደበድቡት ሲሉ አስጣልኩት:: ያላቅሙ እበዳለሁ እያለ ሲንጠራራ ሊደበድቡት ሲሉ ቢያንስ አሥር ጊዜ ያሀል ተደባድቤለታለሁ:: ታድያ እንዲህ ጉድ ይስራኝ?!»

«ምን አረገህ?»

«ቆይ ሲመጣ እሱ ራሱ ይንገራችኋል:: እኔ የ'ዐይን ዐይኑን ባል መስየዋለሁ» ሳቄ አመለጠኝ:: ብርሃኑ አብሮኝ ሳቀ:: ጥላሁን አፈጠጠብኝ::

«ምን ላድርግ? 'ዐይን ዐይኑን' ትዝ አለኝ» አልኩት:: እሱም ሳይፈልግ ሳቅ አለ::

ከንድ አራት ወር አስቀድሞ እስናቀች (የጥላሁን ሚስት) ቤት ሦስታችን ልክ እንደዚሁ ቆመን ስንጠጣ፣ ክንፈ መጥቶ ግማሽ ሰዓት የሚፈጅ አስቂኝ ታሪክ ስለ አንዲት ሴትዮ ነግሮን ነበር:: ታሪኩ መጨረሻ ላይ ሴትዮዋ (ባለ ባል ናት) ክንፈን መኝታ ቤቷ ወስዳው ስታበቃ ፊቱ እምሷን በሽቶ ሳሙና ታጠበችና

«ያን ፎጣ አምጣና አድርቀኝ» አለችው

ሲያደርቅላት ሳለ የሱሪውን ቁልፍ ፈታችና ፈታውራሪን መዘዘችው:: ፈታውራሪ የክንፈ ቁላ ነው፣ በደስታ ቆሞ እስክስታ ይወርዳል:: እያወዛወዘችው «እምዬ ማርያም! ይኸንንማ የት እችለዋለሁ? ዝሆን አይደለም'ንዴ?» አለችና ስታበቃ ዘላ አልጋው ላይ ወጥታ ተጋደመች:: ጭኖቿን ከፍታ «ቶሎ በል!» አለችው

«ኧረ ዝሆን አይደለም እምዬ፣ ፈታውራሪ ነው» አለና ሊከትባት ሲል



«ቆይ!» አለችው

«ምነው?»

«ቁም»

«የት»

«ከበላዬ»

«ለምን?»

«ዝሆንህ እንደ ሊቀ መላኩ ሰይፍ ተመዞ ከላዬ እንዲታየኝ እፈልጋለሁ» ቆመላት:: ፈታውራሪን ወደ ላይ እያየች ትንሽ ካደነቀችው በኋላ

«ቁላ ማለት እንዲህ ነው እንጂ!» አለችው:: «የኛ ቤት ቁላ ባቄላ ነው ምታክለው:: ሲተኛኝ እሁ! ብዬ ከሳልኩ ውልቅ ትላለች:: መከራ ነው እልሃለሁ:: ና ና፣ ና ቶሎ»

አሁንም ሊከትባት ሲል

«ቆይ!»

«ምነው?»

«ተነስ»

«ለምን?»

«ያን ሽቶ አምጣልኝ» አመጣላት:: እምሷን ትንሽ ሽቶ አርከፈከፈችበት

«እንዲሰክር» ብላ የብልቃጡን አፍ ወደ ፈታውራሪ አፍንጫ አስጠጋችው

«ሰክሯል ሰክሯል በቃው» አላት ክንፈ

«እሺ ከተት» ከተተ:: ፈታውራሪ ጥቂት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ካለ በኋላ ክንፈ እግሯን ትከሻው ላይ ተሸክሞ ኩሊ ኩሊ ሲላት

«እፎይ! እንዲያ ነው! በልልኝ ክንፍዬ! ዐይን ዐይኑን! ዐይን ዐይኑን በልልኝ ይህን ገብጋባ ጉድጓድ! ዐይን ዐይኑን አጥፋልኝ ይህን አንድ ዐይና ጠንጋራ! ባቄላ ሰልችቶታል:: ሙገ! እጉርሰው:: በዋርካው ዝሆንህ ዝልጥልኝ ይህን ረኸጥ» አለችው:: ስትጨርስ «ዐይን ዐይኑን!» እያለች አለቀሰች:: በኋላ እሷ ፈታውራሪን ስትጠርግለት፣ ክንፈ እንባዋን ጠረገላት::

ክንፈ ይህን ታሪክ የነገረን ጊዜ ሆዳችንን እስኪያመን ሳቅን:: ከዚያ በኋላ ሲያገኘን «ዐይን ዐይኑን በልልኝ!» እየተባባልን እንቀልድ ነበር::

መጨፍለቅ
እንደፈለገ ገብቶኛል:: ትላንት ቅዳሜ ሌሊት ከከንፈ ጋር ነበርኩ. . .

. . . ወደ አራት ተኩል ላይ ማሚት እሹሩሩ ቤት ስገባ ትርሲት «ጋሼ ከንፈ እስናቀች ቤት እጠብቅሃለሁ እንድትመጣ ብሎሃል» አለችኝ:: እስናቀች የጥላሁን ሚስት ናት:: የምታሻሽጥበትን ቤት «የእስናቀች ቤት» የምንለው ከዚያ ቤት ውስጥ በጣም ቆንጂዬ እሷ ስለሆነችና ቤቱን በጥላሁን ምክንያት ስለምናዘወትረው ነው እንጂ የሷ ቤት አይደለም:: ቤቱስ የአልማዝ ነው:: ታዲያ እስናቀች ቤት ስገባ ከንፈ ከእስናቀች ጋር ቻቻ ይደንሳል:: እንደ ልማዱ አሸብርቋል:: ነጭ ሱፍና ነጭ ሰደርያ፣ ሰማያዊ ኮትና ሰማያዊ ሸሚዝ:: ዘለግ ያለ እንገቱ ዙሪያ ቄንጠኛ የውጭ አገር ሻርፕ አስሯል:: እቺ ሻርፕ ከእንዲት እንግሊዛዊት ልጃገረድ የተሰጠችው መታሰቢያ ስትሆን፣ በሰማያዊ መደብ ላይ ነጫጭ ኮከቦች ተዘርተውባት፣ የተጣጠፈች የተጠመጠመች ሳቲታ ሰማይ ትመስላለች:: ይህን የደስ ደስዋን ከከንፈ ፍንጭት ፈገግታ የተቀበለች ትመስላለች::

ውቤ በረሃ ውስጥ በዋጋው ወይም በጨርቁ ምርጥነት ከከንፈ የሚበልጥ ልብስ ያላቸው ሰዎች አልፎ አልፎ ይታያሉ:: ታዲያ አለባበስ እንደሱ የሚያምርበት አይገኝም::

የበረሃ ሴቶች የሚወድቁለት በዳንስ ችሎታው፣ በኩምክናዉ፣ በስብከቱ፣ በመልኩ ብቻ ሳይሆን ባለባበሱም ጭምር ነው::

ቤቱ ውስጥ ከሰባቱ ሴቶች ሌላ አስራ ስድስት የሚሆኑ ወንዶች አሉ:: ከንፈና እስናቀች ቻቻ ሲደንሱ ሁሉም በጸጥታ ይመለከቷቸዋል:: በከንፈ አለባበስና አደናነስ በጣም እንደተገረሙ ከፀጥታቸውና ከማትኩራቸው ያስታውቃል:: ቻቻ ገና አዲስ አበባ መግባቱ ስለነበረ ውቤ በረሃ ውስጥ ዳንሱን አጠናቀው የሚችሉ ከንፈ፣ ጴጥሮስ እና አንድ ጉረኛ ሰውዬ – ሦስቱ ብቻ ነበሩ:: ሴቶቹ ገና አልተማሩትም::

ከንፈ ሲደንስ የሙዚቃው ታምቡር ከእግሮቹ የሚፈጠር፣ ዜማው ከሰውነቱ ከደሙ የሚፈልቅ ይመስላል:: ዳንሱና ሙዚቃው ከመቀሃደቸው የተነሳ እንዱ ከሌላው ተነጥሎ ሕይወት ሊኖረው የማይችል ይመስላል:: ከንፈን እይቼ ሌሎች ሲፈራገጡ ባየሁ ቁጥር እግራቸውን ሰብረህ ጣል ይለኛል::

እስናቀች ገና ቻቻ ባታውቅም ከንፈ በደንብ ስለሚመራት የምትችልበት ያስመስላታል፣ ደስታና ኩራት ፊቷ ላይ ይታያል:: ዳንሱ ሲያልቅ ሌላ ቻቻ ተደረገ:: ደነሱ:: አሁንም እንደተከበቡ ለአራተኛ ጊዜ ደንሰው ሲያበቁ ከንፈ አንድ ነገር ነገራት:: እየሳቀች እጁን ይዛ ወደ መቀመጫው ወሰደችው:: እናም ገና ቁጭ ከማለቷ በሳቅ



መንከትከት ጀመረች:: ከንፈ ኩምክናውን ሲያወርደው ቆይቷል ማለት ነው:: ሳየው ነገሩ አላማረኝም:: በጭራሽ አላማረኝም::

አንደኛ፣ ከመቼ ወዲህ ነው ከንፈ ከሸርሙጣ ጋር የሚደንሰው፣ እርግጥ፣ ድሮ ገና ሥራ ባለመያዙ ገንዘብ በብዙ ስላልነበረው ሸርሙጦች እንዲወድቁለትና በብላሽ እንዲሰጡት ይደንስ ነበር ዛሬ ግን «ምን አለፉኝ ምን አፈራገጠኝ?» ይላል «ገንዘቤን ከፍዬ በማዕረግ አልበዳም፣ ቢሮ ገብቼ ወምበር ላይ ቁጭ እያልኩ የማፈራው ገንዘብ ለምን ሊሆን ነው?»

ሁለተኛ፣ ምን መጣብኝ ብሎ ነው ሸርሙጣን ቻቻ 'ሚያስተምር? ያውም ጊዜው ቅዳሜ ማታ፣ ከንፈ ሦስት አራቱን እምስ እጭበርብሮ ሊበዳ 'ሚችልበት ማታ! እስናቀች የጥላሁን ሚስት ስለሆነች ለጓደኛው ለጥላሁን ብሎ ነው የሚያጫውታት እንዳልል፣ እንዲህ ያለ ሀሳብ ከንፈ እንጎል ውስጥ ሊገባ አይችልም!

ሦስተኛ፣ እስናቀችን ሊበዳ ፈልጎ ነው እንዳልል፣ ጥላሁን ይገለዋል:: ጥላሁንን እንኳን እጭበርብሬ እመልጠዋለሁ? ቢል እስናቀች ራሷ አትሰጠውም:: እሷን አታልላታለሁ ብሎ ቢያስብ ደሞ ያስናቀች ቤት ሴቶች እንደማይፈቅዱለት ያውቃል:: እምና በሰራው ወንጀል ምክንያት እዚያ ቤት የሚገኝ ሴት ሁሉ እኩርፎ በሩን ዘግቶበታል:: ሺ ጊዜ ቢያንኳኳ አይከፈትለትም፣ በእምና ምክንያት. . .

. . . ቅዳሜ ማታ ነበር:: የደሞዝ ሰሞን:: የእስናቀች ቤት ጢቅ ብሎ ሞልቶ ሰው መተላለፊያ አጥቷል:: ማለት ለከንፈ በጣም ምቹ ጊዜ ነው:: እንግዲህ ሴቶቹ በደምብ የለበሰ ሰው ያጭበረብራል ብለው አያስቡም:: በዚህ እንደሌላው ሰው ናቸው:: ከንፈ ደግሞ በደምብ ከመልበስም አልፎ የአለባበስ ጌታዋ ነው:: እና እንደ ሙሽራ አሸብርቆ እንዷን ለዳንስ ጠየቃት:: በሃይል እቅፍ አድርጎ ያዛትና ፈታውራሪን አቂሞ እያሻሻት እየወጋጋት በጆሮዋ እንዲህ አላት

«ባርባራቱ ታቦት! በሦስቱ ሥላሴ! በወንድ ልጅ አምላክ! እዚሁ ላፈሰው ነው:: በምዬ ማርያም ስጪኝ! የፈለግሽውን እከፍላለሁ:: እንዳንቺ ማንም እቁማብኝ አታውቅም:: ይህን ዳሌሽን! ይህን ሉሚ ተረከዝሽን፣ ብርቱካን ጉንጭሽን፣ ከረሜላ ከንፈርሽን እያየሁ ተሰቃየሁ:: በፍቅር አምላክ ተማጠኚኝ:: አትጨክኚብኝ:: እይ ዕድሌ! ምነው ቀድም ብዬ በተዋወቅኩሽ ኖሮ! ነገ ለሥራ ተልኬ አጋዴን መሔጄ ነው:: ወደዚያ 'ሚልከኝ አለቃዬ ያባቴ ዋና ጠላት ነው:: እሱ እስኪሞት ወይም እስኪሻርልኝ ድረስ ለመመለስ ተስፋ የለኝም:: እስቢው! አጋዴን! ዐሐዩ፣ አሸዋው፣ ውሃ የለ፣ ሴት የለ፣ ቁስ እንኳ የለም! ግመል ብቻ:: እና እዚያ መሔጄ ነው:: ኧረ በወንድ ልጅ አምላክ እሺ በይኝ! ለነብስ

ዕድቅ ይሆንሻል። የፈለግሽውን እከፍላለሁ። መሄዴ ስለሆነ የምስት ወር ደሞዜን አንድ ላይ ተቀብያለሁ። እሺ በይኝ የኔ ቆንጆ! እሺ ካላልሽኝ እዚሁ ላፈሰው ነው። ልሙህ ነው! አንዠበገበኝ፤ ቆላኝ፤ ነደደኩ፤ ጠፋኩ፤ እሺ በይኝ የኔ ድምቡሼ - የኔ ድምቡሽቡሽ፤ የኔ ገላ፤»

«ባሌ አለ'ንጂ- »

«ታዲያ ምን አለበት? አያልቅበት። አንዳንቺ ያለ ደም ግባትና ውበት ለአንድ ሰው ብቻ ሊሆን አይገባም። አምላክ አብዝቶ የሰጠሽ አብዝተሽ እንድትሰጪ ነው። ታዲያስ የኔ ድምቡሼ፣ ዛሬ በጓሮ ልግባ? እሺ በይኝ»

«እሺ» በጓሮ በር ገብቶ ከተኛት በኋላ የመቶ ብር ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ «መልስ ታገኚልኛለሽ?» አላት

«ኧረ የለኝም»

«እንግዳው የመጠጥ ሒሳቡን ስከፍል እስመንዝሬ ያኔ እሰጥሻለሁ»

«እሺ»

ወደ ዳንስ ቤቱ ተመለሰ። ሰው ከመብዛቱ የተነሳ መግባት መውጣቱን ማንም አያስተውልበትም። ሁለተኛዋን ለዳንስ ጠየቀና ልክ እንደ መጀመሪያዋ እቅፍ አድርጎ በፈታውራሪ እየወጋጋት የአጋዴንን ዲስኩር አሰማት። ሰጠችው። እሷም የመቶ ብር መልስ አልነበራትም። ሦስተኛዋንም እንደዚሁ፣ አራተኛዋንም እንዲሁ።

አምስተኛዋን እቅፍ አድርጎ ሲያስደንስ ፈታውራሪ አልቆም አለው «ከአምስት ደቂቃ በኋላ እከተባታለሁ፣ ያን ጭገሯን እስኪጨንቀው አጎርሰዋለሁ» ብሎ አሰበ። አሁንም አልቆም አለው። ዓይኑን ጨፍኖ አስታወሰ። ቅድም የበዳቸው አምስት እምሶች ባለከንፈር፣ ባለጭገር፣ ባለ ለሀጭ! ፈታውራሪ አሻፈረኝ ብሎ ተኝቶ ቀረ።

ክንፈ በሸቀ። ምክንያቱም የሱ ዕቅድ ሰባቱንም ሴቶች ለመብዳት ነበር። ፈታውራሪን ወረደበት «እናትክን አንተ ቂንጥራም!» አለው «እንደዚህ ትከዳኛለህ? ባጭሩ ታስቀረኛለህ? ዕድሜህን ያሳጥረውና! ቆይ! ቆመህ ስትንዠበገብ፣ ትኩስ እምስ ውስጥ እገባለሁ ብለህ ስትዘል፣ አንገትህን አንቄ ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ባልደፍቅህ እኔ ክንፈ አይደለሁም። አንተ የውሻ ልጅ!» በፈታውራሪ መክዳት ምክንያት አምስተኛዋን ምንም ሳያናጋግራት ዳንሱን ጨርሶ ቁጭ አለ።

ሩብ ሰዓት ያህል ካለፈ በኋላ ስለ እምስ ማሰብ ጀመረ። ፈታውራሪ አልቆም አለው «እህ! ረስቼ» ብሎ አሰበ። ፈታውራሪ እንደዚህ ደክሞት በሰድ ንባብ ቢነግሩት መች ይገባዋል? በግጥም ልሞክረው እንጂ



ይድረስ ለክቡር ፈታውራሪ

የበረሃ ዋና የጦር መሪ - የለም። ይሄማ ጥሩ አይደለም።

እስቲ በስማም ብዬ ልጀምር መልክቴን

ወደ ፈታውራሪ ወደ ጀግናው ካፒቴን - ዜሮ! ይኼ ምኑ ያቆማል? እንደገና

ፈታውራሪ ጌታው ፈታውራሪ

እጭን መሀል ጉድጓድ ቆፋሪ- እህ፤ቀጥል

ይገፍ መጣሁ ከመቤቴ ጥሪ - እምጣው፤

በፀጉር ተከቦ

መካከሉ ረጥቦ

በቂጥ ታጅቦ

የፍንድድ አጊጦ

በምኞት አፍጦ

በመጓጓት አብጦ

ይጠብቅሃል እምስ ጣፎጦ

መቼም፣ ምንም ያህል የድካም እመድ ቢያፍነውም፣ የወኔ እሳት ሽለላ ሲሰማ ቦግ ማለቱ የማይቀር ነውና፣ ፈታውራሪም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ጀግና የከተማ አርበኛ እንደመሆኑ መጠን፣ ሽለላውን ሰምቶ ሊነሳ ሞከረ። በስንት ማበረታታት በስንት ድጋፍ በስንት ፀሎት ብድግ አለ። ዳሩ ግን ምን ይሆናል፣ ቀጥ ብሎ ሊቆም አልቻለም፣ እንደሽማግሌ ጎብጦ እየተንቀጠቀጠ ቆመ። ያ ሁሉ የጨበጣ ውጊያ ወገቡን ሰብሮት ነበርና ነው'ንጂ፣ ሌላ ሩብ ሰዓት ቢቆይ በደንብ ቀጥ ብሎ እንደ ወጣት ጀግና እንደ ፋኖ ይቆም ነበር። ግን ጊዜ የለም። አምስት ተኩል ሆኗል። ከስድስት ሰዓት ወዲያ ባቡር መንገድ ውስጥ የሚንቀሳቀሰውን ሰው ሁሉ ፖሊሶች ስለሚይዙት፣ ቤታቸው ሩቅ ስለሆነ መኪና የሌላቸው ሰዎች መሔድ ጀምረዋል። ቤቱ እየጎደለ ሔደ። ከአስር ደቂቃ በኋላ ማጭበርበር ላይቻል ሆነ።

ክንፈ ያቀደው ስድስቱን በተራ ሞልቶ ሲያበቃ፣ ከሁሉ ይበልጥ ያቋመጡችውን እስናቶችን በመጨረሻ ለመብዳት ነበር። ያን ጊዜ ጥላሁንና እስናቶች ዝምድናቸውን ገና አልጀመሩም ነበር። አሁን ግን ፈታውራሪ ስለከዳውና ጊዜ ስላጠረው፣ ሁለቱ ይቅሩብኝ ብሎ፣ የመጨረሻ እስናቶችን ሊሞላ ቆረጠ። ለጊዜው ፈታውራሪ ሲቆም ጎብጦ እየተንቀጠቀጠ ቢሆንም የዛች የእስናቶች ለስላሳ ጣቶች ሲደጋግፉት በደንብ መቆሙ የማይቀር ነው። አይ ፈታውራሪ! ከድቶ

አይከዳም'ኮ!

ከንፈ ይቺን አስናቀችን ለዳንስ አስነስቶ እንደ አራቱ ስለ አጋዴን ሰባበካትና እሺ አሰኝቶ በጓሮ ሔደ። የመንታዎግ በር ለመክፈት ቢታገል፣ ከዳንሱ ቤት አስናቀችና አራቱ የበዳቸው ሴቶች እና ሁለቱ ያልበዳቸው ሴቶች፤ ሰባቱም መጡ። የቢራ ጠርሙስ መተረኪያ ፍልጥ የቡና ዘነዘና ይዘው። ከንፈ ወደኋላ ቀስ ብሎ ማፈግፈግ ጀመረ።

«በኛ ላይ ነው እንዴ?» አለችው አንዷ

«ምን?» አለ

«መተያየሩ – ቡሽቲ! – እናትክን! – እህትክንና እናትክን እያተያየሩ በጀላ ይብዱብህ!– ውሻ!– ባለጌ!» ሁሉም አንድ ላይ ወረዱበት። በግማሽ ጨለማ ቀስ ብሎ ወደ ኋላው እያፈገፈገ «ካልተደማመጥን መሥሀ ምን ይረባል?» እንደሚል ዓይነት ሁለት እጆቹን አንስቶ ዝም አሰኛቸውና፣ ባዘነ አኳኋን ራሱን እየነቀነቀ «እኔ በፍቅር ስመጣ እናንተ በዱላ መጣችሁ?» አላቸው

«ዱላ ይከተተብህ! ቡሽቲ! – ደሞ ፍቅር ይላል'ኮ! የሌባ አደንድረት!» አሁንም አንድ ላይ ወረዱበት። ቀስ እያለ ያፈገፍጋል፣ ቀስ እያሉ ይጠጋሉ። እስካሁን እንግዲህ ዳንስ ቤቱ ውስጥ ወንዶቹ ብቻቸውን ስለቀሩ «ሴቶቹ የት ጠፉ?» ብለው ተከትለው መምጣት ጀምረዋል «ምንድን ነው? ምንድን ነው?» ይላሉ።

ከንፈ ሴቶቹን «ሸሬ ከልክል መሆኑን አላወቅኩም» አላቸው። እስካሁን እያፈገፈገ አጥሩ ጋ ደርሷል።

«እንዴት አባክ አላወቅክም?» አለችው አንዷ

«በነጋሪት ጋዜጣ አልታወጀማ! እምሳሞች! በዳችኋሁ!» አላቸውና አጥሩን ዘሎ ተፈተለከ።

ሲሮጥ «ሌባ! ሌባ! ሌባ!» እያሉ ሲንጫጩ ይሰማዋል። የበራቸውን ጉድ ከወንዶቹ ለመሸሸግ የፈጠሩት ብልሃት ነው። የመንደሩ ውሾች ጩኸቱን ተቀበሏቸው። ከዚያ የሮጠ ማሚት እሹሩሩ ቤት ገባ። በአስናቀች ላይ መዝመት ያልሆነለት ፈታውራሪ በማሚት እሹሩሩ ላይ ዘመተ። ብቻ ምንም ቢወዱትና ምንም ሺውን ቢያንዝዙባቸው፣ የለመዱት እምስ ከአዲስ እምስ እኩል አያቋምጥም፣ ይላል ፈታውራሪ። ይላል ከንፈ። በዚህ አኳኋን የአስናቀች እምስ ቀረበት። እንደቋመጠ ቀረበት። ይኼ እንዳይበቃው የዚያ ቤት ሴቶች የፈረስ ስም ሰጡት «አባ አጋዴን» ተባለ

ታሪኩን አጫውቶኝ እንዳበቃ «ወይኔ አጋዴን!» አለ «አራቱም ቀርተውብኝ እሷን በሞላሁ! አይቀርም የለ? ሹራብ ስትለብስ ጡቷን



አይቶህ የለ? የአሩሲ ከብት ቀንድ አይተህ ማየት ነው፣ ጠባብ ስትለብስ ቂጧ እግሯን ዘራፍ እንደሚል አስተውለሃል?» ትልልቅ ዐይኖቹን እያጉረ በፍንጭት ጥርሱ ሲባ ጣቱን እየቆረጠመ «ሀኝ! ሀኝ! ሀኝ! አለሳት አንድ ቀን» አለ።

ታድያ አሁን ስመለከት ቻቻ ያስደንግጣል፤ ያስቆጥታል። ነገሩ በጭራሽ አላማረኝም። እኔንስ ለምን ሳከብኝ? አብሬያቸው ቀጥ ብዬ ቢራ ካዘዙ በኋላ፣ ቀንጆ ቀይ ፊቷን ለሳቅ እያዘጋጀችና አድናቂ ዐይኖቿን አቶ ላይ እየተከለች

«እሺ ቀጥልልኝ» አለችው

«ምን?» አላት

«የአያትህንና የፈታውራሪ ሀብተጊዮርጊስን»

ስለ ፈታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ማውራት ከጀመረ ይቺ ልጅ ተበሳ የላትም። እሷ አይታወቃትም 'ንጂ ከንፈ «ሊሰራት ተዘጋጅቷል» ማለት ነው። እሱ እንደሚለው ሴቶችን በብዙ ካሳቅካቸው ሳቁ ቀስ እያለ በጉሮሮአቸው እየተንሸራተተ ወደ ሳንባቸውና ወደ ሆዳቸው ውስጥ ይገባል። ከዚያ እንደ አየር ወይም እንደ ምግብ ከደማቸው ጋር ይቀላቀልና ወደ መላ ሰውነታቸው ይሰራጫል። ሳይፈልጉህ ገላቸው ቀስ እያለ አንተን ለመቀበል ይዘጋጃል። ያን ጊዜ አንተ እጅህን ስደድ ማድረግ ብቻ ነው። እግራቸውን ከፊት ያረጉልሃል። ያ ሁሉ ሳቅ ገላቸውን ካዳረሰ በኋላ እምሳቸው ውስጥ ተጠራቅሞ ይጠብቅሃል። እና ሳቂታ እምስም አለ፣ አልቃሻ እምስም አለ። ለምን እንዲህ ሆነ? ብትል፣ ከሴቶቹዋ አይደለም ከሰውየው ነው። እንዴት ቢባል ወዘተርፈ. . .

«የት ላይ ነበርን?» አለ ከንፈ፣ እጇን በጁ እያሻሸ።

«ፈታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ አያትህን በፈረስ አሽቅድድም አሸንፈዋቸው ርስትና ከብታቸውን በሙሉ ከበሏቸው በኋላ «እንግዲህ መናጢ ድሀ አደረግኩህ» ብለዋቸው ሊሄዱ ሲሉ፣ አያትህ «የለም ጌታዬ፣ ገና አንድ ሀብት ይቀረኛል» ብለው በጆሮዋቸው ሊነግሯቸው . . ብለህ አቆምክ»

«አቆምኩ?»

«አቆምክ» አለችው እየሳቀች

«እምን። እያቴ በጆሮዋቸው «እኔ ሚስቴን ሳስይዝና እርስዎ የበሉኝን በሙሉ ያስይዙ» አሉዋቸው። እጤ ምኒሊክ ራሳቸው ሳይቀሩ የእያቴን ሚስት የማይመኙ መኳንንት አልነበሩም። ጡታቸው የሚዋጋ፣ ሽንጣቸው የሚሸሽ፣ ዳሌያቸው የሚጋፋ፣ የወንዝ ዳር ቁጠማ፣ የበረሃ ሎሚ

ነበሩ። ልክ እንዳንቺ ውብ ነበሩ። እንዳውም ስማቸው አስናቶች ነበር። ስለዚህ ፊታውራሪ ሆዬ ቲማቸው እየሳቀ «ይሁን» አሉ አያቴ «ደርሶ መልስ ነው ግን እ?» አሉ

ፊታውራሪ «እዳር ነው 'ጎጂ» አሉ

«እንግዳው ይተውት። ቀረብዎት!»

«እሺ እሺ» አሉ ፊታውራሪ

አስናቶች እየሳቁ «ሁሸትክን» አሏቸው

«ያንቺን ስጋ!» አሉና እጃን መታ። ሳቅ የሚሉት ነገር ፊቱ ላይ አይታይም። ታሪኩን ቀጠለ

«አያቴ 'ንግዲህ ብልጥ ናቸው «የፈራ እንደተሸነፈ ይቆጠራል» አሉ። ፊታውራሪ መቼም ፍርሃት የሚሉት ነገር ለልባቸው ፈጽሞ እንግዳ ነው!

«እሺ ውድድሩ በምን ይሁን?» አሉ «በፈረስ ግልቢያ፣ በዝላይ፣ በጦር ውርወራ ወይስ በምን ይሁን?»

አያቴ «በፈስ» አሉ

«ፈስ?»

«ፈስ»

«የምን ፈስ?»

«የኛ ፈስ። የኔና ያንቱ ፈስ»

«እንዴት እንዴት አንተ?»

«ተቀጥሮ ይበልጥ ብዙ የፈሳ ያሸንፋል»

«አዛዶሃል?»

«ያልት ይጥሏልን»

«እኔ ሀብተጊዮርጊስ፣ እንዳንተ ባቄላ ስቆረጥም እምውል መሰለህ 'ንዴ?»

«ፈሩ?»

«እኔ ሀብተጊዮርጊስ፣ እኔ አባ መላ፣ እንኳን ለእምስ ለመንግሥት ስማያትም ፈሴን አሳስቆጥርም» ብለው ርስታቸውንና ከብቶታቸውን መለሱላቸው።

እኔና አስናቶች እንስቃለን። እሱ ግን ትንሽ ፈገግታ እንኳን አያሳይም። ወሬውን ሊቀጥል ሲል አንዱ መጣና አስናቶችን ለዳንስ ወሰዳት። ከክንፈ ጋር ብቻችንን ቀረን።

«ለምን ና ብለህ ሳክብኝ?» አልኩት



ስግደዊ ክብብ ያንገት ጥምጥሙን እያስተካከለ «አይናለም ለተብስ ደርሳለች» አለኝና «ብሬ ነው ሀይን ሀይኑን ግለት ያለብህ»

ጠይዚህ ቤት ከጥላሁን ጋር ስመጣ ይኸው ዓመት ሆነኝ። ግን ይቺን አይናለምን ከሌሎች አሻሻጮች ለይቼ ማስተዋል የጀመርኩት ክንፈ ወድቃልሃለች ያለኝ ጊዜ ነበር። «እንዴት አወቅክ?» ብለው «ዐይንህን ከፊት» አለኝ። እውነትም ይቺ አይናለም እየሰረቀች ታየኛለች። ሳያት ትሸኮረመማለች። እንደፈለገችኝ ባውቅ ጊዜ ስውር ሙብድ ተገለጸልኝ። ፈገግታዋ ደስ እያለኝ፣ ድምቡሼ ገላዋ ምኞት እያሳደረብኝ ሄደ። አንድ ወር ያህል በሙተያየት ካሳለፍን በኋላ፣ አሁንም ክንፈ እንዲህ አለኝ።

«ለካ አይናለምና አስናቶች ዋና ጓደኞች ናቸው። ታዲያ ያቺ አይናለም አስናቶችን ምን አለቻት መሰለህ? «ይሄ ምናሌ ሸበቱ ደስ ሲለኝ፣ እንደሱ ያለ ወንድ ቢገኝ፣ አ፣ ግን እሱ በጭራሽ አይፈልገኝም» አለቻት። ይህን ከነገረኝ በኋላማ ሳያት ደስ ትለኝ ጀመር። ድምጿ፣ አረማመዷ፣ የዳሌዋ ውዝዋዜ ግሩም መሆናቸው ታየኝ። ልወስዳት ቆረጥኩ። ግን ክንፈ «አሁን አትብዳት» አለኝ።

«ለምን?» ስለው፣ እንደሚያፏጭ ሰው ከንፈሩን አሹሎ አምስት ስድስት የሲጋራ ጢስ ቀለበቶች አከታትሎ ከአፉ አወጣና፣ ቀለበቶቹ በቀዩ አየር ላይ እየተንሳፈፉ፣ እየሰፉ፣ እየተደባለቁ፣ እየጠፉ ሲሄዱ በጥንቃቄ አጠናቸው። እና የተያቱቴን መልስ እዛ ውስጥ ያነበበ ጠንቋይ ይመስል እየተንተተ በሚንተጠተጥ ድምጽ

«በዚች ትድስት ሌሊት የትድስት አይናለምን ትዱስ እምስ በትዱስ ቋላህ ብትቆፍር ትችላለህ» አለኝ «ከክቡም ይፈትጻል፣ ነፋሱም አይታሠምም የቀለበቶቹ ምልክም አይክለክልህም ግን - ግን!»

«ግን ምን?»

«ግን እንደኔ የሆነ 'ንደሆነ በጣም ያልበሰለ እምስና ያልበሰለ ገብስ በጣም ተመሳሳይ ናቸው። እንዴት ቢባል፣ ሁለቱም ያጠግባሉ 'ንጂ ሙሉ ጤና አይሰጡም። እና ትንሽ ብትቆይ ልጅቷ ይበልጥ እየበሰለችልህ ትሄዳለች። በደምብ ከወደቀችልህ በኋላ ታዲያ፣ እምሷ አንተን እያሰበ እብጦ መፍጠጥ ከጀመረ በኋላ» አልጋ ውስጥ ልሿ ጠፍቶ የምታደርገው እንደጨኋንቀት ሲት ዐይኑን ጨፍኖ ፊቱን እያኮማተረና ታጥቦ ፎጣ እንዳጣ ሰው ቀኝ እጁን በኃይል እየሬጨ፣ ብዙ ጠንካራ ስሜት ባፈነው የሴት ድምፅ «ዐይን ዐይኑን፣ ትለዋለህ ያንን ገብጋባ ጉድጓድ፣ ዐይና ዐይኑን ያንንን ለሀጫም ጉድጓን!» አለኝ።

«ግን፣ ግን - ግን!» ክንፈ አንድ ጥያቄ ከመመለሱ በፊት ... ጢስ ቀለበቶችን መሥራትና ማጥፋት ከጀመረ ለጥያቄው



Meysor Bro
t.me/BooksandYou

መልስ የለውም ማለት ነው። መልሱን እስኪፈጥር ከገፈፉን ያሾልና ከአፉ የጢስ ቀለበቶችን አከታትሎ ያወጣል፣ ለጥናት ያህል። ጠያቂው ለጥቂት ጊዜ የከንፈን ፊት ማየት ይረሳና ቀለበቶቹ እየተከታተሉ፣ እያደጉ፣ እየተደበላለቁ፣ እየጠፉ ሲሄዱ በዐይኑ ይከተላቸዋል። በዚህ በጢስ ቀለበቶች ትርኢት ጊዜ ውስጥ ከንፈ አስፈላጊውን ውሸት ፈጥሮ፣ በተገቢ ኩምክና አልብሶ ለጠያቂው መልሱን ያበረክታል።

እና ምን ዕለት ማታ ጢሱን አጥንቶ «አይናለምን አትብዳት ትቆይልህ» ሲለኝ እንዲህ ብዬ አሰብኩ። ለራሱ ፈልጓት ይሆን? እስቲ ምክሩን ልከተልና ምን እንደሚያደርግ እያለሁ። የሆነ ሆኖ እዚህ ቤት ለመብዳት አይደፍርም። ቤቶቹ ይገድሉታል። እና ከአይናለም ጋር ሁለት ወር ስንፈላለግ ከቆየን በኋላ፣ ከንፈ ዛሬ ነው መብዳት ያለብህ አለኝ። ምን እንደሚል ለማየት «የለም ትንሽ ትቆይልኝ» አልኩት

«ምን ማለትህ ነው?» አለኝ «ዛሬ መሆን አለበት ስልህ! እምስ እንደ ሥጋ ጥብስ ነው። ልክ እንደበሰለ አውጥተህ ሆኝ! ማድረግ አለብህ። ለምን ቢሉ ከመብሰል አልፎ ማረር ይመጣልና! ያረረ ጥብስና ያረረ እምስ ደግሞ አንድ ናቸው፣ ሁለቱም ከሰል ከሰል ይላሉ። ጊዜው ዛሬ ነው»

«ታዲያ አሁን ምን ከፍያት ነው 'ምብዳትን' አልኩት። የደሞዝ ቀን ካለፈ ሃያ አምስት ቀን ሆኖታል (ወይም ሊመጣ አምስት ቀን ቀርቶታል)

«እሱን ለኔ ተውልኝ» አለኝ። ከንፈ ደሞዙን በተቀበለ በሳምንቱ ሁን አድርጎ ይጨርስና እስከሚቀተለው የደሞዝ ቀን ያሉትን ሦስት ሳምንቶች ግራና ቀኝ እየተበደረ እያጭበረበረ ያሳልፋቸዋል። ስለዚህ

«ምን ላንተ 'ተውልሃለሁ?' አልኩት «የጌሾ ጊቢ ልጅ መሰለችህ 'ንዴ? ስሙኒና ፍቅር ይበቃታል ብለህ ነው?» ለጥያቄዬ መልስ ያህል ቦርሳውን አቀበለኝ። አርባ አምስት ብር አለው። አሥራ አምስቷን ከቦርሳው አውጥቼ ኪሴ ስከት ዝም ብሎ አየኝ። ቦርሳውን ስመልስለት ራሱን እየነቀነቀና በፍንጭት ጥርሱ ፈገግ እያለ

«ለምን አታምነኝም?» አለኝ

እኔም እየሳቅኩ «አምንሃለሁ'ኮ» አልኩት

«አታልዬህ አውቃለሁ?»

ይህን የጠየቀኝ ሊያታልለኝ ስላሰበ ይሆን? ይቺንስ አርባ አምስት ብር ከማን አጭበርብሮ ወስዷት ይሆን? ዝም ስለው ጊዜ

«በሳ! አታልዬህ አውቃለሁ?» አለኝና አይናለምን ዳንስ ሊጠይቃት ተነሳ። እውነቱን ነው፣ ከዚህ በፊት አታሎኝ አያውቅም።



ከሰው ገንዘብ የተበደረ እንደሆነ፣ ብዙ ገንዘብ ይዞ ባለ ደርሰው ካላናጠጡት ዕዳውን አይከፍልም። እኔ ግን አበድሬው አላውቅም፣ ገንዘብ ያለኝ ጊዜ መጥቶ «ሮክፌለር፣ እስቲ አንድ ሃያ ሚሊዮን ዕደቅብኝ» ይለኛል። መች ትመልስልኛለህ ምናምን ሳልል ሃያ ብሩን አውጥቼ እሰጠዋለሁ፣ ይሄዳል። ሳልጠይቀው መጥቶ ሀያዋን ብር ይመልስልኛል። በዚያውም ጉዊዶ ቤት ወይም ቢልትራሚ ወስዶ አራት ያዘላትና ከዚያ ውቤ በረሃን፣ መርካቶን አብረን እንዞራለን። የትም ቢሆን እኔ ልከፈል ያልኩ እንደሆን «ዛሬ ሮክፌለር እኔ ነኝ ልጄ» ይልና የሁለታችንንም ሂሳብ እሱ ይከፍላል። ማንንም ሌላ ሰው ሲጋብዝ አይቼው አላውቅም (የፈለጋት ሴት ካልሆነች) እሱ ግን ሁልጊዜ እንደ ተጋባዥ ነው። አንድ ቀን ሁለታችንም ሞቅ ብሎን ሳለ እንዲህ አልኩት።

«ውቤ በረሃ ውስጥ የማይጋብዝህ የለም። አንተ ግን ማንንም ስትጋብዝ አይቼህ አላውቅም። የገንዘብ ፍቅር ይዞህ እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ! እንግዲያው ምንድን ነው?»

«ለኔ ብለው ቢጋብዙኝ እጋብዛቸው ነበር» አለ «ግን እነሱ የሚጋብዙኝ እንዲጫወቱታቸው እንዳስቃቸው ብለው ነው። ስለዚህ ካጫወትኳቸው ብድራን መልሻለሁ፣ ከዕዳው ነፃ ነኝ። አይመስልህም?»

«የሰውን ልጅ ትንቀዋለህ እ?»

«አንተ ደሞ ከፈስህም አትቆጥረው» አለኝ «ደሞ ፈስ እንኳ ሲወጣ ቀለል ይልሃል፣ እፎይ ትላለህ፣ የሰው ልጅ ግን ምን ፋይዳ አለው? ሲወለድስ ምን ይጨምራል፣ ሲሞትስ ምን ይቀንሳል? ምን ይረባል? ምን ይጠቅማል? ምን ያረጋል? ምን ዋጋ አለው? ምን?»

«ምንም»

«እናቴን»!

«እናቴን»!

ዳንሱ ሲያልቅ አስናቀችን ያስደነሳት ሰውዬ መልሶልን፣ ከንፈ ደሞ አይናለምን ይዟት መጣና፣ አራታችን ቁጭ ብለን እንደገና ወሬ ተጀመረ

መኳንንቱ ጃንሆይን ለችሎት ወይም ለግብር ሲጠብቁ «እሁን ጃንሆይ በሯን ሲገቡ ቀኝ እግራቸውን አስቀድመው ነው ወይስ ግራ እግራቸውን? ነገ እኩለ ቀን ላይ ፀሀይዋን ዳመና ይሸፍኗታል ወይስ አይሸፍኗትም?» የመኳንንቱ ሚስቶች ሲያረግዙ «ወንድ ይወለዳል ወይስ ሴት?» ብቻ ምን ልበላችሁ በሆነ ነገር ይወራረዱሉ።

አስናቀች «በፊትክ ስትጀምርልኝ፣ እያቴ እጤ ምኒልክን ጉድ እንደሰሩዋቸው ልንገርሽ ብለህ ነበር የጀመርከው» አለችው

«እዎን እዎን። እንግዲህ እያቴ ይሄ የቁማር በሽታ እየባሰባቸው

ሄደ። አንድ ትንሽ ልጅ ከሩቅ ሲያዩ፣ ይህ ልጅ ሽራፋ ነው ወይስ አይደለም?» ብለው ይወራረዳሉ። ቀስ በቀስ ሀብታቸውን በሙሉ አስበሉ። ቢያጭበረብሩ፣ ቢያስመስሉ፣ ቢያታልሉ ማስመለስ አቃታቸው። ችግር ሆነ። አምስት ልጆቻቸውና ሚስታቸው የሚበሉት አጡ። በመጨረሻ ግቢ ሒዱና እጅ ነሱ። እጤ ምኒልክ «ምን ትፈልጋለህ?» አሏቸው

«ግርማዊ ሆይ፤ ከፈረንሳይ አገር ሲያንስ ተምሬ መጣሁ» አሉ እያቴ

«ምንድን ነው ሲያንስ ደሞ?»

«ሲያንስ ማለት ከፎቅ ላይም ሆነ ከጥርካ ወይም ከገደል አፋፍ ላይ ዘሎ በጭንቅላት ተፈጥፍጦ፣ ምንም ሳይሆኑ ብድግ ብሎ ተነስቶ፤ በአንድ እግር እየነጠሩ «እንካሴ - ወጣች ነብሴ!» እያሉ ወደ ሱሉልታ በኩል መሄድ ነው»

እጤ ምኒሊክና መኳንንቶቻቸው ይህን ማመን አልቻሉም፣ ቄሶቹማ አበዱ። ይሄ ሰው ሲጣን ነው፣ ገዘተንዋል አሉ። ጃንሆይ «እንግዲህ ሲያንስህን አሳየን» ብለው እያቴን አዘዟቸው። እያቴ «አሳያለሁ ግርማዊ ሆይ» አሉ «ነገር ግን እንዳንዴ ይህ ሲያንስ ይደናገራል፤ ከተደናገረ ደግሞ ተሰባብሮ መሞት ነው ውጤቱ። ስለዚህ ምናልባት ተደናግሮኝ የሞትኩ እንደሆን ሚስቴንና ልጆቼን አደራ» እጤ ምኒሊክ አደራውን ተቀበሉ። እያቴ የተማሩትን ሲያንስ በነጋታው ጧት እንዲያሳዩ ተወሰነ። እቴጌ ጣይቱ ራሳቸው የተከሉዋትና ውሃ እጠጥተው እሹሩሩ እያሉ ያሳደጉዋት ረጅም ባሕር ዛፍ ነበረች። እዚያ ነው ትርኢቱ።

«በሐይቆ ብት ስትል፣ ቆጳሳቱ፣ ኢጲስ ቆጳሳቱ እንዲሁም ዲያቆናቱና ቀሳውስቱ ጥምጥማቸውን ጠምጥመውና መስቀላቸውን መስቅለው፣ ፂማቸውን ዐምዕመውና ነጠላቸውን ነጥለው፣ ጳዊታቸውን ደውተውና ድግምታቸውን ደግመው፣ ዋንጫቸውን ወንጭፈውና ጣታቸውን ጠጥተው፣ እንዲሁም ዘኪያቸውን ዘክዝከው በተሰበሰቡበት ሊጥዶስ «ይህን ጳግማዊ አርዮስ አንጀቱን በቲጡ ሳይሆን ባፍንጫውና በጆሮው እናስኀለጉለዋለን!» ብለው ባርባራቱ ታቦት፣ በአርባእቱ እንስሳና በሦስቱ ሥላሴ ምለው፣ በፈረሰኛው ጊዮርጊስ ፎክረው እያሽበሸቡ መጡ። መኳንንቱ በበኩላቸው የጦር ልብሳቸውን ለብሰውና ሹመታቸውን ሽምተው፣ ጦራቸውን ጠረው ጋሻቸውን ገሽግሸው፣ ፈረሳቸውን አፍርሰው፣ እጤ ምኒሊክን አምልከው - ማለት አጅበው ከተፍ አሉ ሳር ቅጠሉን በጎራዴ እየከተፉ (ያኔ ጊዜ ሳር ቅጠሉን በጎራዴ የማይከትፍ መኳንንት እንደ ፈሪ ይቆጠርና ማዕረጉን ይገፈፍ ነበር) ተጥሎ እንግዲህ ወይዛዝርቱና እመቤቶቹ ጎፈሬያቸውን ጎፍረውና



ጉትቻቸውን ጎትተው፤ ንቅሳታቸውን ተንቅሰውና ኩላቸውን ተኩለው፤ የእጅ አምባራቸውን አንብረውና የግር አልቦአቸውን አልበው፤ እንደዚሁም ቂጣቸውን ቀጥቅጠውና እምሳቸውን እምሰው እየተሽከረመመው ከባህር ዛፉ ሥር ደረሱ

በመጨረሻ እያቴ መጡና ቃል ሳይናገሩ አንድ የታጠፈ ወረቀት ለእጤ ምኒሊክ አንድ ሌላ ደግሞ ለሊቀጳጳሱ ሰጥተው፣ ከዘለልኩ በኋላ «በምስጢር የሚነበብ» ብለው ሲያበቁ፣ እጃቸው ላይ እንትፍ፤ እንትፍ፤ አሉና የእቴጌ ጣይቱን ባሕር ዛፍ መውጣት ጀመሩ። ወጥተው ወጥተው ግማሽ ላይ ሲደርሱ ተመልሰው ወረዱ። «ይቅርታ ረሰቼ» አሉና የከበቡዋቸውን መኳንንት፣ ቀሳውስትና ወይዛዝርት «ወደዛ ዙሩ!» አሉና እዚያው ስገራ ወጡ።

ወይዘሮ አራራሽ በፍቅር አብደው፣ በሄዱበት «ፍርሀት ሲበዛ ያስራል» ማለት ያመጡት ከዚያች ቀን አንስቶ ነበር።

በኋላ እያቴ ሱሪያቸውን ከታጠቁ በኋላ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስን «ጌታዬ፣ የመጨረሻ ውርርድ» አሉዋቸው። «ከዛፍ ላይ ተወርውሬ ይቼን እር በጭንቅላቴ እመታታለሁ፣ ክሳትኩዋት ሞት ይቅጣኝ። ከመታሁዋት ግን ቀድሜዎት የሞትኩ እንደሆን ተዝካሬን ያውጡልኝ» ፊታውራሪ አልወራረድም አሉ። «ፈሩ?» ሲሉዋቸው ጊዜ «እኔ ሀብተጊዮርጊስ ነኝ የምፈራው? እሺ በል ሞክር» አሉዋቸው። እያቴ እንደገና እጃቸው ላይ ተፍተው ዛፉን መውጣት ጀመሩ።

ከወይዛዝርቱ አንዷ ወይዘሮ አራራሽ ይባሉ ነበር። እውነትም ሩህሩህ የርህሩህ መጨረሻ ነበሩ። ከእያቴ ጋር የሚያሳብድ ፍቅር ይዟቸው ነበር። ታዲያ ለሌሎቹ ወይዛዝርት የእያቴን እር እያሳዩ እንዲህ አሉ

«እዩልኝ እግዜር እሟልቶ ሲሰጥ! አሁን ይህን የመሰለ ቆንጆ እር ታይቶ ይታወቃል? እዩልኝ ቅርፁን! እዩልኝ አወጻደቁን! ተመልከቱልኝ ኩራቱን! እዩልኝ በጧቱ ብርድ ሲጤስ! አይገርማችሁም?»

«ውሽትክን!» አለችው እስናቶች እየሳቀች

«ይኸው!» ብሎ እጇን መታ። ፊቱ ላይ ፈገግታ እንኳን የለም

«እሺ ቀጥል»

እያቴ ዛፉን ይወጣሉ። ንጉሠ ነገሥቱ፣ ቀሳውስቱ፣ መኳንንቱ፣ ወይዛዝርቱ አፍንጫቸውን ይዘው በዐይናቸው እያቴን ይከተሉዋቸዋል። እያቴ ዛፉ ጫፍ ከደረሱ በኋላ ጮኸው «ውይ! እዛ ታች ሆኜ ትልልቅ ትመስሉኝ ነበር። ለካ ሁላችሁም ቅማል ናችሁ!» አሉና «ፊታውራሪ ከዚህ እሯ አትታዩኝም ያመልከቱኝ»

«እችትልህ»

«እሁንም አትታየኝም:: ጦርዎን ይሰኩባት»

«ጦሬ ይቆሽሻል»

«እሺ ከጎኗ ይትከሉት» ፊታውራሪ «ጤናም አልያዘው ይህ ደብተራ» እያሉ እያጉረመረሙ ጦራቸውን ከአሩ ጎን እየተከሉ «የባቄላ አር!» አሉ

እያቴ «መጣሁላችሁ እናንተ ቅማሎች!» አሉና ዘለሉ:: ልክ አነጣጥረው ኸያው ብለው አሯን በጭንቅላታቸው መቷት::

ክንፈ ራሱን ደፍቶ ዝም አለ:: የሲያንስን ነገር የሚያስረዳ ይመስል በቀላሉ «እንጎላቸው ደማቸውና አራቸው ተቀላቀለ» አለ «የሚያስደንቅ ትርኢት ነበር:: ውቢቱ ወይዘሮ አራራሽ «ወይኔ! ያን የመሰለ አር ተጨፈለቀ!» እያሉ ምርር ብለው አለቀሱ:: ወይዛዝርቱ አገነውላቸው አብረው አለቀሱ:: ቂጣቸውን እየደለቁና ጭገራቸውን እየነጩ እንባ በእንባ ተራጩ:: በዚያን ጊዜ የሚለቀሰው ጭገር እየነጩና ቂጥ እየደለቁ ነበረ፣ በኋላ ነው የራስ ፀጉር እየነጩ ደረት እንዲደልቁ የታወጀው::

«ፊታውራሪ መኳንንቱን፣ ቀሳውስቱንና ወይዛዝርቱን «ለተዝካሩ ጠርቻችኋለሁ:: ይህ አራም በፈስ ቢያቅተው በአር ተጫወተብኝ:: ወይኔ ሁብተጎርጊስ!» እያሉ እያጉረመረሙ ጦራቸውን ከተተከለበት ነቀሉ:: አር ነክቶት አይተው ሲናደዱ ጊዜ ወርውረው የወይዘሮ አራራሽን እግር ከመሬት ጋር ሰፉት:: አለቃ ገብረሃና «ይህም ሲያንስ ነው» አሉ

ሊቀ ጳጳሱ እያቴ የሰጡዋቸውን ወረቀት ሲያነቡ እንዲህ ይላል «እናንት ቀጣፊ ቄሶች፣ በሕዝቡ ስትጫወቱ ተራዬን ተጫወትኩባችሁ! ከዚህ አሬን እንደ እማን እያሸተታችሁ በማዕረግ ሸኘታችሁኝ መንግሥተ ሰማያት ተከፍታ ካልጠበቀችኝማ የጉድ ነው:: ግን ለማረጋገጥ ያህል ከመሞቴ በፊት ይኸው ንስሀ እገባለሁ፣ ይፍቱኝ አባቴ:: ከአልጋ ሳይ ደጋግሜ ወድቄአለሁ:: እዚህ የተሰበሰበውን ቄስ በሙሉ (ከሦስት በስተቀር) ሊቀደስ ቤተክርስቲያን ሲሄድ ጠብቄ ሚስቱን በድቼበታለሁ:: ሦስቱ ቄሶች «እኛን በምን ለይቶ ተወን? ቆማጣ ነን ወይስ ምን ጎደለን?» ብለው እንዳያዝኑብኝ የኔ ጥፋት አለመሆኑን ያስረዱልኝ አደራ:: ተራቸው ደርሶ ልበዳላቸው ብሄድ ሦስቱንም ጊዜ አለቃ ገብረሐና ቀድመው ከተው እየጠበቁኝ ተውኩት «ይተዉ አለቃ፣ ዘንድም ይገባሉ ስላቸው «አይ ጌታዬ፣ ካሚለጨው የማይገባ ማን ነው? አሉኝ::

እጤ ምኒሊክ ደግሞ የሳቸውን ወረቀት ሲከፍቱ እንዲህ ትላለች «ዓለምም አር ናት፣ ሰውም የአር ትል ነው:: እኔም ይህን ሁሉ



ትቼው ማለፌ ነው:: ስለሚስቴና ስለልጆቼ የአደራ ቃልዎን እንዳይረሱብኝ»

እያቴ በበነጋታው ጊዮርጊስ ተቀበሩ::

ክንፈ ይቺን አጭር ታሪክ ቀምሞ ለማውራት አንድ ሰዓት ያህል ወሰደ:: እኔ፣ እይናለምና እስናቀች አፋችንን ከፍተን እንሰማለን፣ እንስቃለን:: እሱ ግን ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ሳቅ ወይም ፈገግታ ፊቱ ላይ ሳያሳይ፣ በውን የደረሰ አሳዛኝ ታሪክ የሚናገር አስመስሎ አወራልን:: ሲያወራ እስናቀችን ዐይን ዐይኗን እያየ፣ እጇን እያሻሸ ነው:: ቀስ በቀስ እያደነቀችው እየወደደችው ስትሄድ ይታየኛል:: አንዳንዴ እየተነሳ ቻቻ ያስተምራታል፣ ወይም ድሮ የበረሃ ሴቶች የሚጥልበትን ልዩ የራሱ የሆነ ታንጎ ያስደንሳታል:: ይመለስና የባጥ የቆጡን እየቀባጠረ ያስቃታል፣ እጇንና ጉንጯን ይነካካታል:: አንድ ጊዜ ድንገት እዝን አለ::

«ምን ሆንክ?» አለችው እስናቀች

«ምንም» አላት ራሱን እየነቀነቀ

«ይልቅ ንገረኝ:: ምን ሆንክ?»

«እንዲያው ነው» አለና፣ ጉንጮቿን በእጆቹ ይዞ ቀና እያደረጋት «እንደዚህ ቀና ብለሽ በትልልቅ ዐይኖችሽ ስታይኝ በጣም እህቴን ትመስይኛለሽ»

«እህትህን?»

«አዎን:: እህቴ ናት ያሳደገችኝ:: እታበባ ነበር 'ምላት:: በጣም ነበር 'ምወዳት:: የዛሬ ሦስት ዓመት በወሊድ ሞተች» አለና ራሱን ደፋ

«ውይ እፈር ይብላኝ!» አለችና እጁን በሁለት እጇ ይዛ ማሻሸት ጀረመች::

እኔም በበኩሌ እይናለምን እያስደነስኩ እሻሻታለሁ:: ብቻ የክንፈን ያህል የውሸት እህት እየፈጠሩ መግደል እንደማልችል ስለማውቀው ብዙ አላወራላትም:: ይኼ ሁሉ ሲሆን ክንፈ «Cocktail a' la Fitawrari እንጠጣ:: ኮክቴል አ.ላ. ፊታውራሪ ጠጥታችሁ አታውቁም? ተጎድታችኋላ! ምን ትጠብቃላችሁ? ሁለት ጠብታ ጅን ከኢንግላንድ፣ አራት ጠብታ ኮኛክ ከፍራንስ፣ እና ከሩሲያ ቮድካ ባለመኖሩ ዐዘን እየተሰማን ሰባት ጠብታ ድግምት ዘክንፌ» እያለ ድግምቱን በግዕዝ እያጉረመረመ መጠጦቹን አንድ ትልቅ ብርጭቆ ውስጥ ቀላቅሎ ለአራታችንም አንዳንድ ትልቅ ኮክቴይል አ.ላ. ፊታውራሪ ቀዳልን:: እኔና እሱ እብዛኛውን ድርሻችንን እያረሳሳን ለነሱ አጠጣናቸው:: እስናቀች ሞቅ እያላት ሲሄድ የክንፈን አንገት ማቃቀፍ፣ ሲደንሱ ደረቱ ላይ መተኛት ጀመረች::

አይናለምም አንቱ ማለት ትታ አንተ ማለት ጀመረች::

አምስት ሰዓት ተኩል ሲሆን ክንፈ «ስድስት ሊሆን ነው:: ሳይመሽብን እንሂድ፣ እመቤቶቼ» አላቸው:: አስናቀች ወዲትየ አለችው:: አይናለምን እያመለከተ «እሳቸው እሚቴ ከፊታውራሪ ምናሴ ጋር፣ እርስዎ እሚትዬ ደግሞ ከኔ ጋር» አላት:: አስናቀች ግራ ገብቷት ስታየው

«እ! ረስቼ! ለካ አልነገርኩሽም» አለና ከኪሱ የታሸገ ኢንቨሎፕ አውጥቶ ሰጣት:: ነገሩ ስላልገባት ዝም ብላ ስታየው፣

«ጥላሁን የላከልሽ ደብዳቤ ነው አንብቢው» አላት:: ካሻሻሎቿ አንዷ ማንበብ ታውቃለች:: አስናቀች ጠራቻትና ደብዳቤውን አስነበበቻት::

«ለክብርት ውድ የምናፍቅሽ ፍቅሬ አስናቀች እንዴት፣ በሥራ ምክንያት ቢሾፍቱ ስለተላኩና ከእኩለ ሌሊት በፊት ልመለስ ስለማልችል፣ አደራሽን ከክንፈ ጋር ሒደሽ ብርሃኑ ቤት እንድትቆይኝ:: አደራ! ክንፈ ብቻውን ወይም ከምናሴ ጋር ወይም ከብርሃኑ ጋር መጥቶ ይወስድሻል:: ምናልባት ብዙ የዘገየሁ እንደሆን ክንፈ ያጫውትሻል:: በጣም ናፍቀሽኛልና አደራ እንዳትቀሪብኝ፣ ይላል የሚወድሽ ጥላሁን»

አስናቀች በጣም ደስ አላት «እንግዳው ክፈሉና ውጡ:: እኛ ነጠላ ለብሰን በወድያኛው በር እንመጣለን» አለችና «አይ ጥልዬ፣ ትላንት አብረን አድረን ዛሬ ናፈቅኩት!?» እያለች ከአይናለም ጋር ተያይዘው እየተሳሳቁ ወደ ውስጥ ገቡ::

ነገሩ በፊትም ቀፎኝ ነበር፣ አሁን የባሰውን ቀፈፈኝ:: ደብዳቤው ሲነበብ በእንባቢዋ ትክሻ በኩል ዐይኔን ጣል አድርጌ አይቼው፣ ጽሕፈቱ የጥላሁን አይደለም የክንፈ ነው:: አስናቀች ምንም መጠርጠር አልቻለችም:: ክንፈ ደብዳቤውን ያነበበላት ጊዜውን ጠብቆ በወሬው ከፈዘዘችና በኮክቴይል ኢ.ላ.ፊታውራሪ ከሰከረች በኋላ ነው::

«ጥላሁን እጁን ተሰብሯል?» አልኩት ክንፈን

«ለምን?» አለኝ:: መሳቅ አምሮታል፣ ግን ሳቁን ገና ሳትወለድ ገደላት

«እንዴ ረስቼ ለካ» አልኩት «ጥላሁን ቅዳሜ ቅዳሜ መጻፍና ማንበብ ይረሳ የለም 'ንዴ?» ሳይወድ ሳቁ ፊቱ ላይ ተንሸራሸረች:: መጀመሪያ ዐይኖቹ አበሩ፣ ቀጥሎ ፍንጭት ጥርሶቹ ብልጭ አሉ:: እኔም ሳልወድ እየሳቅኩ «አስናቀችን ብትበዳት የራስህ ቁላ ነው» አልኩት «በኋላ ጥላሁን በፈረሰኛው ፎከሮ አንድ ሁለት ቦክስ ሲያሳርፍብህ የራስህ አፍንጫና ጥርስ ነው:: ግን እኔን እዚህ ጉዳይ



ውስጥ ለምን እንዳስገባኸኝ በግልጽ እንድታስረዳኝ እፈልጋለሁ» ሲጋራውን በረዥሙ ሳበ:: ከአፉ ስድስት ሰባት የጢስ ቀለበቶች እከታትሎ አወጣና ሲንሳፈፉ ያጠናቸው ጀመር:: ጉልህ ዐይኖቹ በረጃጅሙ ሽፋል ጥላ ውስጥ ተደብቀው ሁለት የሀዘን ሃይቆች፣ የምስጢር ሃይቆች ይመስላሉ:: ሊያቀብለኝ የፈለገውን ውሸት ሲያዘጋጅ ለማየት አልቻልኩም:: ግን በሱ ፈንታ ማሚት እሹሩሩና ሴሉቼ የበረሃ ቤቶች ለምን እንደሚወዱት በድንገት የታየኝ መሰለኝ በደንብ ፊት ለፊት ታይቶኝ ሳይሆን እንደዚሁ . . . ባልታሰበ ዩቂታ . . . በዐይኔ ጎን በኩል . . . በጨረፍታ ብጫ . . . እንደ ብልጭታ ዓይነት . . .

ፊሙን ሁልጊዜ ሙሉጭ አድርጎ እንደተላጨ ነው:: ግን ሉጫ የራስ ፀጉሩ ወደ ጉንጩ እንደመውረድ ይልና ልክ ከጆሮው ጫፍ አቅጣጫ ሲደርስ ይቆማል:: በማስመሪያ የተሰመረ እንጂ በምላጭ የተስተካከለ አይመስልም:: ሮክ'ን ሮል አዲስ አበባን ወሮት የበረሃ ቤቶች የኤልቪስ ፕሬዝሊን ስዕል በየመኝታቸው ግድግዳ መለጠፍ የጀመሩ ጊዜ «ይሄ ኤልቪስ የፀጉር ቁርጡ እንደ ክንፈ ነው» ይሉ ነበር «ግን አፉ የሴት ይመስላል:: አፍስ የክንፈ ይምጣብኝ»

ክንፈ — መጠነኛ ቁመት ያለው ወጣት፣ ቀይ መልክ መልካም ፊት የኤልቪስ የፀጉር ቁርጥ፣ ሲስቁ የሰነበቱ የሚመስሉ ጉልህ ዓይኖች፣ ዘወትር የማይታይ ቀንጆ ባለፍንጭት ጥርስ ፈገግታ፣ ሲሰሙት ውለው ቢያድሩ የማይሰለች ጨዋታ፣ ለተመልካች የሚያስደስት አለባበስ፣ የግል የሆነ ልብ የሚያጠፋ አይናንስ:: እና ከዚህ ሁሉ ጋር ማንም የማይስተካከለው የገንዘብ መርጨት — ለበረሃ ቤቶች ‹ክንፈ› ማለት ይሄ ነው:: ዘወትር ተከዞ ያዩታል:: የከበቡት ሰዎች ሁል ጊዜ በሳቅ እንደፈረሱ ነው:: እሱ ግን እንዲያም አያስቅ — እንድያውም መልክ ቀና ፊቱ ላይና ትልልቅ ዐይኖቹ ውስጥ ብዙ ብዙ ሀዘን የሰፈረ ይመስላል::

አንዳንድ ማታ ለብቻው ቁጭ ብሎ ውስኪ እየጠጣ፣ ሲጋራ እያጨሰ በሀሳብ ፈረስ ሲጋልብ ያዩታል:: ከአፉ እየተከታተሉ የሚወጡት የጭስ ቀለበቶች እየራቁ እየሰፉ . . . እየሳሱ . . . እየጠፉ ሲሄዱ ትልልቅ ዐይኖቹ ፍዝዝ ብለው ይከተሏቸዋል:: ዐሳቦቹ ናፍቆቶቹ . . . ትዝታዎቹ ከአንጎሉ ወጥተው ሄደው ከጭሱ ጋር ጥቅልልል ጥምዝዝዝ ያለ ዳንስ ይደንሳሉ. . . . እንዲ ሀሳቡ በአንድ የጭስ ቀለበት አንገቷን ብቅ አድርጋ ምላሷን ስታወጣበት ሲያያት ፊቱ ላንድ አፍታ በፈገግታ ይበራል . . . ግን ከትዝታዎቹ አንዷ ያንኑ የጭስ ቀለበት ተጎናፅፋ ራሷን ደፍታ ስታለቅስ ያያታል ትንፋሽ ይከማተራሉ፣ ከንፈሮቹ በሀዘን ይጋጠማሉ

እይ እንቺ ሕይወት! እንደ ብርጭቆ ውስኪ እየጣመች፣

እያገለፀች የምትሄድ ሕይወት፣ እኛ መጣንንት፣ እንደ ጭስ ቀንደላት እየተሳፉ እየጠፉች የምትሄድ መጣንንት፣ ጠፉ ጢስ ነኝ`ኑ ግን አስጨንቆ መታገል ያሻል የዘመን ጨለማ እንዳይውጠን ቤት ፋ ብርሃን ውስጥ መንደረድር፣ የብርሃና ጉፋስ እንዳይመታን ቤት ወት ተራራ ሥር መጠለል፣ የዕድሜ ብርድ እንዳይነጩን የቤት ጭን መልበስ፣ የሞት ብርፍ እንዳይወስደን እምነ ውስጥ ችካል መትከል፣ የእምነ ገመድ መቋረጠ፣ ቤቶችን መብላት፣ ቤቶችን በሙሉ እንደ ሴአንድ መብላት፣ አንዷች እንኳን ሳትቀር ሁሉንም መብላት፡፡ የጉሮሮን ድብብቆሽ በሙሉ ልብ መጫወት፣ ከሞት ሸሽቶ እምነ ውስጥ መደበቅ፣ መብላት፣ ዐይን ዐይኑን ማለት፣ እሁንም ትንሽ ፈገግታ

ፈታወራሪ አንቺ ፈታወራሪ

ሴትም ቀንም እምነ ስትቆፍሪ

ሟምተሽ ወተ ወንሽ እንዳትቀሪ፣ ፈገግታው እያደገ ይሄዳል፡

የተኳሉ ጉልሀ ዐይኖቹ አብዘኞውን ጊዜ እንደዘጉ ወይም እንደፈዘዙ ነው፡፡ ግን ቤቶቹን በምኞት ሲመለከታቸው ከዐይኖቹ አንድ ዓይነት ብርሃን ይወጣና ዐይኖቻቸውን፣ ፊታቸውን፣ መላ ሰውነታቸውን ያሰሙሳቸዋል፣ እንደ ሙቀት ቢጤ እንደ ፍቅር ዓይነት ያንኳኳፉቸዋል፣ ወደሱ ይስባቸዋል . .

ታድያ «እዚህ ጉዳይ ውስጥ ለምን እንዳስገባኸኝ ንገረኝ?» ስለው ጊዜ የጢስ ቀለበቶቹን ተመለከተና ሲያበቃ

«ውጭ እነግርሃለሁ» አለኝ

«ውጭ እስክንደርስ ይረሳል ብለህ ነው?» አልኩት

«አይ አንተ፣ ባንተ ቤት ዘላለም ሳታልልህ እንደሞከርኩ ነው፡፡ ሌላ ፍላጎት የለኝም፡፡ ግን ተባስተሃል፡፡ ነገሩን ለማስረዳት ጊዜ ስለሚወስድ፣ ሴቶቹ በጓሮ በር ወጥተው ብቻቸውን ውጪ ከሚጠብቁን እኛ ወጥተን እያወራን ብንጠብቃቸው ይሻላል ብዬ ነው፣ አይመስልህም?»

የመጠጣችንን አስራ ሰባት ብር ከፈለ፡፡ ከቤቱ መታፈንና መወበቅ ስንወጣ ንፁህ አየር ፊታችንን ተዝተገ ባለ እጅ ደባበሰልን፡፡ ሰማዩ ንፁህ ነው፣ ብዙ ከዋክብት ፈሰውበታል፡፡ ከንፈ የስልክ እንጨት ስር እየሸና «ንፋሱ ደስ አይልም?» አለ «በበጋ ሙቀት የምትዳስሰው ቀዝቃዛ የቤት ዳሌ አይመስልም?»

በጠባቧ ባቡር መንገድ ጥቂት ሰዎች እያወሩ ወደየቤቱ መጋረጃ እያዩ ይሄዳሉ፡፡ በሁለቱም በኩል የተሰለፉት ቤቶች በጩኸት የጎረና የሰከረ ሙዚቃቸውን ከደም መብራት ጋር ባቡር መንገዱ ላይ ያስታውኩታል፡፡ ከወዲያ በኩል እበሩ ላይ አረንጓዴ ክበራብት ቤት



ፆታት ሰዎች እየተጋፉ እየተሳሳሉ ወጡ፡ [illegible] የሚወትሮው ቆብ ከበሩ መጋረጃ [illegible] ድፎ አንድ ነገር ተናገረ፡፡ [illegible] ቀርቦ [illegible] ቤት [illegible] እንደ ጓደኞችን ቆሙ፡፡ ኢ - ቶ እያረገ፡፡ ፊት [illegible] ቤቶች ነጠላቸውን እንደተሳሳሉ [illegible] እስከሰቶ ሄደ፡፡

በኛ ተርታ ካሉት ቤቶች ከአንዱ ውስጥ አንዲት ወይዘሮ ወጣች፡፡ ባቡር መንገዱን በዐይኗ ቃኘች ተመልሳ ገባች፡፡

«ቆአረቦች መኪና መጢኢት ነው» አለኝ ከበፊ

«የአረቦች?»

«ቂሚን 'ማበዲት ደምባሮች አረቦች አሏት»

«ውሸታም'»

«ምን ያስቀሽኛል? ቂሚ ምን እንደሚያበል አለዋም»

«ቂሚ ተለቀ ብለህ ነዋ»

«ኖ፣ በጭራሽ፣ ቂሚ አረብ 'ሚፈልገው ዓይነት ነው 'ንጂ እራሱ 'ምፈልገው ዓይነት ነዋ»

«እየምርኩ ቂጥ 'በዳለሁ በለኝ»

«አይ፣ እየምርኩ አልበዳም፣ ጥሩ ሳገኝ ግን አልምርም»

«ኢድ፣ »

«ሙት፣ ምናለዐት?»

«ምንም የለበትም እሁስ፣ ብቻ ይቀፋል»

«ባትቀምሰው ነው»

«ይጣፍጣል?»

ሊባ ጣቱን በፍንጭት ጥርሱ እየቆረጠመ «ሀን፣ ሀን፣ ሀን፣ ልብ ነው 'ሚያጠፋው ዐይን ዐይኑን ስትለው» አለ

«ምን ምን ይላል?»

«ቂጥ ቂጥ ይላል»

«ምን ትቀልዳለህ? እኔ የምሬን ነው» አልኩት እየሳቅሁ

«ታዲያ ምን ምን ይላል ለበልህ?»

«ከእምስና ከሱ የቱ ይጣፍጣል?»

«እንደ እምሱና እንደ ቂጡ ነው»

«በል ተወው . . እውነት ይቺን ሴትዮ አረቦች ቂሟን ይበዷታል?»

«እንዴ፣ ያውም ብሎ እየከፈሉ እያስፈነደቁ ነዋ «እንቺ ቶንጂ ቶንጆ፣ መሊኪ፣ ኩስ ቡምጃ፣ ፋ፣ ቅቤና በሻር!» እያሉ ነው።

«ለጠባሻ ግን አትሰጥም»

«ምናልባት አንድ ሁለት የሚሸጡዋቸው ህፃናት እያጠቁም። ግን ጠባሻ ያወራብኛል ብላ ትፈራለች። ለጠባሻ እምስ፣ ለአረብ ቶንጎ፣ ለፈረንጅ እፍ ነው 'ምትሰጠው፣ አዋቂ ነች»

«ኸረ?»

«ክፈለት ደሞ ያስጠብቋታል»

«ይህን ሁሉ እንዴት አወቅክ?»

«በረሀን ሳውቀው ደኅኜው ጠጪኝ ዓመት ሆነን»

«አንተ በድተሃታል?»

«አዎን»

«ምኗን»

«እምሷንም - ቶሟንም - እፏንም»

«የቱ ይበልጥ ይጣፍጣል?»

«እንደ ሰዓቱ ነው። ከጠዋኝ ሰዓት በፊት ከሆነያት እምሷ ነው ጥሩ፣ ከጠዋኝ ሰአት በኋላ ግን ቶሟ ይሻላል፣ ወሮች መንጫጫት ከጀመሩ ወዲያ እፏ ነው ግሩም፣ ከሰኞ ቀን እስከ ሌሊት ከሆነ፣ ብቻይ fantastic ነው»

አሁንም እየሳቅኩ «የውሽ ልጅ፣ እኔ በውነት ለግመት ፈልጌ ስጠይቅህ አንተ ትቀልድብኛለህ?» አልኩት

ድንገት ቦርሳውን ከኪሱ መዞ ከውስጡ ያስር ብር ወረቀት አውጥቶ እኔ ኮት ኪስ ውስጥ ጨመረ። ቦርሳውን እንደገና ወደ ደረት ኪሱ መለሰ። ይህንን ሁሉ በሚያስገርም ፍጥነት ሲያደርግ፣ ወሬውን አላቋረጠም።

«በጭራሽ ቀልዴን አይደለም። አንተ ራስህ አንድ ቀን ሄደህ ለምን አትሞክረውም? - እ፣ እሽቴ፣ ከሆት ብቅ አልክ ጂል?»

ለካ ከኋላዬ እሽቴ መጥቷል። ለከንፈ ያጎቱ ልጅ ነው። አግብቶ ሁለት ልጆች ወልዷል። ድሮ ለከንፈ ሲል በረሀ ይመጣ ነበር። ካጨ ወድያ ግን በረሃን ረግሟት አያውቅም። ከከንፈ ጋር አብሮ አደግ ስለሆኑ ከንፈን በደንብ ያውቀዋል። እኔን ከጨበጠኝ በኋላ ከንፈን በቁጣ «አርባ አምስት ብሬን ጠብ፣ ቶሎ!» አለው።

«የምን አርባ አምስት ብር?» አለ ከንፈ

«ከክብለ ቦርሳ የወሰድክትን!» ሰብለ የእሽቴ ሚስት ናት።



«መቼ?» አለ ከንፈ

«ባሬ ማታ ነዋ፣ ደሞ መቼ ይለኛል'ኮ አንተ ሰው የለም ብለህ ስትገርቅ፣ ቅጣው ድብብቆሽ ሲጫወት ነበር፣ አየሁ» ብሎ አንገቱን አነቀው። ጠብደል ብጤ ነው። ከንፈ ትንሽ እንኳ ሳይታገል «ተሳስተሃል እሽቴ፣ ከምታንቀኝ ለምን አትፈትሸኝም?» ብሎ ቦርሳውን አውጥቶ ሰጠው።

እሽቴ ለቀቀውና ቦርሳውን ከፍቶ «ሦስት ብር ብቻ ቀረች?» ብሎ ሦስቷን ብር ኪሱ ከተተ። ቦርሳዋን በንዴት መሬት ላይ ጣላት። ከንፈ ሊያነሳት ጎንበስ ሲል «ቆይ!» አለና የስልክ እንጨት አስደግፎ ኪሶቹን አንድ በአንድ ፈተሸው። በመጨረሻ ጫማውን አስወልቆ፣ ጫማው ውስጥ እጁን ሰድዶ ፈለገ። ምናልባት እግር ሹራብ ውስጥ ደብቆ እንደሆነ ብሎ እግሩን ቢነካካውም ምንም አላገኘም።

ይህ ሁሉ ሲሆን ከንፈ የስልክ እንጨቱን ተደግፎ ያንን ጥምጥሙን እያስተካከለ ዝም ብሎ ይፈተሻል። እሽቴ ተስፋ ቆርጦ «ሦስት ብር ወስጃለሁ፣ አርባ ሁለት ብር ይቀረኛል በደምዝ ቀን እንገናኝ» አለውና እኔን ጨብጦኝ ሄደ።

ከንፈ ቦርሳውን ከመሬት አንስቶ እራግፎ ኪሱ ከተተና፣ የጫማውን ክር እያሰረ «ታዲያ ያቺ ሲትዮ ለ'ንዲህ ዓይነት በግ ሕዝብ ቶንጎ አልሰጥም ብትል ይፈረድባታል?» እያለ ከእሽቴ ፍተሻ ያመለጠችውን አስር ብር ከኪሲ ወስዶ ቦርሳው ውስጥ እየከተተ «ጎሽ መጡ እንዚያ ቶንጎሬዎች» አለ።

ካጠሳ ለብሰው ኳሽ አስረው እያወሩ መጡ። ሳያቸው ጊዜ ከንፈ ሲያጭበረብረኝ እንደቆየ ገባኝ

«በሩህልኝ አንተ የውሽ ልጅ!» አልኩት

«ምንድን ነው 'ምታወራው?»

«የእረብ የቲጥ ወሬ እያወራህ ጥያቄዬን አስረሳኸኝ»

«በጭራሽ አላስብኩትም - ታድያስ፣ እንሂድ እመጢቶቹ?»

የብርሃኑና የኔ ቤት ሦስት ክፍል አለው። አንዱ የብርሃኑ መኝታ፣ አንዱ የኔ መኝታ፣ ሦስተኛው ምግብና እንግዳ ቤታችን።

ከንፈ የ'ንግዳ ቤታችንን መብራት እያበራ «ግቡዋ» አለ። ገባንና ተቀመጥን። ወደኔ መኝታ ሄደ። ጠርሙስ ውስኪ ይዞ ተመለሰ። መቼ ገዝቶ እዛ እንዳስቀመጠው አላውቅም። እኔ ጧት ስሄድ መጠጥ የሚባል አልነበረችም። ለእራታችንም ውስኪ ቀዳልንና፣

«እንግዲህ እንደ ፀጋዬና እንደ እሙሻው ሲናልኝ ፉት እንበላት» አለን

«ፀጋዬ ያ ገብጋባው?» አለች አስናቀች:: ክንፈ በጭንቅላቱ አዎን ሲላት፣ ወደ አይናለም ዞረችና «ያ ሁልጊዜ አንዲት አሬንጅ አስቀድቶ ሌሊቱን ሙሉ 'ሚያስደንስ፣ ለማንም መጠጥ ገዝቶ የማያውቅ ገብጋባ ነው'ኮ» አለቻት «አታስታውሺውም? ያ ቀለሟን እንኳ አንድ ቀን ወስዶ አሳድሮ ገንዘብ ሳይከፍላት የሰደዳት?»

«እ! ያ ጫማው 'ሚቆንስ ለምቦጫም?» አለች አይናለም

«አውቀሽልኛል! ወይ ክንፍዬ፣ ደሞ እሩቅ አለው 'ንዴ?»

«ያውም ምን የመሰለች ክረዳ!» አለ ክንፈ «አንድ ቀን እሁድ ጧት ይኸውላችሁ፣ ፀጋዬ ከአረብ ቤት አንዲት ሲናልኮ ጠርሙስ ገዝቶ ሲወጣ አገኘሁት::

«ምን ትልቅ ግብዣ አለብህ ዛሬ?» አልኩት

«እረ ለሱ ሲገርምህ!» አለና «ከኪሱ አንድ ጭብጥ የምትሆን ጋኮ አውጥቶ አሳየኝ፣ ያስር ሳንቲም ብስኩት «ወይ አባ መንዝር! ይሄ ሁሉ ምን ሊደረግበት ይሆን?» አልኩት

«ገርል ፍሬንዴን ከቤቶቼ ጋር እንድትተዋወቅ ልጋብዛት ነው» አለኝ

«ታዲያ ይሄ ሁሉ ወጪ ለአንድ ግብዣ?»

«ምን ላርግ ባክህ፣ ያው ዞራ ዞራ የኔ መሆኗ አይቀርም ብዬ ነው» አስናቀችና አይናለም «ይሄ ገብጋባ! ይሄ ቀናሳም!» አሉ::

ክንፈ እንደገና መጠጥ ከቀዳልን በኋላ፣ አስናቀችን ምኞት በሚዋኙባቸው ትላልቅ ዐይኖቹ እያያት ቀጠለ

«ግብዣው አልቆ ፀጋዬ ልጅቷን ቤቷ አድርሷት እንደተመለሰ፣ እናቱ «ትቅርብህ ልጄ» አሉት

«ለምን?» ቢላቸው

«ቅንዘረኛ ናት:: አላየህም 'ንዴ? እኔን ስትጨብጠኝ አባትህን ዐይን ዐይናቸውን እያየች ነበር» አሉት

አባትየው መለሱና «እኔን ስትጨብጠኝ ደሞ አንቺን እያየች ነበር» አሉዋቸው::

ፀጋዬ አስረዳቸው «እንዲህ የመሰላችሁ ሸውራራ ስለሆነች ነው» አላቸው እናትየዋ «ሸውራራ ናት 'ንዴ? እኔን ምች ያጠናግረኝ! ጠንጋራ ናት ለካ:: እኔ'ኮ አንድ ዐይና መስላኝ» አሉ

አሁንም አስረዳቸው «አንድ ዓይና የመሰለችሽ ግራ ዐይኗን ሁሌ ስለምትጨፍን ነው»

«ለምን ልጄ?»



«ብጉሯን ስታፈርጥ እያመጣት አንድ ዐይኗን ስትዘጋ በዛው ለመደባት ጠባይዋ ግን በጣም ጥሩ ነው»

«እረ ባለጌ ናት ልጄ»

«ለምን?»

«እጄን ታጥባ ሳታደርቀው ጨበጠችኝ»

«ታጥባ መች ሆነ፣ እማማ?»

«እንግዲያማ?»

«እጄን ያልባታል»

«ላብ ኖሯል? ላባም ናት በለኝ! እኔን ኩባያ ሙሉ ያልበኝ! እንዲህ ከሆነስ አግባት» አሉት

አባቱ ለብቻው ወስዱና «በጣም ጥሩ መርጠሃል:: እንግዲህ እሷን አግብተህ ማረፍ ነው:: ሸውራራ፣ ብጉራም፣ ላባም በመሆኗ ማንም ስለማይፈልጋት አትባልግብህም:: እኔም እናትህን ያገባኋት ለዚሁ ነበር:: ያውም ከወለደች በኋላ ተሻሽላ አይተሃት ነው 'ንጂ፣ ያገባኋት ሰሞን በጨውም አትቀመስም ነበር»

ከዚያ በኋላ የነበረው ወሬ በጭራሽ ቅጥ ያጣ ይሁን ወይም አቅጣጫ ያልነበረው ይሁን አላስታውስም:: ከዚያም በላይ ቀስ በቀስ ሳይታወቀኝ ሰክሬያለሁ:: ሁላችንም ሰክረናል:: እየጮህን እናወራለን፣ እንስቃለን፣ እንከራከራለን:: ክንፈና አስናቀች ይተቃቀፋሉ፣ እኔና አይናለም እንሳሳማለን::

ክንፈ ቀስ እያለ ወሬውን ወደ እምስና ቁላ አዙሮት ኖሮ፣ አራታችንም ተራ በተራ ስለድሮ ዘመን ውሽማ «በእንተ እግዚአትነ ማርያም! የመሸብኝ እንግዳ አሳድሩኝ» ብሎ የሰው ሚስት እየበዳ ስለሚያድር ተማሪ፣ ጌትየው ዘመቻ ሲሄድ የመቤቱን እግር እያጠበ ቀስ በቀስ ከባት ወደ ጉልበት፣ ከጉልበት ወደ ጭን አሻሽቶ ስለሚበዳ ባርያ «ቼ እያለ ይነዳል፣ በሁለት ጀላ ይበዳል!» እያለ እየዞረ ሴት ወይዛዝርትን ስለሚበዳ ነጋዴ፣ ስለ አለቃ ገብረሃና . . . ስናወራ፣ ስንስቅ፣ ስንቀልድ፣ ክንፈ የአስናቀችን ጭን ሲደባብስ፣ እሷ ቀንድቡን በጇ ስታስተኛለት አየሁ:: ለካ ይህን የእምስና የቁላ ወሬ ያመጣው የአስናቀችን ምኞት ለመቀስቀስ ኖሯል::

በመጨረሻ ሰባት ተኩል አለፈ:: እንተኛ አለ::

«ጥላሁንስ?» አለች አስናቀች

«ከንግዲህ 'ሚመጣ አይመስለኝም:: አልማዝ አለቅ ብላው ሳይሆን አይቀርም»

«የማን አልማዝ?»

ክንፈ ነገሩ ያመለጠው ለማስመሰል «ማን አልማዝ አለ?» አላት

«አንተ ነሃ!»

«እኔ?»

«አዎን»

«ስክሬ ነው አትስሚኝ» ብሎ እስናቀችን ለማረሳሳትና ለማባበል ይመስል

«እንኳን አልማዝን ፀሐይን ራሷን ካንቺ ይበልጥ አይወዳትም» አላት «ኧረ ለሰው እየሰጠችበት እያስቀናችው ነው 'ንጂ እስከ አሁን ይተዋት ነበር:: ባንቺ ስትታይ ምን አላት? ያቀመሰችው መድኃኒት ቢኖር ይሆናል 'ንጂ:: ግን እውነት መናገር ይሻላል፣ ምንም አትል:: እምሷም ጣት ያስቆረጥማል ይላሉ. . . ኡፍ! ምንድነው 'ምለፈልፈው? . . እንሂድ እንተኛ!» ጥላሁን አልማዝንም ፀሐይንም ከተዋቸው ሁለት ዓመት አልፎታል፣ እስናቀችን ከያዘ ገና ዓመትም አልሆነውም::

እስናቀች «እንኳን ሁለት ውሽማ ሃያ ይኑረው ይኼ ውሻ! ደሞ ወንድን ማመን» እያለች እየተንገዳገደች ከክንፈ ጋር ወደ ብርሃኑ መኝታ ገባች::

አይናለም ክንፈን «ደህና እደር፣ ጋሼ አጋዬን» አለችውና ከኔ ጋር እየተንገዳገድን ወደ መኝታዬ ሄድን:: ልብሳችንን አውልቀን መብራቱን አጥፍተን ይህን አንሶላና ፍራሽ እስኪበቃው ድረስ ካለፋነው በኋላ፣ ክንዴን እንተራስኳትና ሁለታችንም እፎይ አልን:: እንቅልፌ መጥቶ በድካም ሻሽ ሸፋፍኖ ሊሰርቀኝ ሲል፣ ከሩቅ ቦታ የአይናለም ድምፅ «ምናስዬ. . .» ሲል ተሰማኝ:: በግማሽ እንቅልፍ ልቤ «እ?» አልኳት

«እስከዘላለም እውድሻለሁ ብለህ ማልልኝና እኔም እስከ ዘላለም እምልልሃለሁ» አለችኝ:: ፍራንዝ ካፍካ የፈጠረው የቅዠት አለም ውስጥ ያለሁ መሰለኝ:: መጠጡና ግብረ ስጋው ባያደክመኝ ኖሮ በሳቅኩ ነበር:: እንቅልፍ በጣም ስለተጫጫነኝ ዝም እንድትልልኝ ብዬ «እሺ» አልኳት

ታዲያ እሷ ዝም ልትል ነው? «ለምን ወደድከኝ?» አለችኝ:: ቂንጥራም! ደሞ እሷን ስወድ ሥራ አጥቼ:: አሁንም በግማሽ እንቅልፍ ልቤ «አንቺስ በምን ወደድሽኝ?» አልኳት

«በፊት'ኮ አልወድህም ነበር:: እንዳውም እስናቀችን «የማነው ይሄ ደሞ ያለጊዜው የሸበተ?!» እላት ነበር:: መቼ ያንተ ፍቅር እንደጀመረኝ ታውቃለህ?»

ዝም አትልም 'ንዴ? «እህ. . .» አልኳት



«ጋሼ አጋዬን «ጓደኛዬ ምናሴ ባንቺ ፍቅር ሊሞት ነው ያሉኝ ጊዜ ነው» እንቅልፌ ድንጋይ እንደወረወሩበት ወፍ ጥሎኝ በረረ::

«ክንፈ ነው እንዲህ ያለሽ?»

አዎን:: ይሄ ውሽታም እባብ! ተጫወቱብኝ የለም 'ንዴ? እኔን «ያቺ አይናለም ወድቃልሃለች» ያለኝ ጊዜ ለካ እሷንም ደሞ ሔዶ «ይሄ ምናሴ ወድቆልሻል» ብሏት ኖሯል::

«ሌላስ ምን'ለሽ?» አልኳት

«ጋሼ ጥላሁን የሰከሩ ወይም የተናደዱ ጊዜ ካንተ በቀር ሊገታቸው የሚችል የለም:: የሆነውን ሰው መስደብ መደብደብ ነው:: ጓደኞቻቸው ተው ያሉዋቸው እንደሆን ዞረው እነሱኑ ይደበድቡዋቸዋል:: አንተ ካለህ ግን ጋሼ ጥላሁን ምንም ቢሰክሩ ምንም ቢናደዱ «ጥላሁን ተው!» ስትላቸው ፀጥ ብለው እንደ ትንሽ ልጅ ይታዘዙሃል»

«ሌላስ?»

«አንተ ዴዘርት 'ምትመጣው ለጨዋታው ነው 'ንጂ ሽርሙጣ ተኝተህ አታውቅም:: አንዳንዶቹ ሽርሙጦች ተኝቶናል እያሉ ያወራሉ:: ግን ስለፈለጉህ ነው 'ንጂ ውሸት ነው:: አንተ ስራም አላጣህ ሽርሙጣ ስትተኛ:: አንተ ምትተኛው የትልልቅ ሰዎች ሚስቶችና ልጆች እያማረጥክ ነው»

«እሺ»

«ቢያንስ ቢያንስ አስር የራስ፣ የደጃዝማች፣ የሚኒስቴር፣ የድሬክተር ልጆች ድንግል ወስደሃል:: የአንድ ትልቅ ሰው ሚስት ወሽመሃቸው ስለወደዱህ ፖፔል መኪና ገዝተው ሰጡህ:: አንተ ግን አልቀበልም አልካቸው:: የባሰውን ወደዱህ፣ አበዱልህ:: በሁለት ወሩ ከኢንግላንድ የተመለሰች ልጃቸውን አልጋህ ውስጥ አገኙዋትና ሽጉጥ ተኮሱባት:: ልቧ ላይ ነበር ያነጣጠሩባት:: ግን ልጅቷ የተማረች ስለነበረችና እንግሊዝኛ ታውቅ ስለነበር «ማይ ጉድነስ ማሚ!!» ብላ ዘወር አለች:: ጥይቱ የግራ ጡቷን ጫፍ በጥሶ ወሰደው:: ከፈለክ እምቢ 'ምትልህ ሴት የለችም:: ግን እስከዛሬ ድረስ ሽርሙጣ ተኝተህ አታውቅም፣ አይደለም?» አለችና በሃይል አቀፈችኝ:: ድጋሚ አምሯት ነው::

«አዎን - አዎን. . . አሁን ተኚ» ብዬ ግንባሯን ስሜ አስተኛኋት::

አይ ክንፈ! ይህን ሁሉ ውሸት የፈሸከላት መቼስ እንድትወድቅልኝ ብሎ ነው:: እኔም በበኩሌ እንድወድቅላት ብሎ ደህና አድርጎ ዋሽቶኛል:: ግን ለምን ይህን ያህል እንድትወድቅልኝ ፈለጋት ይሆን? እስቲ ነገ እጠይቀዋለሁ. . . የውሻ ልጅ! እስናቀች ሙታንቷዋን እንድታወልቅለት ለማድረግ እንዴት ያለ ውሸት - እንዴት ያለ

ሦስት እግር፣ እንዴት ተርስ፣ ግማሽ ቀንድ ያለው ውሸት እየፈጸመች ይሆን? ግን ምን ያቅታል? ከቀፎ ንቦች እንደሚፈልቁ ያህል ከሰ ጭንቅላት ውሸት ይፈልቃል። ከሺው አንዱን ለአስናቀች ግቀበል ነው። ከዚያም በላይ በደምብ አርጎ አዘጋጅቷታል። እንደኛ፣ አስከሯታል። ሁለተኛ፣ በታንጎ፣ በቻቻ፣ በኩምከና፣ በተረት ልጓን አጥፍቷታል። ሦስተኛ፣ ጥላሁን ገና ሳያውቃት የተዋወቃቸውን ቤቶች ስም እያነሳ በቅናት ብዛት ጥላሁንን ለመበቀል ስትል ብቻ እምስ ልትሰጠው እንድትቆርጥ አድርጓል. . . . ይሄኒ ዐይናይኑን ይለዋል ያን ገብጋባ ጉድጓድ፣

ግን በኋላ ጥላሁን ሲሰማ ከንፈ የት ይገባል? ይገለዋል መቼስ! ግን ምን አለ? ቀላል ነው። ለጥላሁን ደሞ አንድ ዐይን፣ ሁለት እና አንድ ክንፍ፣ ግማሽ ቂጥ ያላት ቆንጆ የሆነች ውሸት ያቀብለዋል. . ይሄ ውሻ፣ ወንድ ነው'ኮ ግን. . . ሳስብ ሳሰላስል፣ እንትልፍ መጥቶ በክንፈ ኩምክና እያጭበረበረ ሊወስደኝ ሲል፣ ቀጭ፣ ሲል ተሰማኝ። ዐይኔን በእጄ ሸፈንኩ። መብራቱ በርቶ ዐይኔን እየወጋኝ በምቾት ማየት ሳልችል ትንሽ ቆየሁ። በኋላ ሳይ፣ ክንፈ የብርሃኑን ፒጃማ ለብሶ በሩ ጋ ቆሟል። በእጁ ጠራኝ። የፒጃማዬን ኮት ብቻ እንደለበስኩ፣ የቤት ጫማዬን አጥልቄ ወደሱ ሄድኩ። እንግዳ ቤት አስገባኝና ምናልባት አይናለም እንዳትሰማን በሩን ከዘጋ በኋላ እንደማፈር እያለ

«ሞላሃት?!» አለኝ

«የለም፣ ድንግል ነኝ ብላ እምቢ አለችኝ»

እየሳቀ «ትጣፍጣለች?»

«ምንም አትል»

«እንግዲህ አልጋ የምንለዋወጥበት ጊዜ አሁን ነው» አለ

«ምን ማለትህ ነው?»

«ቤት እንለዋወጥ»

«ለምን?» አልኩት

«ሊሊቱን ሙሉ ከእንዲት ቤት ጋር ስትተኛ አይሰለችህም?»

«ለምን ይሰለቸኛል?»

እንዳዘነልኝ ሰው ራሱን እየነቀነቀ «ባላገር፣ አስናቀችን መብዳት አትፈልግም?» አለኝ እንደመገረም ብሎ

«ይቀፈኛል»

«ለምን ይቀፍሃል? እኔ ስለበዳኋት ነው? አይ ቂሉ! እንዲያውም ያኔ ነው ይበልጥ የሚጣፍጠው»



«ኪድ!» ማካለቢ ነበር፣ ግን እየሳቅኩ ነው

«ባላገር አትሁን! ስምንተኛው ሺ ውስጥ ነው ያለነው። ለመሆኑ የተበዳ እምስ ቀምሰህ ታውቃለህ?»

«ብዙ ጊዜ! እስካሁን መቼስ ድንግል ቀድጄ አላውቅም»

«ምን ትላለህ? ለሁሉም ጊዜ አለው። አሁን የቀልድ ሳይሆን የእምስ ጊዜ ነው። እምስ ምንም ቢሰቅ ቀልድ እንዳይመስልህ። ዋናው ቁም ነገር ነው። ለዚህ ነው እቁመን 'ምንገባበት። እኔ ምልህ፣ ቤትየዋ እንደ ተበዳች ያኔውኑ በትኩሱ ሔደህ በድተህ ታቃለህ ወይ?»

«የለም»

«እንግዳው በዳሁ አትበል!» አየሁት። ውሸቱን ይሁን እውነቱን ለማወቅ አይቻልም። ግን ሁልጊዜ ማሚት እሹሩሩ እሱ እያያት እንዱን መልከ መልካም ወጣት ይዛ ወደ ጠንፍየለሽ መኝታ ስትገባ፣ እንደሊሎቹ ወንዶች ሲቀና ወይም ሲያኮርፍ ወይም ሲበሳጭ አይቼው አላውቅም።

«አንተ በድተህ ታውቃለህ?»

«ቢያንስ በሳምንት ሁለቴ!»

«እንደረጠበ እንደተጨማለቀ ትከትበታለህ?»

«ተንደርድሬ ነዋ ያውም!! ብትቀምሰው ሁለተኛ ያልተበዳ እምስ አታሳዩኝ ትላለህ። ግባና ቅመስ። አስናቀችን በደንብ አብስዬልሃለሁ ስላንተ ያልነገርኳት ታሪክ የለም። ተዘጋጅታ ትጠብቅሃለች»

«አንተስ?»

«እንዳመጣብኝ አይናለምን እሰፋታለሁዋ!»

«ኪድ፣ ውሻ!» አልኩትና ትቼው እየሳቅኩ ወደ መኝታዬ ተመለስኩ አይናለም ነቅታ ቆየችኝ

«የት ሄደህ መጣህ?»

«የትም። ተኚ» አልኳትና መብራቱን አጥፍቼ ገና አልጋ ውስጥ እንደገባሁ፣ ክንፈ በጨለማው

«ልጆች፣ ከናንተ ጋር ካላስተኛችሁኝ አልሆንም» አለ

«ምነው?» አለችው አይናለም

«አስናቀች አባረረችኝ» አለና እየተደናበረ በጥግ በኩል አልጋችን ውስጥ ገባ። አይናለም መሃላችን ሆነች።

«እስይ አይናለምዬ፣ እንዴት ትሞቂያለሽ፣ በወንድምነት ባቅፍሽ ምናለ?»

«አትፈኝ ጋሼ አጋዴንዬ!» እንዴት ላባረው? ዝም አልኩት።

የቀልድ አስመስዬ እሷን «ወደዛ እንዳትሄሪ ልባርጊ» አልኳት

«አልዮርም» እያለች አቀፈችኝ:: አጭር ፀጥታ:: ክንፈ «አይናለም፥ በደምብ አልተመቸኝም:: ትንሽ ፎቅ በይልኝ:: ክንፈ ወደዛ እንደሱ ... ይህን ደሞ ትንሽ ወደዚህ ... እ! ... ይህን ተኚ የኔ ቆንጆ ... በደምብ ተመቻችቻል:: ደህና 'ደረልኝ» ረዥም ፀጥታ::

ክንፈ በእንግሊዝኛ «እሀ! ስንት ሊትር ነው ያፈሰስክባት እኛ ሴት?» አለኝ

«ምን አገባህ?» አልኩት

«ለምን አያገባኝም? ገብቼ የለም 'ንዴ?»

«ከትቼባታለሁ እንዳትለኝ ብቻ!!»

«አይደለ አትበሳጭ:: ቁላዬን ብቻ ነው የከተትኩባት»

«Son of a bitch!»

«ምን ሳኖፋቢች ኪችኪች ትላላችሁ? ሰው በሚሰማው ቋንቋ አታወሩም?» አለች:: ሳላውቀው «እቺ ቀጣፊ! ክስር ኘርሳ ውጣ ከላይ ታወራለች» የሚል ሀሳብ መጣብኝና ሊያበቀኝ ሲል ቶሎ ከአልጋዬ ዘልዬ ወጣሁ - ወደ እስናቀች ሄድኩ::

ክንፈ ስለኔ ምን ግሩም ታሪክ እንደነገራት እንጃ፤ ገና አልጋ ውስጥ ከመግባቴ አቀፈችኝና ጭኗን ከፈተችልኝ ... ድንገት በወይ ሕሊናዬ ጥላሁን መፋቂያውን እንደነከሰ ሲስቅ ታየኝ:: አሁን እንግዲህ ክንፈ በድቷታል:: ስለዚህ እኔ ብበዳትም ባልበዳትም ልዩነት አያመጣም ብዬ አሰብኩ:: ግን ራሴን እንደምደልል ታወቀኝ:: ስካሩ ነው:: አሁንም ራሴን መደለል ... ይልቅ ዝም ብሎ መደሰት ይሻላል ... ራስን ሳይታልሉ ህቅን ተንተርሶ መብዳት:: ይህኔ'ኮ እሷም ራሷን ትደልል ይሆናል .... እስቲ እንጠይቃት::

«ምንድን ነው 'ምታስቢው?» አልኳት

«የጥላሁን ጓደኞች ናችሁ ብዬ ባምናችሁ፤ እስከራችሁ ተጫወታችሁብኝ አይደለም?» ... ይኸውልህ ራስን መደለል ...

ግን ደሞ የተበዳ እምስ ያለልክ ከመርጠቡ በቀር ከተራው እምስ ምንም ልዩነት የለውም:: ተው ግድ የለህም፤ እቺ ክንፈ የተበዳ እምስ እምጪልኝ የሚል ዛር ሳይደይዛት አይቀርም:: ውቤ በረሃ ዛር ቤት ደጃፍ ላይ የማሽላ ቆሎ ሳይሆን፤ እምስ ደጃፍ ላይ የሌላ ወንድ ኃጥያት አርከፍክፉልኝ የሚል ዛር — ትግሬው አበበ ... ግን የለም፤ ደሞ የክንፈ ዛር «ትግሬው አበበ!» ሊል አይችልም «Le Marquis de



Sade!» ማለት አለበት:: ነብዩ ምግሊም አበሮቹ የተባሉቸውን በዱሩና እንዛ ሊያውቃቸው ጀመረ፥ ራስደም ታየው፤ ነጋውም የተምቀቸ ስለት ነበረ፤ በታውም ጃንሚዷ፤ ራስዬም በምስት ገቢር ተገለጸለት፤ እንደሚከተለው

ዝጊር አንድ

ክንፈ ዛሩ ይመጣበትና፤ እሳት እየጎረሰ

«የባስቲይ ነብይ

ለ ማርኪ ዶ ሳድ

የሚያስተምረን ወግጥ አበጻድ

ብዴ ተብዴ፤ ተኝ እፈንድዴ

ብትችሉ ብዴ፤ ባይሆን ተብዴ

ዴ፤ ዴ፤ ዴ፤

ዴ፤ ዴ፤ ዴ፤

እያለ አልፍ ጊዜ ከንቋለጠ በኋላ፤ መሬት ይወድቅና በቁላው እፍ ኃጢአት ይደፍቃል::

ዝጊር ሁለት

ሃምሳ እምስት እምሳም ሴቶች እምሳቸውን እየነፉ፤ ቂጣቸውን እየደለቁ፤

ቀይ ቀይ የት ትበዳለህ?

እኛን እስፈንድደህ

ቀይ ቀይ የት ትበዳለህ?»

እያሉ ብዙ ካለቀሱ በኋላ፤ ከክንፈ ጭኖች መሐል እምስት ቆሏጦች እውጥተው ቅልልቦሽ ይጫወታሉ::

ዝጊር ሶስት

አንድ ቅንዝራም ቄስ፤ ራቁታቸውን ሆምራዊ፤ ጥምጥም እንደጠመጠሙ፤ የቀኝ እግራቸውን አውራ ጣት በግራ እጃቸው ይዘው፤ በግራ እግራቸው እያነጠሩ ይመጡና፤ ክንፈ ወደ ወደቀበት በኩል በስሚያዊ ቁላቸው እያማተቡ

«በምስ እፍ፤ ወወንድ፤ ወፈስ ቁኑስ ገዝቼሃለሁ፤ ተናገር:: አንተ ማነህ?» ይሉታል::

የክንፈ ዛር በክንፈ አፍ ይናገራል፤ «የበረሀ ዛር ነኝ»

ቄስ:- «እንዴት ያዝከው?»

ዛር:- «ምች መትቼ»

ቄሱ፦ «መቼ? በምን ጊዜ? እንዴት? በምን ሁኔቴ? በምንስ አኳኋን?»

ዛር፦ «እምስ ልሶ አፉን ሳይታጠብ ሲወጣ በተሲያት አግኝቼው በጥፊ መታሁት፣ አጮልኩት፣ አጠናገርኩት»

ቄሱ፦ «ማን ላከህ? ከማን ተላክህ? ላኪህስ ማነው?»

ዛር፦ «ለ ማርኪ ደ ሳድ»

ቄሱ፦ «በማን ስም ላከህ? በስመ ማን?»

ዛር፦ «በስመ ጋኔል ወሳጥናኤል»

ቄሱ፦ «እንድትለቀው ምን እናርግልህ? ምንስ ይደረግልህ? ደግሞስ ምን ይጠበስ?»

ዛር፦ «የውርዴ ሦስተኛ፣ የቁምጥና ሰባተኛ ትውልድ በሆነ የቦካ ፂማም እምስ:: ደጃፉ ላይ ሃያ ሁለት የሃጢአት ጠብታ ርጩልኝ፣ አንጠባጥቡልኝ፣ አርከፍክፉልኝ»

ቅንዝራሙ ቄስ በተለይ ከኢየሩሳሌም ያስመጡትን ቅዱስ ቂላቸውን እከንፈ ሃጢአት ውስጥ ነክረውት፣ ድርሳነ ቂላኤልን እየደገሙ እንዷ ወፍራም ሴትዮ እምስ ላይ ይረጩታል:: እምሱ ሦስት ጊዜ ጮሆ ሰባት ጊዜ ካንራ በኋላ፣ አሥር ጊዜ ይስቅና፣ የከንፈን ዛር ይውጠዋል:: ከንፈ ዛሩ እንደለቀቀው ዐይኑን እያሻሸ

«የት ነኝ?. . . ይፍቱኝ አባቴ» ይላል

ሃምሳ አምስቱ እምሳም ሴቶች ከእምሳቸው ነጭተውት የነበረውን ጭገር በጸጥታ እየለቀሙ መልሰው እምሳቸው ላይ ሲተክሉት. . . መጋረጃው ይዘጋል. . .

. . .አስናቀች እየጣመችኝ ስትሄድ እንጎሊ ራዕይ ማየቴን ትቶ ማሰብም አቆመ:: እሷም በበኩልዋ ሊጥማት ጀምሮ ኖሮ፣ በሃይል እያቀፈችኝ «አንተዬ፣ ለመሆኑ እንዴት አስቻለህ?» አለችኝ

«እንዴት ማለት?» አልኳት

«ዓመት ሙሉ በቀን በቀን ስታየኝ. . . የኔ ፍቅር እያቃጠለህ. . . ወንድ ማለት እንዲህ ነው 'ንጂ!. . . በጭራሽ አያስታውቅብህም:: አሁንም ቢሆን ከንፈ አጋዴን ባይነግረኝ አላቅብህም ነበር» አይ ከንፈ! እግዜር ይይለት! «እስይ! እንዴት ነው ምታረገኝ አንተዬ!?. . . ልጃገረዶቹንም እንዲህ ታረጋቸዋለህ? ንገረኝ እንጂ፤ እንዲህ ነው 'ምታረጋቸው?»

«አንዳንዴ»



«እኔ እየመሰልኩህ ነው እውነት?»

«አዎን»

«አይ! እንግዲህ ያንድ ዓመት ፍቅር በአንድ ሰዓት ይውጣልህ. . አይ. . . ይ. . . ይ. . . ! መጣ. . . መጣ. . . መጣ. . .»

ሲበርድልኝ ጊዜ በጣም ቀፈፈኝ:: ትቻት ተነሳሁ:: በጭለማው እንዳልጋጭ እጄን ወደፊት ዘርግቼ ወደነ ከንፈ ስመለስ፣ አንድ ሀሳብ ድንገት መታኝ:: ቅድም ከንፈ በእንግሊዝኛ አደናለምን ከትቼባታለሁ ሲለኝ እውነቱን ነበር? ወይስ እንድሄድለት የፈጠረው ውሸት ነበር? በጭለማው «ቅድም ለምን አላሰብኩበትም?» ብዬ ራሴን እንደ ኮረኮምኩት:: አመመኝ:: እያሻሸሁት እነከንፈ ጋ ደረስኩ:: አልጋ ውስጥ ስገባ

«የት ነበርክ?» አለችኝ

«ሽንት ቤት:: ሊያስቀምጠኝ ጀመረ:: አሜባ ይዞኝ እንዳይሆን ብቻ»

ከንፈ በእንግሊዝኛ «ታድያስ? የተበዳ እምስ ጣት ያስቆረጥም የለ?» አለኝ

«በጭራሽ! አሁን ቦታ አታጣበኝ ሂድልኝ ልተኛበት»

«እሺ መሄዴ ነው:: ብቻ ጠዋት እንዴ መሙላት እንዳትረሳ»

«ለምን?»

«ያኔ ደሞ ልዩ ጣዕም አለው»

«ምክንያቱስ?»

«ትንሽ ይገማላ!»

«ሂድ ከዚህ፣ የውሻ ልጅ!»

«ደራሲ መሆን እፈልጋለሁ፣ ስለሕይወት ማወቅ እፈልጋሁ ትላለህ:: ታዲያ ልጄ፣ የእምስ ግማት እየፈሩ ስለሕይወት ማወቅ ይቻላል ብለህ? «እማን እማን እብለከሙ፣ ዘይፈርሆ ለእምስ ኢይአምሮ ለሕይወት» ይላል 'ንጉሥ ዳዊት» አለኝና አደናለምን «ደህና 'ደሪ የኔ ቆንጆ» አላት

«ደህና 'ደሩ ጋሼ አጋዴ'ንዬ!» አለችው

በእንግሊዝኛ «ዛሬ የሠራነውን ነገ እናስታውስሙም» አለኝ:: እንዳያፍሩ ማለቱ ነው::

«ok»

«ok»

«የተበዳ እምስ ምን ምን እንደሚል አሁን ቀመስክ:: ጥይት ደራሲ

መሆን ከፈለግክ ጠዋት ደሞ የሚገማ እምስ ምን ምን እንደሚል መቅመስ እንዳትረሳ ዘ ኢይቀምስ ኢይአምር ብሎ-ታል» አለኝና በጭለማው እየሳቀ ወጣ::

«ተበድቶ ሲያበቃ እንደገና የተበዳ እምስ መልሶ መብዳት ምን ምን እንደሚል ሞክር ጥይት ደራሲ እንድትሆን» ሳይለኝ እንዴት ሄደ? ብዬ እያሰብኩ ጀርባዬን ወደ አይናለም አዙሬ ባንዳፍታ ለጥ አልኩ::

አይናለምና እስናቀች በማለዳ ተነስተው ወደቤታቸው ሊሄዱ ሲሉ፣ ትላንት ማታ ከክንፈ ወስጄ የነበረውን አሥራ አምስት ብር በግማሽ እንትልፍ ልቤ ለአይናለም ሰጥቻት ተገላገልሁ ተኛሁ::

በስድስት ሰዓት ስኑቃ ክንፈ ቀድሞኝ ተነስቶ ሄዷል:: አሁንም የትላንት ማታውን ጉዳይ እስረዳኝ ብዬ ሳልጠይቀው አመለጠ. . .

. . . እዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ እንደገለጽኩት፣ ጥላሁን ክንፈን እንደ ቱሃን ለመጨፍልቅ፣ እኔና ብርሃኑ ደግሞ እንዳይጨፈልቀው ለመገላገል ማሚት እሹሩሩ ቤት ሃስታችን እየጠጣን፣ እየተጫወትን ክንፈ እስኪመጣ እንጠብቅ ነበር:: ግማሽ ሰዓት ያህል ከቆየን በኋላ ጥላሁን አንዱን ሰውዬ ሠላምታ ሲሰጠው ሳለ ብርሃኑ ቶሎ ብሎ-

«አንድ ሰበብ ፈጥረህ ውጣና ክንፈን ፈልገው» አለኝ:: «እዚህ እንዳይመጣ አስጠንቅቀው፣ እኔ ጥላሁንን እንዳይወጣ አቆየዋለሁ»

ወጣሁና ክንፈን ፍለጋ ጀመርኩ:: ጋዲሴ ቤት፣ ፈትለወርቅ ቤት፣ ታየች ቤት፣ ፀሀይ መጠለያ ቤት፣ Baby Face ቤት፣ እስገደች አላምረው ቤት፣ እስማረች ቤት፣ አልማዝ ቤት፣ ሮዛ ቤት. . . ያላጸረስኩት ቤት የለም:: ክንፈን አጣሁት:: እንዲያውም ዛሬ በረሃ ብቅ ያለ አይመስልም:: አንድ አርባ አምስት ደቂቃ ያህል ስፈልገው ቆይቼ ተስፋ ቆረጥኩ:: በኋላ ወደ ማሚት እሹሩሩ ቤት ተመለስኩ::

የበሩን መጋረጃ ስገልጥ ብርሃኑ፣ ትርሲት፣ አሥራት እንቁ፣ ሦስት ሌሎች ሰዎች እና ጥላሁን ራሱ! ባንክኒው ጋ ቆመው ክንፈን ከበው ይስቃሉ::

ክንፈ ስለ «ሳንሱር» (ማለት ሕዝብን የሚጎዳ ወይም መንግሥትን የሚቃወም ጽሑፍ እንዳይታተም ስለሚቆጣጠሩ ባለሥልጣኖች) ሲነግራቸው ቆይቶ፣ አንድ ታሪክ ጨርሶላቸው እነሱ በሳቅ ሲንከተከቱ፣ እሱ ውስኪውን እየጠጣ ሲመለከታቸው ደረስኩ:: ሳቃቸው ትንሽ ጋብ ሲል ሌላ ታሪክ ጀመረ::

አንድ ቀን ደሞ አንድ ቀጭን ባለመነጽር ሰውዬ መጣ:: ሽማግሌው ተይ እርሳሳቸውን በሴንጢያቸው እየቀረፁ



«መንበር ይውሰዱ እቶ» አሉት

ጣቱን እያንቋቋ ቁጭ አለ:: Nervous ሰውዬ ነው

«ግሩም መጽሐፍ ጽፈዋል በጠቅላላ ማለቴ ነው:: እንግዲህ የምጠይቆት ጥቂት ጥያቄዎች አሉ:: እዚህ መጀመሪያ ገጽ መጀመሪያ መስመር ላይ «የገባችው ፀሐይ» ሲሉ ማንን መጥቀስዎ ነው? ጨረቃስ ማንን ታመለክታለች?»

ደራሲው «ፀሐይም ፀሐይ ነች፣ ጨረቃም ጨረቃ ነች» አላቸው

«እሱማ ነው:: እረ ትርጉማቸው?»

«ምንም ትርጉም የላቸው»

«ትርጉም ከሌላቸውማ እዚህ ውስጥ ምን ይሰራሉ?»

«ምንም አይሰሩም?»

«አይ የዛሬ ወጣቶች! ምንም ካልሰሩማ የእብድ መጽሐፍ ሊሆን አይደል? ብቻ እሱን ለጊዜው እንለፈው:: ሰባተኛው መስመር ላይ «ልጃገረዲቱ በቅል ውሃ ቀድታ ሰጠቻቸው» ብለዋል:: ልጃገረዲቱስ አዲስ አበባችን ትሁን፣ እንግዲህ ውሃው ምንድን ነው? ቅሉስ ማን ወይም ምንድንነው?»

«ምን ማለትዎ ነው?» አለ በቁጣ ድምጽ:: ትዕግስት የሚሏት የለችም::

«አንተ 'ንጂ ምን ማለትህ ነው?»

«እኔማ ልብ ወለድ ታሪክ መፃፌ ነበር»

«እኔ ደግሞ ከንጉሡ ነገሥቱ የተሰጠኝን የሳንሱር ተግባሬን መፈጸሜ ነው:: እሺ እሱንም እንለፈው መጨረሻ መስመር ላይ «እጁን ታጠብኩ» ብለሃል ጲላጦስ ከክርስቶስ ደም ንፁህ ነኝ ሲል ታጠበ:: አንተ ከማን ደም ንፁህ ነኝ ለማለት ነው እጅህን የታጠብከው?»

ደራሲው ከመገረሙና ከመናደዱ የተነሳ ክንፈሩን ነክሶ ዝም አለ::

«ለዚህም መልስ የለህ:: እሺ፣ አሁን ወደ ሁለተኛው ገጽ እንለፍ:: ሦስተኛው መስመር ላይ «ልጆቱ የምትለብሰው ልብስ ስላልነበራት በጨለማ ብርዱ ይገርፋት ጀመር ያልከው፣ ጠቅል አባታችን የት ሄደው ነው እናት ኢትዮጵያን በድንቁርና ጨለማ የረሀብ ብርድ የሚገርፋት? በልኮ መልሱን አምጣ!» አሉና ጠረጴዛውን በመዳፋቸው መቱት

ሁለቱም በመነጽራቸው ተፋጠጡ

ደራሲው «እንብበው ጨርሰውታል?» አላቸው

«አምስት ገጽ አንብቤለታለሁ»

«ከሰጠሁዎት አምስት ወሩ ነው'ኮ!!»

«በወር አንድ ገጽ መሆኑ ነው:: አየህ መጽሐፍህ ብዙ ምስጢር

የቆረቆረችው መሆን አለባት። እንዲያውስ ልበ-ጠባብ መሆን ነው 'ንጂ፣ እስናቀችን ተኛትስ አልተኛትስ ለኔ ምን ልዩነት ያመጣል?

እጁን ትከሻው ላይ ጣል እያደረግኩ «ና እንግባ እንጠጣ» አልኩት

እየተናፈጠ «ጎንቲም የለኝም» አለኝ

«እኔ 'ጋብዝሃለሁ» ብዬ ገፋፍቼ አስገባሁት።

ሁለት ዶፒዮ ዊስኪ አከታትሎ ጅው አደረገ። ከዛ በኋላ እንደ ድሮው የቡምክና ወሬ ጀመረ።

ሞላሁን ነገሮች ሲጨርስ «አሁን እንዳንተ ሃሳብ ክንፈ እስናቀችን ተኝቷታል ወይስ አልተኛትም?» አልኩት

«የተኛት ይመስለኛል። ግን ላይተኛትም ይችላል። ብቻ ተኝቷት ሳይሆን አይቀርም። ግን አልተኛት እንደሆነስ? እቺን ጥያቄ ሳጠና ሳወርድ ለማደር እችላለሁ»

Meysor Bro
t.me/BooksandYou



# ምዕራፍ ስምንት

## ምስጢረ ጴጥሮስ

«ሰው ሆዱን የሠራ ወንዱን
የሚያውቅ የለም»
(የጉራጊኛ ምሳሌ)

እኛ ወንዶች ውቤ በረሀ የምንመጣበት ቀና ምክንያት ንብረ ሥጋ አይደለም። ቢሆን ኖሮ ጃንሆይ ሙዚቃው ባላበሉት፣ ሴትና አልጋ በበቃ ነበር። እንደ ቸርቺል ጎዳና የበረሀ መጠጥ እጥፍ ይከፈልበታል፤ ስለዚህ መጠጥ ፍለጋ ቢሆን ኖሮ ሌላ ቦታ በሄድን ነበር።

ብዙዎቻችን ሠራተኞች ነን፣ ተማሪ አይደለንም። ግን በረሀ መምጣት የጀመርነው በተማሪነታችን ጊዜ ነው። ያን ጊዜ የምንመጣው ለ«Adventure» ነበር፣ ሴት አቅፎ ለማስደነስ፣ መጠጥ ለመቅመስ፣ በረሃ ሄጃለሁ ለማለት፣ ምናልባትም ቢገኝ ሴት ለመተኛት።

አሁን ግን የተማሪ «Adventure» ምናችንም አይደለም። እኛ የምንመጣው ለሌላ ጉዳይ! ብዙዎቻችን ሠራተኞች ነን፣ ትንንሽ ቢሮ ውስጥ የምንውል፣ ትንንሽ ደሞዝ የምንቀበል፣ ትንንሽ ኃላፊነት ያለን ትንንሽ ሠራተኞች። የመሥሪያ ቤት አለቆቻችን ራሳቸው ትንንሽ ሰዎች ናቸው። ቴሌፎን ሲደወል ብድግ ብለው ቆመው የቢሮአቸውን ግድግዳ እጅ እየነሱ «አዎን ጌታዬ! እሺ ጌታዬ!» ብለው የሚያናግሩ ሰዎች፣ ደርሰው እኛ ላይ ትልቅ ባለሥልጣን የሚሆኑብን ሰዎች፣ ተራቸውን «አዎን ጌታዬ! እሺ ጌታዬ!» የሚያሰኙን ሰዎች። እይ መሥሪያ ቤት! እንጀራ ባይሆንበት የሰው ልጅ መሥሪያ ቤት ይውላል?!

ማታ ከሥራ በኋላ ወደ ቤት መሄድ ደሞ አያስመኝም። እንዲያውስ ቤት ምን አለ? ከእራት በኋላ ምን የሚደረግ ነገር አለ? ሰው ዶሮ አይደለ፣ በሐይ እንደገባች አይከተት፣ አባብ እንሽላሊት አይደለ፣ ለብቻው ድንጋይ ስር ተጠቅልሎ አያመሽ። ደጃች ውቤ ሰፈር የምንመጣው ከብቸኝነት ለመሸሽ ነው። ብቸኝነታችንን ሸሽተን ስንመጣ፣ እንደኛው ብቸኝነታቸው አባሮአቸው ከመጡ ሰዎች ጋር እንገናኛለን፣ ብቸኝነት ካስቀመጣቸው ሴቶች ጋር እንተዋወቃለን። ከወንዶቹ ጋር ጓደኝነት፣ ከሴቶቹ ጋር ፍቅር ይፈጠራል። ወይም ጥላቻ ይፈጠራል። እሱም እንደ ፍቅር ነው፣ ከብቸኝነታችን ያስጥለናል።

ከብቸኝነት ሽሽተን የመጣን ወንዶች ብቸኝነት ውስጥ ከሚኖሩ የበረሃ ሴቶች ጋር ስንገናኝ ስንት ዐይነት ፍቅር ይረገዛል! አንዳንዱ ይወለዳል፣ ሲወለድ ሙሉ ይሆናል፣ ወይም ጭንጋፍ ወይም አካለ ጎዶሎ ይሆናል። አንዳንዱ ያስወርዳል፣ ስንት ዓይነት ፍቅር!

ግድ የለሽ ፍቅር፣ ውብ ወጣት ፍቅር — የትርሲትና የብርሃኑ ፍቅር

ፍቺ የለሽ ፍቅር፣ ውትብትብ ፍቅር — የጠንፍየለሽና የጴጥሮስ ዓይነት ፍቅር

የቆየ ፍቅር፣ የተፈተነ ፍቅር — የማሚትና የክንፈ ዓይነት ፍቅር። ስንትና ስንት ዓይነት ፍቅር!

እኛ ወንዶች ጺማችንን ተላጭተን፣ ሱፋችንን ቦርሽን፣ ከራቫታችንን አስረን፣ ጫማችንን ወልውለን፣ ቦርሳችንን እንደአቅማችን አጭቀን - ብቅ እንላለን።

ሴቶቹ ግብር ውሃ ወጥተው፣ ቀሚሳቸውን መርጠው፣ ፀጉራቸውን ተበጣጥረው፣ ፊታቸውን ተኳኩለው፣ ሽቷቸውን አርከፍክፈው፣ በኣርታቸው ጠንቁለው «ቀይ ሽማግሌ ይፈልግሻል» ሲጠብቁን ቆይተዋል።

እንገናኛለን፣ እንዋደዳለን። ስንት ዓይነት መዋደድ! ለውጭ ሰው እንቆቅልሽ የሆነ ምስጢራዊ መዋደድ — የክንፈና የማሚት እሹሩሩ ዓይነት መዋደድ። ደምበኛ ኢትዮጵያዊ የሆነ መዋደድ ከነዱላው — የጥላሁንና የአስናቀች ዓይነት መዋደድ።

ውቤ በረሃ — የመዋደድ አገር፣ የፍቅር ከተማ!!

ደጃፉ ውቤ ሰፈር ብቻችንን የምንመጣ ሰዎች ጥቂቶች ነን። ለምሳሌ ጋሼ አልተገናኘንም፣ እኔ፣ ክንፈ። አብዛኛዎቹ ሰዎች ሁለት ሁለት፣ ሦስት ሦስት ወይም አራት አራት እየሆኑ ይመጣሉ። በማህበር የሚመጡም አሉ — ለምሳሌ የካሳ ወልደአማኑኤል ማኅበር፣ የነ አለማየሁ ማህበር።

ጴጥሮስና ብርሃኑ እንቶኔኔ ሁለቱም ሁልጊዜ አብረው ይዞሩ ነበር። ይህን አብሮ መዞር እንዴት እንደጀመሩት ግን ብርሃኑ አያስታውስም። እሱ በተለይ የሚያስታውሰው አንድ አርብ ማታ ነው። ሰባት ስምንት ቤት አብረው ሲዞሩ ሰንብብተዋል። ውቤ በረሃን በሞላ ተራ በተራ አዳርሰው አይተው፣ ከሁሉ ቤት ይበልጥ የማሚት እሹሩሩ ቤት እንደሚያስደስታቸው ተገንዝበው፣ ገንዘብ ካልተረፋቸው በቀር ሌላ ቤት መሄድ ትተው፣ ማሚት እሹሩሩ ቤት ግን ቢያንስ በሳምንት ሦስት ጊዜ መሄድን ደምብ አርገው፣ እዚያው አንዳንድ



ቤት መርጠው ማብሰል ጀምረዋል። ይህ ሁሉ ግን እነሱ ሆን ብለው ያደረጉት ሳይሆን፣ ነገሩ ራሱ በገዛ እጁ እንደተዘጋጀላቸው ዓይነት ነበር።

ያቺ አርብ ማታ መጀመሪያ ጴጥሮስ መጣና «ልደትህን እናክብር» አለው

«እንዴት አድርገን?» አለ ብርሃኑ

«እሱን ለኔ ተውልኝ»

«ለመሆኑ ልደቴ መሆኑን እንዴት አወቅክ?»

ጴጥሮስ ጥርሱን ሳያሳይ ሳቅ ብሎ፣ ጭንቅላቱን በሌባ ጣቱ እየመታ «አለቻ እዚህ!» አለው

«አለቻ!» አለ ብርሃኑ

«እንግዲህ ዛሬ የኔ እንግዳ ነህ አሉ። እኔ እንዳልኩት ነው ምናገረው። ይሁን?»

«ይሁን»

«ሀ፣ ገላችንን እንታጠብ»

ታጠቡ።

«ለ፣ እንዘንጥ»

እዚህ ላይ ብርሃኑ ትንሽ ቸገረው። ኮሌጅ የሰጠው አንድ ልብስ ብቻ አለው፣ እሱም ሦስት ዓመት ሙሉ አገልግሏል፣ አርጅቷል። ሁለቱም ሸሚዞቹ ቆሽሸዋል። ባለፈው የክረምት ዕረፍት ሰርቶ ያገኘውን ገንዘብ እንዳቀደው ልብስ ሳይገዛበት ውቤ በረሀ ጨርሶታል። ከሰባት መቶ ብር ውስጥ አርባ ብር ብቻ ቀርታዋለች። እሷ ምን ልብስ ትገዛለች? ጴጥሮስ እንዴት ሀሳቡን እንዳወቀበት እንጃ

«ያንተን ዝንጣ ለኔ ተውልኝ» አለው

«ይሁን»

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ውስጥ እጁሱ የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች ህንፃ ውስጥ ናቸው። የክፍላቸው ልጆች ሁሉ ለእራት ሄደዋል፣ ማንም የለም። የጴጥሮስ መኝታ ፎቅ ላይ ነው። ጴጥሮስ መብራቱን አበራ፣ የመስኮቱን ነጭ አቡጀዲ መጋረጃ ዘጋ። ቁም ሳጥኑን ከፈተ። የተለኮሰ ሲጃራ በአፉ እንደያዘ ከርዳዳ ፀጉሩን እያበጠረ «ምረጥልኝ። ምን ልልበስ?» አለው

ቁምሳጥኑ ውስጥ ዘጠኝ ቅያሪ ሱፍ ልብስ በመስቀያ ተንጠልጥሏል። በግራ በኩል ሦስት የቆዳ ጃኬቶች ተሰቅለዋል። ቁምሳጥኑ ስለጠበበና ልብሶቹም በጣም ስለተጠጋጉ የአንዳንዶቹ እጅጌያቸው ብቻ ይታያል።

እታች አስራ ሦስት ጥንድ ጫማ ተሰልፏል:: የቁምሳጥኑ መዝጊያ ላይ ሠላሳ የሚሆን ክራቫት ለቋንጣ እንደተዘለዘለ ሥጋ በገመድ ተንጠልጥሏል::

«እያወቅከው!» አለ ብርሃኑ:: ውሃ አረንጓዴዋን የቆዳ ጃኬት አወጣት:: የቁልፍ መትከያ ቦታዋ፣ እጅጌዋና አንገቷ ውሃ አረንጓዴ ሹራብ:: ሌላዋ ቆዳ:: ስዌድ ቆዳ በጣም ውብ ናት:: ቁልፎቿ ቡና ዓይነት፣ ከእንጨት የተሠሩ ነገሮች «አለቻ ጃኬት!»

«አለቻ taste!» አለ ጴጥሮስ «እሷን አንተ 'ምትወዳትን ያህል ስለማልወዳት ራስህ ልበሳት. . . ባጭሩ፣ ብርሃኑ ጴጥሮስ ያዘጋጀለትን አዲስ ካናቴራና ሙታንቲ፣ ከራሱ ሠላሳ ሸሚዝ ውስጥ የመረጠለትን ቡና ዓይነት ስፖርት ሸሚዝ፣ ከአስራ አራት ሱሪዎች ውስጥ የመረጠለትን ጥቁር ሱፍ ሱሪ፣ እና ያቺን ቆዳ ጃኬት ለበሰ:: ጴጥሮስ ወዲያ ወዲህ ተራመድ ብሎ አጠናው:: በመጨረሻ ሲጋራውን እያቦነነ ትንንሽ ዐይኖቹ እንደ ኮከብ እያበሩ

«Magnifique! አቤት ብታይ እንዴት እንዳማረብህ! ዛሬ ትርሲት ባትወድቅልህ ምን አለ በለኝ!» አለ፣ ልዩ የክት ፈገግታውን እያሳየ:: ጥርሶቹ በጣም ጥቃቅን ናቸው:: ሲስቅ በጣም ቀይ ድዱ ከጥርሶቹ ይበልጥ ጎልቶ ስለሚታይ፣ አፉ በጎራዴ የተከፈተ ቀይ ቁስል ይመስላል:: ስለዚህ ብዙ ጊዜ አይስቅም፣ ማለት አብዛኛውን ጊዜ ሲስቅ ከንፈሮቹን ገጥሞ ነው:: ሽራፋውን ለመሸሸግ እንደሚፈልግ ልጅ:: ኃይለኛ ሳቅ ይዞት አፉን ከፍቶ ከሳቀም ቶሎ ጎንበስ ይላል:: አፉን ሳይከፍት ሲስቅ ግን በጣም ያምርበታል:: ምክንያቱም ትንንሽ ጥቁር ዐይኖቹ ያበራሉ፣ የከንፈሮቹ መገናኛ ላይ ደስ የምትል ተንቀሳቃሽ ትንሽ ሰርጓድ ብጤ ትፈጠራለች::

ጴጥሮስ ሐር መሳይ ነጭ ልብስ ለበሰ:: ነጭ ሸሚዝ፣ ነጭ ቢራቢሮ ክራቫት፣ ነጭ ጫማ፣ ነጭ እግር ሹራብ

«ሁለታችንም ዘንጥን አይደለም?» አለ

«ዘንጥን ብቻ?!»

«መጀመሪያ እራት እንብላ» እራታቸውን ለመብላት በሰይቼንቶ ሲሄዱ፣ አንድ ደቂቃ ሰካራም ከኋላቸው ቁጭ ብሎ ማጉረምረም ጀመረ:: እነሱ ስለትርሲትና ስለጠንፍየለሽ፣ ማሚት እሹሩሩ ቤት ስለሚያበስሏቸው አሻሻጮች፣ በእንግሊዝኛ ያወራሉ:: ሰካራሙ

«ሰማችሁ ወይ፣ የአገራችን ቋንቋ ምን ጎደለውና ነው በውጭ አገር ቋንቋ 'ምታወሩት?» አለ:: ዘወር ብለው አዩት:: ሰክሯል:: ብዙ ብስጭት ያየ፣ በመከራ ብዛት የተጨማደደ ወጣት ብጤ ፊት:: ረዥም አፍንጫ:: ዝም አሉት:: ወሬያቸውን በእንግሊዝኛ ቀጠሉ



«የጃንሆይን ቋንቋ ንቃችሁ ነው?» አላቸው::

ጴጥሮስ «አ-ዎ» አለና ዝም አለ:: ትንሽ ቆይተው ወሬአቸውን ቀጠሉ:: ትንሽ ቆይቶ ሰካራሙ

«አባቴን የገደለው ፋሺስት ነው» አለ:: ብርሃኑን በጣቱ እያሳየ፣ «ቼሊ፣ ያንተ አባት ነው የኔን አባት በመርዝ ጢስ ጋዝ የገደለው:: አንተ ደሞ እዚህ አይ ጎን ማይ ሀውስ እያልክ ትዘንጣለህ»

ጴጥሮስ ድንገት ወደ ኋላ ዞሮ ወንበሩ ላይ ተንበርክኮ ሰካራሙን በግራ እጁ አንቆ በቀኝ እጁ ደጋግሞ በጥፊ መታው:: ሰይቼንቶ ነጂውን «አቁም ወንድም» አለው:: ትዕዛዝ:: አቆመ:: ራስ መኮንን ድልድይ አጠገብ ጴጥሮስ ሰካራሙን «ውጣ!» አለው:: ሰካራሙ ከመደንገጡ የተነሳ ቁጭ እንዳለ ቀረ:: «ውጣ ነው'ኮ 'ምልህ ቅሌታም!» አካለበው:: አይረባህም፣ ግን ድምፁ ያስፈራል::

«የለም'ኮ ወንድም. . .» ሲል ጀመረ ሰካራሙ

«ውጣና ወንድህምን ፈልግ!» ጴጥሮስ ራሱ ወጣና፣ ተቀምጦበት የነበረውን ወንበር ወደፊት አስጎንብሶው ሰካራሙ መውጫ እንዲያገኝ::

«በል'ኮ አታስጠብቀኝ»

«ገበያዬስ ጋሼ?» አለ ሰይቼንቶ ነጂው

ጴጥሮስ አንዴ ዐይኑን ጣል አደረገበት:: በቃ:: ሰካራሙ ወጣ:: ጴጥሮስ በፍጥነት እጁን ጠምዝዞ አንበረከከው:: ልክ ይሄን ጊዜ የመንገድ መብራት ተከታትሎ በራ

«ይቅርታ ለምን» አለው

«ምክንያቱስ እባክ - አይ!» በኃይል እጁን ጠምዝዞ አሳመመው::

«ይቅርታ ትጠይቃለህ ወይስ እጅህን ልስበርልህ?»

«አ-እ! ይቅርታ!» አለ በትንሽ ድምፅ

ጴጥሮስ ወደዛ ገፍትሮ ጣለውና ሰይቼንቶው ውስጥ ገባ:: መኪናው ተነሳ::

ሰካራሙ «እዚህ የሀገራችን ቋንቋ . . .» የቀረውን ቃላት ንፋሱና የመኪናው ሽውታ ዋጠው:: ይሄ ሁሉ ሲሆን ብርሃኑ ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ ዝም ብሎ ይመለከት ነበር:: እሱንም ቢሆን፣ እድሜ ኻያ ዓመት ከሆነው በኋላ፣ በክልስነቱ ምክንያት የተፈጠረ ጥቃት ቢገጥመው ቁጥር፣ መገረምና መሰቃየት ልቡ ውስጥ ስለሚገቡ ምንም ሳይናገር ምንም ሳይሠራ ዝም እንዳለ ይቀራል:: ታዲያ እንዲህ እንዳነደቹ ይህ ዝምታ የፍርሃት ይመስላቸዋል :: ስድባቸውን ሆነ አሹሙራቸውን ሌላ ቀን ይደግሙታል:: ያን ጊዜ ግን ወዮውላቸው:: ምክንያቱም ብርሃኑ ልብ ውስጥ መገረም ጠፍቶ ንዴት ይወለዳል:: ክልስነቱ

[illegible]

«I appreciate what you did» [illegible]

«That's what you think»

[illegible]

«ሸሙ[illegible]» ... «እንዲህ ነው። እዩህ፣ ሀበሻና ውሻ አንድ ነው። ቀድመህ ካላደነቅኸው ጉድ ያረግሃል። አሁን ዝም ብንለው ኖሮ፣ እሱና ጓደኞቹ ማሚት እሹሩሩ ቤት ቢያገኙህ እኔ የሌለሁበት ቀን ጠብቀው ነገር ይፈልጉህ ነበር። ከ'ንግዲህ ግን አይደፍሩህም። እንዲያውም ለሚመጣው ጊዜ ስትገናኙ ይሄ ሰውዬ ለክሬ ነበር ይቅርታ አድርግልኝ ይልሃል። ምን አለ በለኝ። የሚሻለውማ አንተ ራስህ አካልበህ አስወጥተኸው ቢሆን ኖሮ ነበር። ግን ዝም ለማለት እንደቆረጥክ አወቅኩ። ስለዚህ እኔው ገባሁበት። አጠፋሁ?»

ብርሃኑ ግማሽ በአድናቆት ግማሽ በቀልድ «አለቻ ጭንቅላት!» አለ። ጴጥሮስ ከርዳዳ ፀጉሩን በሌባ ጣቱ እየመታ፣ ጥርስ - ድብቅ



[illegible] Fernandel [illegible] Charlie Chaplin [illegible]

ከዛ ሲወጡ ሁለት ሰዓት ተኩል ሆኗል። [illegible] ወደ ደጃቸ ውጪ ሰፈር አመሩ። መጀመሪያ [illegible] ቤት ገቡ፣ ተጫወቱ፣ ደነሱ፣ ወጡ። ቀጥሎ አዝማሪች ቤት፣ ከዛ ታቦች ቤት፣ ከዛ ፈትለወርቅ ቤት፣ ከዛ ጋሻሊ ቤት። [illegible] ቤት ሁሉ ውስኪ። ደግነቱ ጴጥሮስ «ሁለታችንም ከሰከርን አይሆንም» ብሎ የሁለቱንም መጠጥ ብርሃኑ ነበር የሚጠጣው።

በመጨረሻ አራት ሰዓት ተኩል ላይ ማሚት እሹሩሩ ቤት ሄዱ። ይህን ጊዜ ብርሃኑ ብሠው ብሎ ሰክሯል። ነገር ግን ያደረገው ነገር፣ የተናገረው ቃላት ሳይቀር በንጋታው በደምብ ታወሰው።

እንደገቡ ወንበሩ ሁሉ ተይዞ ስለነበር፣ መጠጥ መቅጃው ባንኮኒ ዘንድ ቆሙ። ሆህተ (የግራማፎኑ አለቃ) ከባንኮኒው ኋላ የለችም፣

ግራማፎኑ አምስት ያህል ሸክላ ተጭኖበት ብቻውን ይጫወታል:: ሰው ሙሆ ሲያወራ ሙዚቃው ለደናሾቹ እንዲሰማቸው፣ ጣራውና ሁለቱ ግድግዳዎች የሚገናኙበት ማእዘን ላይ አንድ ድምፅ ማጉያ ተንጠልጥሏል:: የሚያጎላውን ሙዚቃ ያንኑ ያህል ያጎረናዋል፣ ያበላሸዋል:: (መጠጥ ቀጂዋ ገንዘብ ተቀባይዋ) በላይነሽም ከባንኮኒው ኋላ የለችም::

ብርሃኑ ዙሪያውን በየግድግዳው ጥግ የተቀመጡትንና ወለሉ ላይ ታንጎ 'ሚደንሱትን፣ እንዲሁም አብረው እዛው ባንኮኒው ዘንድ የቆሙትን ሰዎች ተመለከተ:: ሁሉም በጣም ደስ አሉት:: ወደዳቸው:: ሁሉንም በየተራ እየዞረ ቢስማቸው ፈቃዱ ነበር:: ሲያዩት ደሞ እነሱም የወደዳቸውን ያህል የወደዱት መሰለው::

«መስከር እንዴት ደስ ይላል 'ባክህን?» አለው ጴጥሮስን:: ጴጥሮስ ልክ እንደገቡ አነጣጣሪ ዐይኖቹን ዙሪያውን ጣል አርጎ ያየውን አይቶ ኖሮ

«ሁላችንን ታስታውስ የለ?» አለው «ሁለታችን አንድ ላይ እንሰክርም:: እኔ ስሰክር እታዘዝሃለሁ:: አንተ ስትሰክር ደሞ እኔ እንጻልኩህ ታረጋለህ»

«እሱን አሁን ምን አመጣው?»

«ትርሲትን ሰዎች ይዘዋታል:: አራት ናቸው:: እኛ ሁለት ነን:: ስለዚህ ጠብ አያስፈልግም:: ሆነ?»

«ሆነ:: ግን እኔ ያለእንዳች ጠብ፣ በፍቅር ብዛት ብቻ እነጥቃቸዋለሁ:: ታያለህ»

«ስለሰከርክ ጭንቅላትህ ከኔ ጭንቅላት እኩል ሊሠራ አይችልም:: ስለዚህ ለኔ ተውልኝ:: እኔ ቀስ ብዬ እቀማቸዋለሁ:: ሆነ?»

«ምን ትጠጣላችሁ?» አለች በናት መሳይ ልዝብ ድምጿ:: ከባንኮኒው ኋላ ቆማ በትልልቅ ዐይኖቿ፣ በለሰለሱ የናት መሳይ ዐይኖቿ፣ ፍቅርና ትዕግስት በሚለግሱ ዐይኖቿ ታያቸዋለች:: በተለይ ሥራዋ ዲስክ ማጫወት ነው:: ግን መጠጥ መቅዳትም በላይነሽን ታግዛታለች::

«ሆሆተ የኔ ቆንጆ!» አለና ብርሃኑ በባንኮኒው ተንጠራርቶ ግንባሯን ሳማት:: ከተንጠራራበት ሲመለስ ባንኮኒው ላይ ከነበሩት ብርጭቆዎች አንዷን በቀኝ እጁ ክልብሶ የባለቤትየውን ሱሪ አበላሸበት:: ሳቅ እያለ «ይቅርታ አላወቅኩም፣ ወንድም» አለው::

«ምንም አይደል» አለው ሰውየው ሱሪውን እያራገፈ:: በአፉ መፋቂያ ይዟል:: ጴጥሮስ የወደቀውን ብርጭቆ አንስቶ ባንኮኒው ላይ አስቀመጠው:: ብርሃኑ ወደ ሰውየው እጁን ዘርግቶ

«ብርሃኑ እባላለሁ»



ሰውየው የብርሃኑን እጅ እየጨበጠና መፋቂያ የነከሱ ጥርሶቹን ደስ በሚል ፈገግታ እየገለጠ

«ጥላሁን» አለ

«ጥላሁን አንተ ነህ?» አለ ብርሃኑ

«አዎን»

«ጥላሁን ረብሻ ማለት አንተ ነህ?!» ጥላሁን ሳቅ ብሎ ዝም አለ::

«በጭራሽ ረባሽ አትመስልም» አለ ብርሃኑ:: ዐይኑን ማመን እንዳቃተው ያህል «ባልሰክር ኖሮ አልጠይቅህም ነበር፤ ግን ልጠይቅህ:: እውነት የተዘጋ በር በቴስታ ትገነጣጥላለህ?»

ጥላሁን እየሳቀ «ከሰከርኩ» አለ

«ስትናደድ ሰባት ስምንቱን በቦክስ ታንጥፋለህ አሉ:: እውነት ነው?»

«እሱን ተወውና ምን ትጋበዛለህ?» አለ ጥላሁን:: ብርሃኑ ወደ መጠጥ መደርደሪያው እያለሁ ሲል ሆሁተን አያት:: እንደ ሁልጊዜ በትዕግስት ቆማ በደግ አይኖቿ ታያቸዋለች:: መጠጡን ረሳና ጥላሁንን እንዲህ አለው::

«እያት እስቲ:: ደስ አትልህም? እንደሷ ያለ ደግ የሆነ ፊት አይተህ ታውቃለህ?» እንደገና ተንጠራርቶ ጉንጯን ሳማት «ቤት ሁሉ ለምን እንደዚህ ደግ አይሆንም? ውይ፤ ረሰቼ:: ጴጥሮስ ጥላሁን፣ ተዋወቁ» ጥላሁንና ጴጥሮስ ሲጨባበጡ Adios Muchachos የምትል ብርሃኑ በጣም 'ሚወዳት ታንጎ መጫወት ጀመረች

«አዲዮስ መቻቾስ! ሄድኩ እንግዲህ ደህና ሁኑ:: አዲዮስ !» እያለ ከትርሲት ጋር ለመደነስ ሄደ:: ካራት ሰዎች ጋር ተቀምጣለች:: አንዱ አቅፏታል:: አረንጓዴዋን ቀሚስ ነው የለበሰችው:: ብርሃኑና ጴጥሮስ እዚህ ሲመጡ ይኸው ሁለት ወር አለፋቸው፣ ታድያ በመጡ ቁጥር ይችኑ ቀሚስ ለብሳ ነው 'ሚያገኙዋት:: ሌሎቹ ሴቶች ግን በቀን በቀን ቀሚስ ይለዋውጣሉ:: ብርሃኑ ያቀፏትን ሰውዬ በወዳጅነት እያየው እጅ ነሳው:: ሰውየው እጁን ከትርሲት ትከሻ ላይ አነሳና ብርሃኑን አሳያት:: ብርሃኑ እጅ ነሳት:: በፀሐይ ፈገግታዋ እንኳን መጣህ እያለች ተነሳች::

መደነስ እንደጀመሩ «ሠላም የኔ 'መቤት» አላት

«ሠላም የኔ ጌታ»

«ሽቶሽ በጣም ደስ ይላል:: ያሰክራል!» በሃይል አስጠጋት:: እቅፍ አረገችው:: ዳንሱ ሲያልቅ ወደቦታዋ መለሳትና ሰዎቹን እጅ ነስቷቸው ወደ ጴጥሮስ ተመለሰ::

[illegible] «Chère madame la comtesse» [illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]



[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

ብርሃኑን እየሙና እየሳቀ እጁን እወዛወዘለት። ብርሃኑም እየሳቀ እጁን እወዛወዘ። ለራሱ «ሃራ ሰው ሁሉ እንዴት ወደኛል!» አለ

ብርሃኑ ምንጊዜም ያላወቀው፣ አሁንም ቢሆን የማያውቀው ነገር ከትርሲት ጋ ቀጥ ብለው የነበሩት አራት ሰዎች የተጣሉን ጓደኞቹ ነበሩ። ተጣሉን ከዚህ ቀደም ሁለት ሦስት ጊዜ ያህል ትርሲትን አብረት አድሮ ደስ ስላለችው ያን ዕለት ማታም አብሯት ለማደር ነበር የመጣው። ግን ብርሃኑን ገና ሲያየው «ጥሩ ልጅ ነው» ብሎ ስለወደደውና፣ ከዚያም በላይ ፍቅር እንደያዘው ተመልክቶ ስላዘነለት፣ ትቶለት ሄደ።

ጲጥሮስና ጠንፍየለሽ፣ ብርሃኑና ትርሲት፣ አራቱ አብረው ተቀምጠው ሲጠጡ፣ ሲስቁ ሙዚቃው ሲጫወት፣ ሰዎች ሲደንሱ ብርሃኑ ሰዓቱ እየፈለገ ትርሲትን ትንፋሿን፣ እንገቷን፣ ፀጉሯን ይስማታል። ስሀብ ሲያዩ ደግሞ ያለአበዛ ይስማታል። ትርሲት ሽርሙጥና ከጀመረች ጀምሮ ለዚህ ዕለት ስለሆነ እስከ አሁን ድረስ ማንም ሰው በደቱ ስሞት ስለማያውቅ በጣም አፍራለች። ግን በጣም ደስ ብሏታል። እፍረቷና ደስታ ጠብም ኅብረት ፊቷን የበለጠ ውበት ስለሰጠው ብርሃኑ እየደጋገመ ይስማታል። እንደገና ከንፈሯ ላይ በኃይል ሳማት፣ ሰውነ ረሲታ መልሳ ሳመችው፣ ከንፈሯን ከፈተችለት፣ አፏ ውስጥ ሳማት፣ ጣመውና አለላት አላት። እሷም ቢተፎል ፈቃዷ ነበር፣ ግን የት እንዳሉ አስታወሰችው። ሲያያት ከመጠን በላይ አፍራለች። እሳዘንችው። ትንፋሿን እየሰበ «ምን ያስፍርሻል?» አላት

መሬት መሬቱን እያየች «አንቺ። አልለመድኩትም» አለችው። እጇን ያዘ። ዝም አለ። ከልቡ ውስጥ ብዙ ብዙ ፍቅር ወደ'ሷ ሲፍሰ ተሰማው።

አንድ ጠብደል ሰውዬ መጣና ትርሲትን ለዳንስ እጅ ነሳት። ብርሃኑ ሰውየውን የመውደድ ሳቅ እያሳየው «አዝናለሁ ወንድም፣ ይቺን ልጅ ዛሬ ለኔ በቀር ማንም አይስደንሳትም። የልደቷ ቀን ነው» አለው

ሰውየው ሳቅ አለለ «መልካም ልደት!» አለውና ተመልሶ ሲሄድ ብርሃኑ «ወንድም!» አለው። መለስ አለ። «ይቻት አስደንሳት» አለው።

ሰውየው ሳቀና «ግድ የለም Enjoy yourself!» አለው

«Thanks!» አለ ብርሃኑ። ፊቱ አስነሳት። አንድ ሰሉት ጊዜ ተቃቅፈው ደንሰው ተመለሱ። እስካሁን እሷም ሰላት ብርጭቆ ውስኪ ጠጥታለች ገና ለመጠጥ እንግዳ ስለሆነች ሞቅ ሊላት ጀምሯል። ሳቅ ሳቅ ይላታል።

ጲጥሮስ በዓቱን እየየ በእንግሊዝኛ «አምስት ከሩብ ሆኗ። በቀ ድሮቱ ውስጥ ከዚህ መውጣት አለብን» አለው። እሱም በበኩሉ ጠንፍየለሽን ሲያስነሳት ቆይቷል። ልክ አንዱ ሲስክ ሲያልቅ ብርሃኑ



ሙክ ብሎ «ሆሆተ Guitar boogie እርጊልኝ የኔ ቆንጆ» አለ። ተነስቶ ተነሳች። ወደ ወለሉ መሃል ወስዳትና ለዳንስ ተዘጋጁ «Madame la comtesse!» አላት። ሙዚቃው ሲጀምር «ጊታር ቡጊ» አይደለም። እንዲያውም ቡጊ አይደለም። ቫልስ ነው።

«ሆሆተ፣ ጊታር ቡጊ አላልኩሽም ነበር? እ?»

«ቀድመው ይሆን የጠየቁ አሉ» አለችው

ከትድሙ ይበልጥ ሙሃ «ይኑሩ፣ ጊታር ቡጊ አርጊልኝ አልኩሽ ይሆን ትዕዛዜን በቶሎታ ካልፈጸምሽ መሞቴ በሀከስ እንትፍቸለሁ» አላት። እልፍ እልፍ ሰዎች ይስቁ ጀመር። ሌባ ጣቱን እንደ ሽጉጥ ሰዎቹ ላይ ተራ በተራ እያንጣጠረ፣ ግራ እግሩን አንድ ቡታ ተከሉ በተን እንዲ አንድ ጊዜ ዞረ። ሙክ ብሎ «እዚህ ውስጥ ትዕዛዜን መቀበም የሚፈልግ እንዳለ እጁን ያውጣ። በሀከስ እንትፈዋለሁ!» አላቸው። በቀጣ መናገሩ ነበር፣ ግን ሳቁ ፊቱ ላይ ይታያል። ምክንያቱም ሰዎቹን ሁሉ ወድዷቸዋል። የሰዎቹ ሳቅ እየበዛ ሄደ። እነሱም ወደዉታል። እንዲ «ጊታር ቡጊ!» አለ። እዚህም እዚም «ጊታር ቡጊ» አሉ። ቫልሱ ተቋረጠና «ጊታር ቡጊ» መጫወት ጀመረ።

ብርሃኑና ጠንፍየለሽ ካንድ አራት ሌሎች ጥንዶች ጋር መደነስ ጀመሩ። ጠንፍየለሽ በውቤ በረሃ በዳንሷ የተመሰከረች እንደመሆኗ መጠን፣ ልክ እሱ እንደፈለጋት ትሽከረከርለት ጀመር። ሳይቀሩም ከሌሎቹም ደነሱ። ብርሃኑ ሙዚቃውን ሲሰማ ያለበትን ቦታ ረሳ፤ ቡጊው ደሙ ውስጥ ከሙሉቱ ጋር ሲዋሃድ ተሰማው። ልክ ከብድ እንደሌለው ዓይነት ይደንስ ጀመር።

ሰዎቹ ማጨብጨብ ጀመሩ «. . . አድያ! . . . እንዲያ ነው . . . ጋዲሚት! . . . አይዟህ! . . .» ሲሉ ተሰማው። ጊታሩ ሲጫወት፣ እንዱ ሲረግጥ፣ እነሱ ሲያጨበጭቡ፣ ጠንፍየለሽ ስትሽከረከር፣ ሁሉም ድንገት የሆነ አንድነት ፈጠሩ። ሌሎቹ ሁሉ ዳንሳቸውን ትተው በብርሃኑና በጠንፍየለሽ ዙሪያ ከበው እንደሚያጨበጭቡ ድንገት ታየው። እሱ ራሱ መደነሱ ቀርቶ የሙዚቃ አምላክ የዳንስ ቅኔ ሲያስደንሰው ተሰማው። ሙዚቃው አለቀ። ሰዎቹ በኃይል እያጨበጨቡ «ደገ! ቢስ!» አሉ።

«ጊታር ቡጊ» እንደገና ጀመረ። አሁንም ብርሃኑ ሲደንስ ያለበትን ረሳ። ጊታሩና ከበሮዎቹ ጭብጨባ የዳንሱን ቅኔ ጠሩና አለመላው። ደነሰ፣ ደነሰ፣ ተሽከረከረ፣ ጉልበቱን አጥብሮ፣ ትከሻውን እንቀጥቀጠ፣ ፈሰሰ፣ ጭብጨባ ጣቱና በመላ ጣቱ ጊታሩ ከሰዎቹ ጭብጨባ እኩል እየገጣጠመ ወደ ጎኑም ሰብሩ . . . ድንገት ጠንፍየለሽ

ልክ እንደፈለጋት ትህግልታለች። እሷንም የዳንስ ቆሊ ሳይገኝ አልቀረም። እሁንም መጨረሻው ሲያቆም ሰዎቹ «ቢስ! ቢስ!» እያሉ አጨበጨቡላት። ሦስተኛ ጊዜ ዳንስ። አራተኛ እንዲደግም «ቢስ ቢስ» አሉ፤ ግን እምቢ እጅ ነሳቸውና ጠንፍየለሽን አቅፎ ወደ ቦታው ተመለሰ።

ጴጥሮስ በነይል ጨበጨበና «Magnifique! ታይቶም አይታወቅ፣ እንደዚህ መሆነህን መቼ አወቅኩኝ» አለው። ብርሃኑ ጠንፍየለሽን በአድናቆት ወደጎ እያየ ካለተመጣች በኋላ፣ እጅ እየነሳች «Merci infiniment madame à confesse» አለች። እየነሳች ብንነቷ እጅ ነሳቸው።

አንድ መነጽር ያረገ የገደለ ቅሬል የሚያክል አሜሪካዊ መጥና በእሌ መብፉ ብርሃኑን እየጨበጠው «That was the most magnificent dance I ever saw. Would you let me buy you a drink by way of appreciation?» አለው።

«No, I won't let you buy me a drink because I am already drunk. But to show you how much I appreciate your appreciation, I will introduce you to my friend.» ከጴጥሮስ ጋር እያጨባበጠ «You are shaking hands with the most intelligent, the most generous of Ethiopians. His name is ጴጥሮስ, meaning Peter. But he dresses with such magnificence that you may call him Haroun, short for Haroun-Al-Rashid, Prince of the Faithful, Defender of Islam, Hero of wonderful adventures, he of the Arabian Nights, he of Bagdad. Excuse me, I didn't catch your name.»

አሜሪካዊው ጴጥሮስን እየጨበጠና ማስቲካ እያኘከ፣

«Hutchins. Jim Hutchins. Quite a friend you've got there?» አለ።

ብርሃኑ አንድ ሦስቴ ትርኢትን አቅፎ አርተ ሩምባና ታንጎ አስደረሳት። ሀገርን ሊያናጋ! ትንፋሽን እንደገና ሲስም፣ ጴጥሮስ መጣና «Sorry እምቢት ተስል ሆኑ። ሰዓት እላፊ እንዳንያዝ አብነት መሄድ አለብን» አለው። በሄድ ትቶቶ አለውጠው። ብርሃኑ ትርኢትን «ደህና እደሪልኝ በአልሜ አይቸኩሉ» ብሎ ሳማት። ሀሁተን ደጃ ብትሆ የኔ መልአክ! ደህና እደሪ፣ እስክ ነገ ትናፍቂኛለሽ» ብሎ ግንባሯን ሳማት። ሲወጣ መጋረጃውን በአንድ እጅ ከፍቶ ደጃፍ በትይዩ ሥም «ሆትዩው ደህና 'ደሪ፣ በሊያችሁ በእምባ ነው» አለ

«ደህና 'ደር... Good night!» አሉት ሰዎቹ። ከጴጥሮስ ጋር ወጡ። የውጪው ንፋስ ቀዝቀዝ ብሎ ደስ ሚያሰኝ፣ ከጥሚት እሸሩሩ ቤት ተነሱ ያለው ቤት በትልቅ ግምብ የተከበበ ነው። ብው ከጥሚት

እሸሩሩ ቤት ሲመጣ ሸንቱን እዚህ ግምብ ስር ይሸናል። ጴጥሮስና ብርሃኑ ሲሸኑ ጴጥሮስ

«ላይፋችንን አልተቀጨንም?» አለ

«በጭራሽ እንደዚህ ተደስቼ አላውቅም»

«ግን ይቺን ምሽት ከትርኢት ጋር ብትጨርሳት ጥሩ አልነበረም?»

«ኦ፣ እሱማ መንግሥተ ሰማያት ነበር»

ጴጥሮስ «ሹፌሩ! ረሳሁ ሳልከፍል ወጣሁ። እየደደቡ ቆየን» አለና ወደ ግሚት እሸሩሩ አጥር ግቢ ተመለሰ ነገ።

ቀዝቀዝ ለስለስ ያለች፣ በከዋክብትና በጨረቃ ያጌጠች፣ በለታ የምትታይ የህዳር ሌሊት። ቀደ ወደም አርንጓዴ መብራት ከሰርሰት ከበለቶቹ ቤት የሂርና የመጫቃ ጨዋታ ይሰማል። ግን ደህ በሎ ጨዋታ የሌሊቱን ፀጥታ እንዲህ ሊያደፈርሰው አይችልምገረው አልቻለም። ጨረቃዋ የምታልበው ብርሃን መንገድ ቀርቶ የሚታይ ፀጥታ ይመስል ነበር። የጊዮርጊስ አደባ ጭር በተከበርጋጊዎቹን በሙሉ ስፍ ያለ ጨለማ እርዳታል። ይበሊራልም! ይሻራልም። መንገዱ ላይ ያለው የኤሌክትሪክ መብራት ወደላይ እስከ ሸዋ ድረስ፣ ወደታች እስከ አቡነ ምኒሊክ አደባባይ ድረስ፣ ተሰቅሎ የተቀመጠ የከዳ ሀብል ይመስል። ይህ መብራት ባይኖር ጨረቃና ከዋክብቱ እንደት ባማሩ፣ የመጫቃው ጨዋታ ባይኖር የሌሊቱ ፀጥታ ምን ያህል ውበት ነበር ግን እንዲሁ ሆኖም ጥሩም ነው።

«እኛ ቢሆርዱሁም አትስማ እሺ» የጠንፍየለሽ ድምፅ። በጠር ሌሊ ጠንፍየለሽ! ጴጥሮስ! ትርኢት፣ ሰዎችን ማመን አቃተው። ግን ብሎ አያቸው። ሽቶ ሆቴል እስኪደርስ አንድ ቃል አልተናገረም። እሌ ውስጥ ገብቶ ትርኢትን ካቀፈት በኋላ እንኳ ቃል አልተናገረም።

ከሦስት ቀን በኋላ ብርሃኑ ተራውን ጴጥሮስን ጋበዘው። ሲገን ሰራት። በመጨረሻ ትርኢትንና ጠንፍየለሽን ይዘው ሽቶ ሆቴል እደረሱ ብርሃኑ ያችን የቀረችውን አርባ ብር ሁሉ አደረገት።

ያን'ለት ሌሊት ትርኢትን ለመጨረሻ እያቀፈ በጨለማው ውስጥ «እንግዲህ እስክ ፍሬ ዘመን ወር እንጃ መገናኘታችንን» አላት

«ለምን?»

«ፈንዜው ግንዘብ የለኝም»

«ታዲያ ለገንዘው ግንዘብ አትከልፈኝ። ሲፈልግ መጠቶ ጊዜንም ለምትልክ ሁለት ብር ተበል ሮጥርስ ጊዜ አለሙጡ ውስጥኝ»

በጨለማው እያቀፈችት፤ ፀጉሯን እየደባበሰ አየዋት «እንድ ሰሞ ደግ ልጅ ነሽ። እኔ ግን መኖር ደህ ነኝ፣ ስንሆም የሚያስፈኝ ሥሙር

የድሃው፡ ትምህርት ቤት ተገቢውን ትንሽ ሥራ እንዲሠሩ ነበር፤ ቤቱ ሃብትን ፕሮፌሰር ደጃው ኣሬ አለቀች፡፡ የዛሬ ወጪን ወር ትምህርቱን አጨርሰን ሥራ እየሰራሁ፡ እስከዚያ ድረስ ግን ቆንጆውን እንዲ ማን እንደሚያደርጉልኝ እንዳ፡ እስከ ወጪን ወር ትረዳኛለሽ፡፡

‹እስከ ወጪን ዓመት አልረዳሽም› አለችው፡፡ ‹እቅዱ እርጋው ትንሽ ከወደቁ በኋላ ‹ሌቀ ደግሞ እንገናኛለን› አለችው

እናንተ ቤት ከመምጣት ፕሮፌሰር ለቤሌልጋል፡፡ እኔ ፕሮፌሰር የለኝም፡ ታዲያ እንዴት እንገናኛለን?

‹ቀን ቀን እየመጣሁ እታያለሁ›

‹እንዴት አድርገ›

‹በር ላይ መንገድ አልጋ፡፡ ብትመጣ ማንም አያይህም› ነው ሌሊ ግን

‹ነገ ትመጣለህ ሌሊታ›

ነገ ትምህርት አለብኝ፡ ሊመጣ ‹ምችለው እርብ ከሰዓት በኋላና ቅዳሜ ብቻ ነው›

‹እሺ›

‹አዎን›

‹እንገናው እየመጣህ ታገኛለህ›

‹በደብታ እሷን ይሄ ውስጥ ልብስ ይወልቃል ወይስ እያወልቅም›

ውለቶ እንደዚያ ኪራይ፡ ብላ እውስጥ በራሱት ገላዋ አቀፈችው

‹ካሁን እንዴት ይበልልላል! የጠነክሩ ሙቀትና መለስለስ ለስለ እንዲ ትምህርቴን ማጥናቴን፡ ትናንሽ ቀን ስመጣ እንደዚህ ልብሶቼን እውልቀሽ ታሳፍሪኛለሽ›

‹ሌላ የተነገ ነገር›

‹ምን?›

‹እኔ ሌላ የለኝም፡፡ ቢኖረኝም ብዙ ጊዜ እየመጣሁ ልብሴን እንድር ነበር›

ብርሃኑ በጣም ተገረመ፡፡ ውቢ በረሃ በቀይ መብራትና በጨሻሻታም መጠጥ በሚገዛበት ጉድ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ መተዋወቁ ነበር፡፡

ጠንቀቀው ማታ ጴጥሮስ ብርሃኑ መኝታ ቤት መጥቶ ውቢ በረሃ ደብበ እንደማን አለው፡፡ ብርሃኑ መሄድ አልፈለገም፡፡ ጴጥሮስ ሲጃራውን



እያጨሰ በግራ እጁ ከርዳዳ ፀጉሩን ወደ ኋላ እያሻሸ

‹ቀድ አትሁን› አለው ‹ብዙዎቹ ቤቶን ፕሮፌሰርን አለፉትን አትተዋም እያበራሽሽ ብትመጣ አለፋታልሁ፡ ብዙዎቹ ከምትችን ሰማያን አደናቆዳም› በሚቀጥለው ወጪን ወደም አበር ወር ወደጣሪን ፕሮፌሰር በረሃ ዉሌሬ፡፡ ቢሆንስ በየምሽት ቃታት ጊዜ ይደበቁ፡ በየምሽት ዐበዩ የሚያበሩልትም ጊዜ ነበር፡፡ ጴጥሮስ ብሎ ፕሮፌሰር ደጃርሮው ብርሃኑን ሠፈራቸን ይሰፍሩለን አስተ፡፡ ከተማሪ ጋር መግደለቸ ቀርቶ፤ ቤጨቀ ደገኑ ሬስቶራንትን ሆደን ራት እንገዛ ከወደን ጋር፡ ይወዳሉ፡፡ ግዳጁ ቤት ወደም ቤሌትርሮ ሄደው እያወሩ፤ እያገሬ ወደም እየጠጡ ይሰበራ፡፡ ከዛ ወጥተው በረሃ እንደ እሬት ቤት ይደንሱና ከመጨረሻ ማደት እንግሩሩ ቤት ገብተው ተቀጣጥተው፤ ትርሲትንና ወንድዋይቱን ይወድዋል ያደርሉሉ፡፡ ጴጥሮስ ብሎ ፕሮፌሰር ከሊሰው እሬት እዚያ ቤተሰቦ በረሃ ሄደው እንደ ሁለት ቤት ዉስረው ማደት እንግሩሩ ቤት ይደርሳሉ፡፡ እንዳንዴ ግን ጴጥሮስ እንደራት ብር ብቻ ትሮርቸቸው፡ ወደ ሆቴት በዓት ላይ ቀብ ብለው እያወሩ እያገሬ ማደት እንግሩሩ ቤት በቀጥታ ይገቡና እንዳንድ እሬቱን እሰው ከትርሲትና ከወንድዋይቱ ጋር መጫወት ይጀምራሉ፡፡

ወንድዋይቱና ትርሲት በጣም ይቀደዱ፡፡ ብርሃኑ ደጋን እንደተመለከተው ወንድዋይቱ ከሌሎቹ ጋር ከረብም እንደሚያወሩ ጉደለኛ በመሆኗ ይደሰታልና፤ ይጠለቀለቸዋል፡፡ ብሮችንት ይሰማታል፡፡ ሰለዚህ ትርሲት ገና ማደት እንግሩሩ ቤት እንደገባች ወንድዋይቱን ጉራ አለችሳት . . . ከብሮችንቷ ለመጠለል ፍቅርን ፍለ፡፡ ትርሲት በበኩሏ ለእንግዳዊቷ ምክንያት የሰደደ አሮ ተደናግሯት ስለነበረ የወንድዋይቱን የደናንነት ዝ በረሰት በደስታ ተቀበለች፡፡ በጣም የሞቀ የጠበቀ መቀራረ ጓደኝነት ሆነ፡፡ የጴጥሮስና የብርሃኑ ጓደኝነት ደህነ የወንድዋይቱንና የትርሲትን መቀራረብ የበለጠ አጠናከረው፡፡ ከሆ በላይ ወንድዋይ ብርሃኑን በትርሲት የተነሳ በጣም ወደደችው፡፡ ጴጥሮስና ትርሲት እርስ በርሳቸው ደህነ ቢሰለም አይቀያየሩም፡፡ ግን እሷም የብርሃኑ ጓደኛና የወንድዋይቷ ወዳጅ ስለሆነ ተቀብለችው፤ እሱም የብርሃኑ ስለሆነች ተቀበላት፡፡

እንግዲህ ትርሲት አሌጋ አይሰሩት እንጂ ወንድዋይቷ ግን አሌጋ ነች፡፡ ደግሞ ወንድዋይቷ ጉደለኛ እንደመሆኗ፤ ፍቅርም ን በለዉ ጉደለኛ ነው፡፡ ትርሲትን የምትወዳት በሙሉ ልቧ ስለሆነ፤ አሌጋዋን ለትርሲት ማካፈል ፈቀደች፡፡ ሰለዚህ ብሎ ጊዜ ብርሃኑ ሲሄድ እርሩ ብሎ ሲሄድ ሲል ወንድዋይቷ ‹ለምን አትድርም› ትለዋለች

‹የትን› ሲላት

‹የኔ አሌጋ ምን ሆነን›

«ጴጥሮስ የት ያድራል?»

«ትላንት አላደረም'ንዴ? ባሬ ተራህ ነው»

ብርሃኑ በጓደኛው በጴጥሮስ ገንዘብ እየመጣ፣ ትርሲት በጓደኛዋ በጠንፍየለሽ አልጋ እያሳደረችው፣ ፍቅራቸው እየተመቻቸው እየሞቀ ሄደ። ብርሃኑ ያንን ጊዜ ሲያስታውስ፣ እሱ እንደልቡ ገንዘብ ቢኖረውና ትርሲትም የራስዋ መኝታና አልጋ ቢኖራት ኖሮ፣ ምናልባት ፍቅራቸው ያን ያህል አይሞቅም አይለመልምም ነበር ብሎ ያስባል።

ብርሃኑና ጴጥሮስ ሲደንሱ ያመሹና ወደ አምስት ተኩል ላይ ማደር ተራው ያልሆነው ትርሲትንና ጠንፍየለሽን ደህና'ደሩ ብሎ ይሄዳል። አዳረው ሂያጁን ራስ መኮንን ድልድይ ድረስ ይሸኙዋል። «ምናልባት ለክፍል ያልደረስኩ እንደሆን በደምብ note ውሰድና ታስረዳኛለህ» ይለዋል።

ጴጥሮስና ብርሃኑ ከሚስቶቻቸው ጋር በተራ ማደር ብቻ ሳይሆን በተራ ይጣሉ ነበር። የውቢ በረሃ ፍቅር መጣላት መደባደብ ካልተጨመረበት እንደ ፍቅር ስለማይቆጠር፣ ሴቶቹ ብርሃኑና ጴጥሮስን አንዳንዴ ሆን ብለው ነገር ፈልገው የሚጣሉዋቸው ይመስል ነበር። ወንዶቹም በበኩላቸው ሴት ከታገሱዋት ጭንቅላት ላይ እንደምትወጣ ስለሚያውቁ መጣላት ባያስኛቸውም አኩርፈው ይሄዱ ነበር። ጴጥሮስና ጠንፍየለሽ የተጣሉ ጊዜ ብርሃኑና ትርሲት ያስታርቁዋቸዋል። ትርሲትና ብርሃኑ የተጣሉ ጊዜ ደግሞ እነዛ ተራቸውን ያስታርቁዋቸዋል።

አንድ ማታ ትርሲትና ብርሃኑ ተጣሉ። ጴጥሮስ ትርሲትን ሲመክራት «ለምን ትጣላላችሁ? ጥሩ አይደለም። እሱ ሲወድሽ ለምን እንዲህ ታበሳጭዋለሽ?» በማለት ለዳንስ አስነሳት።

ጠንፍየለሽ ደሞ በበኩሏ ብርሃኑን ለመምከር መኝታ ቤቷ ወሰደችው። አልጋ ላይ ቁጭ ብለው የደንቡን ከተነጋገሩ በኋላ፣ ማለት በብዙ ቃላትና አረፍተ ነገራት «ለምን እንዲህ ትሆናለህ?» ብላው «በል አሁን ልጅ አትሁን። እዚህ ቆየኝ እመጣታለሁ» ብላው፣ እሱም በብዙ ቃላትና አረፍተ ነገራት «እኔ ምን አደረኩ? እሷ'ኮ ነች 'ምታበሳጨኝ» አላት። ትርሲትን ከጴጥሮስ ጋር ተጋግዛ ልታመጣት ልትሄድ ስትል፣ ጠጋ ብሎ ሰወጠችና እጁን በቀጭን እጇ እያሻሸች፣ ጉራማይሌ ጥርሷን በዛሀን ፈገግታ እያሳየች

«ተው ብርሃኔ እንዲህ አትሁን!» አለችው

«ምን አረግኩ?» ሲላት

«መረረ ድምፅ «ትርሲትን አትጉዳብኝ!» አለችው። ሲታመር ፊቷ በጣም አስተዋይ መሆኑን ባሬ አየ። ግን ትርሲትን ምን ያህል እንደምትወዳትና እንደምትቆረቆርላት ከድምጿ ስላወቀ አስቀያሚነቷን



ወደደላት።

«ምን ብዬ ነው 'ምጎዳት?» አላት

«እያወቅከው!» አለችው «ታላቅ ወንድሜን ስለምታስታውሰኝ በጣም እወድሃለሁ። ደሞ ትርሲት ከልቧ እንደምትወድህ አውቃለሁ። እሰዛ ግን ማንም ወንድ እንደዛ ቢያረጋት እገለዋለሁ አለቀውም። ትርሲትን 'ሚንካብኝ አልወድም፣ እሷን መጉዳት የፈለገ አስቀድሞ እኔን ገሎ መቅበር አለበት»

ብርሃኑ የያዘውን እጇን አጥብቆ እየጨበጠና ሀዩን ሀዩድን እያየ ከምሩ «ትርሲት ብቻዋን ናት እያልኩ አስጋላት ነበር- አለ -አንቺ ከልብሽ እንደምትወጂያት ገና አሁን ነው የታየኝ። አንቺ ካለሽላት ምንም አትሆንም፣ መስጋትም የለብኝ። በጣም ጥሩ ነው። ማንም ወንድ ሊያጠቃት የፈለገ እንደሆን እንድትነግሪኝ እለምንሻለሁ-

ፊቷ መላቅ፤ ቆንጆ መሆን ጀመረ።

«ጥሩ ልጅ ነህ። እወድሃለሁ» አለችና እጁን ሳመችው። በጣም ደነገጠ። ራሱን ደፍቶ የተቆላለፉ ጣቶቻቸውን ሲያይ፣ ግንባሩን ሳመችው። ራሱን እንደደፋ ቀረ። ተነስታ በሩን ከፍታ ስትሄድ ቡሉ ቀና አላለም።

ትርሲት ስትመጣ ራሱን እንደደፋ አገኘችው። ቶሎ በሩን ዘግታ አጠገቡ መጥታ እቅፍ አደረገችው

«ውይ የኔ ቆንጆ! ራስህን አትድፋ ደስ አይለኝም። አዝዘህ ሳያህ ሳለቅስ እፈልጋለሁ» አለችው።

ዞማ በጉሯን እየዳበሰ «አገሬ ስታዩኝ መጥተሽ እትፈን ... ይሰተኛል» አላት። ጥላቸው ደህን ያህል የመረረ ነበር።

የጴጥሮስና የጠንፍየለሽ ጥል ግን አንዳንዴ የምር ጥል ሳይሆን አልቀረም። ምክንያቱም በተጣሉ በነጋታው ብርሃኑ ጴጥሮስን «ትናንት ሌሊቱ እንዴት ነበር?» ሲለው

ሲጃራውን እያቦነነ ከርዳዳ ፀጉሩን በግራ እጁ ወደ ኋላ እያበጠረ «አይጣል ነበር 'ባክህ። ተኳርፈን ጀርባ ለጀርባ ተጋድመን፣ ጠዋት እንደዛው ሳንዘጋ አደርን። ጣጣ ነው ባክህ። እየጨቀጨቀችን እሳቱን ስትለኝ ጊዜ አንድ ሁለቴ በጥፊ ማለት ግድ ሆነብኝ። ከዛምንት በፊት አንቺ መታረቃችንን» ይለው ነበር።

ጴጥሮስና ጠንፍየለሽ እንዲህ እየሆኑም፣ የአልጋው ጉዳይ የተጀመረው በነሱ ነበር። ለካ ደሞ ብርሃኑና ጴጥሮስ ተራ ወቀቱ ከሚስቶቻቸው ጋር የሚያድሩበት አልጋ የጠንፍየለሽ የራሷ ሳይሆን የኪራይ ኖሯል።

«ጋሼ ጴጥሮስ ሥራ ሲይዝ ለትዬ ጠንፌ የባልና ሚስት አልጋ ሊገዛላት ነው:: አንተስ ሥራ ስትይዝ ትገዛልኛለህ?» አለችው:: ጠንፍየለሽን እትዬ ብላ ነው 'ምትጠራት፣ እንደታላቅ እህት

«እስቲ እናስብበታለን» አላት

«ምን ማሰብ ያስፈልገዋል?»

«እየሽ፣ ጴጥሮስ ለጠንፍየለሽ የባልና ሚስት አልጋ ሊገዛላት ይችላል:: ምክንያቱም ሌላ የሚያስፈልጋት ነገር የለም:: አንቺ ግን አንድ ሁለት ቀሚስ፣ አንድ ሁለት ጫማ፣ ውስጥ ልብስ፣ ሙታንታ፣ ጡት መያዣ፣ ምናምን ያስፈልግሻል:: ይኼ ደሞ ብዙ ገንዘብ ይጠይቃል:: ስለዚህ መጀመሪያ አንድ ትንሽ አልጋ ገዝተን፣ የባልና ሚስት አልጋው ቢቆይልን አይሻልም? ምን ይመስልሻል!»

በለስላሳ ገላዋ እቅፍ አርጋ «ብርሃንዬ፣ ልክ እንደ እህትህ ነው 'ምታስብልኝ?»

«እህቴ መሆን ትፈልጊያለሽ?» አላት::

«ውይ! በጣም እፈልጋለሁ. . . ግን እህትህ ብሆን እንደዚህ አታቅፈኝማ»

«ለምን አላቅፍሽም?»

«እንዲህ ራቁታችንን ሆነን?»

«ምን አለበት?»

«እህትህ ሆኜ?!»

«ታዲያስ?»

«ሂድ! ባለጌ»

ብርሃኑ በጓደኛው በጴጥሮስ ገንዘብ እየመጣና ትርሲት በጓደኛዋ በጠንፍየለሽ አልጋ እያሳደረችው ፍቅራቸው እየተመቻቸው እያደገ እየሞቀ እየማረ ሄደ. . .

. . ብርሃኑና ጴጥሮስ ሥራ ሲይዙ ጊዜ ብዙ ነገር ተለወጠ::

ጴጥሮስ ትምህርት ሚኒስቴር ሥራ ሲይዝ፣ ብርሃኑ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ገባ:: ጴጥሮስ ከቤቶቹ ጋር መኖር ሲጀምር፣ ብርሃኑ ቤቶች ስለሌሉት ከኔ ጋር ቤት ተከራይቶ መኖር ጀመረ:: ስለዚህ የጴጥሮስና የብርሃኑ እንደ ድሮው አብሮ መዋልና አብሮ ማምሸት ቀስ እያለ ቀረ:: ኑሮ ያለያያቸው ጀመር::



ቢሆንም ቢያንስ በሳምንት ሁለት ጊዜ ማታ ቢልትራሚ ወይም ጉዊዶ ቤት አብረው እየተጫወቱ እየቀለዱ እራት በልተው፣ ማሚት ቤት ይሄዱና ሚስቶቻቸውን ይዘው ልክ እንደድሮዋቸው ለአራት ሲቀልዱ ሲስቁ ሲደንሱ ያመሻሉ:: ግን ሁለቱም እዛው ከሚስቶቻቸው ጋር አድረው፣ ጧት ቀድሞ የተነሳ ሥራ ለመሄድ ሌላውን ይቀሰቅሰዋል 'ንጂ፣ እንደ ድሮው አንዱ ከሚስቱ ጋር ለማደር ሌላውን አይሸኘውም:: ምክንያቱም ብርሃኑ ልክ ስራ እንደያዘ ከጥሏሁን ገንዘብ ተበድሮ ለትርሲት አልጋ ገዛላት:: ጴጥሮስ ግን ለሚስቱ ቃል የገባላትን አልጋ ደሞዝ እስኪቀበል ድረስ ሊገዛላት አለመቻሉን አስረድቷት «ግድ የለም ኧረ፣ አሁን የምንተኛበት መች አጣን?» ብላው ፍቅራቸውን ቀጠሉ::

የደሞዝ ቀን መጣ:: ብርሃኑ ለትርሲት አንድ ቡና ዓይነት ቀሚስና ባለታኮ ጥቁር ጫማ ገዛላት:: ያን ዕለት ማታ ስትደንስ የብዙ ሰው ዐይን ተከፈተ፣ ቆንጆ መሆንዋን ቤቶቹ ሳይቀሩ ይገነዘቡ ጀመር:: ብርሃኑም ራሱ እንደዚህ ውብ መሆንዋን አያውቅም ነበር:: እጅግ ብዙ ኩራትና ደስታ ተሰማው:: ግን ደስታው ሙሉ እንዳይሆን ትንሽ ቅር ያለው ነገር ነበረ::

ጴጥሮስ ደሞዙን ለመቀበል ባለመቻሉ ለጠንፍየለሽ አልጋ መግዣውን አልሰጣትም:: መሥሪያ ቤቱ ስምህ የደሞዝ መዝገብ ውስጥ አልገባም፣ እስኪገባ ድረስ ደሞዝህን በብድር ስም ከ«ሳጥን» መውሰድ አለብህ ብለውት፣ ከ«ሳጥን» በብድር ስም ለመውሰድ ደሞ ሁለት ወይም ሦስት ሳምንት እንደሚፈጅ ገልጸውለት፣ ይህን ውትብትብ ነገር ለጠንፍየለሽ ነግሯት፣ እሷ «ምንም አይደለም፣ ጊዜው ይርዝም 'ንጂ የሠራህበትን መቼም አይከለክሉህም» ብላ አጽናናችው::

ጴጥሮስ «እውነትሽን'ኮ ነው» ብሏት እንደ ድሮው ለአራት ሲጫወቱ አምሽተው በስድስት ሰዓት ወደየአልጋቸው ተከተቱ::

ሁለተኛው የደሞዝ ቀን መጣ:: ብርሃኑ ለትርሲት አንድ የሀበሻ ልብስ አስፋላት:: ነጭ ባለታኮ ጫማ ገዛላት:: ከነጭ ጉትቻ ጋር ነጭ በነጭ ለብሳ፣ ጥቁር ብርሃን የሆነ ዐጉሯ ጠይም ሳቂታ ፊቷን ከቦ፣ ረዥም አንገቷን በነቃንቀች ቁጥር እትከሻዋ ዘንድ ኻየው ኻየው ሲጫወት - እቤት ማማሯ! ደሞ ባለ ረዥም ተረከዝ ጫማ አርጋ ስትራመድ ዳሌዋ እንዴት ነው 'ሚወዛወዘው! እቤት ብርሃኑ ልብ ውስጥ የሚንፈላሰሰው ኩራትና ደስታ! ግን አሁንም ያው ከቅሬታ ጋር ነው::

ጴጥሮስ ካንድ ስምንት ቀን በፊት ጠንፍየለሽን «አሁንስ ስሜ የደሞዝ መዝገብ ውስጥ ገብቷል:: ለሚመጣው ልደታ የሁለት ወር ደሞዜን አንድ ላይ እቀበላለሁ» ብሏት ነበር:: የደሞዝ ቀን ካለፈ ደኸው አራት ቀን ሆነው:: ጴጥሮስም ከጠፋ አራት ቀን ሆነው::

ሦስት ሳምንት ሙሉ ጴጥሮስ ማሚት ቤት ብቅ አላለም።

ብርሃኑ ጠንፍየለሽ እሱንና ትርሲትን እያየች እንደምትበቃይ በግልጽ ስላየ፣ በተቻለው መጠን እንዳታያቸው ለማድረግ ይሞክር ነበር። ማታ ሲመጣ «እንዴ' ነሽ ጠንፌ?» ብሎ ጨብጧት፣ ቶሎ ብሎ ወደ ውስጠኛው ክፍል ይገባል። ትርሲት መጥታ ትቀመጣለች። እሷም ጠንፍየለሽ እንዳታያቸው ትፈልጋለች። አብረው ሶፋ ውስጥ ተቃቅፈው ቁጭ ብለው ሲያወሩ፣ ሲተያዩ ይቆዩና፣ እንደ አልተገናኘንም እንደ ተራራ ሶፋ ውስጥ ተከምረው ቤቶቹ በተራ እየመጡ ጭናቸው ላይ እንደ ጉም ሲቀመጡባቸው እያዩ ይቆዩና፣ ሲያወሩ ሲተያዩ ሲስቁ ይቆዩና፣ ደስ የሚል ሙዚቃ ሲዘፍን ተያይዘው እዛኛው ክፍል ሄደው ይደንሳሉ።

ዳንሳቸው መሀል ላይ ጠንፍየለሽ ከተቀመጠችበት ወይም ከምትደንስበት ቦታ ሆና ልትከብዳቸው ልትቀፋቸው ትጀምራለች። ዳንሱ ሲያልቅ እንደ ዕፍረት ዐይነት እየተሰማቸው ወደ ውስጠኛው ክፍል ተመልሰው ይሸሻሉ።

ትንሽ ቆይቶ ብርሃኑ በትርሲት ትዕዛዝ ሄዶ ጠንፍየለሽን አንድ ሁለት ጊዜ ያስደንሳታል። ሁለቱም እየደነሱ የሚያስቡት ስለ ጴጥሮስ ብቻ ነው፣ ግን ሁለቱም ስሙን በጭራሽ አያነሱም፣ ልክ እንደረሱት ለማስመሰል። አንድ የሚያስቅ ነገር ይናገሩና «ሁ-ሁ!» ብለው ባዶ ሳቅ ይስቃሉ። ዳንሱ ሲያልቅለት ብርሃኑ ቶሎ ብሎ ወደ ውስጠኛው ክፍል ይመለስና የትርሲትን ፈገግታ የሙጥኝ ይላል።

ደግነቱ የትርሲት መኝታ ቤት ከጠንፍየለሽ ጋር አይደለም፣ ከሙሉ ጋር ነው። አለዚያ ሌሊቱን እንደልባቸው ሊተቃቀፉ፣ ሊተሻሹ፣ ሊዋደዱ፣ ሊንሾካሾኩ አይችሉም ነበር። ያኔ ምን ይውጣቸው ነበር!

ሌሎቹ አሻሻጮች ጠንፍየለሽን ስለሚጠሏትና በፊት በኋላ በጴጥሮስ ፍቅር ይቀኑ ስለነበረ አሁን ጴጥሮስ ሲከዳት ጊዜ እጅግ ተደሰቱ። ግን በጣም ስለሚፈሩዋት በግልጽ ሊቀልዱባት ወይም በአሽሙር ሊሰድቡዋት አይደፍሩም። ስለዚህ እሷ እንድትሰማ አርገው ብርሃኑን «አይ ብርሃኑ! እንዴት ጥሩ ልጅ ነህ! ትርሲትን ሙሽራ አስመሰልካት፣ አይደል?» ይሉታል። ወይም አጠገቧ ሁለት ሶስት ይሆኑና ትርሲትንና ብርሃኑን እያዩ «ውይ እንዴት ያምራሉ! ፍቅር ከተባለ አይቀር እንዲህ ነው 'ንጂ!» ይባባላሉ

ጠንፍየለሽ ስሞታ እንዳልሰማች ውስጡን እየጨሰች ስቃይዋን ትቀበላለች። ፈገግታ የከዳው ፊቷ - በብስጭት የተቆለፉ፣ ቀይ ቀለም የተቀቡ ወፍራም ከናፍሯ፣ ኩል የበዛባቸው ክፉ መሳይ ዐይኖቿ፣ በጠቅላላ መልኳ ላይን አስቀያሚ እየሆነ ሄደ። ደስ ሲላት የምታምር፣ ሲከፋት



የምታስቀይም ሲትዮ ናት። ወንዶቹን እንደ ሁለት ብርጭቆ ውስኪ አስገዝታ ትጠጣና፣ በግድ እህ! ብላ ያማጠችው የሚመስል ያወሸት ሳቅ ሙሃ ትስቃለች። በጴጥሮስ ምክንያት ትታቸው የነበሩት ያድሮ ወዳጆቿ አንዳንዴ እየመጡ ለአዳር ያወስዷት ጀመር።

ከሶስት ሳምንት በኋላ ትዳሚ ማታ ወደ ሦስት ሰዓት ላይ ጴጥሮስ አዲስ ሻንጉርጉር ሱፍ፣ ሻንጉርጉር ሸሚዝ፣ ሻንጉርጉር ክራቫት ለብሶ፣ ሽክ ብሎ ከተፍ አለ። ጠንፍየለሽ እንዳየችው ከጓዶቿ ሰውዬ ጋር እየደነሰች «አይ አንተ!» እያለች ጨፌኒታም የሞቀ ሳቋን ትንከተከተው ጀመር። ጴጥሮስ ባንኮኒው ዘንድ ቆሞ ሲጋራውን እያቦነነ በትንንሽ ዐይኖቹ ያያታል። ዳንሱ ሲያልቅ ያስደነሳት ሰውዬ ጭን ላይ ቁጭ አለችና፣ አንድ እጇን አንገቱ ላይ ጣል አርጋ በሌላው እጇ የውስኪ ብርጭቆዋን እንስታ ጠጣች። ሰውዬው አንድ ነገር ሲላት «ሀ ሀ ሀ!» ብላ እየሳቀች በጉሩን በእጇ ምንጭጨረች።

የጴጥሮስ ፊት በቁጣ ጠቆረ። ሲጋራውን በኃይል ወለሉ ላይ ወረወረና የመጠጡን እንኳ ሳይከፍል በፍጥነት እየተራመደ አንድ ሁለት ሰው ገፍቶ የበሩን መጋረጃ በጥፊ መትቶ ወጣ። ቅናት።

«ውሽቱን'ኮ ነው ይሄ አጭበርባሪ! ሂድና አፍንጫውን ይዘህ አምጣው!» አለች ትርሲት። ከብርሃኑና ከዋሳኩን ጋር ባንኮኒው ዘንድ ቆማ ስትመለከት ነበር። ብርሃኑ ጴጥሮስን ተከትሎ ወጣ። ወደ አጠ ምኒልክ ሐውልት በኩል በፍጥነት ሲራመድ አየው። «ሁዬ ምን ትጨማለቃለህ?» ብሎ ሊገስጸው ነበር። ግን እንደደረሰበት በቀልድ

«የመጠጥህን ሳትከፍል ነው 'ንዴ 'ምትወጣው?» አለው

«አ! ረስቼ» ጴጥሮስ እርምጃውን ሳይቀንስ «ስትመለስ እንድትከፍልልኝ አደራ» አለ

«አንተ አትመለስም?»

«አልመለስም» ዝምታ

ብርሃኑ ለጠንፍየለሽ አንድ ነገር ሊናገርላት ፈለገ፣ ግን ምንም ለማለት አልቻለም። ጴጥሮስ አልመለስም ሲለው በግምባሩ ትናንሽ አትግባ እንዳለው ያህል ነበር። አንድ ቃል ሳይናገሩ በፍጥነት እርምጃ በሙሉቱን አልፈው ፒያሳ መሀል ደረሱ። በመጨረሻ፣ ዝምታው እጅግ ስለከበደው ብርሃኑ

«እኔ 'ምልህ፣ ወደት ነው 'ንደዚህ 'ምንሮጠው?» አለ

ቆሙ። ጴጥሮስ ያለቀ ሲጋራውን መሬት ጥሎ በሹል ጫማ ጫማው እየደፈጠጠ

«ይቅርታ አርግልኝ። ሳስብ ነበር። ርሃሃል?» አለው

«እምን»

«እኔም»

ትዊዶ ቤት ሄደው፣ ልክ እንደ ድሮዎቹው እየቀለዱ መንገድ እየጠጡ ፊታቸውን በሉ። ብርሃኑ ግራ ገባው። አሁን የሚሰማው ስሜት የሚያመነታ፣ ያልለየለት ሆነ። ስለጴጥሮስ ነብስ ስለተጫወተ እየናቀው «ደጁ አብሬው የምስቀው ስሙጴጥ ጓደኛ የቤለው ብላቴ አጭበርባሪ ነው» ብሎ በሃሳቡ እየተፋበት፣ ልክ እንደ ድሮው ከልቡ አብሮት ይስቃል። ደህ እንዳደበቃ ደግሞ፣ ከሬት በኋላ ጴጥሮስ «ምን የመሰለች ቤት አግኝቻለሁ። እንሂድ ላሳይህ» ቢለው «ወይ እንተ፣ ለካ ለዚህ ነው የጠፋኸው!» ብሎት እየቀለደ ወደ ቤትየዋ ቤት ሔዱ። ከቤትየዋ ቤት ሲወጡ ብርሃኑ ቤትየዋን አመስግኖለት «ልብስ ብቻ ሳይሆን ቤትም መምረጥ ታውቃለህ» አለው። ግን ቤትየዋ ደህና ያህልም አታምርም ነበር።

ብርሃኑ «አሁን ከኔ ጋር ማሚት ቤት ትመጣለህ ወይስ አትመጣም?» አለው። በጭራሽ ደህንን ሊል አላሰበም ነበር።

«እንሂድ» አለው

ማሚት ቤት ሲደርሱ ጠንፍየለሽ ከውስጥ ወጥታ አለከፉት አለች። ብርሃኑና ትርሲት እንደ ልማዳቸው ሊያስተርቁ ከሙቀ ቢለምኑዋት፣ መልስም አልሰጠቻቸው።

በመጨረሻ ጴጥሮስ ራሱ «ስሚ ጠንፍየለሽ፣ አንድ የምነግርሽ ነገር አለኝ። በኋላ እጽፍልሻለሁ» አላት

ከፈተችለት፣ ገባ። አደረ። በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ እስከ አራት ሌሊት አብረው አደሩ።

የደምብ ቀን ሲደርስ ጴጥሮስ እንደገና ጠፋ። ደግሞ የተባበ ኤሊ? እሁንም አልተገኘም።

የማሚት አሽከሮች ጴጥሮስ ሌላ ቤት እንደያዘ ሰሙ። ቤትየዋን አብረኞቹ ያውቋታል፣ ተመቻቸው። ጠንፍየለሽን ለማበሳጨት ስለምንም ነገር መነጋገር ግብፈሉት ቀረ። ዋናው አራት ሆነው [illegible] መንት ብቻ በቂ ሆነ። ከጴጥሮስ መካድ የባበ የቤቶቹ ዓት እሳሳቃቸት ሄደ።

እሁንስ የውበት ሳቁንም ተወቻው። ገንም ብላ የመጣውን ወገድ ሲጀራ እያለመነች ስትጨስ ታመሽለች። ብሎውን ጊዜ፣ የተከፈቱ ሀድናዊ ፈገው ምንም ሰለማያዩ፣ ለፈንስ የሚጠይቋት ወንዶች በእቻቸው ካልያዙት ፊቷ እንደተቃመ ልብ አትላቸውም።



ቀን ቀን ከመንፈት ከፍል አትወጣም። ሴቶቹ ለቡና ሲጠሩዋት አማረኝም ትላለች። ለምሳ ሲጠሩዋት አልራበኝም ትላለች። የመንታዋ ወር ሁልጊዜ ክፍት ነው፣ ግን ማንም ደፍሮ አይገባም። ብቻዋን ከርታ እየተጫወተች፣ የራሷን እንጉርጉሮ እያዜመች፣ ብስጭቷን እንዳቀፈች ትመሻለች።

አንድ ቀን ብርሃኑ ትርሲትን «ሂጂና አጫውቻት» አላት

ትርሲት «እትዬ ጠንፈ'ኮ እንደድሮ አይወዱኝም» አለችው

«ለምን?» ቢላት

«በዚያ ንፍጣም ጓደኛህ ምክንያት ይመስለኛል» አለችው

«አንቺም ጠልታኛለች በይኝ?»

«እንተንም አይጠሉህም። ብርሃኑ ሲስቅ፣ ሲናገር፣ ሲጽፍ ሁሉ ታላቅ ወንድሜን ያስታውሰኛል ይላሉ። ታላቅ ወንድማቸው ሞቷል»

ብርሃኑ የጠንፍየለሽና የትርሲት ጓደኝነት መሞት እንደጀመረ አልቶ አያዉቅ፣ ጴጥሮስን የከለሙን እየናቀው ሄደ።

ትርሲትን «አሁን ጓደኛሽ ማን ነች?» አላት «ጓደኛ የለኝም። እኛን ጠላት እኛ ደግ ወደ ትንሷ እያስጠጋች «አንተ ነህ ጓደኛዬ» አለችው

ዐይን ልቡን ጭምምቅ አደረገው። በሌላው እጅ ፀጉር ወገቧን እያሰተኛ «ትርሲትዬ» አላት። ለስላሳ ትንሿን እጁ ላይ እያሻሸች ፍቅር የሞላቸው ዐይኖቿን ፊቱ ላይ እያንከራተተች

«አቤት የኔ ብርሃን» አለችው

«ትርሲቴ»

«ወይ» ገም ብለው ተያዩ

ብርሃኑ እንደአንድ ቀን ጠንፍየለሽ ከፍል በሩ ደጃፍ ነበር። ቀን ቀን የምትለብሰው አንድ የሱማሌ ጃኖ አላት። እሱንና አንድ ነጠላ ለብሳ አልጋዋ ላይ ትሞቂ ብላ ለብቻዋ እያንጎራጎረች ከርታ እየተጫወተች ነው ጎምቶቷም። ብርሃኑ ሲያጫውታት ሲመጣ፣ ለማውራት፣ እንደ ድሮዎቹው ለመቀለድ ይሞክራል። ግን ሁሉቱም ስለ ጴጥሮስ ለማውራት [illegible] ደጉም ስሙን እንኳ እንዳይነሱ ሁሉቱም በጣም ይጠነቀቃሉ። ስለዚህ ወሬ ማውራት ያቅታቸዋል። ከርታ ያጫውታቸዋል። ወሬያቸው «ትፈልጊ» «አሁን ወዲህ» «ለንተ» ብቻ ይሆናል። በመጨረሻ አንድ ሰሞት ጊዜ ከርታ ተጫውታው፣ ብርሃኑ የጴጥሮስን ስም [illegible] ጨዋታ ያለውን [illegible] ወደ ትርሲት [illegible] አደረሰ

ፈገግ ስትል ያያትና ውድድ ያረጋታል። ጸጉሯን ወይም ጉንጯን እያሻሸ «አለሽ?» ይላታል

አንድ ቀን ግን ከጠንፍየለሽ ጋር ካርታ ሲጫወት «አይ ብርሃኔ እንዲዚህ መልአክ ልጅ ሆነህ ከዚያ ከውሻ ጋር እንዴት ጓደኛ ሆንክ» አለችው

ምን ሊላት ይችላል? ዝም ብሎ ካርታ መበወዙን ቀጠለ።

«የራሱ ሕሊና 'ንኳ ባይኖረው አንተን እያየ አያፍርም? ከብርሃኔ ጋር እኩል ጀምረን፤ አሁን እሱ ትርሲትን እንዲህ ሲያንቀባርራት እኔ እንዴት ለጠንፍየለሽ የዋሸሁላትን አልጋ 'ንኳን አልገዛላትም ብሎ አያስብም? ሰው ምን ይለኛል ብሎ አያስብም? ደሞ'ኮ እኔ ምንም አልጠየቅኩትም ነበረ። እሱ ራሱ ነው የጀመረው። ሥራ ቢበዛ የባልና ሚስት አልጋ እገዛልሻለሁ አለኝ፤ እሺ አልኩት። እሱ ለካ ያ በምን ገንዘብ ስጠን እንዳልለው፤ አልጋውን እያሰብኩ ዝም ብዬ እንዳሳድረው ብሎ የፈጠረው ብልሃት ኖሯል። ግን ይህ ሁሉ ብልሃት አያስፈልግም ነበር። ምንም ባይለኝ እንዲሁ ለሳድረው ነበር። እስር ዓመት ሙሉ ደስ እያለኝ አሳድረው ነበር። እሱ ልብ ስለሌለው አይገባውም 'ንጂ ፍቅር ይዞኝ ነበር። እሱ በብልሃት ዓመት ሙሉ የተበደሁለት መስሎታል። አይ መብዳት እንዲህ አርጎም የሴት ልብ ክሌትስ የበስ መራራ ሳቅ ሳቀች።

ማስዘኗ ደሞ ማስጠላቷ፤ መጠጥ፤ ሲጀራና ምግብ ጥርሷ ላይ ቆሻሻውን ለስንውታል። እንዲን ጥርሷን ልትፍቅ አፏን ከተጉመጠች ሳምንት ሳያልፋት አይቀርም። ትንፋሿም ያስታውቃል። ፊቷን ሰሌተጠበች ያትላንት ሜካፕ የከንፈር ቀለምና የፊት ዱቄት ፊቷ የተጣገት ማታ የማብዣ ትራፊ አስመስለውታል። መቅፈፏ

አልጋውስ ይቅር፤ ፍቅሩም ይቅር እሺ። ደሞዙን ሲቀበል አያሙቁ ደሞዙ አልቆ ሌሎች ቤቶች አጣኒድር ሲሉት ይምጣና ከኔ ጋ ይደር እሺ። ገንዘቡን ሌሎች ላይ አያፈሰ እኔን እየመጣ ሰወትቀኝ እስኪበቃው ድረስ ይስርረኝ እንደ ቁስ በትሉ፤ እሺ ዝሎንም እሺ አልኩ። ይህ ሁሉ እንዳያበቃው እዚሁ ትርሲታችን ፊት ፎገር ምን በደልኩት? የፈለገውን አየከፈትኩ በስሙ እንደ ይሰፍርብኛል ቁንጂ አይፈራልም?»

በተጨባበጠ እጇ የሊቃውን እጇን መናፍ ያገኘው እየመታት አፍ ውስጥ ደጥርዋን እየመታጠች

ሕሊን 'ንግዲህ ደሞዙ ወደ ግልቲያው ሳይሆን አፍታ ። ሽ ወደ ተንዝመናያ ይመጣል። አንድ ሦስት ቀን ደግሞ ወይበት ይቀርፈኛል። እንደፈረደብን።



ብርሃኑ ንዴቱ ድንገት ገነፈለ «አንቺ ደግሞ ዝም ብለሽ ትቀፈሪስታለሽ!» አላት።

«ምን ላርግ ብለህ ነው?»

«እምቢ በይዋ!»

«ዋ! ብርሃኔ! እምቢ ማለት ብችልማ!»

የያዘውን ካርታ አልጋው ላይ ጣለና ብድግ ብሎ ወጣ። ከጴጥሮስ ከፋት የባሰ የሷ መቀበል አስቆጣው። ደሞ ስትነግረው የተጠቀመችባቸው ቃላት እየታወሱት እየቀፈፉት የባሰውን አቃጠሉት «እስኪበቃው ድረስ ይስርረኝ! እንደ ቁስ በትሉ ይቆፍረኝ» አሁን ይህን ምን አለኝ? ራሷን ማዋረድ ደስ ብሏት ነው? እቺ ቂንጥራም አሮጊት!

«አሮጊት» የሚለው ቃል የብርሃኑን ዐይን ከፈተለት። ምስኪን ጠንፍየለሽ! ማርጀቷ ነው ለካ። እንዴት እስካሁን አላስተዋለም? ቢያንስ መላላ በባት ዓመት አታጣም። ሸርሙጥና የጀመረችው አሥራ ስድስት ዓመት ሲሆናት ነው። ወይስ አሥራ አምስት ነበር ያለችው? ብቻ የው ነው ሃያ ዓመት ሙሉ በሸርሙጥና አሳልፋለች። ከሃያ ዓመት ልፋት በኋላ አልጋ 'ንኳ ስለሌላት በኪራይ አልጋ ትተኛለች። አሁን የሷ ኑሮ ኑሮ ይባላል? በሃያ ዓመት ውስጥ ስንቱ በድቷታል፤ ስንቱ ተደስቶባታል፤ ስንቱ አልፍቷታል— እንደ ቁስ በትሉ። ታዲያ አሁን መኝታ አልጋ 'ንኳ የራሷ የላትም።

ምናልባት ጨርሶ እስኪታረጅ አንድ አምስት ዓመት ቀርቷታል። በዚህ ዓመታት ውስጥ የሚያለፏት ወንዶች ቁጥራቸው እያነሰ ይሄዳል። ከዚያ በኋላ ግንም ዘወር ብሎ አያያትም። ያን ጊዜ ምን ትሆናለች? ያለፉትን ዓመታት ዘወር ብላ ስትመለከት፤ ሰማቸውን እንኳ የማታስታውሳቸው ወንዶች ሕይወቷ ውስጥ እንደ ጠጠር ተበትነው ሲታዩዋት፤ ከዚህ ሁሉ ወንድ ምን አገኘሁበት? ስትል ምን ይሰማታል? ሙሉ በዱኝ ሄዱ! ምንም አልተውልኝ ብላ ስታስብ ምን ይሰማታል? ምስኪን ጠንፍየለሽ! ታዲያ ያ የእባብ ልጅ ጴጥሮስ እንዲህ ይጫወትባት? እንዴል አለው! ተምሯል! ለምን አያስብም? እንደ ታ'ፋቱን ደፍሮ በሸርሙጣ ነብስ ይጫወታል? ያውም በማርጀት ላይ ያለች ሸርሙጣ። እናቱን መድብደብ ነበር። መርገጥ! በፊር ማለት።

«መጣሁ! ምን ሆንክብኝ?» አለችው ትርሲት

«አንቺ ደሞ ዝም በይኝ» አላት

ዝም አለች። መሬት መሬቱን ታየች። አላበችው። ራሷን ደፍታ መሬት መሬቱን ሲታይ ለጠንፍየለሽ ሲሰማው የነበረው ሁሉ ሙሉ በሷ ተተካው። የጠንፍየለሽ እርጅና እሷም አንድ ቀን ሲቀርባት ታየው። እርጅናና ሐጅ እንቀጠይኖቸት እንዲሁ ተቀምጧል።

እንደሚለው ያህል «እሷስ የኔ ናት አትንካብኝ!» ብሎ እንደሚነካቱ ያህል፣ ትርሲትን በኃይል እቅፍ አርጎ

«ትርሲትዬ! ትርሲት! የኔ ትርሲት!» አላት

«እባክህን አትቆጣኝ:: ስትቆጣኝ እፈራለሁ» አለችው

እቅፍ ጭምቅ አደረጋት:: ፀጉሯን፣ ጉንጯን፣ አንገቷን እየሳመ «ትርሲትዬ! ትርሲትዬ! የኔ ትርሲት! አልቆጣሽም አልቆጣሽም ቆንጆ፣ አልቆጣሽም የኔ ትርሲት! አልቆጣም:: እወድሻለሁ ነኝ አልቆጣሽም:: እወድሻለሁ'ኮ! ካንቺ ጋር ነኝ፣ እሺ? ካንቺው ጋር ነኝ፡ እወድሻለሁ»

ምን እንደነካው ሳይገባት፣ ግን አንድ ነገር እንደሆነ እየታ ለሚናገረው ሁሉ «እሺ የኔ ጌታ፣ እሺ፣ እሺ» እያለች በድምፂ መለስለስ የልቡን ማዕበል እያባበለች ዝም አሰኘችው::

በደከመ ድምጽ፣ በተሸነፈ ድምጽ

«መጋረጃውን ዝጊና እቀፊኝ:: እቅፍ አርጊኝ እሺ?» አላት

«እሺ የኔ ጌታ፣ እሺ» ብላ መጋረጃውን ጋርዳ፣ ኮቱን አውልቃለት፣ አልጋው ላይ ተጋደመችና እጆቿን ዘረጋችለት:: እቅፏ ውስጥ ወደቀ:: ደረቷን አንተራሰችው፣ ራሱን አቀፈችው:: ዝም አሉ:: ብዙ ጊዜ ቆዩ::

ጠንፍየለሽ እንዳለችው ጴጥሮስ ያን'ለቱኑ ማታ ሸክ ብሎ ከተፍ አለ:: ያላንዳች ፈገግታ፣ ያላንዳች ንግግር ከጠንፍየለሽ ጋር ምስት ጊዜ ያህል ደነሰ:: ሁለት ሦስት ውስኪ ጋበዛት:: አብሯት አደረ:: አራት ሌሊት አከታትሎ አደረ:: ከዛ በኋላ እንደገና ጠፋ:: ጠንፍየለሽ እንደገና ከካርታዎችዋና ከእንጉርጉሮዋ ጋር መዋል ጀመረች:: ከጥቂት ቀናት በኋላ ጴጥሮስ ወደ ብርሃኑ መሥሪያ ቤት መጥቶ

«በሥራ ምክንያት አዲስ አበባን መልቀቄ ነው» ብሎ ተሰናበተው:: ምን ዓይነት ሥራ እንደሆነ አልገለጸለትም:: ብርሃኑም ማወቅ አልፈለገም:: ዝም ብሎ «ሹመት ያዳብር» አለው:: እንደ ጓደኞቹ ሳይሆን፣ በሩቅ እንደሚተዋወቅ ሰው ተጨባበጡ:: ተለያዩ::

ብርሃኑ ማታ ማማሚት ቤት እንደደረሰ ትርሲት አንድ ደብዳቤ ሰጠችው:: ከጴጥሮስ ነው:: በእንግሊዝኛ እንዲህ ይላል፦

«ብርሃኑ፣

«ይህን ደብዳቤ እንዴት እንደምጀምር አላውቅም:: በጣም አስቸጋሪ ነው:: ነገር ግን መጻፍ አለበት:: በጣም ተወዳጅ ጠባይ ስላለህ፣ የማያውቁህ ሰዎች ሁሉ ካንተ ጋር ጓደኛ ለመሆን ሲሻሙ፣ ይህን



መልካም ጓደኝነትህን አንድ ዓመት ሙሉ ለኔ ስለሰጠኸኝ ትልቅ ኩራት ይሰማኛል፣ ደሞም እስከመቼውም አልረሳውም:: ከዚግኑና ከሽመገልኩ በኋላም ቢሆን የጉርምስናዬን ዓመታት ሳስታውስ፣ ውቢ በረሃ ትዝ ሲለኝ፣ ይህ ትዝታ ባንተ ጨዋታና ጓደኝነት ምክንያት ወርቅና ብርሃን ለብሶ እንደሚታየኝ እርግጠኛ ነኝ:: ለዚህም ከልቢ አመሰግንሃለሁ::

«ትንሽ ቅር የሚለኝ ወደ መጨረሻ ላይ ከጓደኝነት መዝገባህ ስለ ሰረዝከኝ ነው:: ቢሆንም ለሚትህ ይገባኛል:: በትን ልብህ ስትመለከተው ጠንፍየለሽን በድያታለሁ:: ግን ምንም ነገር ቢሆን፣ ለተመልካቹና ለአድራጊው አንድ አይደለም:: ቁጭ ብለን ወይም ቆመን ኳስ ጨዋታ ስንመለከት፣ አንዱ ኳሱን ሲስት በጣም ይገርመናል፣ አንዱ ደሞ ኳሱን ወደ ጎሉ በኩል ላለው ወገኑ ሲያቀብለው እንደሚያገባ እያየን ሳያቀብለው ሲቀር፣ ዝም ብሎ ብቻውን ቢፍጨረጨርና ኳሱን ሲነጠቅ ያበሽቀናል:: ኳስ ጨዋታው ውስጥ ብንገባበት ግን ያኑ ያህል እንሳሳታለን፣ የሚመለከቱን ደሞ ይገርማቸዋል፣ እንዳንዴም ይንቁናል::

«ስለኔና ጠንፍየለሽ ጉዳይ በሰፊው ላስረዳህ በፈቀድኩ፣ ግን ምንም ልነግርህ አልችልም:: ምክንያቱም በኔና በሷ መሃል ነው:: ብቻ አንድ ጥያቄ ፍቀድልኝ:: እኔ እሷን የምበድላት፣ እሷ ራሷ መበደል ስለምትፈልግ እንድበድላት እያስገደደችኝ ቢሆንስ? ምን ይመስልሃል? ሌሊት አልጋ ውስጥ ምን እንደምንሰራ፣ ምን እንደምንነጋገር ሳታውቅ እንዴት ፍርድ ለመስጠት ትችላለህ?

«የሆነ ሆኖ፣ እሱን እርሳው:: ለአንድ ዓመት በሥራ ምክንያት ከአዲስ አበባ መውጣቴ ነው:: ዓመቱ ሲያልቅ ደግሞ መሥሪያ ቤቱ ለሁለት ዓመት ትምህርት እንግሊዝ አገር ወይም አሜሪካ ይልከኛል:: ማለት የኔና የጠንፍየለሽ ጉዳይ አልቋል:: ደሴው ተዘግቷል::

«ያቺን የምትወዳትን ቆንጆ ትርሲት ጋ ትቼልሃለሁ:: ኪሷ ውስጥ አንድ ማስታወሻና አንድ ምክር አስቀምጬልሃለሁ:: ማስታወሻውንም ምክሩንም ያለ ቅሬታ እንደምትቀበለኝ ባለሙሉ ተስፋ ነኝ::

ያንተው

ጴጥሮስ ገብረ እግዚአብሔር»

ብርሃኑ ይህን ደብዳቤ ሲያነብ ስፍራት እየተሰማው ሄደ:: ለመሆኑ ጴጥሮስ እኔን በምን አስቀይሞኝ ያውቃል? ለኔ ሁልጊዜ ጥሩ ነበረ:: የጠላሁት በጠንፍየለሽ ምክንያት ነው::

ግን በሁለቱ መሃል ምን አገባኝ? ደሞስ ስለሁለቱ የግል ግንኙነት ምን አውቃለሁ? ብሎ ጴጥሮስን በመበደሉ ፀፀት ይሰማው ጀመር::

አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ ደብዳቤውን ሲያነብ ትርሲት ቆማ ትጠብቀው ነበር፡፡

«ምንድን ነው?» አለችው

«በኋላ እነግርሻለሁ፡፡ ጴጥሮስ ልቶ አልተወልኝም?» አለች፡፡ በባውንደሪ ወረቀት የተሸፈነ ልብስ ግድግዳው ላይ ተሰቅሎ ነበር፡፡ እሱን አሳየችው፡፡

«እሺ ሱቅ ቆይኝ» አላት

«አንተስ?»

«ትንሽ ቆይቼ 'መጣለሁ»

«ሱቅ ብዙ ሰው የለም፣ መሄድ የለብኝም፡፡ ካንተ ጋር ልቆይ»

«የለም፣ ሂጂ መጣሁ» ብሎ አስወጥቷት በሩን ዘጋው፡፡

ከጴጥሮስ ጋር ብቻውን መሆን እንደፈለገ ያህል እንደገና ቁጭ ብሎ ደብዳቤውን አነበበ፡፡ ተነሳና ጃኬቷ ከተሸፈነችበት የባውንደሪ ወረቀት አውጥቶ አየት፡፡ በልዩ ጥንቃቄ ታጥባ አዲስ ትመስላለች፡፡ ውሃ አረንጓዴ ቆዳ፣ ውሃ አረንጓዴ ሹራብ እጅጌ፣ ቡናማ የእንጨት ቁልፎች፡፡ ኮቱን አውልቆ ለበሳት፡፡ በሀሳቡ ጴጥሮስን

«አለቻ ጃኬት!» አለው

ጴጥሮስ ሲጀራውን እያቦነነ፣ ጥርስ-ድብት ፈገግታውን እያሳየ፣ ከርዳዳ ፀጉሩን በግራ እጁ ወደ ኋላ እያስተኛ፣ ትንንሽ አይኖቹ እንደ ከዋብ እያበሩ

«አለቻ ትርሲት ባራ ፈረደባት፣ እንጃ ወድታ መንሳቷን» አለው

ብርሃኑ ጴጥሮስን እያስታወሰና እየተዘወተ፣ እንደልማዱ እጆቹን ጃኬቷ ኪስ ውስጥ ከተተ፡፡ ቀኝ ኪሱ ውስጥ ጩቤ፡፡ ተዘግታ ኪስ ውስጥ የምትቀመጥ ጩቤ፡፡ እጀታዋ ላይ ሜን ሲጫን ድንገት ቃ ብሎ ስለቷ የሚወጣ ጩቤ፡፡ ብርሃኑ ባለፈው ዓመት ውስጥ እንዲህ ዓይነት ጩቤ ፍለጋ ያላዳረሰው ሱቅ አልነበረም፡፡ ጴጥሮስ ከየት አገኛት ይሆን? አይ ጴጥሮስ፣ «አለቻ ጩቤ»

ግራ ኪሱ ውስጥ የታጠፈ ወረቀት እንዳለ ይላል

«የትርሲትን ቁንጅና ከኔ የበለጥ አንተ ታውቀዋለህ፡፡ ነገር ግን የማታውቀው ነገር አለ፡፡ ይኸውም፣ አንተ ዳንስ ካስተማርካትና ጫማ፣ ትትቃ፣ ምናምን ከገዛህላት ወዲህ የሚያዩዋት ወንዶች ሁሉ ሊመኙዋት ጀምረዋል፡፡ በአንድ ማታ አምስት ስድስት ሰው «የፈለግሽውን እከፍላለሁ፡፡ አንድ ጊዜ እንሂድ» ሳይሏት አያመሽም ሲባል እሰማለሁ፡፡ እምቢ ማለቷን መንገርም አያስፈልገኝ፣ አንተው ታውቀዋለህ



«የበረሃ ወንዶች፣ ኢትዮጵያውያን ወንዶች በጠቅላላ፣ ውሸታሞች ናቸው፡፡ በግልፅና በትክክል ማድረግ fair play ለእነሱ እንግዳ ነገር ነው፡፡ ቃሉ 'ንኳ ባማርኛ የለም፡፡ አራት አምስት ሆነው አድፍጠው ይጠብቁህና በዱላ ያደበድቡሃል፡፡ ወይም ሩብ አስመስለው ዳንስ ቤት ውስጥ ጩቤ ይሰኩብሃል፡፡ ስለዚህ ተጠንቀቅ እያልኩህ

«በጉዳዩ ገባህበን ብለህ አትቀየመኝና፣ አንድ ምክር ልምከርህ ፍቀድልኝ፡፡ ለምን ሁልጊዜ ማሚት ቤት ታድራለህ? ለምን ራስህን የማያስፈልግ አደጋ ውስጥ መከተት ትፈልጋለህ? ሌሊት ተንተህ መጥተው ለአምር ቢደበድቡህስ? ቢገድሉህስ? ለምን ትርሲትን ቤትህ እየወሰድክ አታሳድራትም? ለኪራይ ችሎት ቢሆን እዛ አይጎዳችሁም፣ ይርቅባታል እንዳትል ቤትህ ለበረሃ በጣም ቅርብ ነው፡፡ ታዲያስ ጉዳዩ ትንሽ ነው፡፡ ይህን ያህል መጨነቅ የሚያስፈልገው አይደለም፣ ብለህ ካሰብክ በጣም ተሳስተሃል፡፡ ትርሲትን እንደልብህ ስለምታገኛት፣ የሚያዩዋትን ወንድ ምን ያህል እንደምታስጎመጀው ሊገባህ አይችልም፣ በእጅ ያለ ወርቅ መዳብ ነውና፣ እመነኝ ብዙ ወንድ በጣም በጣም ይመኙታል፡፡ ሲነግሩብህ የሰማ ሰው ነግሮኛል፡፡ የቆመብት ኑሮምና የፊብው ጅብ አይታመንም፡፡ ስለዚህ ተጠንቀቅ፡፡ ደልቱንም የመጠጥ ቤት ራብሽ ስታገድ ግላጋይነት እንዳትገባ፡፡

«ግን ጩቤዋን የምሰጥህ ለዚህ ብቻ አይደለም፡፡ ማስታወሻ እንድትሆንህ ብቻ ነው፡፡ እንዳንድ ከኪስህ አውጣትና ቃ አርገህ ክፈታት፡፡ እና አብረን በሲኒማ ስናያቸው የነበርነውን የሲካጎ የኒውዮርክ ዱርዬዎች በየጠባቡ መንገዱ እየተከተሉ ጩቤዎቻቸውን ቃ አርገው ከፍተው ሲዋጉ አስታውስ፡፡ እኔንም አስታውሰኝ፡፡ ግን ከጠንቶታልሽ ጋር ጠቅልለህ አታስታውሰኝ፡፡ ጉዊዶ ቤት ወይም ቤልትራሜ ቁጭ ብለን ስፓጌቲ እየበላን፣ ቢሉቱካ እየቆረጥን፣ ኪያንቲ እየጠጣን ኮሚክ ወሬ እያወራን ስንስቅ አስታውሰኝ፡፡ እኔ የማስታውስህ እንደዚሁ ነው፡፡

ያንተው

ጴ! ጴ! ጴ! ታስታውሰዋለህ»

ብርሃኑ ይህን ወረቀት እንደገና አነበበው፡፡ እግር ኪሱ ከተተው፡፡ ጩቤዋን እጀታውን ባውራ ጣቱ ተጫናት፡፡ አዲስ ስለቷ ቃ ብሎ ወጥቶ በመብራቱ አብለጨለጨ፡፡ «አለቻ ስለት!»

ብርሃኑ የጴጥሮስን ጃኬት እንደለበሰ፣ የጴጥሮስን ጩቤ እንደያዘ ለረጅም ጊዜ ስለ ጴጥሮስ ተከዘ፡፡ መቼ ይገኛ ይሆን? መቼ አብረው ጉዊዶ ቤት ወይም ቤልትራሜ ስፓጌቲ እየጠቀለሉ፣ ኪያንቲ

[illegible]

Meysor Bro
t.me/BooksandYou




# ምዕራፍ ሰባት

## ትርሲት

[illegible]

[illegible]



እንደ ወረደ
③ ከ 151-232 መጨረሻ
ሌቱም አይነጋልኝ
ከስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

## ምዕራፍ [illegible]

## ትርሲት

[illegible]



Meysor Bro
t.me/BooksandYou

ብርሃኑ ሥራ ሲይዝ አንድ ሶስት ቀሚስና ጫማ ገዛላት። ፀጉር መስሪያ፣ ትባት መግዣ እንደልቧ ይሰጣት ጀመር። እና ዱሮ መኖሯን እንኳን ዞር ብለው የማያዩ ወንዶች ሁሉ፣ አሁን ሲያይዋት፣ ረዥም ፀጉሯ ዞማ መሆኑን፣ ፈገግታዋ ልብ የሚያጠፋ መሆኑን አስተዋሉ። ስትራመድ የዳሌዋ ውዝዋዜ ምኞት እንደሚቀሰቅስ፣ የእግሮችዋ ማማር ጥቂቶቹ የሀበሻ ሴቶች ላይ ብቻ እንደሚታይ ተገነዘቡ። እና ይሻሟት ጀመር። ለብቻዋ መስታወት እያየች «እስቀያሚ ነኝ ለካ» ለማለት እስክትደርስ ድረስ ዘወር ብሎ የሚያያት ወንድ ታጣ እንደነበር እያስታወሰች፣ ያለፈው የእንግድነቷ ጊዜ ትዝ እያላት፣ ላይ ላዩን እየሳቀችላቸው ውስጥ ውስጡን ትንቃቸው ጀመር። እንውሰድሽ ብለው ሲለምኗት ይሄ ውስጣዊ ንቀት በግልፅ ፊቷ ላይ እየታየ «ባል አለኝ» ትላቸዋለች። ይህ የንቀት እምቢታ የባሰውን እንዲለምኗት ያደርጋቸዋል። የበለጠውን እንደሚመኟት ስታይ የባሰውን ትንቃቸዋለች። ብርሃኑን የበለጠውን ትወደዋለች።

ክንፈም በበኩሉ ለብሳ፣ አጊጣ፣ በብርሃኑ ፍቅር ተከባ ሲያያት ጊዜ አማረችው። ፈለጋት። በጣም ፈለጋት። ይኸው ሊያገኛት ሲሞክር ዓመት ሊሆነው ነው። ግን ሊያገኛት አልቻለም። ምክንያቱም አንደኛ፣ የሷና የብርሃኑ ፍቅር ማንንም ወንድ ሰማያስገባ አጥር ነው። ሁለተኛ፣ የብርሃኑና የትርሲት ፍቅር ባይኖርም እንኳ፣ ክንፈ የማሚት እሹሩሩ ባል ስለሆነ፣ ትርሲት ደሞ የማሚት እሻሻጭ ስለሆነች በምንም አኳኋን እሺ አትለውም። ሶስተኛ፣ ትርሲት ከብርሃኑ ሌላ ወንድ የምትፈልግ ቢሆን ኖሮ እንኳ ክንፈ ተስፋ አይኖረውም ነበር፣ ምክንያቱም የብርሃኑ ጓደኛ ነዋ። ከዚህም በላይ እኔና ጥላሁን አለን.. ሁለታችንም ትርሲትንና ብርሃኑን በጣም ስለምንወዳቸው እንደ ክንፈ ያለ ተንኮለኛ እባብ መሀላቸው ገብቶ ገነት ፍቅራቸውን ሊያበላሽባቸው ሲል ዝም ብለን አናየውም። እኔ እንቅፋት እሆንዋለሁ። የኔን ተንኮል አምልጦ አልፎ ከሄደ ለጥላሁን እነግረዋለሁ፣ «ፈረሰኛውን!» ብሎ ይደበድባዋል።

ክንፈ ይሄን ሁሉ ያውቃል። ግን ትርሲትን ለመተኛት መሞከሩን አልተወም። ደሞ አልፈርድበትም። በዚያ መልክ፣ በዚያ አለባበስ፣ በዚያ ጨዋታ፣ በዚያ ተንኮሉ ማንንም ሴት ቢፈልግ ያገኛል። ሽርሙጣ ሆነች፣ ፈት ሆነች፣ የሰው ሚስት ሆነች፣ ብቻ ይፈልጋት ያገኛታል። እንዲህ ሴትን እንደልቡ ሲያገኝ ሳይሰለቸው ይቀራል? እስካሁን ከፈለጋቸው ሴቶች ውስጥ ትርሲት ብቻ አስቸገረችው። ስለዚህ እንዴት ሊተዋት ይችላል?

በውነቱ አይደለም፣ ማንም ሰው ቢሆን እሱ ራሱ የብርሃኑ ጓደኛ ሆኖ፣ በዚህ ላይ የማሚት እሹሩሩ ባል ሆኖ፣ ከዚያም በላይ ትርሲት



በጭራሽ እንደማትፈልገው እያወቀ፣ ይህ ሁሉ ሆኖ ትርሲትን ሊተኛት ቢሞክር አላናግረውም ነበር፣ እንቀው እተፋበት ነበር። እደበድበው ነበር። በጣም ጉልበተኛ ከሆነም ለጥላሁን ነግሬ አስደበድበው ነበር። ወይም ለብርሃኑ ለራሱ እነግርበት ነበር። ግን ምን ይሆናል፣ ሰውየው ክንፈ ስለሆነ ትርሲትን ለማግኘት በመሞከሩ አልንቀውም፣ አደንቀዋለሁ ነጂ። «ክንፈ» ማለት ምን ማለት ነው? ለብዙዎቹ «ክንፈ» ማለት አስቲኝ የሆነ መልክ መልካም አጭበርባሪ ሰካራም ወጣት ነው። ለኔ ግን «ክንፈ» ከሰዎች ሕግ በላይ፣ ከእግዚአብሔር ሕግ ውጪ የሚኖር የነፃነት ነብይ ማለት ነው። ወይስ «ተወዳጁ ሰይጣን» ልበለው?

ትርሲት በጣም ቆንጆ ልጅ ናት። መልክ ብቻ ሳይሆን፣ ግድል የሚያደርግ የደስ ደስ አላት። የድሮ ሰዎች «የደም ግቦ» የሚሏት አይነት ናት። ታዲያ ክንፈ ቢፈልጋት ይፈረድበታል? የብርሃኑ ጓደኛ ሆኖ የብርሃኑን ሚስት ስለፈለገ ይፈረድበታል? ክንፈኮ ጓደኝነትን ከሙያ አይቆጥረውም። የማሚት «ባል» ሆኖ የማሚትን እሻሻጭ ስለፈለገ ይፈረድበታል? ክንፈኮ «ባልነትን» ከቁም ነገር አይቆጥረውም። ሰውንም ከጉዳይ አይቆጥርም። ሰው ምን ዋጋ አለው? እንዲያውስ በክንፈ አይን ምን ዋጋ ያለው ነገር አለ? ምናልባት እምስ?

አንድ ማታ ቁርስ ስንበላ ክንፈ የተገመጠ ዳቦ የያዘ እጁን ወደ ብርሃኑ መኝታ በኩል እያመለከተ «እሱ ወዴ?» አለን። ብርሃኑንና ትርሲትን ነው። «አዎን» ሻይና ዳቦውን እንደያዘ ወደነሱ ለመሄድ ተነሳ

«ቁጭ በል» አልኩት። ቁጭ አለና በጥያቄ አይን አየኝ

«አሁን ሰው አያስፈልጋቸውም» አልኩት

ፊቱ ላይ ከዚህ ቀደም አይቼው የማላውቀው የቅናት ጥላ ሲያርፍ ታየኝ። በጣም በመገረም

«ቀናሁ እንዴትለኝ ብቻ» አልኩት

ለመሳቅ እየሞከረ፣ ግን እያቃተው፣ በተለወጠ ድምፅ «እኔም ራቤ ገርሞኛል» አለ

«ማሚት አይደለችምኮ»

«በማሚት መቅናት ከተውኩ ዘመን የለኝም»

«ታዲያ ትርሲትን ብርሃኑ ተኛት ብለህ ትቀናለህ?»

«ፈልጌ ነው 'ንጂ ምቀናው?»

«ወይ ማሳዘንህ!» አልኩት

«ለምን?»

«ፍቅር ይዞህላ»

«አንተ ትቀልዳለህ?!»

«ለምን አልቀልድም? አንተ ሁልጊዜ በሰው እየሳቅክ፣ አንዳንዴ 'ንኳ ሰው ሳይስቅብህ ነው?»

«አሺ ሳቅ፡፡ እኔም ተራዬን እስቅብሀ የለ?» ብሉ በቆንጆ ፍንጭት ጥርሱ ሳቅ አለ፡፡ ብቻ እኔው የፈጠርኩት እንደሆን እንጃ፣ መልከ መልካም ፊቱ ላይ ተንኮል ሲያደፍጥ የታየኝ መሰለኝ፡፡ ራሴኑ «ተዘጋጅ» አልኩት፡፡ ግን ካንፈ በየት በኩል እንደሚመጣ ማወቅ አይቻልም፡፡ ስለዚህ መዘጋጀት ዋጋ የለውም፡፡ መጠንቀቅ፣ ነቃ ብሎ መጠበቅ ነው 'ሚሻለው፡፡ ቢስቅብኝ 'ንኳ ግድ የለም፣ እኔም ተራዬን እስቅበታሁ፡፡ እኔ 'ምጠነቀቀው ሳላውቅ ስቆብኝ እንዳያልፍ ነው፡፡ ከንፈ ሊላ ዳቦ ሊበላ ማርማላታ እየቀባ

«ምክንያቱስ ፍቅር ይዞሀል 'ምትለኝ?» አለኝ

«ማሚት ያንተው ነች፡፡ ግን ስንቱ ጎረምሳ እየተቀባበለ ሲደሰትባት ቅናት አይሰማህም፡፡ ቀናተኛ ሰው አይደለህም ማለት ነው፡፡ ትርሲት ግን ያንተ አይደለችም፡፡ እንዲያውም አንድም ቀን አቅምሳህ ኢታውቅም፡፡ ግን ይኸው ልትተኛት ስትሞክር አመት ሊሆንህ ነው፡፡ ታዲያ ተኝተሃት የማታውቀውን ሴት ባሏ ለምን ተኛት ብለህ ስትቀና ፍቅር አልያዘኝም ትላለህ?» አልኩት፡፡

እሱ ደሞ ከተኮሰኩበት ጥይቶች የቷን አነጣጥሮ እንደሚመልስብኝ በቀላሉ እንዳላውቅበት ተራውን ቃላት አበዛብኝ

«አሁን ያልከው እውነት ሊሆን ይችላል፣ ማለት ከቀናሁ ፍቅር ቢይዘኝ ነው፡፡ ግን ይህን ለመካድ አይቻልም 'ንዴ? አንደኛ፣ ፍቅር እና ቅናት ሁልጊዜ አብረው ናቸው? ማነው ፍቅርና ቅናት ተለያይተው አያውቁም ያለህ? ፍቅር ያለ ቅናት ሲኖር አይተናል፡፡ ሩቅ ሳንሄድ ትርሲትና ብርሃኑን ውሰድ፡፡ ፍቅራቸውን ማንም አይክድም፡፡ ደግሞ ቅናት እንደሌለባቸው ታውቃለህ፡፡ ፍቅር ያለ ቅናት ከኖረ ቅናት ያለ ፍቅር ሊኖር አይችልም ወይ? ነው 'ምልህ፡፡ ማለት የትርሲት ፍቅር ሳይዘኝ እንዲሁ ልቀናባት አልችልም ወይ? አታምንም 'ንጂ ማሚትን በጣም ነው 'ምወዳት፡፡ በመቶ ትርሲቶች አልለውጣትም፡፡

«ሁለተኛ፣ እስካሁን ስታይ ስትመለከት፣ አንድ ወንድ የሚቀናው ቀምሷት የጣፈጠችውን ሴት ሌላ ወንድ ሲቀምስበት ነው እንጂ. . . .»

ይኸዋ! «ተኝተሀት የማታውቀውን ሴት» የሚለው ጥያቄ ነጥሮ ተመለሰ፡፡ ግን ይህን የሚል የጥይት ጨዋታው ላይ ለማሸነፍ ነው፣ ወይስ በእውነቱ ተኝቷት ይሆን? ይህ ሀሳብ ባንጎሌ እንደሚመጣ አውቆ ነው እቺን አረፍተ ነገር ጣል ያረገብኝ፡፡ ግን ለጨዋታ ብቻ



ነው ወይስ. . . እሸንፈ ይኸ ውኸ!

«አንድ ወንድ እንዲሁ በአይኑ የወደዳትን ሴት ባሏ ስለተኛት አይቀናም፡፡ ስለዚህ ቅድም ፊቴ ላይ ያየኸውና አሁን ድምፄ ውስጥ 'ምትሰማው ስሜት ቅናት አይደለም ማለት ነው. . .» (እቺ 'ንኳ ማሸነቱን እንዳላወቀ ለማስመሰል የታቀደች ናት). . . መቅናቴ ካልሆነ 'ንግዲህ ምንድነው? እኔ በበኩሌ መነጫጀቴ ነው እላለሁ»

«ምን ማለትህ ነው?»

«አየህ፣ ቅናት ገንዘቤ የሆነ እምስ እንዴት ይወሰድብኛል? ብሎ የሚበሳጭ ክፉ ስሜት ነው፡፡ መነጫጀት ግን «ወይኔ! ያን እምስ ለኔ ባረገው!» ብሎ የሚመኝ ቂል ስሜት ነው፡፡ ገባህ?»

ትኩር ብዬ እየሁት «ብድተሀታል?» አልኩት

«ማንን?»

ዝም ብዬ እየሁት፡፡ ፊቴ ላይ ምን እንዳነበበ እንጃ፣ ከት ብሎ እየሳቀ

«ፍቅር የያዘሀስ አንተ» አለኝ፡፡ ምን እንደምመልስለት ጨንቆኝ ስታገል

«ቁርስ!. . . ዳቦ!. . . ቁርስ!. . . ስኳር» እሉ ትርሲትና ብርሃኑ ዝገሉኝ «መጣሁ ብሉ!» አልኳቸው፡፡

ትርሲት ጥቁር ውስጥ ልብስ እንደለበሰች እየሮጠች መጥታ «ውይ! እንዴት አደሩ ጋሼ ከንፍዬ» ብላ ጨብጣው እልጋዬ ውስጥ ስትገባ የከንፈ አይኖች ዳሌዋ ላይ ተንከራተቱ፣ ጠወለጉ፡፡ ብርሃኑ ከእሳቶቹ የወረሰውን ረዥም ለስላሳ ፀጉር እያበጠረ መጣ፡፡

እራታችንንም እየተቃለድን፣ ዳቦውን እየተቀማማን፣ እየተሰደደብን፣ እየተጫጫህን ቁርስ ስናበቃ፣ ብርሃኑ ከጠረጴዛው ላይ ጥቁር ደብተሩን አምጥቶ ሰጠኝ፣ አየሁት፡፡

«አንብብልን» አለኝ

ካንድ አምስት ቀን በፊት እራት እንደበላን ሲኒማ እንሂድ ብሉኝ «አንዲት አጭር ታሪክ መጻፍ ጀምሬያለሁ፡፡ እሷን ሳልጨርስ ሲኒማም በረሀም አልሄድም» ብዬው ነበር፡፡

«ገና አልጨረስኩትም» አልኩት

«ውሸታም! አልቋል አንብቤዋለሁ፡፡ አንብብልን» አለኝ

ባይ ጊዜ ሶስቱም ሊያስነብቡኝ ቆርጠዋል፡፡ ስለዚህ ሆነታ ሳላበዛ ማንበቤን ጀመርኩ፡፡ ግማሽ ሰዓት ያህል ሳነብ በፀጥታ ቁጭ ብለው ሰሙኝ፡፡

ታሪኩ ስለ አንዲት ሸርሙጣ ነው። አንድ ወሬት በጣም ገንዘብ ቸግሯታል። በዚህ ወሬት ውስጥ ታረግዛለች። ድሮውንም ጤናዋ እጅግም ነው። ከገንዘብ ችግርና ከእርግዝና ጋር ስትታገል ይኸ ጤናዋ እየተበላሸ ይሄዳል። ድካም ይሰማታል። ቀኑን ሙሉ ያቅለሸልሻታል እንደምንም ብላ ትንሽ ገንዘብ አጠራቅማ ሀኪም ጋር ስትሄድ ልዩ ልዩ አይነት መርፌ ቪታሚን እና ጥሩ ጥሩ ምግብና ብዙ እንቅልፍ ያዝላታል። ሁኔታዎች እንዲህ ሲሄዱ የሚፈልጋት ወንድ እያነሰ ይሄዳል። የቤቷ ባለቤት «ኪራይ ኪራይ» እያለ በቀን አሥር ጊዜ ይጨቀጭቃታል። ገንዘብ ከየት ታገኝ? አንድ ማታ አንዱ አዳር ጠየቃት። ዱሮ ከአሥር ብር በታች እሺ አትልም ነበር። ዛሬ ግን በአራት ብር ካላሳደርሺኝ ይቅር ይላታል። እሺ አለችው።

ሰውየው የማይጠግብ አይነት ኖሮ ሌሊቱን ሙሉ ፋታ አልሰጣትም። ሊነጋጋ ሲል በጣም አቅለሸለሻት፤ ለማስታወክ ተነሳች። አስታወከት። እየተንገዳገደች ሄዳ ስትመለስ ሰውዬው በደስታ ጠግቦ ተኝቶ ያንኮራፋል። የሰውየውን ቦርሳ ከፍታ ብታይ አራት መቶ ብር አለው። ሶስት መቶውን ወስዳ ፍራሽ ሥር ደበቀች። ረሀቡ በሽታው ችግሩ የሀሳቧን ኃይል ቀንሶታል። ሰውየው ጠዋት ተነስቶ አራት ብሩን ሊከፍላት ቦርሳውን ሲከፍት እንደሰረቀችው ያውቃል። በጥፊ አላትና ስትወድቅ ወንበሩ ሆዷን ይመታታል። ሰውዬው ገንዘቡን ፈላልጎ ፍራሽ ሥር ሲያገኝ የተዋዋሉትን አራት ብር 'ንኳ ሳይከፍላት እንደው ተፍቶባት ይሄዳል።

ከጥፊው ይበልጥ ወንበሩ ሆዷን የመታት አመማት። ከሆድ ማመሙ የባሰ ግን ስለተፋባት ትልቅ ውርደት ተሰማት።

«አራት ብሬስ? እህ? አራት ብሬስ?» እያለች ከት ብላ መሳቅ ጀመረች።

በነጋታው የአዲስ አበባ ሰዎች ጋዜጣቸው ውስጥ አንዲት ስሟ ያልታወቀ ነብሰጡር ከራስ መኮንን ድልድይ ላይ ዘላ ወድቃ እንደሞተች አነበቡ።

ታሪኩን አንብቤ ጨርሼ ቀጥ ስል ሶስቱም ዝም ብለው ያዩኛል። ትርሲት ጉንጯ ላይ እንባው በፀጥታ ይወርዳል። ብርሃኑ እቅፍ አደረጋት። ሲያቅፋት ጊዜ ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች። ምን እንደማደርግ ጨንቆኝ ደብተሩን ይዤ ቁጭ እንዳልኩ ቀረሁ። ክንፈን ሳየው በእጅ ምልክት ልብስህን ልበስ አለኝ። ቶሎ ደብተሬን አስቀምጬ ፒጃማዬን አውልቄ ልብሴን ለበስኩና ብርሃኑን በጃችን ደህና ዋል ብለነው ከቤት ወጥተን ሄድን።

ባቡር መንገድ ስንደርስ ክንፈ «አይዞህ አትስጋ አሁን አቅፎ ሲስማት ሀዘኗን ትረሳለች» አለኝ



«አውቃለሁ።»

አንድ ቃል ሳንነጋገር ኪንግጆርጅ ባር ሄደን ቁጭ አልን። ክንፈ ሁለት ቢራ አዘዘ። ከቢራው ጋር ከመጣው አቾሎኒ አንዷን ፍሬ አፉ ውስጥ ወርውሮ ከተተና፣ ቢራውን እንዴ ተጎንጭቶ ሲጋራ አቀጣጠለ። የሲጃራ ቀለበት ሳይሰራ

«ከሁላችንም አንተ ትሻላለህ» አለኝ። ማንንም ሰው እንዲህ ሲል ሰምቼ አላውቅም አየሁት።

«ግሩም ትጽፋለህ» አለኝ።

«ህ!» አልኩት «እሱን ተወው!» እንደማለት

«እውነቴን ነው። ቅድም ካነበብክልን አጭር ታሪክ የሚበልጥ አጭር ታሪክ አንብቤ አላውቅም»

«እስቲ ዛሬ 'ንኳ ቀልድ ውሸቱን ተወው። እውነት ምን ይመስልሀል?» አልኩት

«አልኩህ'ኮ። በጣም ጥሩ ነው። የትርሲት እንባ ይመስክር። ግን ሳቅ ይጎለዋል»

«ሳቅ?»

«አዎን ሳቅ። የሰው ልጅ ሁልጊዜ እንባ ውስጥ እንደዋኘ ነው። ነገር ግን በየጊዜው ከዋናው ወጣ እያለ ተጋድሞ የሳቅን ፀሐይ እንደሚሞቅ ደግሞ አትርሳ»

ዝም ብዬ አየሁት። እውነቱን ነው።

«ሌላስ?» አልኩት

«እውነትን አታብዛ»

«ምን?»

«ሕይወት ውስጥ እውነት ብቻውን አይገኝም። ህይወት እንደ ቡና በወተት ነው። ወተቱ እውነት ቡናው ውሸት ይሁን። ግን ያለ ልዩነት ብንነሳችን ውስጥ ይኑር እንጂ. ሲኒው ውስጥ ባንድ በኩል ቡና በሌላው ወተት የለም። ሲኒው ውስጥ ያለው ቡና በወተት ነው። ሕይወትም ውስጥ በቀኝ በኩል እውነት በግራ በኩል ውሸት አይገኝም። ሕይወት ውስጥ የምታገኘው የእውነትና የውሸት ቅልቅል ነው። ለምሳሌ እናና ማሚትን ውሰድ። አንዳንዴ እያለቀሰች «እወድሃለሁ፣ እወድሃለሁ» ትለኛለች። እውነቷን ነው? ከሆነ ለምን እኔ እያለሁላት በቀን በቀን ጎረምሳ ትቀያይራለች? ውሸቷን ነው? ከሆነ ለምን ዘወን አመት ሙሉ አብራኝ ታድራለች? እውነቷን አይደለም። ውሸቷንም አይደለም። እውነትና ውሸቷን ነው። ገባህ?»

«አዎን ቀጥል» አልኩት

«ታሪክህ ስንት ገፅ አለው?»

«ሀያ ሰባት»

«ሀያ ሰባት ገፅ ሙሉ ስለ አንዲት ሸርሙጣ ስትፅፍ እምስ፣ ቂላ፣ መባዳት እና ይህን የመሳሰሉትን ቃላት በጭራሽ አንዴም አልተጠቀምክባቸውም:: ስለ አንድ ገበሬ ሀያ ሰባት ገፅ ስትፅፍ ሞፈር፣ ቀምበር፣ ጭቃ፣ አፈር የሚሉትን ቃላት ፈጽመህ እንደመሸሽ ያህል ነው:: ማለት ቃላትን ከመሸሽ የተነሳ ውሸታም መሆን ነው:: እንደ ፈረንጆቹ ደራሲያን ፈሪ መሆን ነው:: ምን ፈሪ ብቻ:: ግብዝ መሆን ነው:: እሱን ሙተው አለብህ»

«ቀጥል ቀጥል» አልኩት

ሳቅ እያለ «ምን እቀጥላለሁ? በቃ 'ኮ:: ትልቅ ደራሲ መሆን ትችላለህ:: ግን ሀዘንና ሳቅን መደባለቅ አትርሳ:: እውነትንና ውሸትን ለማዋሀድ ሞክር:: ቃላትን አትፍራ:: አለዚያ የምትፅፈው ከሕይወት ይርቃል፣ ማለት ውሸት ይሆናል»

«ምን ነካህ?» አልኩት

«አልኩህ'ኮ:: ከሁላችንም አንተ ትሻላለህ:: አትሳቅ:: እኔ የምሬን ነው:: እኛ ስካር ስናባርር፣ የአንድ ደቂቃ ደስታ ስናሳድድ፣ ላንድ ደቂቃ እምስ ስንሻማ፣ አንተ ይህን ከንቱ ሀብት ንቀህ ዘላለማዊውን እውነት ለመንካት ትንጠራራለህ:: እውነቱ ቀልድና ምር መሀል ነው»

እየሳቅኩ «የማገኘው ይመስልሀል?» አልኩት

«ብታገኘው ባታገኘው ልዩነቱ ትንሽ ነው:: እንዲያውም ይሄ አንተ የምትፈልገው እውነት አይኖርም ይሆናል:: ቢኖርም ባይኖርም አንተ ስትፈልገው፣ ይህ መፈለግ ለኑሮህ አቅጣጫ ወይም ትርጉም ይሰጠዋል»

«አንተ ታዲያ ለምን እንደኔ አትፈልግም?»

«እፈልጋለሁ:: ግን የኔ እውነት የሚገኘው ማሚት ጭኖች መሀል ነው»

«አሁን አሁን ከሁላችንም ትሻላለህ ስትለኝ አልነበረም?»

«አስታውስ፣ እሱ እውነትም ውሸትም ነው»

ሁለታችንም በሀይል ሳቅን::

ከዚያ ቀን ወዲህ ከንፈ. ስለምንም ነገር ብጠይቀው «ለመጽሀፍህ ነው?» እያለ እየሳቀ በሰፊው ይነግረኛል:: ያስረዳኝ፣ ይገልፅልኝ ጀመር:: በመጨረሻ «ታዲያ አትርሳ እ? አሁን የነገርኩህ ሁሉ እውነትም ውሸትም ነው» ይለኝና ወሬ እንለውጣለን::



አንድ ቀን. . . «ባገኘሽኝ ቀጥር ስለኔና ስለ ማሚት ከምትጠይቀኝ፣ አንድ ቀን ጨክነህ ኪንግ ጆርጅ ባር ውሰደኝና፣ ባንተ ኪሳራ ውስኪ እየቀመቀምኩ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ልንገርህ» አለኝ

«አሁኑኑ እንሂድ» አልኩት

«እንሂድ»

# ምዕራፍ ሰባት

## ማሚት

«እንኳን ሞት እርጅና አለ»
/አለ አንበሳ/

ክንፈ ለመጀመሪያ ጊዜ ማሚት እሹሩሩ ቤት ሲገባ በሩ አጠገብ እንደቆመ ቀረ:: ማሚት ነጭ ጉትቻ እርጋ ቀይ ሹራብና ነጭ ጉርድ ለብሳ ባንኮኒው ዳር ብቻዋን ቆማለች:: የጡቶቿ መቾል፣ የወገቧ መቅጠን፣ የዳሌዋ መወፈር፣ ቅላቷ፣ የአይኖቿ ንጣትና መጉላት፣ የአፏ ዕጌረዳነት፣ እንደሷ ያለች ሴት አይቶ አያውቅም:: እሷም አይኗን እሱ ላይ እንደተከለች ቀረች::

በኋላ ጓደኞቹ ወደ ሌላ ቤት ለመሄድ ሲነሱ እሱ በአይኑ የማሚትን ፊት «ልሂድ ወይ?» ብሎ ጠየቀ:: የተኳሉ ንፁህ አይኖቿ «አትሂድ» አሉት:: ቀረ:: ልክ ስድስት ሰዓት ሲሆን የዳንስ ቤቱ በር ተዘጋ::

ክንፈ ማሚትን ወደ መኝታ ቤቷ ተከተላት:: በሩን ዘጋች:: ኮቱን ተቀብላ ወንበር ላይ ሰቀለችው:: ሰፊው አልጋ ላይ ቁጭ አለች:: አየችው:: አጠገቧ ቁጭ አለና መሬት መሬቱን ያይ ጀመር:: ያኔ ገና አስራ ስምንት ዓመቱ ነበር:: እጁ ጉልበቱ ላይ እንዳለ እጇን አሳረፈችበት:: ድንገት ዘወር ብሎ ውብ አፏን እስማለሁ ሲል ጥርሷን በጥርሱ ገጨ:: አፈረ:: እሷ ቀስ አርጋ አንገቱን በለስላሳ እጇ እየደባበሰች ሳመችው:: ጉንጮቹን በእጆቿ ይዛ አይን አይኑን እያየች «ከነፍንጭት ጥርስህ እንዴት ታምራለህ!» አለችው:: የመጀመሪያ ቃላቷ ድምጿ ከክንፈሮ ይበልጥ ምኞቱን ቀሰቀሰበት፣ ወፈር ያለ ለስላሳ ድምፅ:: ቶሎ ብሎ ራሱን ደረቷ ላይ ደፋ::

በጉሩን እያሻሸች «ምንድን ነው የኔ ቆንጆ?» አለችው:: ጆሮው ጉሮሮዋ ጋ ስለነበረ ወፍራም ድምጿ እንደ አንድ ትልቅ የምኞት ማጉረምረም ሆኖ ሆዱ ውስጥ ተርበተበተ:: ራሱን ጨርሶ ደረቷ ውስጥ እንደመቅበር አለ::

አሁንም እያሻሸችው «ምን ሆንክብኝ?» አለችው

«ፈራሁ» አላት በትንሽ ድምጽ፣ በፈራ ድምጽ

«የመጀመሪያ ጊዜህ ነው?» አለችው፣ ራሱን ከደረቷ ላይ አንስታ ፊቱን በለስላሳ እጇ እያሻሸች፣ አይን አይኑን በሚስጥራዊ አይኖቿ እያየች «አትፍራ:: ምንም የለው አይዞህ» አለችው፣ የሸሚዙን ቁልፍ



እየፈታች

«ልብሳችንን እናውልቅና አልጋ ውስጥ ስንገባ ፍርሀቱ ያተውሀል አይዞህ» አለችው::

ዝም አላት::

«መብራቱን ላጥፋልህ?»

«አዎን»

«ይኸው:: በል እቀፈኝ»

በጨለማው እየሳመች ልብሱን አስወለቀችውና አልጋ ውስጥ ገቡ:: እሷ ልብሷን መቼ እንዳወለቀች እንጃ:: ራቁታቸውን በለስላሳ ገላዋ ስታቅፈው ጊዜ በምኞትና በደስታ ሰከረ:: ላብና ሽቶ የተቀላቀለበት ጠረኗ አሳበደው:: ጉንጯን፣ አንገቷን፣ ጡቷን፣ ሆዷን፣ ጆሮዋን፣ ጭኗን ሳይቀር ይስማት ጀመር:: እሷም ያልሳመችው ቦታ የለም::

እጆቿ ደሞ! አቤት እጆቿ ሲነካኩት! ያለበትን ረሳ:: መቼ ጭኗን ከፍታ መንግሥተ ሰማያት እንዳስገባችው በጭራሽ አላወቀም:: በኋላ ደረቷን እንተርሳው ፀጉሩን እየደባበሰች በለስላሳ ድምጿ

«አየኸው አይደለም? በጭራሽ አያስፈራም» አለችው

«በጭራሽ! መንግሥተ ሰማያት ነው» አላት «ግን አንቺ ስለሆንሽ ነው 'ንጂ. . .» በረፍተ ነገሩን ለመጨረስ ያህል በኃይል ተጠጋትና ዝም አለ::

«እውነት የመጀመሪያ ጊዜህ ነው?» አለችው

«አዎን:: ምነው?»

«አሥር አመት የኖሩብት 'ንኳ እንዳንተ አይችሉበትም:: ሳመኝ እስቲ፣ አፍህ እንዴት ደስ ይላል!»

እንደገና ጀመሩ

ሌሊቱን አደሩበት

ሟት ቁርሱን አመጣችለትና ውብ ፈገግታዋን እያጠጣችው

«ብላ የኔ ፍንጭት ሰይጣን» አለችው

እሱም እየሳቀ «ምክንያቱስ ሰይጣን 'ምባልበት?» አላት

«እኔ አውቅ. . .»

. . .ክንፈ ታሪኩን ሲነግረኝ «እውነት ስትበዳ የመጀመሪያ ጊዜህ ነበር?» አልኩት

«ምን መሆንህ ነው?» አለኝ «አሥራ ስምንት አመቴ ነበር እያልኩህ! የሰው ልጅ አሥራ ስምንት ዓመት እስኪሆነው ሳይበዳ ይቆያል? ማሚትን ከመብዳቴ በፊት ቢያንስ ቢያንስ እንዲት የጎረቤት ሚስት፣

አንድ አስር ሽርሙጣ፣ አንድ አምስት ገረድ እና አንድ ሶስት እህያ አዳርሻለሁ»

«እህያ?»

«አዎን። እህያ በድቼ አላውቅም ልትለኝ እንዳይሆን»

«በድቼ አላውቅምና»

«ትቀልዳለህ? እህያ ሳትበዳ እንዴት ደራሲ ለመሆን ታስባለህ? የሚሆን አይደለም! እየው እየው፣ ጥያቄው አይንህ ውስጥ ሲፈጠር ይታየኛል። ያህያ እምስ ምን ምን ይላል? ልትለኝ ነው አይደለም?»

«አንተ ደግሞ ያህያ እምስ ያህያ እምስ ይላል፣ ልትለኝ ነው?»

«አዎን»

«እሺ አህያዋን እንዴት ነው 'ምትበዳት?»

«ቂላህን እምሷ ውስጥ ትከተዋለህ»

«ችጋራም! እንዴት ትከተዋለህ?»

«አቱመህ ነዋ! እሺ 'ሺ አትቆጣ። መጠየቅ ያለብህን ጥያቄዎች በሙሉ ስለማውቃቸው ሳትጠይቅ እመልስልሃለሁ። እየህ ነገሩ Scientific ነው። መጀመሪያ አህያህን መምረጥ አለብህ። የከበደች ወይም የምታጠባ ከሆነች አታስጠጋህም። ምርጫ ካለህ ብልቷ አበጥ ያለውን መምረጥ ደግ ነው። መጀመሪያ ከኋላ አትጠጋት። አለዚያ በእርግጫ ቆለጥህን ታፈርጠዋለች። ከጎን ተጠግተህት ትንሽ ስበካት «እንዴት ነሽ የኔ ቆንጆ? አይ ስታምሪ! ብልትሽ ግልብጥ ብሎ ሲያስጎመጅ! ምነው ጭራሽን ባደረገኝ!» እያልክ ይህንና ይህን የመሰለ romantic ንግግር እያሰማሀት፣ ቀስ ብለህ በእጅህ ብልቷን ነካካት። ሳር መጋጥና እምቧዩ እምቧዩ! ማለት ትተዋለች። ንግግርህን ቀጥል «ጅብ ቢያገኝሽ በጭራሽ መፍራት የለብሽም። ይህን ብልትሽን አይቶ ሆዱን ይረሳል። ምኞቱ ይቀሰቀሳል! አይ ብልት!! ይህን ጊዜ ጭራዋን ብድግ ታደርጋለች።

«ባህያ ቋንቋ ከፍታ መስጠቷ ነው። አሁን ነው ወደ ኋላዋ መሄድ። ቀስ አርገህ ትከትባታለህ፣ ግን እዚህ ላይ መጠንቀቅ አለብህ። ቁላህን ገባ ወጣ አታድርግ፣ ልክ እለሌው እንደሚያደርገው ከተህ እዚያው ተወው። ይመዝምዘው። አለዚያ ግራ ይገባትና እህያ አለመሆንህን አስታውሳ ደንግጣ ትፈረጥጣለች። ገባህ? እረስቼ፣ መጠንቀቅ ያለብህ ዋና ነገር አለ። ከሁሉ በፊት አስቀድመህ እዚያ ስፈር ያለውን ወንድ እህያ በሙሉ ማባረር አለብህ። አለዚያ አገር ጤና ብለህ ስትከት፣ ከኋላህ መጥቶ እንዴ በርግጫ ይልህና እሱ ይከትባታል»

«ደርሶብህ ያውቃል?»

«አንድ ቀን እህዮቹን በሙሉ አባረርኳቸው። እንዱ ቁስላም ከሲታ



መንቀሳቀስ እንኳ የማይችል፣ ሊሞት እንድ ሐሙስ የቀረው ግጣባ ነበር። ለሴት እትም የለውም ብዬ ንቄ ተውኩት። ታዲያ ከትቼ ብሁ ቆይቼ፣ ልክ ማፍሰስ ስጀምር፣ መጥቶ እንዴ በርግጫ ቢለኝ ወደቅኩ። እንዴ በርግጫ ሆዱን አልኩት። ●ደቀ። ተናደድኩና ብድግ ብዬ ከዚያ በኋላ እህያ መብዳት ተውኩ እልሀለሁ። እዚያው ሞተ።

«ሳንዲት እህያ ውሽማዬ ፍቅር ስል፣ የሰማንያ ባልዋን በእርግጫ ብዬ የገደልኩ ሰው በዓለም ታሪክ ውስጥ እኔ ብቻ ሳልሆን እቀራለሁ? ምን ይመስልሀል?»

«እሱን ተወውና ወደ ታሪካችን እንመለስ። ማሚትን ለምን ድንግል ነኝ አልካት?»

«እንድትወደኝ ነዋ። ሽርሙጦች ድንግልህን ሲወስዱብህ በጣም ነው 'ሚወዱህ፣ የፈለግከውን ያረጉልሀል። ለአንድ ሶስት ወር ያህል ማእታቸው ነህ። ይኸው እስከ ዛሬ ድንግሌን ስድስት ወይም ሰባት ጊዜ አስረክቤያለሁ»

«ይህ ሳይኮሎጂህ ማሚት ላይ ሰራ?»

«ትጠይቃለህ? ፀሐይ ወይ ንፋስ ሳይነካኝ፣ እንደ ሙሽራ ካልጋ ሳልወርድ፣ ቀንም ሌትም ማሚትዬ ጭኖች መሀል ሳለከልክ ሁለት ወር ሙሉ ኖርኩ። አንድ ቀን «አሁንስ ገመምተኛ መሰልክ። ወጣ ብለህ ተንሸራሸረህ ና፣ ትንሽ ንፋስ ይምታህ» አለችኝ። ውነትሽን ነው አልኳት። ታዲያ ልወጣ ብል፣ በየት በኩል? ወገቤ እልቆ እንደ ክዘራ ለሁለት ታጥፌ እንደ ጃጀ ሽማግሌ እጅና እግሬ ይንቀጠቀጣል። እንደ ሽባ ዱላ እየተሞረከዝኩ መሄድና እሥር እርምጃ ተራምጄ አንድ ደቂቃ ማረፍ ግድ ሆነብኝ።

ማሚት በበኩሏ እየተስማማት ጭኗ እየለሰለሰ፣ ቂጧ እየወፈረ፣ እምሷ እየጣፈጠ ሄደ። አቤት ያኔ ልብሷን አስወልቀህ ብታያት! ከማማሯ የተነሳ ተንበርክኬ ጉልበቷን የምስምበት ጊዜ ነበር»

«ጉልበቷን ብቻ?»

«ጭኗንም»

«ጭኗን ብቻ?»

«ሌላው 'ንግዲህ እንኳን ለልጆች ለንስሀ አባት አይነገርም»

«እሺ ቀጥል»

የመጀመሪያው ሁለት ወር ፍቅር ብቻ ነበር። ጧት እንደተቃቀፉ ይነቃሉ። ራሱን ደረቷ ላይ ደፍቶ ጠረኗን በሀይል ወደ ውስጥ እየተነፈሰ፣ በሽታዋ እየሰከረ፣ የሚሞቅ ለስላሳ ገላዋ ላይ እጁን ያንሸራሽራል።

አንሶላና ብርድልብሱን ወደዚያ ይገልጥና ቁጭ ይላል። ራቁቷን እንደተጋደመች ዝም ብሎ ያያታል። አይኖቹ ውብ ገላዋ ላይ ይንከራተታሉ

«ምን ሆንክብኝ?» ትለዋለች

«ጭንቅ አለኝ»

«ምነው?»

ፊትዋን በእጁ እየነካ «ብርሃን ፊትሽን፣ አበባ ከንፈርሽን እንዳልስም ገላሽ ሊቀርብኝ ሆነ» በሁለት እጆቹ ጡቶቿን እየደባበሰ «ሞገት ፍሬ ጡቶችሽን እንዳልስም ወገብሽ፣ ዳሌሽ፣ ጭኖችሽ ሊቀሩብኝ ሆነ። ጭንሽን እንዳልስም ሌላው ሁሉ ይቀርብኛል። ምን ይሻለኛል?»

በለስላሳ እጆቿ ፊቱን እያሻሸች፣ ትንፋሶቿን እያስተናች «ሁሉም ያንተ ነው አይቀርብህም፣ ይቆይልህ 'ንጂ። አይኖችህ እንዲህ ሲያዩኝ እንዴት ደስ ይላሉ?! ሁለመናዬን በልዩ ብርሀን፣ በልዩ ሙቀት የሚሸፍኑኝ ይመስለኛል» ትለውና እጆቿን ትዘረጋለች። እቅፍ አድርጋ ወፍራም ለስላሳ ምኞት በሚንቀጠቀጥበት ድምጿ ጆሮው ውስጥ . . .

«ወይንህ በድተሽኝ እሳት ለቀቅክብኝ» ስትለው፣ ትንፋሹ ጉሮሮውን አንቆ ያደርገዋል

«ላብርድልሽ?»

«እኔም ላብርድልህ?»

«ሺህ ጊዜ ብትሰጪኝም አይበርድልኝ»

«ሺም አይበርድልኝም. . .»

ከዚያ ይተጣጠፉና ማንፏለፏል ወይም እንቁላል ጥብስ ይበላሉ። ከንፈ ማሚት የዝግጅቷን ሰማያዊ ፒጃማ እንደለበሰ አልጋው ላይ ይጋደማል።

«ዐጄ አልበላም» ይላል «እጄ ላይ የምግብ ሽታ አልፈልግም» እጁን ያጠትና «ያንቺን ጠረን ብቻ ነው እጄን 'ምፈቅድለት» እሷ ነች የምታጉርሰው። ጊሬጂ ማሚትን እስታጥብ የቁርስ ሰቃዎቹን ካሰሳች በኋላ፣ ከንፈ በሩን ይቆልፍና ማሚትን እያቀፈ፣ እየሳመ፣ እያሻሸ ልብሷን ያስወልቃታል

«ተው አታብዛው ትክለሰህ» ትለዋለች

«አንቺ ግን ግሬኛ ነሽ» ይላታል

«ለምን?»

«እኛ ቁርስ በልተን እነሱ ቁርስ ሳያደርጉ ቢውሉ ምን አይመታቸውም?»



«ታዲያ ቅድም ቁርስ አላደረጉም?»

«መቼ?»

«አሁን አሁን ከኛ በፊት»

«እኔ አላስታውስም። እስቲ ፊታውራሪን ልጠይቀው» [illegible] «ቁርስ አርገሃል?» ብሎ ወይደል ትር ትር ያደርጋል። [illegible] አላደረኩም አለ» ይላታል

«ውሸታም! ጭንቅላቱን እንዲህ እንዲህ ይያደርግ [illegible] ነው»

«እሱማ የኛ ቋንቋ ነው። የሱ ቋንቋ የተለየ ነው»

«ምክንያቱስ?»

«በጭለማ ስለሚተያዩ»

ድንገት ቀልዷን ያቋርጥና ወይደል [illegible] አትከልክይኝ ማሚትዬ [illegible]

«ውይ! እኔ ልሙትልህ የኔ ፍቅር! [illegible] አርገኝ!» እንደተቃቀፉ አጭር እንቅልፍ ይወስዳቸዋል።

እሁድ የሆነ 'ንደሆነ ማሚት [illegible] ስትመለስ ትቀሰቅሰዋለች። [illegible] ያረፍዳሉ

የምሳ ሰዓት ሲደርስ የማሚት አሽከሮች [illegible] ፍሬ አጣጥመቻቸዋ እራት ብቻ ነበሩ — [illegible] አስገደች። አብረው ለስድስት [illegible] እያዳመጡ በሩ ይጠጣሉ።

ከንፈ ይስምትላቸዋል። እሱ ወሬ [illegible] ኑሮ፣ ስለ ውቤ በረሃ ኑሮ፣ [illegible] ወሬ

ወደ ዘጠኝ ሰዓት ላይ አሽከሮቹ [illegible] ማሚትን እጁን አንተርሶ ያንተኛታል። [illegible] እንዳይቀሰቅሳት እየተጠነቀቀ ጭንቅላቱን [illegible] በማግሽ እንዳትልፈ ስትከትብኝ [illegible]

ወደ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ [illegible] ልክ ብቻውን እንዲት ትንሽ ከፍል [illegible] ከመጋረጃው ወዲያ እመልከቻው [illegible] ጽጉር እያበጠረች ሁለቱ [illegible] የሚመለከተው መስኮት ተከፍቷል። [illegible] ሲጫወቱ ይሰማዋል።

ፀሐይዋ ቀያይ ዳመናዎች ለብሳ ከተራራው ኋላ ስትገባ ትታየዋለች። ብቻዋን ነች። ዘላለም ብቻዋን ነች። ልቡ ውስጥ ምክንያት የሌለው ሀዘን ቀስ ብሎ ሰርቆ ይገባል። ፀሐይዋ እየጠፋች ስትሄድ፣ ሀዘኑ እየከፋ ይሄዳል፣ ልቡን ይሞላዋል፣ እልቅስ እልቅስ ይለዋል። ብቸኛይቱ ፀሐይ ትናፍቀዋለች፣ እብድት ያልዋለ ፀሐይ የቀን ተግባሯን ፈጽማ ስትሄድ ትናፍቀዋለች፣ በስምንት ዓመቱ እናቱ የሞቱ ሰሞን ይናፍቃት የነበረውን ያህል አሁን ጠፊዋ ፀሐይ ትናፍቀዋለች። ናፍቆቱ ለፀሐይዋ ነው? ወይስ ማሚት አልጋ ውስጥ ላጠፋው ቀን ነው? ወይስ ሳይጠግባቸው ለሞቱት እናቱ ነው? ሀዘን፣ ናፍቆት፣ ብቸኝነት። ሰፊ ሀዘን፣ ባዶውን ሰማይና ሙሉውን መሬት የሚያለብስ፣ የሚጠቀልል ሀዘን።

ፀሐይ ጨርሳ ገብታ የዳመናዎቹ ቀለማት እየጠፉ ሄደው ፀጥተኛውን ሰማይ፣ ሜሚታማዋን ምድር ጨለማ ውጧቸዋል። ሰማያቱ ከዋክብቶቻቸውን ማብራት ጀመሩ። ሰዎችም ኩረንቲያቸውን ወይም ሻማ ኩራዛቸውን ማብራት ጀምረዋል። አጥር ጊቢው ውስጥ ልጆቹ ኩኩሏቸውን አቁመዋል። ከሩቅ መኪናዎች ግርሸ ሲተደሩ፣ ውሾች ሲጮሁ፣ እናቶች ልጆቻቸውን ሲጣሩ ይሰማዋል፣ መሸ።

የዳንስ ቤቱ ሙዚቃ መዝፈን ጀመረ። ውቢ በረንዳ ነጋለት። ደጁ ቀይ መብራት በርቷል፣ ሴቶቹ ለብሰው ተኳኩለው ዳንስ ቤት ውስጥ ቁጭ ብለው ወንዶች እስኪመጡ ይጠብቃሉ።

ማሚት ለባብሳ አልጋው ላይ ተቀምጣለች። ለካስ ስትኳኳል በጣም ታምራለች።

«ምን ሆንክብኝ?»

«ምንም»

«ቅር ብሎሃል። በዚች ሰዓት ሁልጊዜ ቅር ይልሃል። ምንድን ነው የኔ ፍቅር፣ ምንድን ነው?»

«ምንም። ፀሐይ ስትገባ ነው»

«እውነትክን 'ኮ ነው። እኔም አንዳንዴ ቅር ይለኛል። ፀሐይ 'ንደ እናት ነች። ስትጠፋ ሆድ ታባባለች»

«እናትሽ ሞተዋል?»

«ባሰራ አንድ አመቴ ሞተች። ያንተስ?»

«በስምንት አመቴ»

«ውይ የኔ ቆንጆ! ሀዘን ነበርካ» ትልና ልክ 'ንደ እናት ደረቷ ላይ ታስተኛዋለች። ግንባሩን እየሳመች ራሱን እያሻሸች ቃል ሳትናገር ብዙ ከቆየች በኋላ፣ ፊቱን ቀና አድርጋ «በቆንጆ ፍንጭትህ ሳቅ በልልኝ እስቲ» ትለዋለች።



ግማሽ ሰዓት ያህል ካጫወተችው በኋላ፣ መስኮቱን ዘግታ የራስጌውን መብራት አብርታለት ትራሶቹን እንዲደገፍ አመቻችታለት መጽሐፍ ቅዱሱን አቀብላው የጣራውን መብራት አጥፍታ በሩን ቆልፋ ወደ «ቢሮዋ» ትሄዳለች።

«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ» ተከተሉ አዳምና ሄዋን፣ ቃኤልና አቤል፣ ማቱሳላ፣ ኖህና የጥፋት ውሃ፣ አብርሃምና ሉጥ፣ ይስሐቅና ርብቃ፣ ኢሳውና ያእቆብ፣ ያእቆብና ራሄል፣ ዮሴፍና ወንድሞቹ፣ እስራኤል በግብጽ ሀገር፣ ሙሴ — አይ ሙሴ ኮልታፋው፣ ወንድ ነበረች'ኮ! እግዚአብሔር ራሱ ሳይቀር ይለማመጣት ነበር። አንድ ግብጻዊ ገድላ ትጠፋና ተመልሳ ደግሞ ከፈርኦን ጋር ትሟገታለች። ትጨቃጨቃለች። «ሕዝቤን እስራኤልን ልቀቅ» ትለዋለች። ታዲያ አንዲት በትር ይዛ ነው። በቃ። ምን ዓይነት በትር! አንዴ እባብ ትሆናለች፣ አንዴ ወንዙን ደም ታረገዋለች፣ አንዴ ቀይ ባህርን ትሰነጥቀዋለች፣ አንዴ ከምድረ በዳ ምንጭ ታፈልቃለች።

ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እንደ በግ ነድቶ፣ ከግብፅ አውጥቶ ቀይ ባህርን አሻግሮ አርባ ዓመት ሙሉ በምድረ በዳ መርቶ እየገሰጸ፣ እያስፈራራ፣ ሕግ እየሰጠ፣ አገራቸው ካደረሳቸው በኋላ፣ እሱ አገሪቱን ሳይረግጣት ሙትት! ሙሴ ከሞተ በኋላ እነ እያሱ ከተማ እያፈረሱ፣ ሰው እየገደሉ፣ ሴትና ሕፃን ከብትም ሳይቀር እየፈጁ . . . . . ክንፈን አሰለቹት። ሙሴ ወንድ የጀግኖች ጀግና ነበረች። እነዚህ ግን ተሰብስበው የሙሴን አንድ አስረኛ የማያክሉ ነብሰ ገዳዮች . . . ደሞ የስማቸው መብዛት! ክንፈ የእስራኤልን ታሪክ አቋርጦ የኢየሱስን ታሪክ ማንበብ ጀመረ።

ይህን ሁሉ ሲያነብ የመጠጥ ቤቱ የዳንስ ሙዚቃ እየተሰማው ስለሆነ፣ አንዳንዴ ታሪኩና ሙዚቃው ይያያዛሉ። እነኖህ ቫልስ ይደንሳሉ፣ አብርሃም ሩምባ ይረግጣል፣ ሙሴና ፈርኦን ቡጊ እየደነሱ ይሽከረከራሉ. . . . አንዳንድ በጣም ደስ የሚሉት ሸክላዎች ሲዘፍኑ መጽሐፉን ትቶ ዐይኑን ዘግቶ ይሰማቸዋል። Guitar Boogie, Blue Danube, La Comparsita, እና ሌሎች ስማቸውን የማያውቃቸው ዜማዎች። ማሚት ከ«ቢሮ»ዋ ብቅ እያለች ታየዋች። ለሩብ ሰዓት ያህል አጫውታው፣ ስማው አሳስቃው፣ አሻሽታው የመጠጥ የሲጃራ የሽቶና የተፈጥሮ ጠረኗ ተቀላቅሎ ያስከረውና የሚሆነውን ሲያጣ ሊተኛት ይፈልጋል።

«ባውቅሽ ምን አለበት?» ይላታል። ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ ሲላት አልገባትም ነበር። አስረዳት። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «አዳምም ሚስቱን ሄዋንን አወቃት፣ ወንድ ልጅም ወለደችለት፣ ስሙንም ቃኤል አለው። አብርሃምም ሚስቱን ሳራን አወቃት፣ ወንድ ልጅም ወለደችለት፣

ስሙንም ይዘዛት አሉት። እኛም ማስቱን ወይዘሮን አወቃት፣ ወንድ ልጅም ወለደችለት፣ ስሙንም ማሞ አሉት። ቁላም ማስቱን እምቢን አወቃት፣ መንታ ልጆችም ወለደችለት፣ ስማቸውንም ቀለጥ እና[illegible] ቁንጉር ቀልቃሊት አሏቸው። እግዚአብሔርም የቁላንና የእምቢን ዘር ባረከ፣ መሬትንም ሞላት ይላል» አለች

«ባባትህ ልመቅኸ»

«እሱን እያደለም»

«መቼ?»

«በኋላ። በኋላ የፈለግከውን ያህል ታውቀዋለህ. . .» ብላ አሳሳቢው ትሂደለች። ወደ መጽሐፍ ቅዱሱ ይመለሳል።

በመጨረሻ ወደ እምቢት በሩት ላይ መጥታ እምቢት ደቂቃ ያህል ብዙ አሜውታው፣ እሱ ጭንቅን ሲያንብብ፣ እሷ ብሌቱን እያንቆቆቆለት መቁነጥነጥ ሲጀምር

«አቁመኸው ቆየነና ቢሌን ዘጋሻሽ በመጣ ትትትብኛለህ። በማም አምርሻል» ብላው ትሄደለች።

ልቡ በድቢት በሩት ሲያገ ትመጣና በራን ቆልፋ፣ በጠርሙስ ውሃ ሪብሷቸው እንቁ፣ ልብሷን አውልቃ አልጋው ውስጥ ገብታ «ብርድኛል እመቀኝ» ትለዋለች

እንግዲህ ሊሊቱ ይጀመራል።

ማስቱታ የሊሊው እጭር ሊሊት . . . የማሚት እሌጋ ለብቻው ከሚለምንና ከጎዴ ተንገት ተፈናግሮ ሄዶ ልዩ ራሱን የቻለ ሊሊት ያሆናል። ተፍቅር ሊሊት፣ የምጣት ሊሊት፣ የሥጋ ሊሊት . . . የዚህ ሊሊት ክምክብብት የማሚት ቃላት፣ ብቻ ግሌት የሚለው የማሚት ንግግርና ሳቅ፣ ለስላሳ ሰውነቷን የሚያርበተብተው የከንፈሯ ልብ የሚያብሰለው ውስ ሳቅ . . . የሊሊት እረፍት፣ የማሚት ጣቶች መላ ሰውነቱ ላይ እየተንሸራሸሩ እንቅልፍ የሚያሳቱት እረፍት . . . ማስቱታ የሊሊው፣ ከመቅደቢት የማገጋ ሊሊት። የመተቃቀፍ የመሳሳሳምና ሊሊት።

ከዘመናትም እሰከ ዘመናትም ማስቱታ የሊሊው ከመቅደቢት የማገጋ ሊሊት፣ የፍቅር ሊሊት

እንዳንድ በመናሪያም ለበሳ ይምጂ «ስጥፍኝ» ትለዋለች

«ወዴ»

«እባክህን እንዳትተወኝ» ብላ ትመተልልያለች

«አልተውሽም የኔ ቆንጆ» ይላታል፣ እያቀፈ ጸጉሯን እያሸ

«እስቲ መጽሐፉን አብራልኝ ልይው። እንዴዚህ ሳይሆን ደስ ትለኛለህ በመጽሐፉ እንደዛ በመጽሐፉ»



ስትናገር በመብራቱ ጥርሷ ብልጭ ብልጭ ይላል። እንዳ ያቁረሩ ዐይኖቿ በሀዘን በፍቅር ራሱ ላይ ሲንከራተቱ የሚያለዉልዉሉ። ፊቷን እያሸሸ እንባዋን እያበሰ

«ምን ሆንሽብኝ? ቅድም እስመሞቻሽ።» ሲላት ራሷን በስሱ ታነቃንቃለች

«ታሚያም»

«ፈራሁ»

«ምን ያስፈራሻል?»

«እንዲህ አስልምዶኸኝ የተውሽኝ ጊዜ ምን አደርጋለው» ሲሊት እንጂት ያሰጋልኛል?»

እንቁ ያረጋቸና ንገዉን እንባዋን እያበሰ

«በጭራሽ አልተውሽም»

«ስታገባስ ምን አደርጋለው?»

እንጂቱን ትስማዋለች። ራሱም እስቢት ማሌቱ ያልፈለጋል

«እላገባም» ያላታል

«ታገባለህ»

«ብገባም አልተውሽም»

«መቼ?»

«መቼ እንዲት እተውሻለሁ? ሲታገኝ አቤቶሉን 'ምትውሽ እመሰልሻለሁ»

ይተያያሉ። ሳቅ እያሉ

«እሱን ምኝታቱን ተይውና፣ በውቅሽ ምን ይመስልሻል?»

ሳቅ እያለች «እኔ ቤቴት ልመጣም»

«አትችይም የኔ ቆንጆ። እንጂ መታጠቢ እንጂ ማወቅ አትችይም»

«እንቱ ነዉ ያልኩሽው፣ ስለምን ነዉ ብዙ ተሳምሉኝና አስተያቸሉ»

ስትስመዉ የምታሰጋ ሙሉ ጥርሷ ፍንጭት ውስጥ ኬት ከንተሳሳቆች በጋለ እያሳቀችበት

«ታዲያስ አለመቻልህም?»

«አውቀኸናል። መጽሐፉ ቅዱሱ ውስጥ፣ ማሚትንም ብዙን ከርሰን አውቀዋው፣ ከንፈሯም እጂን ተደሰቱ። ብላን እናስገባሽን እስን ተፈልግን በውቅሽ ምን ይመስልሻል?»

«በብርሀን ነው በጨለማ ስተውቀን ምትፈልጊው?»

«ቤቴት ተገሺና በዐይኔ ልውቅሽ»

ተንስታ አልጋው ላይ ትቆምለታለች። እንደተጋደመ በይኖቹን ሽጋ ገላዋ ላይ ያንሸራሽራቸዋል። ወደዛ ዙሪ፣ እንዲህ ቁሚ፣ እግሮችሽን እንደዛ አጠፍ አርጊ፣ እያለ ውበቷን ሲያደንቅ ከቆየ በኋላ

«ሊበርደኝ ጀመረ» ትለዋለች

እጁን ሲዘረጋላት እቅፉ ውስጥ ትወድቅና

«መጀመሪያ እየሳምክ አሙቀኝና በኋላ ሳታስጠንቅቀኝ ድንገት በኃይል ክተትብኝ» ትለዋለች

«ተይ ያምሻል»

«ይመመኝ»

«ሳሳምምሽ ደስ ይልሻል?»

«በኃይል ደስ ይለኛል። ካሳመምከኝ በኋላ ስታባብለኝ የሚሰማኝ ደስታ!»

በኃይል ያሳምማትና «አይ!» ብላ ኩምትር ስትል ያባብላታል

አንዳንዴ ሌሊት በጇ ነካክታው ስታበቃ፣ በደምብ ሲቆምበት ጭኗን ትከፍትና ስታስገባው፣ ልክ በ'ንቅልፍ ልቡ እንደሚያወራ ሰው እያቀፋት «እንኮዬ ወለቴ! አይ የባሪያ እምስ ሲጣፍጠኝ! ብቻ ማሚት እንዳትደርስብኝ 'ንጂ» ይልና በኃይል ጉንጯን ይስማታል። እንኮዬ ወለቴ የማሚት አባት ባሪያ ነበረች። አሁን የማሚት እንጀራ ጋጋሪ ናት፣ ወደ ሰባ አመቷ ነው። ማሚት ከት ብላ እየሳቀች

«እሱን ተወው! በ'ንቅልፍ ልብህ ስበዳህ ጊዜ ቁጭትህን ለመወጣት ነው 'ምትሰድበኝ»

«እ! እ! የት ነኝ?» ይልና ሲነቃ «በ'ንቅልፍ ልቤ ተናገርኩ 'ንዴ?» ይላታል

ከዚያ እንግዲህ ቀልድ ይጀምራሉ

የራስጌ መብራት ያበሩና በሆነው ባልሆነው ነገር ሲስቁ አንድ ሰዓት ያህል ካሳለፉ በኋላ፣ ሳቅ፣ ደስታ፣ ፍቅር፣ ምኞት ፊቷ ላይ እያበራ

«አይ ክንፌ! እንዳንተ ጉደኛ እዚህ ዓለም ላይ ይገኛል?» ትለዋለች

«ጉደኛ?»

«ሲያስኝህ እያስለቀስከኝ ትበዳኛለህ፣ ሲያስኝህ እያሳቅክ ትበዳኛለህ። አሁን 'ስቲ እንደ ሰዎች ሳታስለቅስም ሳታስቅም ብዳኝ»

«እሺ። እንግዲያው በደምብ እንድጀምር ልምዘዘው?»

«የለም አትምዘዘው»

«ይመገምዘው?»



«ይበዝብዘው»

«ይወጥውጠው?»

«ይበልዘው»

«ይመርዘው?»

«ይሰርዘው»

«ይቀዝቅዘው?»

«እየው 'ንግዲህ እያረሳሳህ ስታስቀኝ። አልፈልግም በቃ መብራቱን አጥፋ» መብራቱን ያጠፋል. . .

የመጀመሪያው ሁለት ወር ፍቅር ብቻ ነበር።

አንዳንድ ማታ እሸቱ እየመጣ ያጫውተዋል። እሸቱ ያጎቱ ልጅ ነው። አሁን አግብቶ ሁለት ልጆች ወልዶ ከሚስቱ ጋር በደስታ ይኖራል። በረሃን በእግሩም አይረግጥም። ያን ጊዜ ግን እሱና ክንፌ አስራ ሁለተኛ ክፍል ሆነው ለኮሌጅ ፈተና የሚዘጋጁበት ወራት ነው። ክንፌን ለማጫወትና ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለስ ለመሞከር፣ እንደዚሁም ክንፌን ከጥፋት ጎዳና ወደ እግዚአብሔር መንገድ ለመምራት ማሚት እሹሩሩ ቤት ብቅ ይላል። ሲመጣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ የክፍል መጽሐፍት አምጥቶ ሰጥቶት «ሌላው ነገር ሲሰለችህ ለማንበብ ሞክር» ብሎ ይመክረዋል። ማሚት እንደልማዷ ከቢሮዋ ብቅ ስትል ለሦስት ሆነው ያወራሉ። እንግዲህ ማሚት ክንፌን ወደ ገሀነም የምትመራ የሰይጣን አገልጋይ በመሆኗ እሸቱ እንደ ጠላት ይቆጥራታል። እሷም በበኩሏ እሸቱ የክንፌን ፍቅር ሊያስቀርባት መሞከሩን ስለምታውቅ ትጠላዋለች። ታዲያ «አንቱ እርሶ» እየተባባሉ እየተከባበሩ ሲነጋገሩ ክንፌ ውስጥ ውስጡን ይስቅባቸዋል።

ግን ቀስ በቀስ ሲተዋወቁ እየተዋደዱ ሄዱ። በመጨረሻ እንዲያውም በክንፌ ላይ ተሻረኩበት «የኮሊጁን ፈተና ተፈተን» እያሉ አስቸገሩት። እምቢ አልፈልግም ሲላቸው፣ ለኛ ስትል እያሉ ጨቀጨቁት። እሸቱ የሌለ ጊዜ ማሚት እንደዚህ ትለዋለች «ይሄ እሸቱ በጣም ይወድሃል። ላንተ ሲል እዚህ ይመጣል። ትምህርት ቤት ሄዶ ታሚል ይልልሃል። አባትህ ሲጠይቁት ደሞ ትምህርት ቤት ነው ጥናት በዝቶበታል ይልልሃል። መጽሐፍ ያመጣልሃል። ጥሩ ልጅ ነው። ለራስህ ወይም ለኔ ስትል እንኳ ባይሆን ለሱ ስትል ተፈተንለት። ማን ያውቃል? ታልፍ ይሆናል» ማሚት የሌለች ጊዜ ደግሞ እሸቱ «እቺ ማሚት'ኮ ምንም አትል» ይለዋል «ሸርሙጣ ባትሆንማ በጣም ጥሩ ሴትዮ ነበረች። ከልቧ ትወድሃለች። እንደሰማሁት ከሰላሳ ብር በማያንስ ዋጋ ማንንም አታሳድርም። አንተን ግን ይኸው፣ በዜሮ ከማሳደሯ በላይ ትቀልብሃለች፣ ፒጃማ ትገዛልሃለች፣ ካንተ ጋር ለማደር ስትል ስንትና ስንት ገንዘብ

እምቢ ትላለች:: እንዲህ እየወደደችህ በኋላ በሷ ምክንያት ትምህርትህ እንዳቋረጥክ እየተገነዘበች ስትሄድ ምን ያህል እንደሚቆጫት አይታይህም? ለራስህ ወይም ላባትህ ወይም ለኔ ጓደኛህ ስትል እንኳ ባይሆን ለማሚት ስትል ተፈተንላት»

ሌሊት ማሚት እንደልማዷ የራስጌውን መብራት አብርታ የፍትወት ጭኖቿ መሀል አስገብታው፣ በምኞት ከናፍሯ እየሳመችው፣ በፍቅር ዐይኖቿ እያየችው፣ በጠረኗ መርዝ እያሰከረችው፣ በወፍራም ለስላሳ ድምጿ

«ክንፍዬ!» ትለዋለች:: «ዬ» ስትል ከንፈሯ ክፍት ሲልና ጥርሷ ብልጭ ሲል ክንፈ የሚሆነውን አጥቶ ከንፈሯንና ጥርሷን እየላሰ እፏ ውስጥ «ወይዬ!» ይላታል:: ጥውልግ ሙትት እስኪል ትስመውና ፊቱን ቀና አርጋ በንፁህ ዐይኖቿ እያየችው

«ትወደኛለህ?» ትለዋች፣ የምኞት ፍስሐ ባደከመው ድምፅ

«እወድሻለሁ እሞትልሻለሁ» ይላታል

ሌላ ጊዜ «እኔም እሞትልሃለሁ» ነበር 'ምትለው:: ዛሬ ግን «አንድ ነገር ብለምንህ ታረግልኛለህ?» አለችው

«የፈለግሽውን»

«ሙት?»

«ሙች!»

«ማልልኝ»

«በምን ልማልልሽ? በአሁኑ ፍቅራችን እምልልሻለሁ! ምን ላርግልሽ?»

«በኋላ እነግርሃለሁ:: አሁን ማውራት አልፈልግም እስቲ እንዳ በኃይል አሳምመኝና በኋላ አባብለኝ፣ ውድድ አርገኝ:: አቤት ማባበሉን ስታውቅበት! ሙትት ነው የምልልህ መቸስ!»

እንደገና አዲስ ፍቅር ይይዛቸዋል

ምኞታቸው አልቆላቸው፣ ለመተኛት መብራቱን አጥፍተው፣ ደረቷን አንተርሳው፣ ፀጉሩን እየደባበሰች

«ክንፍዬ!» አለችው

«እ?»

«ታዲያስ፣ የማልክልኝን ታደርግልኛለህ?»

«ንገሪኝ»

«አትቆጣኝም?»

እጇን እየሳመ «በጭራሽ»



«ሙት?»

«ሙች!»

«ፈተናውን ተፈተንልኝ»

«እሺ»

በኃይል ተጠመጠመችበት:: ሳመችው:: ዘለለችና መብራቱን አበራች:: ጉንጩን፣ ግምባሩን፣ አፍንጫውን አስር ጊዜ ሳመችው:: በጣም ደስ አላት:: ፊትዋ ልዩ ብርሃን ለበሰ

«ምን ላርግልህ ክንፍዬ? ምን ላርግህ የኔ ፍንጭት?» አለችው

«ሁልጊዜ 'ንደዚህ ውደጂኝ»

«ለዘላለም እወድሃለሁ፣ ፍቅሬ»

ግንባሯን ሳመ፣ መብራቱን አጠፋ:: እጁን እንተራሳት፣ ባንድ አፍታ እንቅልፍ ወሰዳት:: እሱ ግን ሊተኛ አልቻለም:: ማሚት ምን ያህል እንደምትወደው ድንገት ሲታየው ጊዜ ልቡ በፍርሃትና በደስታ ተሸበረ. . .

ፈተናው አንድ ሳምንት ብቻ ነው የቀረው:: በመጀመሪያ ማሚት አልጋ ውስጥ ያሳለፈው ሁለት ወር በበሽታ መሆኑን የሚመሰክር የሐኪም ወረቀት ያስፈልጋል:: ደግነቱ ነርስ የሆነች ዘመድ አለችው. . . ሌላስ? ለፈተናው መመዝገቡን በፊት ተመዝግቧል:: ብቻ እሱ ግዴለም:: ለፈተናው ጉዳይ እሸቱ አለ . . .

ያስጨነቀው ይሄ የማሚት ፍቅር ነው:: ምን ያህል እንደምትወደው ለምን እስከ ዛሬ አልታየውም? እጁን ተንተርሳ እንገቱ ላይ ትተነፍሳለች:: ቀኝ እጇ ወገቡ ላይ አርፏል፣ ግራ እጇ የት እንደሆነ 'ንጃ፣ አዎን አዎን፣ ጡቷ ስር ነው፣ አንድ ጭኑ ጭኖቿ መሀል ነው:: አንገቱ ውስጥ ትተነፍሳለች:: ፀጉሯን ሳመ፣ እንዳይቀሰቅሳት እየተጠነቀቀ እቅፍ አደረጋት፣ ግንባሯን ሳመ፣ አንገቱ ላይ ትተነፍሳለች:: ምን ሊያደርግላት ይችላል? ገንዘብ ቢኖረው 'ንኳ ስጦታ ብጤ ይሰጣት ነበር:: ግን ሁለት ብር ብቻ ነች ያለችው:: ያቺ ሁለት ብር በመቶ ተባዝታ ሁለት መቶ ብትሆንለት!. . .

በማለዳ ተነስቶ ቀስ ብሎ ለብሶ ማሚት ሳትሰማው ወጣ:: ቀኑን ሙሉና ማታም እስከ ሁለት ሰዓት ድረስ ዘመድ ሲጠይቅ ዋለ:: የክንፈ ዘመዶች ተቆጥረው አያልቁም «በጣም ደግ፣ ቸር፣ ርህሩህ» የሆኑ ዘመዶቹ ግን ጥቂት ናቸው:: ማለት አንድ ዘጠኝ አሥር ይሆናሉ:: እነሱም አክስቶቹና ያክስቶቹ ባሎች፣ አጎቶቹና ያጎቶቹ ሚስቶች፣ እና ሁለት ያባቱ የቅርብ ጓደኞች:: ወንዶቹን ቢሮዋቸው፣ ሴቶቹን ቤታቸው ሄዶ አንድ በአንድ ጠየቃቸው:: ለያንዳንዳቸው ምን እንደሚላቸው፣ እነሱ ምን እንደሚመልሱለት፣ ቀጥሎ ምን እንደሚነግራቸው እያሰላሰለ

ሲሄድ፣ ሳያውቀው በአንድ ጉልት አጠገብ ሲያልፍ አንዲት «ኮሬንቲ» የሆነች ሀሳብ እንደ መብረቅ አንጎሉ ውስጥ ብልጭ አለችበት። እሱ አላሰባትም። እሷ ነች ራሷ የታሰበችው። ወይም ሰይጣን ወርውሯት የክንፈን አንጎል ጨረፈችው

የሆነ ሆኖ፣ በዚች ሀሳብ ትእዛዝ በጉልቱ ከተቀመጡት ቢቶች ብትን በርበሬ ቆንጥሮ ወስዶ መሀረቡ ጫፍ ላይ ቋጥሯት መንገዱን ተጠለ። «በጣም ደግ፣ ቸር፣ እርህሩህ» የሆኑ ዘመዶቹን አንድ በአንድ ሲጠይቅ፣ ስሟቸው ቁጭ ካለ በኋላ

«ጠፍተህ ከረምክ»

«የኮሌጅ ፈተና ደርሶ ጥናት በዝቶብኝ ከትምህርት ቤት መውጣት አልቻልኩም» ይላቸዋል

«ጥሩ ነው። ታዲያስ፣ በደምብ ተዘጋጅተሀል?» ሲሉት እንግዲህ፣ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደዚያ ይሄድና ጀርባውን ወደጠያቂው እያዞረ መሀረቡን አውጥቶ አይኑን ይጠርጋል። መሀረቡ ጫፍ ላይ የተቋጠረችውን ብትን በርበሬ አይኑ በማስጠጋት «በርበሬ እንባ» ሲያለቅስ «ደም እንባ» የሚያለቅስ ይመስላል። አንድ ሁለቴ ያስነጥሰዋል፣ ግን ሳይፈልግ ነው። በአፍንጫው እንደ ጥሩምባ በኃይል ጡጥ እርጎ ይናፈጣል

«ምን ሆንክ? አይዞህ አታልቅስ። ምንድነው? ንገረኝ» ሲሉት፣ የለቅሶ «ስቅታ» በሚቆራርጠው አሳዛኝ ድምፅ

«የዛሬ ሁለት ሳምንት አባባ ለፈተናው ብለው የሰባ አምስት ብር ቻርከር ብዕር ገዝተውልኝ ነበር። ትምህርት ቤት ሰረቁኝ። አሁን አባባን እንዳልነግራቸው ይገሉኛል። ገዝም እንዳልል ፈተናዬን በምን እጽፋለሁ?» ይቺን «ትራጀዲ» ያባዛታል፣ ያሰፋታል፣ ይገነባታል። በመጨረሻ ብዕር መግዣ አንድ አስራ አምስት ብር ተቀብሎ፣ ራሱን እየነቀነቀ «ይሀን ደግነት እስከሞት አልረሳውም» ወይም «አባባ እንትና፣ አንተ አጎት አይደለህም፣ አባት ነህ» «እማማ እገሊት፣ አንቺ አክስት አይደለሽም፣ እናት ነሽ» ብሎ የስሜቱ ብዛት ጉሮሮውን አንቆ አላናግር ስለሚለው እየሮጠ ወጥቶ ይሄዳል።

ግን ሁሌ የብዕር ጉዳይ አልነበረም። እንደሱማ ቢሆን ይሰለቻል። ሌላ ጉዳይ አንድ ትልቅ Dictionary ነበር። «በትምህርት ቤቱ» አንድ እሱ ብቻ ነው ያለው። የመጨረሻ ክፍል ለሆንነው ተማሪዎች ተራ በተራ ይደርሰን ነበር።

ተራዬ ደርሶኝ ሰረቁኝ። አሁን ዳይሬክተሩ የመጽሐፉን ዋጋ ሀያ አምስት ብር ካልከፈልክ አናስፈትንህም አሉኝ። ላባባ እንዳልነግራቸው ይገሉኛል»



ሌላ ጉዳይ «ከለንደን የሚላክልን ፈተና ገንዘብ ይከፈልበታል። ለያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት አምስት ብር። የዛሬ ሁለት ወር አባባ ገንዘቡን ሰጥተውኝ በአውቶብስ ስሄድ ኪስ አውላቂ ሰረቀኝ። አሁን ላባባ እንዳልነግራቸው ይገሉኛል። ምን እንደማደርግ ጨነቀኝ» ወይም «እማማ እንትናን የመሰለች እናት እያለችኝ፣ አባባ እገሌን የመሰለ አባት እያለኝ፣ ሰላሳ አምስት ብር በማጣት ትምህርቴን እንዴት አቋርጠዋለሁ በማለት አንተ ጋ ወይም አንቺ ጋ መጣሁ»

ሌሎችም ይህን የመሰሉ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ነበሩ። ቢሆንም፣ ጉዳዮቹ ይለዋወጡ 'ንጂ «ለአባባ እንዳልናገር ይገሉኛል» «ያላንተ ማን አባት አለኝ» ወይም «ያላንቺ ማን እናት አለኝ» የሚለው ንግግርና የበርበሬ እንባው አልተለወጠም።

ነገሩ ወይም ፕሮግራሙ ትንሽ የተለወጠው «እማማ ሳይኮ» ቤት ነበር። እማማ ሳይኮ እማማ ሳይኮሎጂ ማለት ነው። የክንፈ «ሳይኮሎጂስት» አክስቱ ናቸው። Psychology, psychiatry, behaviourist psychology, abnormal psychology ምናምን ሲያነቡ ነው 'ሚውሉት። Freud, Jung, Adler ,Watson የፃፉት መጽሐፍ አብዛኛው ቤታቸው ይገኛል።

እንግዲህ ያገኙትን ሰው ሁሉ «Psychoanalyse» እንዳደረጉት ነው። ክንፈ በርበሬውን ይዞ እላቸው ጋ ሲያለቅስ አንድ አምስት ጊዜ አስነጠሰው።

«ምነው ያስነጥስሃል?» አሉት

ጉድ ፈላ! ብሎ ደንግጦ 'ሚለውን በማጣት

«ስፈራ ያስነጥሰኛል» አላቸው

«ስትፈራ ያስነጥስሀል!? Strange phenomenon. Freud ይህን case አይጠቅሰውም። እስቲ፣ በልጅነትህ አጠገብህ በርበሬ ሲወቀጥ ወይም ሽንኩርት ሲከተፍ በጣም ደንግጠህ ነበር?»

«እኔ 'ንጃ»

«አስታውስ 'ስቲ። ሞክር በል»

«አላስታውስም»

«Nonsense! ለምን አታስታውስም? ቁጭ በልና relax አርግ። ሻይ እየጠጣን ስናወራ ይመጣልሃል። Memory is a matter of will and relaxation. You sit down and relax. The sub-conscious will do the rest »

ክንፈ «እንግዲህ እቺ እብድ አሮጊት እዚህ ልታውለኝ አይደለም? የፈለገችውን ልንገራትና ልሂድበት» ብሎ ቆረጠ። ትንሽ ጠያየቃቸውና ምን እንደሚፈልጉ ሲገባው፣ ድንገት

«መጣልኝ መሰለኝ እረ!» አላቸው

«I told you the sub-conscious would do it! ንገረኝ»

«አንድ ስምንት አመቴ ይሆናል መሰለኝ:: እማማ ላትዋት አትራቢያ:: በነጋታው ትልቅ ግብዣ ነበር መሰለኝ:: በድንጋይ ቤት እየሰራሁ እጫወታለሁ:: ድንገት ዐይኔን ዘወር አረግኩ:: በቀኝ በኩል አንዲት አስቀያሚ አስደንጋጭ አሮጊት በትልቅ ጥርሳቸው እየሳቁ፣ እኔን እኔን እያዩ በትልቁ ቢላ ሽንኩርቱን ይከትፋሉ፣ ልክ እኔን የሚከትፉኝ መሰለኝ:: በጣም ደንግጬ ዘወር ስል በግራዬ በኩል ደግሞ ሁለት ጠብዢራ ኩሊዎች ከንፈራቸውን ነክሰው ላባቸው እየተንጠፈጠፈ እህ! እህ! እያሉ በርበሬ ይወቅጣሉ:: ልክ እኔን የሚወቅጡኝ መሰለኝ:: በወዲህ በኩል አሮጊቷ ሲከትፉኝ፣ በወዲያ በኩል ኩሊዎቹ ሲወቅጡኝ፣ እሪ ብዬ አለቀስኩ:: በርበሬው ይሁን ሽንኩርቱ ደጋግሞ ሲያስነጥሰኝ አስታውሳሁ:: ሽንኩርት የምትከትፈው አሮጊት ልታባብለኝ መጣች:: በፍርሃት ብዛት ሽንቴ አመለጠኝ»

«እናትህ የት ነበረች?» ምን መልስ እንደፈለጉ ሊያውቅ አልቻለም::

«እንጃ» አላቸው

«መጥታ አላባበለችህማ?» የለም እንዲላቸው የፈለጉ መሰለው፣ ግን ለማረጋገጥ ያህል

«መጥታ ብታባብለኝ አሁን ካደግኩ በኋላ ስፈራ ያስነጥሰኝ ነበር?» አላቸው

«አይመስለኝም:: ምክንያቱም the sense of security following immediately, the traumatic effect would be reduced considerably, almost to nil»

«እኔም እንደሱ ነው የመሰለኝ»

«እናትህ አላባበለችህማ?»

«የለም»

«Just as I thought! this is fascinating"

"Most fascinating! አሁን ለፈተናው መዘጋጀት ስላለብኝ ከፈተናው በኋላ መጥቼ በሰፊው ብንነጋገርስ?»

"Excellent idea! እስከዛው I will study your case theoretically And then we will go deep into the matter."

«ይመስልኛል፣ እብድ አሮጊት!» ብሎ እያሰበ «ለፈተናው» የሚከፈለውን ሰላሳ አምስት ብር ተቀብሏቸው ሲሄቸው ወጣ::

ከአራተኛው ዘመድ በኋላ ከንፈን ሲያዩት «ምነው ዐይንህ በርበሬ



መሰለ?» ስለሚሉት አሳዛኝ ታሪኩን በቀጥታ ይጀምርላቸው ነበር::

ከንፈ ማታ ወደ ሁለት ሰዓት ላይ ዘመድ ጥየቃውን አብቅቶ ገንዘቡን ሲቆጥር ሁለት መቶ አስራ አምስት ብር ሆነለት:: ግን በበርበሬው ደማቅ መብራት ስላስፈለገው፣ ጉዊዶ ምግብ ቤት ገብቶ መቁጠር ግድ ሆነበት:: በዛውም ቁርስና ምሳው አምልጦት ስለዋለ ምን የመሰለች «ፓስታ ሹታ አሮስቶ ዲቪቶሉ ጂኒ ቁልቋል ዲሮማ» ውጥቅ አድርጎ በላ

ከዛ ባለ በርበሬ መሀረቡን ስሞ ተሰናብቷት ሲያበቃ፣ እንደ ደንቃራ መንገድ ዳር ጣላትና ሌላ መሃረብ ገዝቶ ሲኒማ ገባ::

ወደ ስድስት ሰዓት ገደማ ማሚት መኝታ ቤት ሲገባ ከአልጋዋ ውስጥ ዘላ አንገቱ ላይ ተጠመጠመችበትና የደስታ እንባ ባፈነው ድምጽ ደጋግማ

«ብቻዬን ትተኸኝ! ብቻዬን ትተኸኝ! ብቻዬን ትተኸኝ!» አለችው::

አሁንም ፍርሃትና ደስታ ልቡን አሸበረው:: አንገቱ ውስጥ እንደተደፋች፣ ሲናፍቀው የዋለ ውብ ጠረኗን ወደ ውስጥ በሃይል እየተነፈሰ፣ ራሷን እያሻሸ

«አይዞሽ የኔ ማሚት፣ አይዞሽ የኔ ገላ፣ አይዞሽ አይዞሽ» አላት:: እንዲህ ተጠምጥማበት ፊቷን አንገቱ ውስጥ ደብቃ ብዙ ከቆየች በኋላ፣ ቀና ብላ እምባ በሞላቸው ዐይኖቿ ወደ ላይ እያየችው

«ለምን ብቻዬን ትተኸኝ ሄድክ? ምን አረግኩህ?» ብላው ገና ሊመልስላት ሲል እንደገና ተጠመጠመችበትና

«ፈተናውን ተፈተን ያልኩህ 'ኮ ላንተው ስል ነው:: እንጂ የምትወላኝ ከሆነ ተወው ይቅር አትፈተን:: ብቻ አትተወኝ የኔ ጌታ፣ አትተወኝ!»

ቀስ በቀስ አባብሏት የፈተናውን ጉዳይ ለማጣራት መሄድ ነበረብኝ ብሎ አስረድቷት፣ በሩን ቆልፈው አልጋ ውስጥ ገቡ::

ስትስመው ስታቅፈው «ሳለቅስልህ ዋልኩ» ስትለው፣ ስታቅፈው ስትስመው «አደራ ሁለተኛ ላምስት ደቂቃም ቢሆን ሳትነግረኝ እንዳትወጣ» ስትለው:: «እሺ» ሲላት፣ ሲያሻሻት፣ ብዙ ከቆዩ በኋላ፣ አንገቷ ውስጥ እየተነፈሰ «እሰይ! ከሁሉ የናፈቀኝ ጠረንሽ ነበር» አላት

«እኔ ደሞ ከሁሉ የናፈቀኝ ፍንጭትህና ዐይኖችህ ናቸው:: ልያቸው 'ስቲ?» ከላዩ ሆና እያየችው

«ምን ሆና ነው ዐይንህ እንዲህ የቀላው?» (በርበሬው)

«ሳለቅስ» ፊቱን እያሻሸ

«ምነው? ምን ነካህ የኔ ቆንጆ?»

«ምንም»

«ውይ ንገረኝ የኔ ጌታ፣ ምንድነው ያስለቀሰህ?»

ወደ ላይ አይን አይኗን እያየ በሹክሹክታ

«አንቺ ናፈቅሽኝ» አላት

«ውይ የኔ ፍቅር!» ብላ በኃይል ተጠመጠመችበትና ፊቷን ደብቃ «እኔ ደም እንባ ላልቅስልህ የኔ ቆንጆ! እኔ ላልቅስልህ!»

ሙቅ እንባዋ አንገቱ ላይ ሲፈስ ተሰማው:: መብራቱን አጠፋ::

«አቀፈኝ! አቀፈኝ! በኃይል አቀፈኝ!» አለችና ጭኖቿ መሀል አስገባችው:: ሌሊቱ ተጀመረ:: የመተቃቀፍ፣ የመቆላለፍ፣ የመታገል ሌሊት፣ በኃይል የመተንፈስ፣ የማቃሰት፣ የማለክለክ ሌሊት፣ የሙቀት፣ የወበቅ፣ የላብ ሌሊት፣ የመሳሳም፣ የመላላስ፣ የመጣባት ሌሊት፣ የመናከስ ሌሊት. . .

የምትወብቅ፣ የምትጨንቅ፣ ጠባብ ሌሊት፣ ትኩስ፣ እርጥብ የምታሟልጭ ሌሊት. . . እፍረትን የማታውቅ፣ ነውርን የማትፈራ ሌሊት፣ ራሷን ለማስታወስ የማትደፍር ሌሊት. . . ሚስጥራዊት የግል ሌሊት. . .

በነጋታው አንድ መቶ ሀምሣ ወይም ሁለት መቶ ብር ያህል ቢኖረኝና የፈለግሽውን ልግዛልሽ ብልሽ ምን ትመርጪ ነበር? ብሏት፣ አንተን ዘወትር እንዳስታውስህ መስቀልና ሀብል አሰርቼ ካንገቴ አልለየውም ነበር አለችው:: ሁለት መቶ ብሩን ሰጣትና፣ ከሰዓት በኋላውኑ ወርቅ ሰሪው ቤት ሄደች::

ከንፈ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናውን ጨርሶ የለንደኑን ፈተና ሊፈተን ሶስት ቀን ሲቀረው፣ ወርቅ ሰሪው የማሚትን መስቀልና ሀብል ጨረሰላት:: ግን ከንፈ ፈተናውን ጨርሶ ማለፉን እስከሰማ ወርቁን አላረገውም ብላ አስቀመጠችው::

«ያላለፍኩ 'ንደሆንስ?» ሲላት

«ታልፋለህ አለችው»

እውነትም አለፈ:: ማለፉ በጣም ገረመው:: መጥቶ ሲነግራት ማሚት ዘለለችና ተጠመጠመችበት፣ ጉንጬን፣ ግንባሩን፣ አፍንጫውን ደጋግማ ሳመችው:: ፊቷ ልዩ አይነት ብርሀን ለበሰ፣ የደስታና የኩራት ብርሃን::

«እሰይ! እሰይ! እሰይ!» እያለች እንደ ትንሽ ልጅ እያጨበጨበች ዘለለች:: የከንፈ ልብ በፍርሃትና በደስታ አብሯት ይዘል ጀመር::



እቅፍ አደረጋት::

«ለመሆኑ እንደማልፍ እንዴት አወቅሽ?»

«ለቁሉቢው ተስያለሁዋ!»

ሆዱ ቦጭ ቦጭ አለ:: የፍቅር ስሜት እንጀቱን ሸመቀቀው:: አያት:: በጭራሽ ሊያውቃት አልቻለም:: እቺ ሴትዮ ማን ትሆን? ሌሊት ሌሊት በስጋው ስጋዋን ያውቃል:: ግን ማን ትሆን? ማንች? ማነው ብላ ይሆን እሱን እንዲህ 'ምትወደው' ባይደ ሲታይ ምን ቢመስል ይሆን?

«እንደትንሽ ልጅ ሳብድ ዝም ብለህ ታየኛለህ?»

እንደገና እቅፍ አደረጋት

«ለምንድን ነው ይሆን ያህል 'ምትወጂኝ?»

«የኔ ነህ!. . . የገዛሀልኝን ወርቅ ላሳይህ»

መስቀል፣ ሀብል፣ እና ተንጠልጣይ ጎታች:: ጉትቻው እንዴት ነው ያማረባት! ከንፈ አፉን እንደከፈተ ቀረ

ማታ «ቢሮዋ» አልገባችም:: የከንፈን ፈተና ማለፍ ለማክበር አብረው አልጋ ውስጥ አደሩ:: በፊት ትደብቀው የነበረ ብዙ ብዙ ነገር ነገረችው::

ስለ ልጅነቷ፣ ስለ ሰርጓ፣ ስለ አማቾቿ፣ ስለ መፍታትዋ፣ አዲስ አበባ እንዴት እንደ መጣች፣ ሽርሙጥና ለምን እንደጀመረች:: ድህነትን፣ ችግርን፣ የሰውን ልጅ ክፋትና ጭካኔ ያየች ሴትዮ ኖራለች::

ቀስ በቀስ፣ ሳይታወቃቸው ማሚትና ከንፈ ፕሮግራማቸውን ለወጡ:: ሲመሽ ማሚት ቢሮዋ ለመግባት ስትኳኳል፣ ከንፈ ተነስቶ ተጣጥቦ ፀጉሩን አበጥሮ አየር ለመቀበል ይወጣ ጀመር:: ማሚት ጭን መሀል ሲቀቀል ውሎ ወጥቶ ንፋሱ ሲመታው ልዩ አይነት ደስታ ይሰማዋል:: ግን አብዛኛውን ጊዜ ይሄ ደስታ ፀሐይዋ ስትገባ ከሚወርረው ሀዘን ጋር ይቀላቀልና አንዳንዴ አልቅስ አልቅስ ይለዋል:: ምክንያት የሌለው ሀዘን ልቡን ሞልቶት አዲስ አበባን ይዞራታል::

አብዛኛውን ጊዜ ወደ ላይ ጊቢ በኩል ይሄዳል:: በስድስት ኪሎ ወርዶ፣ ባራት ኪሎ ተጠምዞ ወደ ፒያሳ ይወጣል:: ወይም ታች ጊቢ ደርሶ፣ ቁልቁል ወደ ጦር ሚኒስቴር ወርዶ ቸርችል ጎዳናን ይወጣል:: ለአራት ቤቱ ወይም ከብዙ ዘመዶቹ አንዱ ቤት ይሄዳል:: አባቱ እንዳይቆጣጠሩት «ጓደኛዬ ቤቶቹ ውጭ አገር ሄደውበት ብቻውን ትልቅ ቤት ውስጥ ስለሚኖር ቤቶቹ እስኪመለሱ አብሬው ልኑር» ብሎ አስፈቅዷቸዋል:: አራት የበላበት ቤት ከዘመዶቹ ጋር ሲያወራ ሲጫወት ያመሸና (ስለሚያስቃቸው ቶሎ አይለቁትም) ወደ አምስት

ሰዓት ላይ ደህና 'ደሩ ብሎ ወደ ውቤ በረሃ ያመራል።

ገንዘብ ያለው ጊዜ እራቱን አትላንቲክ ወይም ንዊጺ ቤት ወይም እቴጌ ሆቴል በልቶ ሲኒማ ይገባል።

ቅዳሜ ቅዳሜ (አንዳንዴ እሁድም ጭምር) ካነቱ ልጆች፣ ካከሉቱ ልጆችና ጓደኞቻቸው ጋር አንድ ዘጠኝ፣ አስር፣ አስራአንድ ሆነው ውቤ በረሀ ከቤት ቤት እየዞሩ ይደንሳሉ። ከንፈ አብሮቻቸው ይዞራል። መደነስ ሲሰለቻቸው ዙሪያውን ይሰበስብና ያስቃቸዋል፣ ግን እነሱ ሲያበስሉ ወይም ሲተኙ፣ ሸርሙጦቹ እንደ ሌሎች ቤቶች እንደ መሆናቸው መጠን፣ በዚያ መልኩ፣ እንደዚያ አጊጠ ለብሶ «እንደ አርቲስት» ሲደንስ ስለሚያዩት፣ ሁል ጊዜ በሳቅ ተከቦ፣ ግን እሱ ራሱ ሳይስቅ ስለሚያዩት እና በተለይም በማሚት እሹሩሩ ምክንያት እነሱን በፍጹም እንደማይፈልጋቸው ስለሚያውቁ፣ አብዛኞዎቹ በየበኩላቸው ይፈልጉት ጀመር።

ዘመዶቹ ቤት ወይም ሲኒማ ወይም በረሃ አምሽቶ ወደ ስድስት ሰዓት ላይ ማሚት ቤት በጓሮ በር ይገባል። አልጋ ውስጥ ገብቶ የራስጌውን መብራት አብርቶ መጽሐፍ ቅዱሱን የሆነ ቦታ ከፍቶ አንድ ምዕራፍ እያነበበ ይቆያታል።

ትመጣና በሩን ቆልፋ ሻሽዋን ስታስር፣ ቀሚሷን ስታወልቅ፣ ጉድ ጉድ ስትል፣ በአይኑ ይከታተላታል። አይ ስታምር!

«እንዴት ናፍቀሽኝ አመሸሁ!» ትለዋለች

«አንቺም በጣም ናፍቀሽኝ ነበር»

አንዳንዴም «ቤት አልተኛህም ዛሬ?» ትለዋለች

«የለም»

«እንዴት አስቻለው?»

«አስችሎት አይደለም'ኮ። ሌላ ቤት ሊተኛ ስለማይችል ነው»

«ውሸታም» ትለዋለች እያቀፈች እየሳመች

«አንቺስ ስንት ወንድ ተኛሽ ዛሬ ማታ?» እሱ መቀለዱ ነው። ግን ልቡ የምር መምታት ይጀምራል

«ሶስት ብቻ»

ቀልዷን እንደሆነ እያወቀም በቅናት «ቂንጥራም!» ይላታል

«አንተ አራተኛ ነህ»

ጠረኗም ትንሽ የተለወጠ ይመስላል። ግን ይሄ እማማ ሳይኮ Suggestion የሚሉት ነገር መሆን አለበት» በሽቆም እየቀለደም

«ተበጂ!» ይላታል



«ብዙኝ»

ጭኖቿ መሀል ይገባና እየሳመ «ማሚትዬ! የኔ ቆንጆ፡ የኔ ንጉ» እያለ እያገባ፣ እያወጣ እያቀረ፣ ሲለፈልፍ፣ ገመዱን ስትፈልግ ድንገት በኃይል ያሳምማታል

«አይ!» ብላ ስትጮህ፣ ከምትር ስትል

«ሁለተኛ ሰሰት ወንድ ተኛኝ፣ አራት ወንድ ተኛኝ እያሉ መቀለድ ይቅር!» ብሎ እንደገና በኃይል ያሳምማታል።

እንዳለመማት ለመደበቅ እየሞከረች እየሳቀች

«ቀልዴን መች ሆነ?» ትለዋለች። ቅናቱ እየከረረ ይሄዳል። እውነም ሲያሳምማት «አይ! ሙት ቀልዴን አይደለም» ስትለው፣ ሁሉቱም እልህ ይዟቸው ደጋግሞ ሲያሳምማት፣ ደጋግማ ውሸቴን ነው ስትለው፣ ብዙ ከቆዩ በኋላ ትሸነፍለታለች

«ውሸቴን ነው የኔ ጌታ፣ ውሸቴን ነው። ሌላ ወንድ እንዴት ልተኛ 'ምችል ይመስልሀል?» ትለዋለች

«ስለዋሸሽ» ብሎ አንድ ሁለት ጊዜ ካሳመማት በኋላ፣ ማኩረፍ ስትጀምር ያባብላታል። «አይዞሽ ማሚትዬ። አይዞሽ የኔ ቆንጆ፣ አይዞሽ። ከልቤ ስለምወድሽ፣ ውሸትሽን 'ንደሆነ እያወኩም እቃጠላለሁ። አይዞሽ» ብሎ መብራቱን ያጠፋል።

አብሯት አድሮ አብሯት ውሎ፣ ሲመሽ ነፍስ ለመቀበል ይወጣና ያመሸበት አምሽቶ ሌሊት ወደ ስድስት ሰዓት ላይ ይመለሳል።

አንዳንድ ቀን ግን ጥሩ ልብወለድ መጽሐፍ ሲያገኝ፣ ነፍስ ለመቀበል ይወጣና እራቱን በልቶ ወደ ሁለት ተኩል ላይ ተመልሶ በጓሮ በኩል ማሚት ቤት ይገባል። ፒጃማ ለብሶ አልጋው ውስጥ ተጋድሞ የዳንስ ቤቱን ሙዚቃ እየሰማ ልብወለዱን ያነባል። ልክ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያነበው። አሁን ግን ማሚት እንደድሮዋ ብቅ አትልም።

የማሚት እሹሩሩ ቤት ቀድሞ ሲታቀድ እንደሚከተለው የነበረ ይመስለኛል። ዋናው ቤት አራት ክፍሎች አሉት።

እንግዳ ቤት፣ መብል ቤቱን መኝታ ቤት አድርጋዋለች። ከዋናው ቤት በስተኋላ በግራና በቀኝ በኩል እርስ በርሳቸው የሚተያዩ ሁለት ረጃጅም ጠባብ የክፍል ተርታዎች አሉ። እያንዳንዱ ተረታ አራት ክፍሎች አሉት። የልጆች ክፍል፣ ያሽከሮች ክፍል፣ ማድቤት፣ እቃ ቤት መዘተርፈ። በአንዱ ተርታ ያሉት አራት ክፍሎች የማሚት አሻሻጮች መኝታ ቤቶች ሆነዋል። ሌላው ተርታ ማድቤት እቃ ቤት፣ እና የዘበኞች መኝታ ቤቶች ሆኗል።

በዋናው ቤትና በሁለቱ የክፍል ተርታዎች መሀል፣ በሶስት ግድግዳዎች የተከበበች የምትመስል ትንሽ ሜዳ አለች:: ሶስት ኮባዎች በቅለውባታል::

የማሚት ቤት ግቢ በአጠና አጥር ተከቦ፣ ከቆርቆሮ የተሰሩ የፊትና የኋላ በሮች አሉት:: የፊት በሩ ዳንስ ቤቱ እስኪዘጋ ድረስ ክፍቱን ሲቆይ፣ የኋላ በሩ ልክ እንደመሸ ይወረወራል::

ክንፈ እራቱን በልቶ፣ ተንሸራሽሮ ወይም ሲኒማ አምሽቶ ሲመለስ በኋላው በር መጥቶ እጅጌውን ይሰበስብና ቀስ አድርጎ እጁን በሁለት አጠና መሀል አሾልኮ፣ የተወረወረውን በር ይከፍታል:: ከገባ በኋላ መልሶ ይወረውረዋል:: እኩለ ሌሊት ሆኖ ማሚት እስከትመጣ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ልብወለድ እያነበበ ይቆያታል::

አንድ ማታ ወደ አራት ሰዓት ላይ ይሆናል:: ክንፈ የተወረወረውን የጓሮ በር ለመክፈት እጅጌውን ሲሰበስብ፣ እሻሻሮጮቹ ተርታ የመጨረሻው ክፍል፣ ማለት በሩ አጠገብ ያለው ክፍል፣ የጠንፍየለሽ መኝታ፣ ድንገት በራ:: አይ ጠንፍየለሽ ኮሚክ! ደርሶ መልስ ስትሰጥ ቆይታ ነው:: ክንፈ በጨለማው አደፈጠ:: ጎሽ! ነገ ምሳ ሲበሉ መቀለጃ አገኘ:: ትንሽ ቆይቶ በሩ ተከፈተ:: አንድ የአየር ኃይል ወጣት ቆቡን እያስተካከለ ወጣ:: ወደ ዳንስ ቤቱ ሲራመድ የኮባውን ቅጠል በቦክስ መታውና እንዴ ዘለለ የደስታ:: ጠንፍየለሽ በደንብ ስጥታዋለች:: ሰውየው ወደ ዳንስ ቤቱ ገባ:: ክንፈ ማሰላሰል ጀመረ:: አሁኑኑ በሩን ከፍቶ ሂዶ ጠንፍየለሽን ምን ስታረጊ ነበር አንቺ ተንኮለኛ? ይበላት? ወይስ አገር ጤና ብላ መብራቷን አጥፍታ በሯን ዘግታ ልትሄድ ስትል በጨለማው በወፍራም ድምፅ «ጠንፋ! አንቺ ቀጣፊ!» ይበላት? ወይስ ዝም ይበልና ነገ ምሳ ላይ ትላንት ማታ ወደ አራት ሰዓት ላይ አሮፕላን ስትማሪ ነበር? ይበላት? የቱ ይሻላል?

ከውስጥ ወደ በሩ በኩል ወጣ ስትል አያት:: ጠንፍየለሽ አይደለችም፣ ማሚት ራሷ ናት! ማሚት:: ክንፈ እዛው እንደቆመ ቀረ:: ማሚት መብራቱን አጠፋችና በሩን ዘጋች:: ወደ ዳንስ ቤቱ ተራመደች:: ክንፈ እዛው እንደቆመ ቀረ:: ማሚት::

ብዙ ከቆየ በኋላ ልቡ በኃይል እንደሚመታ ታወቀው:: ልቡ በፍጥነትና በጩኸት እየመታ እያበጠ ሄደ:: ደረቱን ሞልቶት ጉሮሮውን አጣበበው፣ ሸሚዙን ጠቦት ጉሮሮውን አነቀው:: የሸሚዙን ቁልፍ ለመፍታት እጁን ቢሰድ ሸሚዙ ክፍቱን ነው:: ሆዱ ደግሞ ይገለባበጣል:: እግሮቹ ተብረከረኩ:: እዛው አጠገቡ ጭለማው ውስጥ አንድ ትልቅ ድንጋይ አየ:: እሱ ላይ ቁጭ አለ:: ድንገት ሽንቱ በኃይል መጣበት:: ቁጭ እንዳለ ሸና፣ ግን አስር ጠብታም አትሆንም:: የሱሪውን ቁልፍ መልሶ ሲቆልፍ ሱሪው ረጥቧል:: መቼ 'ንደሸናበት 'ንጃ::



ለረጅም ጊዜ ፊዞ ቁጭ ካለ በኋላ አንጎሉ ይሰራ ጀመር:: ግን አንድ ሀሣብ ብቻ (ወይም አንድ ትርኢት ብቻ) ደጋግሞ ይታየዋል:: ማሚት አልጋ ላይ ተጋድማ፣ ቀይ ልስልስ ጭኖቿን ከፍታ፣ ወጣቱ አይሮፕላን ነጂ ሲከትባት! ሌላ ሀሣብ የለም:: የማሚት ጭኖች እንደተከፈቱ፣ መሀላቸው ቅድም የዘለለው ሰውዬ ቀስ በቀስ ይህ ትርኢት እየተደጋገመ እየተደጋገመ እንደ እብድ ዘፈን እየተደጋገመ፣ እንደ እሳት ድምፅ እየተደጋጋመ፣ ሰውዬው ማማሚትን እየከተተባት፣ ክንፈ ላይ ያልታሰበ ጉድ ፈጠረ! በኃይል አቆመበት!

በኋላ፣ ካንድ ስምንት አመት በኋላ ክንፈ «ነገሩን ላስረዳህ አልችልም:: እኔም ራሴ አልገባኝም:: ግን እንዲህ በመላ የሚመስለኝን ልንገርህ» አለኝ

«የቅናት ስቃይ ከመብዛቱና ከመጠንከሩ የተነሳ ሊያሳብደኝ ሆነ:: ስለዚህ ውስጣዊው ሕይወቴ እብደቱን ለመከላከል ሲል፣ ያ የተኛት ሰውዬ እኔን መሳይ መሆኑን ገለፀልኝ:: ሰውዬው እኔን መሳይ ከመሆኑም አልፎ እሱ ሲተኛት ያው እኔ እንደተኛኋት ያህል እንደሆነ አይነት ነገር ሆነ:: ባጭሩ ውስጣዊው ሕይወቴ ማሚትን እኔ ራሴ በሌላ ሰው አማካይነት እንደተኛኋት፣ በሌላ ሰው ቁላ እንደ በዳኋት አሳመነኝ:: እንዲያውም ስምቼው ወይም አስቤው የማላውቅ አዲስ አይነት አበዳድ ስለሆነ፣ ልዩ ጠንካራ ጣፋጭ የሆነ ስሜት ፈጠረብኝ:: ሀሳቤ ተታለለ:: ስለዚህ ቆመብኝ:: በዚህ አኳኋን ሰውነቴ እንደጣመው አይቶ፣ መቼም ቢሆን ከመሰቃየት መደሰትን ስለሚመርጥ፣ የስቃዩን ጉድጓድ ወደ ደስታ ምንጭ ለወጠው:: ግን'ኮ ይሄ አሁን የምነግርህ በፍፁም ከእውነት የራቀ ሊሆን ይችላል:: ማን ነው ራሱን የሚያውቅ? ይኸኔኮ ጥንት፣ ስልጣኔ ከመወለዱ በፊት፣ ወንዶች ሴቶቻቸውን ይፈራረቁባቸው ነበር ይሆናል:: ስለዚህ ማማሚትን የሚጋራኝ ሰው ላይ ሰውነቴ የጥንቱን የሴት መፈራረቅ አስታውሶ በኃይል ቆሞበት ይሆናል:: ብቻ እኔ አላውቅም»

ክንፈ በጨለማው ውስጥ ድንጋይ ላይ እንደተቀመጠ፣ ለመሰቃየት ሳይሆን ለመደሰት በሀሳቡ ማማሚትና ሰውየው እንደተቆላለፉ እየተመላለስ ሲያያቸው ብዙ ከቆየ በኋላ፣ አንድ ሰው ወደሱ በኩል መጣ:: በጨለማው በደምብ አልታየውም፣ ግን ቀሚስ ቢጤ የለበሰች መሰለው:: እንግዲህ ከማማሚት ቤት በስተጀርባ (አሁን ክንፈ የተቀመጠበት ቦታ) ትንሽ ሜዳ ብጤ አለች:: ቀን ቀን የሰፈሩ ልጆች በድንጋይ «ጎል» ሰርተው በጨርቅ ኳስ ይጫወቱባታል:: ማታ ማታ በዙሪያው ያሉ ትንንሽ ጎጆ-ቢጤ ቤቶችና ጣሳ ቤቶች፣ ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች በጨለማው ግብር ውሃ ይወጡባታል::

ታዲያ አንዲት ቤትዮ ከንፈ ባለመንቀሳቀሱ ስላላስተዋለችው፣ ስተት ብላ እሱ አጠገብ መጣችና ተሚሪን ገልባ ቂጢጥ ብላ መሸናት ጀመረች። ሽንቷ ቶሽ ሲል በኃይል አቆመበት። እሱ እንዳይበቃት ደጋግማ ጡጥ አርጋ ፈሳች። ከንፈ በምኞት ብዛት ሲርመሀ ምንም አልቀረው የማሚትና የሰውየው መቆላለፍ የቀሰቀሰው ልዩ መርገዝ አይነት ምኞት ወደዚች መልኩ-የለሽ የጨለማ ቤት ዞረ። ልክ እሷ ማሚት እንደሆነች ሁሉ፣ በሀሳቡ ጭንገራም እምሷ ቀይ አፉ ተከፍቶ ታየው። ብድግ አለ።

«እምዬ!» አለች በትንሽ ድምፅ፣ ድንጋጤ ባነቀው ድምፅ። ቀጢጥ እንዳለች ቀረች።

«ጭጭ! አለዛ በጩቤ ነው ምዘለዝልሽ» አላት። ዝም አለች። ተትቶ አስነሳት። ጡቷን ነካ። ወጣት ናት። በተሚሪሷ ላይ ቂጧን እየደባበሰ፣ የቂጧ መለስለስ የባሰውን እየቆመበት «ቤትሽ የት ነው?» አላት። በእጇ ወደዛ አመለከተች

ከትንንሾቹ ቤቶች አንዱ በሩ ተከፍቶ ውስጡ አንዲት ኩራዝ በርታ ትታያለች።

«የለም እዚሁ» አላት

«እሺ» አለች። በጣም ፈርታለች

እዛው ሳሩ ላይ ተጋደሙና፣ ሲያስጨንቀው የቆየውን እንግዳ የቅናት ስቃይና ምኞት ውስጧ አፈሰሰባት። ሲለቃት ቀስ ብላ ቤቷ ገባችና በሯን ዘጋች። ጨለማው ውስጥ ብቻውን ቀረ።

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

«ቤት አልተኛህም ዛሬ?» አለችው እንደወትሮዋ እየሳቀች። በሌላ ጆሮ ሰማት። ይህን ጥያቄ የምትጠይቀው ሁልጊዜ አይደለም፣ አልፎ አልፎ አንዳንድ ማታ ነው. . . እሷ ሌላ ወንድ የተኛች ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። ልቡ እየዘለለ

«አልተኛሁም። አንቺስ ስንቱን አጋደምሽ ዛሬ ማታ?» አላት

«ዛሬስ አልቀናኝም ልጄ» አለችው

«ምነው?» አላት፣ ልቡ እስኪያመው ድረስ እየመታ

«ሁለት ብቻ ናቸው» ሆዱ ተገለበጠ። ጉሮሮው ድርቅ ብሎ ደጋግሞ መዋጥ ይፈልጋል፣ ግን ምራቅ የሚሷት ካፉ ውስጥ የለችም፣ አፉ ደርቋል

«ስንት ኖሯል ሌላ ቀን 'ምትተኚው?»

«አራት አምስት»

ድምፁ እንደ ጩቤ ሆዱን ወጋው «ሸርሙጣ!» አላትና ራሱን ደረቷ ውስጥ ደበቀ የሙጥኝ

ራሱን እየደባበሰች «ዛሬ ግን ሁለት ብቻ ነው። አንተ ሰስተኛ ነህ» አለችው። ጠረኗም ትንሽ የተለወጠ ይመስላል። ግን ይሄ እማማ ሳይኮ suggestion የሚሉት አይደለም፣ የተኟት ወንዶች ላባቸውና ጠረናቸው ተላክከውት ከሷ ጥሩም ጠረን ጋራ ተቀላቅሎ ነው።

ደረቷ ውስጥ «ተበጂ! አስር ጊዜ ተበጂ! ግድ አለኝ? ተበጂ» ብሎ ቀና አለና፣ አይን አይኗን እያየ «ተበጂ! ተበጂ!» አላት

«ይልቅ ከምታከርፍ አትበዳኝም?» አለችው እየሳቀች። ልቡ እንደዱሮዋ እየሳቀች!!

«ሸርሙጣ!» አላት ድንገት [illegible] «ምንው ትደጋግመዋለህ? ሸርሙጣ መሆኔን [illegible] ዛሬ ነው'ንዴ የሰማኸው?» አለችው። በጣም አሳዘነችው። [illegible] ራሷን እየደባበሰ

«አትቀየሚኝ ማሚትዬ፣ ቀንቼ ነው'ኮ» አላት። በኃይል ተጠመጠመባት።

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

ጊዜ ከተለማመጣት በኋላ፣ ቀስ በቀስ መንሰቅሰቋን ተወችው:: ትንሽ ቆይቶ እንባዋም መፍሰሱን ተወ:: ክንፈ የራስጌ መብራቱን አጠፋና እጇን እንተርሶ አስተኛት::

ሌሊት ሲነቃ መብራት በርቷል:: እሱ 'ንደተጋደመ ማሚት ከበላዩ ቁጭ ብላ ታየዋለች:: ፊቷ ሀዘን ለብሷል::

«ምነው?» አላት

«አይሀለሁ»

«ለምን አዘንሽ?»

«እንዲሁ»

«ለምን አዘንሽ?»

«አፍ! እንዲሁ ነው አልኩህ! እቀፈኝ»

ሳማት፣ ተሻሸት፣ ቀስ እያለ እያጫወተ ሀዘኗን አስረሳትና፣ መሳቅ መቀለድ ከጀመሩ በኋላ

«ምን ሆነሽ ነበር እንደዛ ምታይኝ?» አላት

ሀዘኑ ፊቷ ላይ ተመለሰ:: ግን አልናገር አለችው:: ብዙ ሲጨቀጭቃት ጊዜ

«ልትተወኝ ነው» አለችው

«ማነው ያለሽ?»

«ሸርሙጣ መሆኔን መገንዘብ ከጀመርክ በቅርቡ ትተወኛለህ ማለት ነው:: ያኔ ምን እሆናለሁ?» አለችና ተጠመጠመችበት:: እንዴት ነው ያሳዘነችው! ደሞ እንዴት ነው የወደዳት! የሚለውን ሲያጣ ጊዜ

«ልታባርሪኝ አስበሻል 'ንዴ?» አላት

«ውይ የኔ ጌታ! እባክህን አትሂድብኝ የኔ ብርሃን! አትሂድብኝ!»

«እሱን ተይው! በአሽሙር በቃኸኝ ሂድልኝ ማለትሽ ነው:: እኔ'ንደሆንኩ በሽጉጥ ብትይኝም አልሄድልሽ»

በወፍራም ኮሚክ ድምፅ «ፐረሰኛውን! እኔ የንኩዬ አባት! ማንም ቢፐልግሽ አፒንጫውን ብዬ አፐር አበላዋለሁ 'ንጂ አልሄድልሽም! ፐረሰኛውን!»

በግድ መሳቅ ጀመረች:: አንድ ሰዓት ያህል የሆነ ያልሆነውን እየቀባጠረ ሲያስቃት ከቆዩ በኋላ ጭኗ መሀል አስገባችው:: እጁን ዘርግቶ መብራቱን አጠፋ::

እንደ ዛሬ አቅፏው፣ እንደ ዛሬ ስሟው፣ እንደዛሬ ሰጥታው አታውቅም:: እንደዛሬ ልቡን አጥፍታው አታውቅም:: ሁለቱም አበዱ::



እብደቱ መሀል ላይ ክንፈ የማታውን አውሮፐላን ነጂ አስታውሶ እየቀና

«ለምን ከሌላ ወንድ ጋር ትተኛለሽ?» አላት

«ለገንዘብ ስል ነው:: ገንዘብ ያስፈልገኛል»

ከሌላ ወንድ ጋር መተኛቷን ትክዳለች ብሎ ነበር:: እውነቱን ስትነግረው ጊዜ በጣም አደነቃት፣ ከልቡ አከበራት፣ እንደምትወደውም የሚል ግሩም ስሜት ፈጠረበት:: የሚያስጨንቅ ግን ደስ የሚል ግሩም ስሜት ፈጠረበት::

«እኔ 'ምወደው አንተን ብቻ ነው፣ ታውቅ የለ?» አለችው

«አዎን»

«ታዲያ ምን ቸገረህ? ሌላው ዋጋ የለው:: እኔ ለገንዘባቸው ስል እንጂ ስሜትም አይሰጡኝ»

«ሙችን?»

«ሙት!» በወፍራም ለስላሳ ድምጿ ጆሮው ውስጥ «እኔ 'ምወደው አንተን ብቻ፣ የሚጣፍጠኝ ያንተ ቁላ ብቻ:: ብዳኝ 'ስቲ በሀይል ብዳኝ፣ ልቤ 'ስኪጠፋ ብዳኝ!»

በአልጋው ምሽግ ውስጥ በጨለማው ተደብቀው፣ ሙቀትና ላባቸውን ለብሰው ብዙ ሕግ ጣሱ፣ ህግ በመጣሳቸው ከድሮዋቸው ይበልጥ ተቀራረቡ፣ ተዋደዱ፣ ተባዱ፣ ተላላሱ፣ ተኛኙ፣ ተገለባበጡ፣ አቃሰቱ፣ ተበጫጨሩ፣ ተቃቀፉ፣ ተቆላለፉ::

ይህን የሕይወት ትግል ሲጨርሱ ጣፋጭ ሞትን ሞቱ፣ እንደተዋደዱ እንደተቃቀፉ ተኙ:: ሰላም:: ከስጋ ማዕበል በኋላ የመንፈስ ሰላም:: እንትልፍ፣ አጭር ሞት::

ከዚያች ሌሊት በኋላ ያልጋ ግንኙነታቸው ተለወጠ::

የክንፈ ቅናት ለጊዜው ይጥፋ 'ንጂ መመለሱ አልቀረም:: እንደ ልማዷ በስድስት ከሩብ አልጋ ውስጥ ገብታ ስታቅፈው፣ በጠረኗና በሁኔታዋ ከሌላ ወንድ ጋር እንደነበረች በቀላሉ ያውቅ ጀመር:: እሷ ደሞ አትደብቀውም:: ሲጠይቃት እንደድሮ የቀልድ እያስመለሰች «ስስት ተኛሁ፤ አራት ተኛሁ» ትለዋለች::

ያነፍሩል:: ትለማመጠዋለች:: እቅፍ ታረገውና እየሳመች እያባበለች «አንተ ምን ቸገረህ ቢተኙኝ? ለገንዘባቸው ስል ነው 'ንጂ ስሜትም አይሰጡኝ:: እኔ 'ምወደው አንተን» እያለች ጭኖቿ መሀል ታስገባዋለች::

ሆን ብሎ በድንገት ድርግም ይልባታል::

አሚት ስትርሙህ፣ እንደሚገባበል የባሰውኑ ያሳምማታል::

በተለወጠ ድምፅ በማቃሰት በሚቆራረጥ ድምፅ «እ! ተወኝ 'ንጂ። ሀ...እ! ምነው የኔ ጌታ?! እ! ውይ! ምን አረኩህ!?» ስትለው ስትለማመጠው «የባሬን ማረኝ የኔ ፍቅር» እያለች ስትሰጠው፣ ስትለዉ ለማምለጥ ስትሞክር፣ በጭራሽ አይለቃትም። አንዳንዴ ተፍጨርጭራ ከጭኖቿ መሀል ስታስወጣው፣ ትክሻዋ ላይ እንገቷ ስር ያሉት ሁለቱ ጉድጓዶች ውስጥ ሁለት አውራ ጣቱን ከቶ በኃይል ይጫንና፣ ፊቷ በስቃይ ሲጨማደድ እያየ፣ በጨካኝ ድምፅ

«በይ'ኮ ክፈች!» ይላታል

«ይኸው'ኮ»

«አስገቢኝ»

«ራስህ አስገባው»

«እኔ መቼ አወጣሁት» ይልና እንገቷ ስር አውራ ጣቶቹን በኃይል ሲጫን

«እሺ እሺ ይኸው» እያለች ትታዘዛለች።

እንደዚህ ብዙ ካሰቃያት በኋላ፣ መፍጨርጨርም መለማመጥም ትተውና «እንደፈቀድክ አርገኝ፣ ብትፈልግ ግደለኝ» ብላው ማልቀስ ትጀምራለች

እንባዋን ሲያይ ቅናቱ በቀሉ ጭካኔው ይጠፋል። በጣም ታሳዝነዋለች። ያባብላታል፣ ይለማመጣታል፣ እንባዋን እየጠረገ ጉንጯንና አርጥብ አይኗን እየሳመ

«ማሚትዬ! አይዞሽ የኔ ቆንጆ፣ አይዞሽ . . . እሺ ይቅር፣ የኔ ቆንጆ፣ ይቅር ይቅር የኔ ቆንጆ የኔ ፍቅር . . . አይዞሽ የኔ ማሚት፣ አይዞሽ»

«ስወድህ ለምን ትጠላኛለህ? ለምን እንዲህ ታረገኛለህ? ለምን ትጨክንብኛለህ?» እያለች ጉንጩን አንገቱን አይኑን አፉን ትስመዋለች። እያለቀሰች እየሳመችው እያቀፈችው እየተጠመጠመችበት፣ በእጅና በጭኖቿ እያቀፈችው . . . በፍቅሯ ታሸንፈዋለች

«እንዲህ እየወደድኩህ ለምን ትጨክንብኛለህ? አሳሳዝንህም?» ትለዋለች

«ምን እንደምሆን 'ንጃ። ጠላሺኝ?»

በሀይል ጥምጥም ትልበትና «ውይ የኔ ፍቅር፣ እንዴት እጠላሀለሁ? እንዲያውም ከድሮ ይበልጥ ነው 'ምወድህ። አይታወቅህም?» ትለዋለች። ፍቅርና ሰላም ይለብሳሉ።

እንደተቃቀፉ እንቅልፍ ያመሰግናቸዋል።



«እንግዲህ እንጦጦ ላይ ፊቱን ያንጉደጉደውና አዲስ አበባ ላይ ሽንቱን ያዘንበው ጀመረ» አለ ክንፈ ታሪኩን ሲቀጥልልኝ።

«ክረምትና ቅናት እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲመጡ ጊዜ የውቤ በረሃን ሽርሙጦች የሙጥኝ አልኩ»

ሲመሽ እንደድሮ ከማሚት አልጋ ይወጣል። ግን እንዳይንሸረሸር ዝናብና ጭቃው በየት በኩል? ማሚት አልጋ ውስጥ ተጋድሞ ሙዚቃ እየሰማ እንዳያነብ በቅርብ የተወለደው ቅናት አያስቀምጠውም።

«ማሚት አሁን የት ትሆን? እንዴ አጣብቆ ያስደንሳት ይሆን? ሙታንታዋን አውልቃ ጭኗን ክፍት አርጋ ትሰጠው ይሆን? ስቃይ። ዘመዶቹ ቤት ሄዶ እራት መብላት ያስጠላው ጀመር። ሰዎች ሁሉ እንዲሁ ሲያያቸው ወይ ሲሰማቸው ብቻ ያለምክንያት ስለሚያበሽቁት ብቻውን ከቅናቱ ጋር መኖርን መረጠ። ከቅናት፣ ከብስጭትና ከብቸኝነት ጋር ሲጃራ መጣ።

ሲመሽ ከማሚት ቤት ወጥቶ «አፍሪካ ሆቴል» ወይም ሊላ የሀምስ ሳንቲም ሆቴል ሄዶ በዝግታ እራቱን በልቶ፣ ከዚያ ቡና ቤት ሄዶ የሲጃራ ጢስ ቀለበት መስራት እየሞከረ ቆይቶ እስኪመጣ ድረስ ሁለት ሶስት ሰዓት ይሆንለታል። ያን ጊዜ ዘፍጭ ቡና ዓይነት የዝናብ ልብስ ከነተበተ፣ ከነቆቧ ይለብስና ወደ ውቤ በረሃ ያመራል። ግን ማሚት ቤት ብቅ አይልም።

መልኩ ቆንጆ ስለሆነ፣ ልብስ ስለሚያምርበት፣ ጥሩ ስለሚደንስ ቤቶች ይወዱታል። ግን በነዚህ ምክንያቶች ደሞ ወንዶች እንደሚጠሉት እንደሚገላምጡት ስለሚታየው በደምብ ተዝናንቶ አይጫወትም፣ አይደንስም። ትንሽ ትንሽ ይፈራል። ደብን ፍርሃት ለማስመሰል እንደ ሁለት ብርጭቆ ኮኛክ አከታትሎ ይጨልጣል። ቶስ በቶስ ፍርሃቱ ይለቀዋል። እንደሚያፈሩቸው ሲያዩ ወንዶቹ ግልምጫቸውን ያቀዛቅዛሉ። እንደማያገላምጡት ሲያይ መዝናናት ይጀምራል። ቆንጆዎቹን ቤት ይመርጥና በዳንስ ያጣድፋታል። ቋንቋ ምሽት በሚገበኛቸው ሶስት ወይም አራት ቤቶች ውስጥ ቆንጆ ቤት ካልጠፋ፣ ግራማፎኑ ዘፈኑን ከተጠለ፣ እና ኮኛኩ ሥራውን ካልቋረጠ፣ ማሚትና የቅናት ስቃይ እስከ ስድስት ሰዓት ኃይላቸውን ያጣሉ። እልፎ እልፎ ብቻ እንጂቱን ጭምጭ ያረጉትና ይለቁታል።

ክንፈ ከማይፈልጋቸው ቤቶች ጋር እንደሚሉ ለመሄድ ከነገረኛቹ ወንዶች መከላከያ እንደሚያስፈልገው ታየው። መጀመሪያ ነገረኛቹ ወንዶች በጠቅላላ ሁለት ዓይነት እንደሆኑ አየ። አብዛኞቹ ፈሪዎች ናቸው። ፈሪነታቸውን ለመደበቅ ጨዋኛትና መፍጨርጨር ያበዛሉ ያገኙትን ወንድ መጀመሪያ በትንሽ ነገር ይፈልጉታል። ነገሩ ከሆነላቸው ግን ወይም ይሸሹታል ወይም የፍቅ ዓይነት ያያዙታል

እንደዚህ አይነቶቶቹን ከንፈ ሁለት ሶስት ኮኛክ ከገለበጠ በኋላ «እንደአንበሳ» ይገላምጣቸው ጀመር:: ነገር መፈለጉን በመጠኑ ተውት::

ብቻ አንዳንዶቹ ነገረኞች በጭራሽ ፈሪ አይደሉም:: እንዲያውም ጎበዝ ናቸው:: እነሱን 'ንግዲህ ከንፈ ቶሎ ብሎ ይተዋወቃቸዋል:: ትንሽ ይኮምክላቸዋል:: የትኛዋን ሴት እንደሚፈልጉ ያስተውልና «ተው ግድየለህም፣ ኢቺ አንትና ሳትወድቅልህ አልቀረችም:: አንተ በማታያት ጊዜ ስታይህ ብታያት! ፊቷ ላይ ፍቅር ተጽፏል:: አይኗ ውስጥ ምኞት ያበራል» ይላቸዋል:: ሌላ ጊዜ ደሞ ሲደንሱ ያጠናቸውና በጭራሽ ዳንስ ባይችሉም በመገረም «እንቺ ሰውዬ'ኮ ጡንቻ ብቻ ትመስለኝ ነበር:: ለካስ አሪፍ ደናሽ ነሽ» ይላቸዋል:: ይጋብዙታል፣ ስለሴትየዋ ይነግሩታል:: ጎበዞቹን በጓደኝነት እየያዘ እንደ ጋሻ ከሌሎቹ ነገረኞች መከላከያ አደረጋቸው:: በዚህ አኳኋን መንገድ ተጠርጎለት ሴቶቹን የላንዳች እንቅፋት ሊጠጋቸው ቻለ::

ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ቤት ሲገባ በተለይ ዘንጦ ይመጣና ይከራል:: ዊስኪ ያዛል:: ሴቶቹን በሙሉ አንድ በአንድ እንደ ዕቃ ያጠናቸዋል:: ደስ ያለችውን፣ በተለይ አይኑ ያረፈባትን ላኪስትራይክ ሲጃራውን እያጨሰ ሩብ ሰዓት ያህል እያየት በአይኑ አድንቋት፣ ያስቀዳውን ዊስኪ ሳይነካ ሂሳቡን ከፍሎ ይወጣል:: አምስት ስድስት ማታ አከታትሎ በዛችው ሰዓት መጥቶ፣ ያቺኑ ሰርቶ ይሄዳል. . . ብቻ አለባበሱ አምስቱንም ጊዜ ልዩ ልዩ አይነት አዘናንጦ ነው::

እስካሁን 'ንግዲህ ሴቶቹ ማን ነው ይኸ ቆንጆ ኩራተኛ፣ ብለው አጠያይቀው የማሚት «ባል» መሆኑን አውቀዋል:: ከንፈ የሚቀጥለውን ሳምንት እዛች ቤት አይደርስም:: በሳምንቱ የተቻለውን ያህል ዘንጦ ኩተፍ ይላል:: በአይኑ ሲያያት የነበረውን ሴትዮ ታንጎ ያስደንሳታል:: ልዩ አይነት፣ ግሩም አይነት ታንጎ ያስደንሳታል::

ከሲኒማ ቀድቶ፣ ከዳንስ መጽሐፍ አጥንቶ፣ ብዙ ጊዜ አስቦበት፣ ከዘመዶቹ ልጃገረዶች ጋር ልምምድ ሲያደርግ ብዙ ሰዓት አጥፍቶበት፣ በመጨረሻ ከደሙ የተዋሀደ አደናነስ:: ሴትየዋን ይህን «ተአምራዊ» ታንጎ አራት አምስት ጊዜ አከታትሎ ያስደንሳትና፣ ልትፈልገው እንደጀመረች ሲያስተውል እርግፍ አድርጎ ይተዋታል:: በአይኑም ዘወር ብሎ አያያት::

ከጓደኛዋ ጋር የታንጎውን ያህል የሚያስደስት ቡጊ ይደንሳል:: በዛውም ወሬ እያወራ በሳቅ ልቧን ያፈርሳታል:: እንደቀልድ እያስመሰለ «ለጓደኛሽ ወደኩላት፣ እባክሽ አማልጂኝ» ይላታል:: በኋላ እንደምትነግራት ያውቃል:: የመጨረሻ አንድ የማይሆን ወሬ አውርቶ በኃይል ያስቃትና «በይ ደህና እደሪልኝ» ብሏት፣ የሚፈልጋትን ጓደኛዋን ግን በአይኑ 'ንኳ ሳያያት ሂሳቡን ከፍሎ ውልቅ ይላል::



ከሁለት ወይም ከሶስት ቀን በኋላ ተመልሶ፣ እንደዚያው ያችን በፀጥታና በኩራት ታንጎ አስደንሶ፣ እቺን በቀልድና ኩምክና ቡጊ አስደንሶ «እረ 'ባክሽን አማልጂኝ!» ብሏት ይሄዳል:: እንደዚህ ሁለት ሳምንት ሙሉ ከጣረ በኋላ የልፋቱን ዋጋ ያገኛል:: ሴትየዋን «የመኝታ ቤትሽን አሳይኝ» ይላታል:: እሺ ትለዋለች:: የቀረው ቀላል ነው:: ከዛ በኋላ በሳምንት ሁለቴ ያህል እዛ ቤት ብቅ እያለ ታንጎውን እየደነሰ የልፋቱን ዋጋ ይከፈላል:: ብዙ ሰው ያለ ጊዜማ መደነስም የለበት «በጓሮ ልግባ 'ባክሽን» ይላታል:: መጥታ ትሰጠዋለች:: አንድ ሶስት ቀን ከሰጠችው በኋላ ከኩራቱና ከታንጎው ጋር ኩምክና እየጨመረ ብዙ ያስቃታል::

በዚህ ዘዴ ወይም «ቴክኒክ» በክረምቱ ውስጥ አንድ ስድስት ሴቶችን ያዘ:: ዛሬ አንዷ «ባሏ» ስላለ፣ ወይም «ንፁህ» ስላልሆነች፣ ወይም በሌላ ምክንያት ልትሰጠው ባትችል፣ ለነገ ወይም ለተነገወዲያ ቀጠሮ ይቀበልና ሌላ ቤት ይሄዳል:: ከስድስቱ ውስጥ አንዷ እሺ ማለቷ ስለማይቀር ማታ ማታ ቢያንስ አንድ አለው::

ሲጠጣ፣ ሲደንስ፣ በጓሮ ገብቶ በድብቅ ሲተኛ፣ ሲጃራ ሲያጨስ የመሸና ወደ ስድስት ሰዓት ላይ ማሚት ቤት በጓሮ በር ገብቶ አልጋ ውስጥ ተጋድሞ ይጠብቃታል:: በስድስት ከሩብ ትመጣለች:: ምኞት፣ ትናንት፣ ፍቅር ማሚት ገላ ውስጥ ተደባልቀው ለከንፈ ገነትማዊ መንግስተ ሰማያት ይሰራሉ::

አምስት ስድስት ሴቶች ይበቁት ነበር፣ ግን እንደሚሰለቻቸውና ካልከፈልከን እምቢ 'ንደሚሉት፣ ወይም እነሱ 'ንደሚሰለቹትና ሌላ ሴት 'ንደሚያምረው ስለሚያውቅ፣ እነሱን እየተደሰተባቸው፣ ለወደፊቱ ደግሞ ሌሎች ቤቶች ውስጥ ሌሎች ሴቶችን በዛችው «ቴክኒክ» ሊያበስል ይጀምራል:: አሁንማ ከልምድ ብዛት የተነሳ ስህተቶቹን እያረመ አዳዲስ ብልሀቶችን እየጨመረ ቴክኒኩን በጣም ስላሻሻለ፣ ሴቶቹን ባጭር ጊዜ ውስጥ እሺ ያሰኛቸው ጀመር::

ዋናው ብልሀት ሁለቱንም ነገር በድብቅ መስራቱ ነበር:: ማሚትም ባትሰማ ይሻላል፣ ሴቶቹን ከሚፈልጉ ወንዶችም ጋር ግጭት ቀረለት:: ዋናው ነገር ደግሞ ሴትየዋን ታንጎ እያስደነሰ «በጓሮ ልግባ?» የሚላት ጊዜውን ጠብቆ፣ የዳንስ ቤቱ ሰውና ጨኸት በሚበዛበት ሰአት ስለሆነ፣ እና ሴትየዋ እሺ ስትለው ልክ ወደ ቤቱ ወይም ወደ ሌላ መጠጥ ቤት እንደሚሄድ ደህና እደሪ ብሎ ጨብጧት ሂሳቡን ከፍሎ በፊት በር ስለሚወጣ ከሱና ከሴትየዋ በቀር ጉዳዩን የሚያውቀው ሌላ ሰው የለም:: ሴትየዋም ራሷ የሥራ ጓደኞችዋ «በብላሽ ትደፋለች» ብለው እንዳይንቋት፣ ወይም ቀንተው ከ«ባሏ» ወይም «ከውሽሞቿ» ጋር እንዳያጣሏት በማለት ነገሩን ትደብቅለታለች:: ስለዚህ እያንዳንዷ ሴት ከንፈን ከማሚት ላይ ለብቻዋ በድብቅ የምትሰርቀው ይመስላታል::

ማሚት በበኩሏ ምን ትሰራ ይሆን? ክንፌ አያውቅም፣ ማወቅም አይፈልግም:: እንደምትወደው ያውቃል፣ እሱም እንደሚወዳት ያውቃል፣ በቃ:: ሸርሙጣ እንደሆነችና ለገንዘብ ሲትል ከሌሎች ጋር እንደምትተኛ ያውቃል፣ እሷም ሩሷ ይብቃው አታውቅም::

እሙሩ አዉሀ ላይ ይቆማል:: ሂዶ በጨለማ በጋር በር ቆሞ ለሰልስ መንዳርደሻ መኪና ውስጥ ይርስ መልስ ለመለወት ማሚት ክንፌ ጋር ስትገባ ሊያያት ይችላል:: ግን ራሱን ለማሰቃየትና በሌላ ማሚትን ለማሰቃየት እንደሆነ ነው'ንጂ ምንም ጥቅም አያገኝበትም:: ቢቀርስ? ባይሆን ሰድስት ሰዓት አለበሆንለትና ሂዶ ለሰልስ ደረቷን ተንተርሶ መፍሪም ድምጿን እየሰማ ከርቢ ጠረኗን እያሸተተ ድርስ ሴት ማሳደድ ይችላል::

እምቤ እምቤ እምቤ ቀይ እምቤ፣ ጠይም እምቤ፣ የተብጠረ ጨቃ እምቤ፣ ጭገሩ የተቀጥቀጠ ጹርጹ እምቤ፣ የተላጨ መላጣ እምቤ፣ መጠሻ እምቤ፣ ትኩስ እምቤ፣ እምቤ እምቤ እምቤ ሲያድሙ፣ ሲያቁርር፣ ሲድጉ፣ በጋር ንበቶ ሲበጽ፣ ሰገ ቀጠሮ ሲቀበል፣ እንዲ እሙሩ ጋራ በታጉን አይተንቀባረረ ለሚመጣው ላምንት እምቤ ሲያጠምድ ያመሻል:: የሴቼሩ ቀልቤት እያሰራ አልአል ሲገለብጥ፣ ሲያምክ፣ ሲያጭበረብር፣ ሲያታልል ያመሻል:: ደሂ ሁሉ ሴሶች ማሚትን ሂዶ አስለማያቃናበት በሷት ማሚትን ለመርሳት::

ሰድስት ሩብ ወይም አስር ጉዳይ ሲሆንለት እፎይ ብሎ ይወጣ ከንቱ በሱት አርግፍ እርጎ ግቡ፣ እንደ «ቱታ» የሥራ ልብስ አውልቆ ግሎት፣ ወደ ማሚት ቤት ያመራል:: እሱ 'ማጠብቁው አረፋን፣ የማጠብቁው ፋቅር፣ የማሚት ገላ፣ ድምፁ፣ ጠረኗ፣ ማቀፏ፣ የ ትናቷ፣ የ ብቻውን ሲሆን የሚያስፈራራው ትናቷ፣ ከነላምና ከጠረኗ ጋር ሲዋሀድ ምንኛ ማለም አለው!! ማሚት::

እንዲህ ሲል ከረምቱን አሰለ

አንድ ማታ፣ እንደልማዱ አልጋ ውስጥ ንብቶ መጽሐፍ ትጸሁን እያነበበ ሲጠብቃት ሰድስት ከሩብ አለፈ፣ አልመጣችም:: ሰድስት ተኩል፣ አልመጣችም:: የጻንስ መዘቃው ቆመ:: ማሚት አስበትመጣ ጊዜው መርዘሙ:: ክንፌ መቁነጥነጥ ጀመረ:: ሰባት ሩብ ጉዳይ . . . ሰባት፣ ሰባት ከሰባት፣ ሰባት ካምስት፣ ሰባት ከሰድስት፣ ሰባት ከአር. . .

ሉብሱን ለበሰ:: ወደ መደንሻው ከፍል የሚወስደውን በር ቶሎ ብሎ ከፈተ:: ጭለማ:: ቤቱ ከተዘጋ ዘመን የለውም:: በጭለማው፣ ወደ መውጫው በር በኩል፣ እንዱ በእንቅልፍ ይተነፍሳል:: ከመኝቹ አንዱ ወይም ከገረዶቹ አንዷ



ማሚት የት ሄ . . . ? [illegible]

[illegible]

"We shall fight them on the beaches, we shall fight them in the streets

We shall fight them in the villages, we shall never surrender"

እያ ቸርቺል" ወንድ ነች'ዝ ከሙሴ በኋላ ማን ወንድ ተወልደ

ቢሉ፣ አኒባልና ቸርቺል በቃ:: ታዲያ አሁን ሙሴ፣ አኒባል ወይም ቸርቺል ሸርሙጣ ቢወዱና ሌላ ጋ ብትሄድ ምን ያደርጉ ነበር? ማሚት ጭዷን! ክንፈ ተገላበጠ:: መብራቱን አበራ:: ገና ስምንት ሰዓት 'ንኳን አልሆነም::

ሞከረ:: ማሚትን ካንጎሉ ለማባረርና ለመተኛት ሞከረ:: አልቻለም:: እየተመላለሰች ትመጣለች:: ዳማ መጫወቻ ላይ ጥቁሮቹ ቦታዎች እልፈው እልፈው እንደሚመጡ:: ጭዷን ከፍታ ለሌላ ሰው:: እቅፍ አርጋው ሊላውን ሰውዬ:: ክንፈ ማሚትን ማባረር ሲያቅተው ጊዜ መብራቱን አጠፋና ይውጣላት ላስባት ብሎ ስለሷ ማሰብ ጀመረ:: አይኑን ጨፈንና ያያት ጀመር:: ትስቃለች:: አንዱን ሰውዬ አቅፋ ትስመዋለች:: ልብሷን ታወልቅለታለች:: ጭዷን ትከፍትለታለች፣ ትገለባበጣለች:: ትጎርስዋለች:: ራቁታቸውን ናቸው:: ተቃቅፈዋል:: እሱ ጭድ መሀል ነው:: ይላታል፣ ይላታል፣ ይላታል፣ ሁለቱንም ያልባቸዋል:: ይቆፍራታል:: ክንፈ ቀስ በቀስ የማሚት መበዳት ደስ እያለው፣ እየቆመበት ሄደ:: የአንድ ቀኗ የኩራዝ ቤት ሴት ግን አሁን ከየት ትምጣ? የማሚትን የውስጥ ልብስ አሸተተው:: ደስ ማለቱ! አልጋው ላይ ወረወረው:: ሌላው መሳቢያ ውስጥ አንድ አስር ሙታንታዎች አሉ:: አንዱ ነጭ ነው:: ሌላው ተለብሷል:: ይሆችንስ አልጋው ውስጥ ሳልገባ አላሸታትም ብሎ ወደ አልጋው ላይ ወረወረ:: ወደ ቁምሳጥኑ ተመለሰ:: እንዲህ ሲፈታትሽ ነበር ትልቅ ቦርሳዋ ውስጥ አንድ የወንድ ቦርሳ ያገኘው:: ውስጡ የወንዶች ፎቶግራፍ አለ:: ሆዱን በሀይል አመመው:: ቦርሳውን ይዞ አልጋ ላይ ቁጭ አለና ፎቶግራፎቹን አንድ በአንድ አየቸው:: ያሁኑስ ቅናት ልዩ፣ ቀፋፊ፣ አስቀያሚ ቅናት ነው:: አስራ አንድ ልዩ ልዩ ወንዶች:: ማሚት እንዴት ቀፈፈችው! ያን ጊዜ ሸርሙጦችን እሺ ማሰኘት ይወቅ 'ንጂ እነሱን ራሳቸውን አያውቃቸውም ነበር:: መኪና መንዳት እየቻሉ ስለሞተር ምንም የማያውቁ ስንት ናቸው? የበረሀ ሸርሙጦች የወንድ ስዕል መሰብሰብ እንደሚወዱ ገና አያውቅም ነበር:: ፎቶግራፎቹንም፣ ውስጥ ልብሷንም፣ ሙታንታዋንም ኮሞዲኖው ላይ አስቀመጠና አልጋ ውስጥ ገባ::

ዘጠኝ ከሩብ:: መብራቱን አጠፋ:: ቸርቺል መንግስተ ሰማያት ሲገባ ሮዝቬልት፣ ስታሊንና ሂትለር እንደ ትንንሽ ልጆች እየሮጡ ይመጡና ዊንስተንን «እንኳን ደህና መጣህ!» «ምን እመጣለሁ? ሞቼ የለ?» «ስለጦርነቱ አንዳንዴ ስናስታውስ እዚህ በኖርክ ብለን እንመኝ ነበር:: አንተ ተንኮለኛ! ስንት ጉድ ሰራኸን» ይሉታል

ቸርቺል ሲጋሩን እየሳበ ሂትለርንም ይገላምጣትና «ወይድ! አኩያህን ፈልግ!» ይላታል:: ሂትለር እየሳቀች:: «ቺሉ! የጦርነቱን



ቅዥት አስታውስህ ነው? እስከዚህ ዋጋ የለውም» ይለዋል:: «እሱ ዋጋ አይኑረው 'ንጂ ዳንከርክ ላይ የፈሰሰው የእንግሊዝ ደም ስዘላለም 'ኮ፣ ቅዥት ነበር» ስታሊን «ትቀልዳለህ ዊንስተን? ያ ሁሉ እውነት አልነበረም

«ቅዥት?»

«አዎን!»

«እንግዲያውስ ያ ሁሉ አመት በህልማችን ነበራ?»

ሮዝቬልት «አንተስ ስታስበው ዊኒስተን፣ እግዚአብሔር አምላክ እያለ ያን ሁሉ ጭቦና ጭቅና በውን ይፈቅድ ይመስልሃል?»

«እንግዲያውስ ቅዥት ነበራ?»

«አዎን»

«እሮይ! እንግዲያው ሕይወት ራሷ ሕልም ናት!»

«ታድያስ! ሞት ማለት ህልምህን ስትጨርስ ነው»

«እንግዲያው ማሚት ትታኝ የሄደችው ህልም ነዋ!»

ህልም፣ ህልም፣ ህልም፣ ህልም. . .

ነጎድጓድ ቀሰቀሰው::

መጀመሪያ ማሚት አጠገቡ እንደሌለች ሲሰማው ድንግጥ አለ፣ ግን ያኔውኑ አስታወሰ:: ዝናቡ ይዘንባል:: መስከረም ገብቶ ስሞኑን ብራ ሰንብቶ ነበር:: ታዲያ አሁን ከረምቱ ቆርቆሮውን እንደ ጥፋት ውሃ ያገርፈዋል:: አሁን ማሚት ብትኖር ኖሮ! ሲዘንብ እንትልፍ ወስዶትም ቢሆን ቀስቅሳ «እቀፈኝ ይዘንባል» ስትለው አስታወሰ

ውጪ ሲዘንብ እየሰሙ ተቃቅፈው ሲስቁ «ዝናቡ ደስ አይልም?» ስትለው «አንቺ ነሽ በዝናቡ ደስ 'ምትይ» ብሎ እየሳመ ጭዷን ሲደባብሳት፣ ወፍራም ለስላሳ ሳቋን በጆሮው እየሳቀች

«እንበለው በዚህ በዝናብ?» ስትለው፣ ለስላሳ ጭድ ሙቀት ውስጥ ገብቶ

«እንበለው!» ሲላት፣ ሲሉት፣ ውጭ ዝናቡ የሚሰራውን ብርድ ያህል እነሱ አልጋቸው ውስጥ ግሩም ሙቀት ሲሰሩ — ይኸኔ 'ኮ በዚህ በዝናብ ካንዱ ጎረምሳ ጋር ትለዋለች:: ትበለዋ! እናቷን! ደሞ ለሷ::

መብራቱን አበራ:: አስራ አንድ ከሃያ:: አጠፋው:: ዝናቡን እየሰማ ኖህንና የጥፋት ውሃን፣ እርግቧንና ቀስተደመናዋን፣ ከዛ እያደር የነአብርሃምን የነሙሴን ነገር ሲያስብ እንትልፍ ወሰደው::

በማለዳ ተነስቶ የማሚትን ልብሶች ቦታቸው መልሶ፣ አስራ አንዱን ፎቶግራፎች ኮሞዲኖው ላይ እንደመጫወቻ ካርታዎች ዘርዝሮ «እሷ

እስክትመጣላችሁ ጣራውን እድንቀት» ብሏቸው፣ እንዲህ በማለቱ በራሱ ላይ ስቆ፣ በጓሮ በር ወጥቶ ሄደ። ለአንድ ወር ማሚት ቤት ብቅ እንዳይል ቆርጧል።

እንዴት እንደሆነ ሳይታወቀው እማማ ሳይኮ ቤት ሄደ። አንድ ሰባት ሆነው ለጉዞ ሲዘጋጁ፣ እቃ ላንድሮቨር ላይ ሲጭኑ፣ እርስ በርሳቸው ትእዛዝ ሲሰጣጡ፣ ሲጯጯሁ ደረሰባቸው። ለሶስት አራት ቀን ላንጋኖ መሄዳችን ነው፣ አብረኸን ና አሉት። ከማሚት ብቻ ሳይሆን ከውቤ በረሃ ለመሸሸ ተመቸው። ሄደ።

ከውቤ በረሃ ጪኸት፣ ትምባሆ፣ መጠጥና ጠቅላላ መበስበስ ጋር ሲነፃፀር፣ ላንጋኖ ንፋሱ፣ ፀሀዩ፣ ሀይቁ፣ አሸዋው፣ ዛፎቹ ከነወፎቹ ገነት ነበር። ቢሆንም አራቱ ቀን ለክንፈ አራት ወር መሰለው።

እማማ ሳይኮ ባይኖሩማ አራት አመት ይመስለው ነበር። እኚህ እማማ ግን እብድ እየመሰሉ ሳይታወቅባቸው በጣም ጤነኛ ሴትዮ ናቸው። የማያውቁት ነገር የለም። ስለ እንስሳት ከጉንዳን ጀምሮ እስከ ዝሆን፣ ራቁታቸውን ከሚሄዱ ጎሳዎች ጀምሮ እስከ ኒውዮርክ አስደናቂ ስልጣኔ፣ ስለ ፍጥረት በጠቅላላው፣ ከምናየው የከከቦች አለም ጀምሮ በማይክሮስኮፕ እንኳ ስለማይታየው micro cosmos ስለሚባለው አለም፣ ስንትና ስንት ክንፈ ሰምቶት የማያውቅ ተአምር ነገሩት። ደግሞ እንደ አብዛኛው አዋቂ ዘመድ እሳቸው ብቻቸውን አይለፈልፉም፣ እንዲህ አርግ እንዲህ አታድርግ ልጅ ነህ፣ ያዋቂ ምክር ስማ አይሉም። ልክ'ንደ እኩያቸው ያነጋግሩታል። ክንፈ ሳይታወቀው፣ ቀስ እያለ ስለማሚት ብዙ ብዙ አስወሩት። ልጅ ነህ ለሴት ጊዜህ አልደረሰም ወይም ከሸርሙጣ ጋር አትጨማለቅ ወይም ሌላ ሌላ ይሄን የመሰለ ነገር ከአፋቸው አልወጣም። ክንፈ ስለማሚትና ስለኑሮዋ በጠቅላላ የሚነግራቸውን ሁሉ ዋጋ እንዳለው ቁም ነገር እህ ብለው ይሰሙታል። ሳያውቅ መንገሩ የሚያሳፍር ቦታ ሲደርስ

«እለፈው አይዞህ። ከዛ በኋላስ?» ይሉታል

ቀስ እያለ ስለማሚት ሁሉንም አጫወታቸው። በአራተኛው ቀንም ሻሸመኔ አብሯቸው የመጣው ከማሚት ለመሸሽ መሆኑን ሳይቀር ገልፆ አስረድቶ

«አሁን ምን ማድረግ ይሻለኛል?» አላቸው

«በጣም አስቸጋሪ ነው» አሉት «ምናልባት ልክ ምንም እንዳልሆነ ያህል ልክ ዛሬ ጠዋት ከቤቷ እንደወጣህ ይመስል፣ ድሮ የምታደርገውን ማድረግ ሳይሻልህ አይቀርም» አሉት። ትንሽ ተመለከቱና እጁን ይዘው

«አትክፋባት አደራህን» አሉት

አያቸው። እንዴት እስከዛሬ አልተጠጋቸውም? እንዴት እስከዛሬ



አልወደዳቸውም?

«እሺ» አላቸው

«አስበው» አሉት «አንተ በፈለክበት ጊዜ ሄደህ ታገኛታለህ። እሷ ግን ራስህ ካልሄድክላት ምንም ያህል ብትፈልግህ አታገኝህም። የት ይሆን? ምን ይሰራ ይሆን? ደህና ይሆን? መች ይመጣ ይሆን? ብላ እስከሞት ብትጨነቅልህም፣ የት ብላ ትፈልግሃለች? ማንን ትልክብሃለች?»

«በጭራሽ አስቤበት አላውቅም»

«ለዚህ'ኮ ነው 'ምነግርህ። ስለዚህ፣ መጥፋት ያማረህ ጊዜ ሳትነግራት አትጥፋ። አለዛ እሷ ከልቧ የምትሰጥህንም ፍቅር በጥፋት መመለስ ይሆናል። አንዳንዴ ነገሩን በሷ ቦታ እየሆንክ ማየት ጥሩ ነው Life is a game that must be played fair»

ክንፈ ብዙ ስሜት ልቡ ውስጥ ሲንቀሳቀስ፣ ማሚትን በሌላ አይን እያየ ሲወዳትና ብቻዋን ትቷት መምጣቱ ሲቆጨው፣ እማማ ሳይኮንም በሌላ አይን ሲያያቸውና የስሜቱ ብዛት ሲያስጨንቀው መሬት መሬቱን ሲያይ፣ እማማ (እንግዲህ በክንፈ አይን እማማ ሳይኮ መሆናቸው ቀረ) «ምነው ዝም አልክ? በጉዳይህ ገባሁብህ?» አሉት

ቀና አለና እያያቸው እየወደዳቸው ፈገግ አለ።

ቃል መናገር አላስፈለገውም።

ክንፈ ልክ እንደድሮው በጓሮ በር ገብቶ ማሚት አልጋ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ እያነበበ ቆየ። ግን መጽሐፉን ከፊተ 'ንጂ ማንበብ አልቻለም። ስትመጣ ምን እንደሚላት፣ ምን እንደምትለው ሲያሰላስል ጠበቃት። ስድስት ሰዓት ሲሆን ሲል የዳንስ ሙዚቃው ቆመ። ክንፈ አይኑን ማሚት 'ምትገባበት በር ላይ ተከለ። ብዙ ብዙ ቆይቶ በሩ ተከፈተ። እንዳየችው በድንጋጤ ትንፋሿ እየተቋረጠ «ክንፍዬ» አለች፣ ውብ ፊቷ በደስታ በርቶ ሁለት እርምጃ ተራመደች። እና ድንገት ቆመች። ደስታው ከፊቷ ጠፋ። ቁጣ ፊቷን አጠቆረው። በፀጥታ ተመልሳ በሩን ቆለፈች። አንድ ቃል ሳይወጣት፣ ክንፈን እንደም በአይኗ ሳታየው፣ ልብሷን አውልቃ፣ ግን ውስጥ ልብሷን እንደለበሰች አልጋ ውስጥ ገባች። ፊቷን ወደ ግድግዳው አዞረች። ተኛች።

ክንፈ ምን እንደሚያደርግ ጨነቀው። መጽሐፍ ቅዱሱን አስቀምጦ በጀርባው ሲጋደም ማሚትን ነካ አደረጋት። ልክ ሰውነቷን እንደተቃጠለች ያህል ወደ ግድግዳው ተጠጋች። እሱም ኩራቱ ተቀሰቀሰ። ወደ አልጋው ዳር ፎቀቅ አለ። ጀርባ ለጀርባ ሆኑ። በመሀከላቸው ኩርፊያ፣ ዝምታ ተጋድሟል። ረጅም፣ ከባድ፣ አስጨናቂ፣ ቀፋፊ ዝምታ።

ክንፈ እያመነታ እጁን ሰዶ ዳሌዋ ላይ አሳረፈ:: አልተንቀሳቀሰችም:: ቀስ ብሎ ወደ'ሷ ዞረ:: ተጠጋት:: አሁንም ሲፈራ ሲቸር አቀፋት:: ትከሻዋ ጋ ጀርባዋ ይንቀጠቀጣል፣ ፊቷን በእጇ ይዛ ትራሱ ውስጥ ታለቅሳለች:: እቅፍ አደረጋት፣ በሰውነቱ ሽፋናት፣ በፍቅር በሀዘን ድምፁ እየተንቀጠቀጠ

«ምነው የኔ ቆንጆ፣ የኔ ፍቅር? ምንድነው?» አላት

የባሰውን መንሰቅሰቅ ቀጠለች::

«ዙሪልኝ የኔ'መቤት፣ ነይ ልቀፍሽ የኔ ቆንጆ!» እያለ በግድ ወደ'ሱ አዞራት:: ተጠመጠመችበት:: አንገቱ ውስጥ መራር ለቅሶዋን ቀጠለች

«ይቅር የኔ ቆንጆ! አታልቅሺ ይብቃ» እያለ ፀጉሯን፣ ትከሻዋን እየደባበሰ ብዙ ካለቀሰች በኋላ

«ምንድነው 'ንዲህ የከፋሽ ማሚትዬ? ምንድነው እንዲህ ብስጭት ያደረገብኝ የኔ ገላ?» አላት

በሀይል እያቀፈችው እየተጠጋችው፣ ምርር ባለ ድምፅ «ለምን 'ንደዚህ ታደርገኛለህ? ለምን 'ንደዚህ ታደርገኛለህ? ለምን? ለምን? ለምን?» እያለች የባሰውን ስቅስቅ ብላ አለቀሰች::

«እሺ አይለመደኝም፣ አይለደመደኝም የኔ 'መቤት ይቅር አይለመደኝም፣ ይቅር ይቅር አይለመደኝም» እያለ ብዙ አባበላት::

ቀስ በቀስ ለቅሶዋ እየበረደላት ሄደ:: ፊቷንና ጉንጯን እየሳመ እንባዋን ጠርጎላት፣ ውስጥ ልብሷን አወለቀላት:: እቅፍ አድርጎ አስተኛት::

ሌሊት ነቁና ጥምጥም ብለው ተቃቅፈው

«አንተ ሳትኖር ቀኑ መሰልቸቱ! ሌሊቱ መርዘሙ! አይነጋም በቃ አንተ ካላቀፍከኝ አይነጋልኝም:: እቀፈኝ ክንፍዬ፣ እቅፍ አርገኝ!» አለችው

«ይኸው አቅፍሻለሁ የኔ 'መቤት»

«በኀይል እቀፈኝ፣ እንደሱ! ሳጠፋ ተቆጣኝ፣ ብትፈልግም ግረፈኝ:: ብቻ ትተኸኝ አትጥፋ:: አትጥፋ! አትጥፋ! እሺ ክንፍዬ? አትጥፋ!»

«አዕ በፍፁም የኔ ቆንጆ፣ አልጠፋም:: መጥፋት ብፈልግም አልችልም»

ሌሊቱን ሙሉ ተፋቀሩ፣ ተቃቀፉ፣ ግን ስላለፈው የሷ ውጭ ማደር ወይም የሱ አራት ቀን መጥፋት ምንም ሳይነጋገሩበት አደሩ::

በነጋታው ቁርስ ከበሉ በኋላ ማሚት ነስራ አንዱን ፎቶግራፎች ከክብረት ጋር አመጣችና ክንፈን



«አቃጥለው» አለችው

«እነሱ ምን አጠፉ?» አላት

«ይልቅ አቃጥላቸው» አለችው:: ድምጿ ውስጥ አዲስ ነገር ተሰማው፣ እምቢ ለማለት የማይቻል ትዕዛዝ

«ቡሄ አልፏል፣ ደመራ ገና አምስት ቀን ቀርቶታል፣ ብንቆይ አይሻልም?» አላት

በጭራሽ አልሳቀችም:: ፊቷ ላይ ሀዘን ወይም ቁጣ ሳይሆን ዝምታ አይነት ነገር አለ

በዝምታ አይኗ ታየዋለች:: ክንፈ በግማሽ ልቡ ሊስቅባት፣ አቅፎ ሊስማት ፈለገ፣ በግማሽ ልቡ ፈራት:: ምን እንዳስፈራው አልገባውም፣ ብቻ ፈራ:: እንደዚህ ሆና አይቷት አያውቅም:: ዝም ብላ ታየዋለች::

ፎቶግራፎቹን አቃጠላቸው:: ማሚትን አያት (ድሮ በልጅነቱ አጥፍቶ እናቱ ሲቆጡት፣ እንዳይመቱት ፈርቶ ቶሎ ሲያቅፋቸው ትገዘ አለው)

ማሚት የተለመደው ፍቅር ወይም ቀልድ፣ ሀዘን ወይም ለቅሶ በሌለበት በልዩ አይነት ድምፅ

«የምነግርህ ነገር አለኝ» አለችው

ፍርሀቱ እያደገ ዝም ብሎ አያት::

«እርጅና ሳስበው ያስጠላኛል:: አየህ፣ አሁን ወጣት ነኝ:: ቆንጆ ነኝ:: ወንዶች ውሃ ይሆኑልኛል:: የጠየኩትን ይከፍሉኛል:: ግን ቁንጅና እንደ ፍሬ ነው:: እየበሰለ ሲሄድ በጣም ያስጎመጃል:: አንድ ሀሙስ ቆይቶ ይበሰብሳል፣ ይረግፋል:: መልኬ ሲጨማደድ፣ ቁንጅናዬ ሲረግፍ ምን እሆናለሁ? ያኔ 'ንግዲህ ወንዶች አይፈልጉኝ፣ የሚጦረኝ ልጅ የለኝ:: ምን እሆናለሁ? እንደ 'ንኮዬ ወሌቱ ሰው ቤት እንጀራ 'ጋግራለሁ? ምን እሆናለሁ? እየዞርኩ እለምናለሁ? እርጅናው እየተጫጫነኝ፣ እግሬ አልሸከምሽ እያለኝ ሲሄድስ? ብቻዬን መንገድ ዳር ኩርምት ብዬ እለምናለሁ? ምን እበላለሁ? ከማን ጋር እነጋገራለሁ?»

ክንፈ እየሰማት የወደፊት ብቸኝነቷን እያየ ፈራላት:: ከልቡ አዘነላት:: እስካሁን፣ ይህን ሁሉ ጊዜ በፍቅር አብሯት ሲኖር፣ ብቸኝነት፣ እርጅና፣ ድህነት እና መንገድ ዳር መውደቅ እነዚህ ፍርሀት የወለዳቸው ጅቦች ከበዋት ሲጮሁ፣ አፋቸውን ከፍተው ሲተነፍሱባት፣ ጥርሳቸውን ሲያፋጩባት፣ በየቀኑ፣ በየሰአቱ ሲቃጡባት ሲያስፈራሯት ይኖራሉ:: ሁልጊዜ አብረዋት፣ እንደ ቀሚሷ ከበዋት፣ እንደ ፀጉሯ ተጭነዋት ይኖራሉ::

ነገር ግን ድምጿ ውስጥ ፍርሀት ወይም ለራሷ ማዘን የሚሉት ነገር የለም። ልክ የሂሳብ ፕሮብሌም እንደምታስረዳው ያህል ረጋ ባለ ድምፅ ትነግረዋለች። እንዴት ጎበዝ ብትሆን ነው! ክንፈ እጅግ አደነቃት። ትላንት እማማ ፍቅርተ (የቀድሞዋ እማማ ሳይኮ) የነገሩትን፣ አሁን እሷ የምትነግረውን ራሱ አስቦ ስላላደረገ ገና ገና ትንሽ ልጅ መሆኑ ተሰማው። እቺ ጎበዝ ሴትዮ፣ እቺ ብቻዋን ከሕይወት ጋር የምትታገለው አስደናቂ ሴትዮ የምትናገረውን የሕይወት ጨካኝ ትግል በአክባሪ ልብ ዝም ብሎ አዳመጠ።

«ስለዚህ አሁን ቶሎ መልኬ ሳይረግፍ ጥቂት ገንዘብ አጠራቅሚ ወይም አንድ ትንሽ ንግድ ማቋቋም፣ እሱ ባይቻለኝ ደሞ አንድ ትንሽ ርስት ገዝቼ ወይም ተመርቼ አንድ ደህና የሚከራይ ቤት መሥራት እፈልጋሁ። ሳረጅ የምወድቅበት ቦታ እንዳሳጣ»

መሬት መሬቱን እያየች «ስለዚህ፣ አልፎ አልፎ ከሌላ ወንድ ጋር የሄድኩ 'ንደሆነ በጣም አትቀየመኝ። ገንዘቡ ስለሚያስፈልገኝ ነው 'ንጂ ልቤ ያንተ ነው» ቀና ብላ በጉልህ አይኖቿ እያየችው

«ይህን ታውቅ የለ?» አለችው

ያለ ድምፅ በከንፈሩ ብቻ «አዎን» አላት

«እኔስ ለገንዘብ ስል ነው 'ንጂ የምወደው አንተን ብቻ ነው። አንተ ግን ለገንዘብ ብለህ አይደለም። ለምን በላዬ ላይ ሴት ትቀያይራለህ?»

ከመደንገጡ ብዛት ለመካድም አልቻለም።

«ምነው ገረመህ? የማላውቅ መስሎህ ኖሯል? ከመጀመሪያ ጀምሬ አውቅ ነበር» ብላ ያብዛኛዎቹን ሴቶች ስም ጠራችለት። ጆሮውን ማመን አቅቶት ዝም ብሎ ሰማት። እንኳን እሷ፣ ከተኛቸው ሴቶች ከራሳቸው በቀር ሌላ ማንም ሰው የሚያውቅ አይመስለውም ነበር።

«አይ ክንፌ! ገና ልጅ ነህና። የሴቶች ፀባይ ገና አልገባህም። አንተ'ዛ ሴት ስትቀያይር እኔ'ዚህ ብቻዬን ስንት ጊዜ 'ንዳለቀስኩ ማን በነገረህ»

በልጅነቱ ምክንያት ትልቅ እፍረት ተሰማው። ይኸን ሁሉ ጊዜ የማታውቅበት እየመሰለው ምን ያህል እንዳስቀየማትና እንዳሳዘናት በግልጽ ታየው። ባንድ በኩል ስለ እርጅናዋ ስትሰጋ፣ በሌላ በኩል በሱ ምክንያት ስትቀና ስትሰቃይ ታየችው።

«ደሞ ዳንስ እንዳንተ 'ሚችል የለም አሉ። ለምን እኔን እንዳንዴ 'ንኳ እየመጣህ አቅፈህ አታስደንሰኝም? ዋጋ የለኝም እኔ? ስለወደድኩህ ነው ዋጋ የሌለኝ? የኔ ፍቅር ሊሰለችህ ጀምሯል፣ አይደለም?»



«የለም» አለ ራሱን እየነቀነቀ

«እሱን ተወው! አይ ክንፌ!» ብላ ትንሽ አየችው

እና ድንገት ጭንቅላቱን በእጆቿ ሳብ አድርጋ ወደ ደረቷ አስጠጋችው። ፊቱን ጡቶቿ ሙቀት መሀል አስገብታ፣ ራሱን በእጆቿ እያሻሸች፣ ፍቅር በሞላበት ለስላሳ ድምጿ «ምነው ክንፍዬ የኔ ሆድ? ምን ሆንክብኝ የኔ ጌታ?» ስትለው ማልቀስ እንደጀመረ ታወቀው። እንደዚህ አቅፋው ጠረኗ እየሸተተው ጡቷ ውስጥ ማልቀስ ምንኛ ይጥማል! ደሞ ስታባብለው ስታቆላምጠው ደስ ማለቱ! ጥምጥም አለባትና ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ።

«ክንፍዬ የኔ ጌታ አይዞህ! ይቅር የኔ ወርቅ! ይቅር አታልቅስ፣ እሺ ይቅር. . .» እያለች አባበለችው። ማልቀሱን ሲያበቃ እንባውን ጠርጋለት፣ ፒጃማውን አውልቃለት፣ እሷም ልብሷን አውልቃ አልጋ ውስጥ ገብተው እቅፍ አደረገችው። እየሳመች እያሻሸች ጭኖቿ መሃል አስገባችው። ምን ያህል እንደምትወደው አሳየችው፣ ሌሎች ወንዶች አስር ጊዜ ቢተኙዋትም ዋጋ እንደሌላቸው አሳመነችው።

እሱም በበኩሉ «ሌሎችን ሴቶች የምተኛው አንቺን ስለምወድሽ ነው» ብሎ፣ እሷን እስከሚያቅፍበት ሰዓት ሌሎች ሴቶች ጋ ካልሄደ ቅናቱና ፍቅሩ ሊያስችል ብለውት እዚህ መጥቶ እንደሚያስቸግራትና ከሚፈልጓት ወንዶች ሁሉ ጋር እየተጣላ ገበያዋንም አበላሽቶ ራሱንም እንደሚጎዳና የሷንና የሱን ፍቅር እንደሚያበላሽ፣ ስለዚህ እኩል ሌሊት ደርሶለት እሷን እስከሚያቅፍበት ሰዓት ድረስ ሌሎች ሴቶችን ማቀፍ ቢያደርግ እንደሚሻል በስፊውና በረጅሙ ውሸትም እየጨማመረ አስረዳት። አሳመነችውም ግን «እሺ ይሁን» አለችው።

እየመሸ እየነጋ ቀናቱ ሲያልፍ ማሚትና ክንፈ በሙሉ ስምምነት መኖርን ተማሩ። እሷም በበኩሏ ለገንዘብ ስል ነው እያለች እንደፈቀዳት ወንድ ትቀያይራለች፣ እሱም አንቺን በማይሆን ጊዜ እየመጣሁብሽ ገበያሽን ከምዘጋብሽ እያለ እንደፈቀደው ሴት ይቀያይራል። ዞረው ዞረው ማሚት አልጋ ውስጥ ይገናኛሉ።

እየመሸ እየነጋ ቀናቱ ሲያልፍ፣ እየዘነበ እያባራ አመታቱ ሲሄድ፣ የማሚትና የክንፈ ፍቅር እየተለወጠ ሄደ። ነገር ግን አልሞተም። ማሚት መጠጥ ቤቷን አሻሻለች፣ ያሻሻጮቿንም ቁጥር ከአራት ወደ ዘጠኝ አበዛች። ምን የመሰለ ቤት ካዛ ፓፓላሬ አሰራች፣ ክንፈም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ገባ፣ ሁለተኛ አመቱን እንደጨረሰ ስልችቶት ወጣ። ሥራ ያዘ፣ ስካራም አጭበርባሪ ሆነ፣ አስወጡት፣ ሌላ ሥራ ያዘ። ይህ ሁሉ ሲሆን ማሚትና ክንፈ ቀናቱን ተራምደው አመታቱን ዞረው ማሚት አልጋ ውስጥ ይገናኛሉ።

ማሚት የወንድ መአት ትቀያይር 'ንጂ፣ እሷና ክንፌ የሚተኙብትን አልጋ ማንም ሌላ ወንድ ገብቶበት አያውቅም ይባላል:: ክንፌም በበኩሉ የሴት መአት ይቀያይር 'ንጂ ማንም ሌላ ሴት አልጋ ውስጥ አድሮ አያውቅም ይባላል::

የማሚትና የክንፌ ፍቅር ከተጀመረ ዘጠኝ ዓመት ሆነው:: ኖና ይቀጣጣል፣ ይቀጣጣል እየተለዋወጠ፣ እንሱንም እየለወጠ፣ ቀናቱን እየተረመደ አመታቱን እየዞረ፣ ማሚት አልጋ ውስጥ እየተገለባበጠ እየተለዋወጠ...

Meysor Bro
t.me/BooksandYou



# ምዕራፍ ሰባት ተኩል

## መጪው ትውልድ

«ሰው ከሚያደርሰበት በላይ መንጠራራት ይገባዋል፤
እንዲያ ካልሆነማ መንግስተ ሰማያት ምን ሊሰራ ነበር?»
ሮበርት ብራውኒንግ

ቀለሙ የማሚት ፍቅር ያዘውና አንድ ሰሞን ገም ብሎ መምጣት ጀመረ:: አንድ ማታ ሰክሮ ጓደኞቹ ሊያስተኙት ሲሉት «የማሚት እሹሩሩን ቺንገር በሙዳይ ካላመጣችሁልኝ አልተኝም» ብሎ አላቸው:: ሌላ ቀን ማሚት ደህና ስትሰማ ጊዜ «ውይ እደኒ ይፍለዘ ያ ቆንጆ ትንገዝ ልጅ ነው 'ንዲህ ያለው?» አለችና፣ በሙዳይ ላይ እንደናቶቿ ደምብ በአልጋ አቀረበችለት::

ከዚያ በኋላ ቀለሙ «የማሚትዬን እምብ ጫፍ እንዳያስመኘኝ» ብሎ፣ አምስት ወር ሙሉ እምብ ያመ:: እሱንም ማሚት ደህና ስትሰማ «ውይ እደኒ ይፍለዝ እኔ ልሙምልት» አለችና ያመ ልጓሙን ፈታችለት:: ለብሱን ከለበሰ በኋላ ወርሳውን መጨ ያለውን ገንዘብ በሙሉ አወጣና «ያለኝ ይኸው ነው» ብሎ ሰጣት::

ቆጥራ «ስማንያ ብር፣ አይበዛም?» አለችው

«እስ 'ንጂ! የሚገባኝ ባገኝ ትበልን እሸፍልሽ ነበር» አላት

«ለምን?» ስትለው

ለእናቴትቱ እንደሚያዝልይ ሰማት እጆቹን እያገላበጠ «ቆንጆዬ ነሽ የሽጋ መጨረሻ ነሽ:: እጅን ታጥቦ ነው የሚጠረሽ:: የመቶ ሴቶች ውበትና የሺ ሴቶች ደም ግባት ስትቶኚል:: ድምጽሽ ገላ ጀንበር ነሽ:: እየሩሳሌም ነሽ»

«አንተም ቆንጆዬ ነህ:: የት ነው 'ምትማረው?» አለችው

«ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ»

«ስንት ዓመትህ ነው?»

«ብዙ ነው»

«ስንት ነው?»

«ለሃያ አንድ ፈሪ»

እየሳቀች «አንተ ውሸታም! አስራ ስድስት ዓመትህ አይደለም?»

«አሥራ ስምንት» አለ፤ በእድሜው ብዛት እየኮራ «ትግሬ መጫወት ከጀመርኩ ሁሉን የለኝም፤ ጎበዝማ ሲሻገር ብሉ ንገሬኝ» አለባት

«ኦ ዋሪደ ነው» አለችው

«ያሹውልሽ» አላት

እየሳቀች ስግንያ ብዬን መለስችለትና «ለጎንዙበ አይደለም፤ ደስ ስላለኝ ነው 'ጎጂ'» አለችው

«እንግዲያውስ ምን ላድርግልሽ?» አላት

«በፈተና አንደኛ ወጣልኝና መተብህ ንገረኝ» አለችው

«እሺ» አላት

«እንዲቀናህ» አለችና፣ እስኪያዋርበት ሰማው ስታበቃ፣ አንደኛ ለብሁን አስመለቀችው።

ከሁለት ወር በኋላ ተመልሶ «እንዳልኩሽና አንደኛ ለመውጣት ሞክርኩ፡ ሳወራ በሪያ 'ጎኒ' ብቅ አላልኩም። ግን አንደኛ ልወጣ አልቻልኩም፤ ሁለተኛ ሆንኩ፡ ይቅርታ አድርጊልኝ» አላት

«ገር የለም የኔ ሽጋ፤ መሞከርህ በቂ ነው። ና» አለችና፣ ለብሁን አመሰፈቀ ስታበቃ «ምን ያህል እንደምትወደኝ አሳየን 'ስቲ'» አለችው

«በኋላ የፈለኩትን ታረግልኛለሽ?» አለችው

«የፈለግሽውን፡ ብትፈልጊ ዛሬ ሌሊት ከሰማይ ላይ ጥምጥ ከከብ ለቅሜ፣ ጫት አንደ የጠሀይ ሙሬ አስጥሰና፣ በብርሃን ከር በክብ ደቃ ልቶ ያንንት ሀብል እሰራልሻለሁ። ጨረቃዋን ሰርቄ መኪታወት እንድትሆንሽ እሰጥሻለሁ። ቀስተደመናዋንም ከሰማይ ላይ ገፍፌ ለመቀነትሽ እሰጥሻለሁ። ሰማዩ ባዶውን ይቅር፤ ላንቺ ያልሆነ ለማን ሊሆን ይችላል?»

ሳቋ እንዳያመልጣት ለማስመሰል እየሞከረች «እኔ እሱን ሁሉ አልፈልግም» አለችው

«ታዲያ ምን ትፈልጊያለሽ?»

«ደህን መሰከር መሆኑን፤ ከአጉል ጓደኞች ጋር መዋር ተውና፣ በርትተህ ትምህርትህን አጥና። ለሚመጣው ፈተና አንደኛ ውጣልኝ»

«እሺ ያይኔ ብርሃን የልቤ ሙቀት፤ እሺ የኔ ፀሐይ። እንቺ 'ንዳልሽ የንሀቤ ብሌኮታ የሁባቤ ጨረቃ፣ ማግኔትዬ የኔ ኮከብ፤ የኔ ፋናስ፣ የኔ ኮረንቲ፤ የኔ እሳት፤ የኔ ችግ ብርሃን፤ የኔ ኩራዝ»



ችግና ኩራዝ ላይ ሳቋን መቋጠር አቃታትና ከት ብላ ሳቀች።

ቀለሙ አፍሮ መሬት መሬት እያየ «ችግና ኩራዝ ተሳስቼ ነው የጨመርኩት» አላት

ሳቋ እንዳይጎዳው እቅፍ አድርጋ ሳመችውና «ንግግርህ ደስ ይላል። ግን እኔ ቁም ነገር ነው 'ማወራልህ» አለችው «እሺ? ማጥናት ሲደክምህ ወይም ሲሰለችህ ኳስ ተጫወት፤ ቢኒማ ግቡ። እንጂ መጠጥ እንዳትጠጣ፣ ሽርሙጣ ቤት እንዳትሄድ። እሺ?»

«በዚህ ከተስማማን በሁለት ሳምንት አንዴ እየመጣህ እንዳዬሁት ተጫውተን ትሄዳለህ»

«እዬ!?»

«ሙት!»

«በሁለት ሳምንት አንዴ?»

«አዎን። እነስ?»

«ኧረ የለም የለም! እንዲያውም በዛ። የለም የለም አልበዛም። እንዲያውም አነሰ። የለም አላነሰም። ም. ም. ምን ይሻለኛል?»

«አይዞህ 'ምትለው ገብቶኛል»

«እኔስ ዛሬ የመጨረሻዬ ነው ብዬ ነበር። የዛሬ ሁለት ሳምንት እንድመጣ ትፈቅጂልኛለሽ?»

«አዎን። በሁለት ሳምንት አንዴ እየመጣህ ታየኛለህ። በሚመጣው ፈተና አንደኛ ከወጣህልኝ ደሞ በሳምንት አንዴ ይሆናል»

«ሙች?»

«ሙት!»

«ይሄ ነገር በህልሜ ይሆንና ብቻ!»

«አይደለም የኔ ሽጋ» አለችና ሳመችው

«ብቻ አትቀልጂኝ 'ጎጂ'፤ ለምን ይህን ሁሉ ታረጊልኛለሽ?»

«እኔ እንጃ። ደስ ትለኛለህ። ምናልባት አሥራ ስምንት ዓመትህ ስለሆነና፣ አይጋህ ትልልቅ ስለሆነና፣ ፍንጭት ጥርስ ስላለህ ይሆናል» አለችው

አሁን ቀለሙ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ውስጥ በትጋት ትምህርቱን ሲከታተል፣ ሲያነብ፣ ሲያጠና ይስነብታል። የመንግሥት ሰማያት ማታ ሲደርስለት ገላውን ታጥቦ ልብሱን ቀይሮ፣ በምኞትና በመጓጓት ልቡ እየዘለለ ማሚት እሹሩሩ ቤት ከተፍ ይላል . . .

ጉዳዩ ቤት እራት በልተን ቡና ስንጠጣ ነበር ፡ ክንፈ ይህን ታሪክ ስነግረው ሲስቅ ቆየና ተስበቀስ ያዝን ጀመር። ላስናናው ሞከርኩ

«እንተን ስለሚመስላት'ኮ ነው። እሱን ከመበሳሸት ስታድነው አንተን ያዳነች ይመስላታል። ምን ያህል እንደምታፈቅርህ አይታይህም?» አልኩት

«ይታየኛል። ግን አንተ የማይታይህ ነገር አለ» ድምፁና አይኖቹ ውስጥ ብዙ ሀዘን! «ከንግዲህ እኛ መጨረሻው ትውልድ መሆናችን ቀረ፣ በጂው ትውልድ ነን። አዲሱ ትውልድ የኛን ቦታ መውረስ ጀመረ። ልጅነትን ጨብጠነው ስንል ምን እንደደረሰብን አይ። እንግዲህ እርጅናን መሸሽ እንጀምራለን። አንድ ቀን ስንነቃ ተራውን እንደ ሎሚ ይዞ ሲጨምቀን ሲያጨማድደን እናየዋለን፡ ተጥሎ . . . » ዝም አለ። ሁለታችንም ተከዝን።

ክንፈ «ትድም አንድ ትንሽ ልጅ «አባባ ስዓት ስንት ነው? አለኝ» አለ። አሁንም ዝም አልን

«ለኔ ደግሞ ትላንት አቶብስ ውስጥ አንድ ተማሪ ወንበር ለቀቀልኝ» አልኩት

ዝም

«ባለፈው ሳምንት ማማጊት ፀጉሬ ውስጥ አንዲት ሽበት አገኘች» አለ «እና መሳት ክተወኝ ይኸው ሳምንት ሊሆናት ነው»

ዝም

«ከእርጅናና ከሞት የቱን ትጠላለህ?» አልኩት

«ሁለቱንም»

ዝም

«አለመወለድ ይሻል ነበር ይመስልሃል?» አለኝ

«እኔ 'ንጃ»

ዝም

«የሚያስቅ ነገር አጣህ በቃ?» አለኝ

«ከዚህ ሁሉ መሸበር በኋላ፣ ከዚህ ሁሉ መጨነቅ፣ ከዚህ ሁሉ መናጨርጨር በኋላ፣ ፈጣሪን ብናገኘው የምንወቅሰው ይመስልሃል?» አለኝ

«እኔ 'ንጃ»

ዝም

«የሚያስቅ ነገር አጣህ በቃ?» አልኩት



«አጣሁ»

«በል ተወው»

ዝም

«ገንዘብ ይዘሃል?» አለኝ

«አዎን»

«ባባትህ ሄደን እንስከር»

«ልጅነታችንን የወጪ እንጋብዘው?» አልኩት

«ተነስ እንሂድ»

እርጅና በር ሲያንኳኳ እንዳይሰማን ስክረን ስናበቃ፣ ልጅነታችንን በጓሮ በር ሸኘነው። ሳንስመው ተሰናበትነው። የት እንገናኝ አናውቅም እንሳመው?

# ምዕራፍ ስምንት

## አለም

የማሚት እሹሩሩ አሻሻሮች ብርሃኑን ከመጀመሪያውኑ ወደውት ነበር፡፡ ጴጥሮስ ጠንፍየለሽን ሲጫወትባት ታዝበው ብርሃኑ ጓደኛው ትርሲትን እንደ ባሏ ሲያንቀባርራት ሲመለከቱ ጊዜ፣ ከመውደድም አልፈው «ወንድማቸው» አደረጉት

ቀስ በቀስ ቤተኛ ሆነ፡፡ አንድ ላይ ተሰብስበው ቡና እየጠጡ ወሬ ሲያወሩ፣ ስለወንዶቻቸውና ስለልብሳቸው፣ ስለእቁብና ስለገንዘብ፡ ስለሌላ ቤት አሻሻሮችና ወንድ ስለመቀማማት፣ ስለ ፀጉር ሰራ ቤትና እዚያ ስለሚያዩዋቸው ልጃገረዶች፣ ስለፍቅር፣ ስለጥንቆላ፣ ስለወንድና ስለማታለል፣ እነሱ ስላታለሉት ወንድና እሱ ስላታለላቸው ወንድ፡ ማለት ባጭሩ የቡና ወሬ ሲያወሩ፣ ብርሃኑ ቃል ሳይተነፍስ ቁጭ ብሎ ይሰማቸው ነበር፡፡

መጀመሪያ ላይ ወሬያቸው አፉን ያስከፍተው ነበር፡፡ እየለመደው ሲሄድ ግን ይሰለቸው ጀመር፡፡ ወሬያቸው ያው እንደ ኑሮዋቸው ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታይ ሲሰማ ያስገርማል 'ንጂ፣ በኋላ ራሱን ይደጋግማል ይሰለቻል፡፡

ብርሃኑ እድል ያጋጠመው ጊዜ እያንዳንዳቸውን ለብቻ ሲያዋራቸው፣ እንዴት ሽርሙጥና እንጀመሩ ምን እንደሚመኙ፣ ምን እንደጎደላቸው፣ እንዴት እንደተበደሉ፣ ኑሮ እንዴት እንደሚጫወትባቸው ሲያወሩለት፡ የተጣመመ የተሰናከለ እድላቸውን እያየ ያዝንላቸው ነበር፡፡

ፅጌ ደህና ትጸር ነበራት፡፡ አንድ ቀን ባሏ በሥራ ምክንያት ደሴ ሄዶ ሳለ፣ የባሏ ጓደኛ ሊያጫውታት መጣ፡፡ እራት በሉ ጠጅ ጠጡ፡፡ ጠርሙስ ውስኪ ይዞ መጥቶ ነበር፣ አሰከራት፡፡ አብሯት አደረ፡፡ ባሏ ሲመለስ ፈታት «ታዲያ አሁን ባሌና ያ ጓደኛው እንደዱሮዋቸው ጓደኛሞች ናቸው፡፡ አንዳንዴ አብረው እዚህ ይመጣሉ፡፡ አይገርምም?»

ሮዛ የጣልያን ክልስ ናት፡፡ እንግሊዝኛ ትችላለች፣ እስከ ዘጠነኛ ክፍል ድረስ ተምራለች፡፡ ዘጠነኛ ክፍል ሳለች አንድ አስተማሪዋ አስረገዛት «አረገዝኩ» ስትለው «ከማን?» አላት «ካንተ ነዋ» ብትለው

«በቾክ ይረገዛል 'ንዴ?» አላት

ወለደች፡፡ ለናቷ ሰጠች፡፡ ሽርሙጥና ገባች፡፡



ሁሉም የራሳቸው ታሪክ አላቸው፡፡ ስንቱን ዘርዝረን እንችላለን፡ እንተወው፡፡ እንዲሁ በደፈናው ብርሃኑ ስለነሱ በጠቅላላ ያስተዋለውን እንናገር፡፡ በጣም በጣም አሳጥረን፡፡

ብርሃኑ በሀሳቡ እንዲት አሻሻጭ መጠጥ ስትጋበዝ የጠጣችው መጠጥ ዋጋ ሩብ ወይም ግማሽ ለሷ የሚታሰብላት ይመስለው ነበር፡፡ በኋላ ያያል፣ ገባው፡፡ በሙሉ ለቤቱ ነው፡፡ (ማለት ለማሚት እሹሩሩ ነው) አሻሻጯ ሳንቲምም አታገኝም፡፡ ግን አሻሻሮቹ የሚመጣውን ወንድ «ጋብዘኝ፣ ውስኪ ግዛልኝ፣ ቢራ ግዛልኝ፣ ጋብዘኝ» እንዳሉ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ወንዱ የተወሰነ ገንዘብ ለማውጣት ዝግጁ ነው፡፡ ለምሳሌ አምስት ብር እንበል፡፡ ሴትዮዋ ደግሞ ይህን ያለጥርጥር ታውቃለች፡፡ ታዲያ መኝታ ቤቷ ወስዳ የፈለገውን ስጥታው አምስት ብሯን መቀበል ስትችል፣ በመጀመሪያ የሁለት ወይም የሶስት ብር መጠጥ ታስገዛውና፣ በኋላ ለራሷ 'ንግዲህ የቀረውን ሁለት ወይም ሶስት ብር ትወስዳለች፡፡

ለምን? ለመታየት፡፡ መጠጥ መጋበዟን ሌሎች አሻሻሮች እንዲያዩላት፣ እና ይልቁንም እትዬ ማሚት ራሳቸው ከማንም እንደማታንስ እንዲያውቁላት፣ ሎኸ ብላ

«ሆሁተ! ውስኪ!» ትላላች፡፡ ትንሽ ቆይታ የውስኪ ብርጭቆውን ለሆሁተ እያሳየች ሎክ ብላ «ሆሁተ! ድገሚኝ!» ትላለች

እትዬ አንድ ፈገግታ ጣል ያደርጉባታል፡፡ ምናልባት ጋባዥ በዝቶ የሰከረች 'ንደሆነ፣ በነጋታው በቡና ሰዓት እትዬ የሷን ወሬ ያነሱና፣ ልክ ጀብዱ 'ንደሰራች ያክል ያደረገችውንና የተናገረችውን አስደናቂ ነገር ቀምመው፣ አስፋፍተው ለሌሎቹ ያወሩላታል — ደስ እንዲላትና ሌላ ጊዜም እስክትሰክር መጠጥ እንድትጋበዝ፣ ለሌሎቹ አሻሻሮች ደግሞ አርአያ እንድትሆን ያወሩታል፡፡

አንድ ቀን ብርሃኑ ካንድ ሶስት አሻሻሮች ጋር ሲያወራ

«መጠጥ ስትጋበዙ የዋጋው ሩብ ወይም ግማሽ ለናንተ 'ሚከፈላችሁ ይመስለኝ ነበር» አላቸው፡፡ ሳቁበት

«አይ አንተ! የማታስበው ጉድ የለ!»

«እረ 'ትዬ ደግ ስለሆኑ ነው'ንጂ ሌሎች ቤቶች ብታይ፡፡ አሻሻሮቹ ለቤት ኪራይም ማዋጣት አለባቸው፡፡ አንዳንዴ ለምግብም፡፡ እኛ ግን ለምግብና ለቤት ኪራይ ማሰብ የለብንም» አሉት

የሴቶቹን ሀሣብ ስማንያ በመቶ የሚሞላው ልብስና እቁብ ነው፡፡ ልብሱም የፍላጎት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ያው እንደመጠጡ የውድድር የፉክክር ጉዳይ ይሆናል፡፡ በእትዬ ብርታት፡፡

ከሴቶቹ አንዷ አንድ ቀሚስ ስታሰፋ፣ እትዬ ቀሚሷን ሊያደንቁላት፡

[illegible]

እንባዋ ይወርዳል:: መተረጉንም ተወው:: የሚለውን አጣ:: በሌጁ ብቻ ንንጭዋን ቀስ እያለ ያሻሻል:: እንደሚያለቅስ ትንሽ ልጅ ንፍሟን ወደ ውስጥ ሳበች:: መሀረቡን አውጥቶ አናፈጣት:: እያዞረ አላት:: ሌላ ምን ይበላት? ምን ይበል? ምን ያድርግ?

«እንዳቸው 'ንኳ ቢያመኝ ቢያቅፉኝ፣ እና ገንዘቡ ቢቀርብኝ!» ድምጿ ውስጥ መጓጓት፣ ሀዘን፣ ፀሎት፣ ክስ፣ ብስጭት ተቀላቅሏል

«ሾርሙጣ መሆን! አይ ብርሃንዬ! ለጠላትም አይስጠው!»



[illegible]

ኃይለሚካኤል የጠባቂዎቹን አጅ እንደያዘ «እረ» አለው

ብርሃኑ አሁንም በኃይል ሙሾ «እምን እንተ» አለውና መሙውን ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሰተዋለ ቀስ ብሎ «ፊተቃት» አለው

ኃይለ ሚካኤል ለቀቃት:: ወደዛ ሸሸች::

«ሁል ጊዜ ቤቶችን ስትመታ እያያለው:: እስቲ ዛሬ'ንኳ ከመንድ ጋር ተማታ:: ና» አለውና ኮቴን እጥልቆ ወርውሮለት እሱ ራሱ ወደ ኃይለሚካኤል ተወረወረ:: ኃይለሚካኤል ነገሩ በጣም ድንገተኛ ስለሆነበት ለጠብ ባለመዘጋጀቱ ብርሃኑ በተከናው ደረቱን ሲመታው

ወደ ኋላው ተፈንገለ። ብርሃኑ በእግሩ ረገጠው። «እሆ» አለና ሲገላበጥ ኮላሊቱን ደገመው። ያህን ጊዜ ተመልካቾቹ ከድንጋጤያቸው ነቁና ዘለው ብርሃኑን ያዙት። ኃይለሚካኤልን ከወደቀበት አንስተው ደግፈው ወንበር ላይ አስቀመጡትና በብርጭቆ ውሃ አጠጡት። ሁለት ሰዎች ደግፈው ወደ ውጭ ሲወስዱት ዘወር አለና በሚያቃስት ድምፅ ብርሃኑን

«እንገናኛለን» አለው

ብርሃኑ «ነገ 'ዚሁ ነኝ» አለው

ትርሲት መጣችና ኮቱን አለበሰችው። ጫማው ተፈቶ ነበር። እሰሮ ቶና ሲል ማሚት በትልልቁ አይኖቿ ታየዋለች። ፊቷ ላይ ፍርሀትም የለ፣ ጥላቻም የለ። ሌላ አይነት ስሜት አለ። ብርሃኑም ዝም ብሎ አያት። አይኖቿ ድንገት ሰብር አሉ፣ ተርገበገቡ። ወደዛ አየች።

በነጋታው ማታ ብርሃኑ ማሚት ቤት ቁጭ ብሎ ሲጠብቅ ኃይለሚካኤል ከጥላሁን ጋር መጣ።

«ጥላሁን ሁለታችሁም ለኔ ጓደኞቼ ናችሁ። ለኔ ስትሉ ታረቁልኝ» ብሎ አስታረቃቸው። ለሶስቱ ቢራ ጠጡ።

ከንድ አራት ቀን በኋላ፣ ሌሊቱ ወደ ስምንት ሰዓት ላይ (ይሄ ሁሉ የሚሆነው ሰዓት እላፊ ከተረ በኋላ ነው) ብርሃኑና ትርሲት የመጨረሻ ዳንስ ደንሰው ቤቱ ሲዘጋ፣ ሙዚቃው ቆሞ ብርሃኑ ሂሳቡን ከፍሎ ወደ ውስጠኛው ክፍል ገባ። በስ በኩል ወደ ትርሲት መኝታ ቤት ሄደ።

ሶስት ሰዎች ብርሀኑን ለመከተል ተነስተው ወደ ውስጠኛው ክፍል ሊገቡ መጋረጃውን ሲከፍቱ፣ ማሚት ከባንኮኒው ኋላ እንደቆመች ገንዘቧን ስትቆጥር ነበር።

«ወዴት ነው?» አለቻቸው ገንዘብ መቁጠሯን ሳታቋርጥ። አንደኛው ትርሲትን እንደሚፈልግና ለሶስት ብርሃኑን ደብድበው ሊወስዷት እንዳቀዱ ገብቷታል

«ወደዚህ ነው» አለ አንዱ።

«መውጫ በር ያቺው ነው?» አለቻቸው

«ለመውጣት አይደለም»

ሆሁ ቆማ ይህን ስትመለከት ነበር። ማሚት

«ሆሁ፣ ዘበኞቹን ጥሪልኝ። ዱላ ይዛችሁ ኑ በይልኝ» ብላ ሰዎቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ቀና ብላ በውብ አይኖቿ አየቻቸው

«ትርሲት ልጄ ናት። ብርሀኑ ደሞ የልጄ ባል ነው። እስቲ ማን



ወንድ ነው ልጆቼን የሚነካብኝ?» አለችና ገንዘብ መቁጠርዋን ቀጠለች። ውቤ በረሀ ውስጥ ማሚትን የሚደፍር የለም። የፖሊስ ካፒቴን ሻለቃ ምናምን የሆኑ ወንዶች አሏት። ሶስቱ ሰዎች ከርከር ሳያበዙ ሂሳባቸውን ከፍለው በሰላም ሄዱ።

በነጋታው ብርሃኑ ለስራ ተልኮ ለአራት ወር ያህል ወደ ጂጂጋ መሄድ እንዳለበት ሰማን። ይህን በሰማን በሁለት ሳምንቱ እኔ ጥላሁንና ብርሃኑ ትሪያኖን ቡና ቤት ቁጭ ብለን ቢራ እየጠጣን ስንጨዋወት፣ ብርሃኑ «ለመሆኑ፣ ክንፈ ፈሪ ነው ስንል አልነበረም?» አለ

ጥላሁን «ብትጠይቀው እሱ ራሱ ፈሪ፣ ቅዘናም ነኝ ይልሀል»

«እናንተም ቅዘናም ነው ትሉኛላችሁ። እኔ ግን ፈሪ ለመሆኑ ማስረጃ የለኝም። እናንተስ? ያው እንደኔ ናችሁ ወይስ በእውነት ፈርቶ ሲሸሽ አይታችሁት ታውቃላችሁ?»

እኔና ጥላሁን ተያየን። ፈርቶ ሲሸሽ አይተነው አናውቅም። ግን ፈሪ መሆኑን እርግጠኛ ከመሆናችን የተነሳ «በእውነቱ ፈሪ እንዳልሆነስ?» ብለን ራሳችንን ጠይቀን አናውቅም። ብርሀኑ ጥላሁንን እያየ

«እርግጥ ነው፣ ሰዎች ነገር ሲፈልጉት አንተ ብዙ ጊዜ ተደባድበሀለታል። ግን አንተ እዚህ ባትኖር ኖሮ እነዚህን ነገር የፈለጉትን ሰዎች ይሸሻቸው ነበር ወይስ ይጣላቸው ነበር?»

አሁንም እኔና ጥላሁን ዝም አልን።

ብርሃኑ ቀጠለ «ይህን የምልበት ምክንያት አለኝ። ከአምስት ወይም ከስድስት ቀን በፊት፣ እርብ ማታ ነበር ይመስለኛል፣ እኔና ክንፈ እሹሩሩ ቤት ቁጭ ብለናል። ሙዚቃው ቆሟል። ቤቱ ሊዘጋ ነው። በሩ ጋ አራት የካሳ ጭፍሮች ቆመዋል — ዮሀንስ፣ ታደሰ፣ ሉልሰገድ፣ ሀብቴ። ሞቅ ብሏቸዋል። ካሳ ራሱ የለም። ታውቃላችሁ 'ንግዲህ፣ ካሳ ያለ እንደሆነ አንድ ሰው ተጋግዘው እንዲመቱ አይፈቅድላቸውም። አንድ ለአንድ ብቻ ነው 'ሚፈቀድላቸው፣ ወይም በሚዛን ሁለት ለሁለት፣ ሶስት ለሶስት። ብቻ ምን ልበላችሁ፣ በሚዛን «fair fight!» ካሳ ከሌለ ግን ሰባት ሆነው አንዱን ሰው ቢደበድቡት ቅር አይላቸውም። ይህን ሁሉ ክንፈ በደምብ ያውቃል። እና እንዳልኳችሁ፣ እኔና ክንፈ ቁጭ እንዳልን አራቱ ባንኮኒው ጋ ቆመው፣ ትርሲት ከውስጠኛው ክፍል ወጥታ ወደኛ ልትራመድ ስትል፣ ሀብቴ እጇን ዘርግቶ ፀጉሯን ያዘና ጎተታት «እይ!» አለች። በተዘረጋ መዳፉ ቂጧን ጧ አደረጋት።

ከመናደዴ የተነሣ አንድ ጥፊ ብሰጠው እንደሚሞት እርግጠኛ ነበርኩ። ታድያ ልገድለው ልነሳ ስል፣ ክንፈ በእጁ ትከሻዬን አጥብቆ ያዘና

«ለኔ ተውልኝ» ብሎኝ፣ እሱ ራሱ ብድግ ብሎ ወደነሱ ተራመደ

«ሀብቴ!» አለ:: ድምፁ ውስጥ ያለው ሥልጣን፣ ትእግሥና ስድብ ይሄ ነው አይባልም:: ያስፈራል:: ሀብቴ ደንግጦ ትርሲትን ቶሎ ለቀቃት:: ልክ አባቱ በድንገት እንደ ሙኸበት ልጅ! ትርሲት ፀጉሯን እያስተካከለች ወደኔ መጣች:: ክንፌ እዚያው እንደቆመ ከአራቱ ጋር ትንሽ ከተፋጠጠ በኋላ በሚያንቋሽሽ ድምፅ

«አዎን! ካሳ 'ዚያ ብቻውን ይደባደባል፣ እናንተ ጀግኖች እዚህ ተጨማለቁ» አላቸው::

«የት የት?» አሉት

«ጋዲሴ ቤት» አላቸው

ተንጋግተው ወጡ:: ክንፌ የበሩን መወርወሪያ ቶሎ ብሎ ወርወር አያደረገ ወደኛ ጋ መጣና ቁጭ አለ

«ትርሲትዬ፣ በታክቲክ ስላስጣልኩሽ አልሳምም?» አለና ጉንጩን አስጠጋላት:: ሳመችው:: ሌላ ጉንጩን አዞረላት::

«እዚህ» አላት:: እየሳቀች ሳመችው:: ውስኪውን ጨለጠና

«በሉ መሽቷል እንተኛ» ብሎ ተነሳ:: እኔም በጣም ገርሞኝ ዝም ብዬ አፌን ከፍቼ ሳየው

«ደህና'ደሩ» ብሎን ሲጋራ እያቀጣጠለ ወደ ማማት መኝታ ሄደ:: እኛም ወደ መኝታችን ሄድን:: ልብሴን ካወለቅኩ በኋላ መገረሙ ትንሽ አለፈልኝና «ለምን እንደዚህ እንደሰራ እጠይቀዋለሁ ብዬ አሰብኩ:: በነጋታው ማት ጠየቅኩት::

«አንተ በአንድ ምክንያት ጄኔቫ መሄድ ያልቻልክ 'ንደሆነ፣ ባንተ ፋንታ ማን ይላካል?» አለኝ

«በቀለ» አልኩት

«ሀብቴ የበቀለ ያክስት ልጅ ነው» አለኝ

«ታዲያስ?» ስለው ጊዜ በሽቀ

«ታዲያስ ታዲያስ! ምን ታዲያስ ትለኛለህ? አስበህ ድረስበት» አለኝና ሄደ::

ብዙ ገዜ ካሰብኩበት በኋላ ገባኝ:: ከሀብቴ ጋር ስጣላ ወይ ፖሊስ ጣቢያ እንሄዳለን ወይ ይከሰኛል ወይ አንድ ያሰቡልኝ ነገር አለ:: ወይም የበላዮቼ ውቤ በረሃ የሚረብሽ ዱርዬ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት መልዕክተኛ ሆኖ እንዴት ይሄዳል? ብለው ያስተናኛል:: ወይ የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ የመውጫ ቪዛዬን ይከለክለኛል:: ወይም የፍርድ ቤት ቀጠሮ ይኖርብኝና መሄድ አልችልም ይሆናል:: ማለት በኔ ፋንታ የሥራ ባልደረባዬ አቶ በቀለ ወደ ጄኔቭ ይላካል::



ገባችሁ?»

እኔና ጥላሁን ዝም አልን:: ክንፌን የምናውቀው መስሎን ነበር:: ለካስ አናውቀውም::

ይሄ ነገር በተደረገ በነጋታው ክንፌ ሀብቴን መሥሪያ ቤቱ ድረስ ሄዶ በሚከተሉት ቃላት ገሰፀው «አንተ ሀብቴ፣ ለመሆኑ በግ ነህ ወይስ ምንድነህ? ብርሃኑ የቀናተኛ መጨረሻ መሆኑን እያወክ፣ በቢሱ ሽጉጥ ይዞ እንደሚዞር እያወክ፣ የትርሲት ፍቅር እንዳሳበደው እያወክ፣ ይሄን ሁሉ እያወቅክ፣ ቁጭ ብሎ በአይኑ እያየ ትርሲትን ቲማን ትመታለህ? እርግጥ ነው፣ አንተን ገድሎ የትም አይገባም:: ግን አንተ ከሞትክ በኋላ እሱ ቢታነቅ ቢሰቀል ላንተ ምን ይጠቅምሀል? አብድ ነህ ወይስ ጤነኛ ነህ?»

ሀብቴ ክንፌን አመስግነው፣ ከሞት አድነኸኛልና እስከመቼም ቢሆን አልረሳውም አለው:: ቢራ ጋበዘው:: ብዙ ካወሩ ከተጫወቱ በኋላ ክንፌ ያጋጠመውን «የገንዘብ ችግር» በወዳጅነት አጫውቶት ኖሮ፣ ሊለያዩ ሲሉ ሀብቴ በግድ አስገድዶ መቶ ሃያ ብር አበደረው:: ሀብቴ 'ንኳ እርዳታ ሊሰጠው ነበር የፈለገው፣ ክንፌ በብድር ስም ካልሆነ አልቀበልም ብሎት፣ ሀብቴ ደግሞ እሺ አንተ እንዳልክ፣ ግን እኔ ባትመልስልኝ እፈቅዳለሁ ብሎት፣ በስንትና ስንት ፍቅርና ጓደኝነት ተለያዩ::

ብቻ ይህን በኋላ ነው ክንፌ እየሳቀ «ለመጽሐፍህ ነው?» እያለ ያጫወተኝ:: ስለዚህ አሁን ወደ ትሪያኖን ቡና ቤት እንመለስና፣ እኔና ጥላሁን ዝም ብለን ስናየው ብርሃኑ ሌላ ወሬ ቀጠለ

«እንዳልኳችሁ፣ ይሄ የሆነው ያለፈው እሮብ ማታ ነበር:: የነገ ሳምንት መሆኑ ነው:: ከትላንት ወዲያ ሊሊት ደግሞ አንድ ነገር ደረሰብኝ:: እሱስ ልክ ሲኒማ ውስጥ እንዳለሁ ያህል ነበር:: ስሙኝ

«ከትርሲት ጋር መኝታ ቤት ገባን:: በሩን ዘግተን ልብሳችንን አውልቀን አልጋ ውስጥ እንደገባን ድንገት በሩ ኳ! አለና ተበርግዶ ተከፈተ:: ትርሲት «ብርሃኔ!» ብላ ተጠመጠመችብኝ:: በሩን የበረገደው ጠብዚራ እንደ ሁለት እርምጃ ተንገዳግዶ ገባ:: ሁለት ሌሎች ተከተሉት:: ይታያችሁ 'ንግዲህ፣ ራቁቴን አልጋ ውስጥ ነኝ:: ትርሲት ደንግጣ ተጠምጥማብኛለች:: ከበላዬ ሶስት ጀግኖች ቆመዋል:: እንዴት ቀን ፈርቼ አላውቅም:: እንደኛው ስውዬ ትርሲትን

«ልብስሽን ልበሺ» አለና ውስጥ ልብሷን ወረወረላት:: እኔ እጄን ወደ ሱሪዬ በኩል ስዘረጋ ሁለተኛው ሰውዬ

«You stay put!» አለኝ:: እጄን መለስኩት:: ትርሲት ውስጥ ልብሷን ስታጠልቅ

እንዱ ሰውዬ፣ መልኩ በጭራሽ እንዳይታይ ኩታ ተከናንቦ በሩ ጋ ቆሟል። በቆን እጁ ሽጉጥ ይዟል።

«የመሸበት እንግዳ በር ጥሶ ይገባል 'ንዴ? ወይ ስምንተኛው ሺ!» አለና፣ ሽጉጡን ሰዎቹ ላይ እንዳነጣጠረ ከበሩ ዘወር ብሎ መንገድ እየለቀቀላቸው እንዲወጡ በእንገቱ አዘዛቸው። እርስ በርሳቸው ተያዩና ትተው ወጡ

ሰውየው በበሩ እንገቱንና ትከሻውን አውጥቶ «ተበላሽህ ዛሬ!» አለና አንድ ጊዜ ተኩሶ። በድንጋጤ ነጠርኩ። ትርሲትም ደንግጣ እንደገና ተጠመጠመችብኝ

«አይዞሽ ምንም አይደለም» አልኩና አቀፍኳት። በሀሳቤ ሰውየው ጥላሁን ይሆን 'ንዴ? አልኩ። ግን ጥላሁን ፊቱን አይሸፍንም፣ ሽጉጥም አይዝም። ዘሎ ገብቶ በክስና ቴስታ ነው። ሰውየው ወደኛ ተመልሶ እየሳቀ

«እንዴት እንደፈረጠጡ ብታዩ!» አላት

«ምን?» አለችው ትርሲት

«ፈረጠጡ!» አላት

ኩት ብላ መሳቅ ጀመረች። ክንፈ ኩታውን ከጭንቅላቱ አወረደና ሱሪዬን እያቀበለኝ «መጨረሻ የነበረው ሰውዬ እንቅፋት ሲመታው ጊዜ ተደናቅፎ ከፊቱ የነበረውን ሰውዬ ቂጥ ነከሰው። የተነከሰው ምስኪን ደንግጦ

«ዋይ! እማምዬ! ጅብ በላኝ!» እያለ እየጮኸ ቂጡን እያሻሸ ፉጧውን ቀጠለ» አለ። ትርሲት ሳቋን ስትለቀው የጤና ያለመሆኑ ተሰማኝ። በጣም 'ሚያስደነግጥ ሳቅ ነው። ያበደች መሰለኝ። መንከትከቷን ቀጠለች።

ክንፈን ሳየው ጢጋ ብሎ «እንደ ሲኒማ» አለና እንዴ በጥፊ መታት። ሳቋ ቀጥ አለ። እቅፍ አደረኳትና ብዙ ጊዜ ቆየሁ

ክንፈ «እዚህ ልታድሩ አትችሉም» አለን። ልብሳችንን ለበስን። ክንፈ ነጠላውን አውልቆ ትርሲት አልጋ ላይ ተወውና አብሮን ቤት ድረስ መጣ። እየሄድን «ብቻ ለማንም እንዳትናገሩ። ሌላ ቀን ይጠቅመን ይሆናል» አለን። «ደሞ የተሰረቀበት ሰውዬ ይጣላኛል»

የክንፈ ተንኮልና ሳቅ ፊቱ ላይ መታየት ጀመሩ። ቅድም ስለ ማሚትና ስለብርሃኑ ስነግረው አለም ቀልደኛ መሆኗን ለጥቂት ጊዜ ረስቶ ነበር። አሁን ግን የሰረቀውን የውሸት ሽጉጥ እያስታወሰ፣ ሕይወት የምትባለውን ቀልድ እንደልማዱ ሊሰቅባት፣ የድሮው ክንፈ ሊሆን ጀመረ።



ሌላ ጊዜ ክንፈን ስለዚህ ጉዳይ ጠይቄው «ጉብዝና ምናምን አልነበረም። የውሸት ሽጉጥ ነው እየተባልክ?» አለኝ

ብርሃኑ ወሬውን ሲጨርስ «ታዲያስ፣ ምን ይመስላችኋል?» አለን እኔና ጥላሁንን

«እሱማ የሰራኸውን ነገር የበለጠ ጉብዝና ያደርገዋል። ብቻ ጉብዝና አልነበረም ልበልልህ። እሺ ለምን አደረከው?» አልኩት

«ራስህ ማሚት ለብርሃኑ እንደመውደቅ ብላለች እያልከኝ!? ስለዚህ ብርሃኑ መሄድ አለበት»

«እንደፈለገችው ሳታገኘው ሲሄድባት የባሰውኑ እየጓጓችለት፣ የባሰውኑ ፍቅር አይዛትም?» አልኩት

«አዎን»

«ታዲያስ?»

«ታዲያስ ምን ልበልህ? ቂል ነህ! እሱ ለአራት ወር ይሄዳል። ባራት ወር ውስጥ ስንት ነገር ያደርጋል። ማሚትን ዘጠኝ አመት ሙሉ አብሬያት ኖሬያለሁ። ባራት ወር ውስጥ አንድ ፍቅር ነቅዬ ማውጣት ያቅተኛል?»

«ቢያቅትህስ?»

«አያቅተኝም»

«እንዲያው ቢያቅትህስ?»

«ፕላን አለኝ»

«ፕላንህ ቢፈርስስ?»

«የማይፈርስ ፕላን ነው። ተመልከት»

አሁንማ ያው የማውቀው ክንፈ ሆነ። አለም ቀልድ ናት። ክንፈም ቀልደኛ ነው። ሁለቱም ተጫዋች ናቸው። ሰው መጫወቻቸው ነው። አለም በሰዎችም ላይ በክንፈም ላይ ትጫወታለች። ክንፈ በሰዎችም ላይ በአለምም ላይ ይጫወታል።

ሁለት ቢሬታ አዘዘና «ተመልከት» አለኝ «መጀመሪያ ብርሃኑ አዲስ አበባን መልቀቅ አለበት። ምቀኞች እንዳያስቀሩት እጠብቃለሁ፣ እድሜ ለሽጉጤ!» አለና እየሳቀ የደረት ኪሱን መታ መታ አደረገ። «ብርሃኑ ሄደ። እንበል እንግዲህ ጥላሁን ይመጣል። ማሚት ስትስቅ ጥላሁን እንዴት አፉን ከፍቶ እንደሚያያት አይተሃል? ስትራመድ ከኋላዋ ሆኖ በዳሌዋ ውዝዋዜ እንደሚሰክር ልብ አርገሃል? እሷ ስትኖር ከልማዱ የባሰ ለጠብ እንደሚቸኩል አስተውለሃል? ቆይ'ኮ! ጥላሁንና ብርሃኑ ጓደኞች መሆናቸውን ማሚት ታውቃለች። ስለጥላሁን ጉብዝና

አንድ ሶስት ሰአት ያህል ካወራሁላት በኋላ፣ ጥላሁን ብርሃኑን ጠብ እንዳስተማረው ጣል አድርጌላት ሳበቃ፣ ስለጥላሁን ደግነትና ሀቀኝነት ደሞ እሞላታለሁ። ለጥላሁን አትወድቅለትም፣ ግን ትንሽ በሌላ አይን ታየዋለች። ገባህ?»

«ቀጥል»

«ብርሃኑ ሲሄድ ትርሲትን ላንተና ለጥላሁን አደራ ትቶላችሁ ይሄዳል። ማሚትን ስለጥላሁን ብዙ ብዙ ሰብኬ ካዘርኩባት በኋላ፣ ብርሃኑ በሄደ በሁለት ወሩ፣ እኔና ማሚት ጥላሁንና ትርሲትን ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ናይት ክለብ እንጋብዛቸዋለን። አራታችንም እንሰክራለን። ማሚት ጥላሁንን ልቡን ታጠፋዋለች። ትርሲትን ለኔ ይተውልኛል።

«እንግዲህ ትርሲት ወንድ ካገኘች ሁለት ወሯ ነው። ሰክራለች። ተ.ኃ.ስ ናይት ክለብ በጨለማው አጣብቄ ታንጎ አስደንሳታለሁ። የሰበከት መአት አጠጣታለሁ። ይታይሃል? ከዛ ጥላሁን ቤት እንሄድና እዛ ያስቀመጥኩትን ጠርሙስ ውስኪ እንጨርሳለን። ጥላሁን ሰፊ አልጋ ላይ አራታችንም እንተኛለን። እንደምንም ብዬ ጥላሁንና ማሚትን አንድ ላይ አስተኛቸዋለሁ። የደምቡን ይጀምራሉ። ትርሲት ሰክራለች። ወንድ አምሯታል። ሌሊት። ትሰማቸዋለች። እኔ እዛው ነኝ ስራ አልፈታሁም። ታዲያ የሚያስችላት ይመስልሃል?

«በዚህ አኳኋን ብርሃኑን ከማሚት ልብ ባልነቅለውም አነቃንቀዋለሁ። ቀስ ብሎ ራሱ ይነቀላል። ትርሲትንም ያንድ አመት ምኞቴን እወጣባታለሁ። አይን አይኑን አልላታለሁ!! ሰላም ጥቅም ነው። ባጭሩ ሁሉም ተጠቀመ፣ ጥላሁንም ማሚትን ሞላ፣ እሷም የብርሃኑን አይነት ወንድ አገኘች»

ቢራውን ችው አርጎ ጨረሰና አውቆ በሀይል «እስ!» ብሎ አገሳ

«ታዲያስ፣ ምን ይመስልሃል?» አለኝ

«እውነትም የማይፎርሽ ፕላን ነው። ግን ይፎርሻል»

«ለምን?»

«እኔ አስፎርሸዋለሁ»

ተንኮለኛ ሳቁ ከአይኖቹ መንጭቶ ፍንጭቶ ጥርሱ ድረስ እየወረደ «አታስፎርሸውም» አለኝ

«ሄጄ ለጥላሁን እነግረው የለ?»

«አትነግረውም»

«ማነው ያለህ?»

«እኔ ራሴ»



«እንተም ፕላኑ ውስጥ አለህበታ!»

«እኔ?!» አልኩት እየሳቅኩ

«ቆይ ላስረዳህ» አለኝ። ሌላ ቢራ አዘዘና

«ደራሲ መሆን ትፈልጋለህ» አለ «ደራሲ ለመሆን ዋና የሚያስፈልግህ ነገር ምንድነው?»

«ምንድን ነው?»

«ሰውን ማወቅ ነው። መብላት፣ መጠጣት፣ ስራ መሥራት፣ ልብስ መልበስ፣ መተኛትና ሬሳ መሆን ላይ ሰው ሁሉ ያው ነው። ማንም ከማንም አይለይም። አንድ ሰው ከሌላው የሚለየው መውደድና መጥላት፣ መደሰትና ማዘን ላይ ነው። ስለዚህ አንተ ማወቅ ያለብህ፣ የምትጽፈው ስለስሜትና ስለሀሣብ፣ ስለፍቅርና ጥላቻ፣ ስለሳቅና እንባ መሆን አለበት» ቢራ ለመጠጣት አቋረጠ «ግን ስለዚህ ጉዳይ ስንትና ስንት መጽሐፍ ተጽፏል። ስለዚህ አንተ ስትጽፍ ካንተ በፊት ሌላ ደራሲ የተናገረውን እንዳትደግም መጠንቀቅ አለብህ። ለዛ ለዛሬ ደራሲ መሆንህ ቀርቶ የገደል ማሚቶ ትሆናለህ እየጠጣህ 'ንጂ» አለኝ።

ጠጣሁ። እሱም ጠጣ። ቀጠለ።

«እንግዲህ ወደ ጉዳዩ መጣን። ከዚህ በፊት ማንም ደራሲ ሞክሮት የማያውቅ ልዩ አይነት ታሪክ እንድትጽፍ ላግዝህ ዝግጁ ነኝ»

«እንዴት አርገህ?»

«ቆይ። ብርሃኑ እስኪመለስ ድረስ፣ እኔና ትርሲት፣ ጥላሁንና ማሚት፣ አራታችን ለምናደርገው ግንኙነት እንቅፋት እንዳትሆነን ቃልህን ስጠኝና እነግርሀለሁ»

«ንገረኝና ከተስማማን እሺ»

ያለቀ ሲጋራውን መኮስተሪያ ውስጥ እየደፈጠጠ

«እሺ። መጽሐፉ በሁለት ይከፈላል። ክፍል አንድ፣ እኔና ማሚት ፍቅራችንን በሰላም ስንቀጥል፣ ብርሃኑ ድንገት ብቅ ብሎ የማሚትን ፍቅር ይሰርቅብኝና ይጠፋል። በቃ። ከእንግዲህ ወዲያ ብርሃኑ መጽሐፉ ውስጥ የለበትም። ግን መጽሐፉ በሙሉ ስለብርሃኑ ነው። ይታይሃል? እኔ በሁለት ወር ውስጥ ብርሃኑን ከማሚት ልብ ነቅዬ ጥላሁንን በሱ ፈንታ እተክላለሁ። ግን ጥላሁንን ስተክል በቀላሉ እንዳይነቀል አድርጌ ነው»

«ልክ 'ንደ ችግኞች» አልኩት

«ልክ 'ንደ ችግኞች። ግን ሁለት ወር ይፈጃል። ደሞ ምን ያህል ሳይኮሎጂ እንደሚያስፈልገው አትርሳ። ይሄ ሲደረግ ማሚትን ጥላሁንንና ትርሲትን አንድ ሁለት ጊዜ ሀገር ፍቅርና ተ.ኃ.ስ ናይት

ክለብ እጋብዛቸዋለሁ:: ሁለተኛው፣ ክፍል ለማዘጋጀት ያህል:: ገባህ?»

«ቀጥል»

«ክፍል ሁለት፣ እኔ ማሚት ጥላሁን ትርሲት ቀጋስ ናይት ክለብ ሄደን ምን እንደምናደርግ ቅድም ነግሬሃለሁ:: ግን አትርሳ፡ ብርሃኑ አራታችንም ሀሳብ ውስጥ አለ:: እሺ ከዛ ጥላሁን ቤት እንሄዳለን፡ ስሜታቸውን እስኪረሱ ድረስ አስከራቸዋለሁ:: ጥሩ expression ነው አይመስልህም? ስሜታቸውን እስኪረሱ:: መጽሐፍህ ውስጥ እንድታስገባው እንዳትረሳ

«እንግዲህ አራታችንም ጥላሁን አልጋ ውስጥ ገባን:: አልጋ ውስጥም ብርሃኑ አብሮን ይገባል:: ሁለቱም ሴቶች የሚወዱት ብርሃኑን ነው፡ የምንበዳቸው ግን እኛ ነን:: እንግዲህ እኔስ ትርሲትን ስበዳት ምን ይሰማኛል? እሷስ ምን ይሰማታል? ጥላሁንስ እኔ እዚያ ሆኜ ማሚትን ሲበዳብኝ ቅን ልቡ ውስጥ ምን ስሜት ይተራመሳል? እሷስ 'ኔ እዛው ሆኜ ጥላሁን ሲበዳት፣ ስለ 'ኔና ብርሃኑ እያሰበች ለጥላሁን ስታንቋልጥ ምን ይሰማታል? ትርሲት? የማሚት አሻሻጭ ሆና ከማሚት ጋር አንድ አልጋ ተኝታ የማሚት ባል ሲበዳት፣ ያውም የብርሃኑ ጓደኛ ሆኖ፣ ያውም ሌላው የብርሃኑ ጓደኛ (ጥላሁን) እዚያው እያለ፣ ትርሲትስ ምን ይሰማታል?» አራታችንን አንድ በአንድ ስትወስድ::

ሀ/ ስለ ብርሃኑ ምን እናስባለን?

ለ/ ስለ እርስ በርሳችንስ ምን እናስባለን?

ሐ/ ስለ ራሳችንስ ምን ስሜት ይሰማናል?

እነዚህን ሶስት ጥያቄዎች ሶስት ጊዜ መላልሰህ ትጠይቃቸዋለህ

1/ ቀጋስ ናይት ክለብ ስንደንስ

2/ ስክረን አልጋው ላይ ስንባዳ

3/ ስካሩም ብዱም ካለፈ በኋላ

"Naturally የምሰራውን፣ የምናገረውን፣ የማስበውን የማሳስበውን፣ የማስተውለውን የምሰማውን ሁሉ አንድ ሳይቀር በቀን በቀን እየመጣሁ ላንተ እነግርሃለሁ፣ አንተ notes ትወስዳለህ:: ብርሃኑ ሲመለስ ደሞ አምስታችንንም ታየናለህ:: ከዛ መጽሐፉን ትጽፋለህ:: መጽሐፉ ብርሃኑ ሲሄድ ይጀምርና ብርሃኑ ሲመለስ ያልቃል:: ማለት መጽሐፉ በሙሉ ስለብርሃኑ ነው ግን ብርሃኑ የለበትም

«ታዲያስ? ጥይት መጽሐፍ አይወጣውም? . . . ምን ዝም ብለህ ትሰትብኛለህ? ተናገር 'ንጂ»

«እሱስ ጥይት መጽሐፍ ደወጣው ነበር»

«ታዲያስ?»



«ማን ማን ይጽፈዋል?»

«አንተ ነህ!»

«እንዴት አድርጌ? ምን form እሰጠዋለሁ? በየት በኩል ጀምሬ በየት በኩል እጨርሰዋለሁ? ደሞ አማርኛ እንደ 'ንግሊዝኛ Scientific ቃላት የለው:: ስለዚህ የናንተን ዝብርቅርቅ፣ ውትብትብ ታሪክ በምን ፊሉዞፊ እሰበስበዋለሁ:: በምንስ ቃላት እቋጨዋለሁ?»

«እሱ 'ንግዲህ የራስህ ጉዳይ ነው:: እኔ ድንጋዩን፣ ጭቃውን፣ ሳሩን፣ አጣናውን አቀብልሀለሁ:: ቤቱን መሥራት ያንተ ፈንታ ነው:: ታዲያስ ተስማምተናል?»

«እንጃ»

«እንዴት 'ንጃ ?»

«እዚህ ጉዳይ ውስጥ ብርሀኑንም፣ ማሚትንም፣ ጥላሁንንም፣ ትርሲትንም እያታለልክ ትጫወትባቸዋለህ:: እኔንም ብትጫወትብኝስ? ምን መከላከያ አለኝ?»

ተንኮሉ ፊቱ ላይ ከሳቅ ጋር ይንሸራሸር ጀመረ

«እንዴት አድርጌ ነው 'ምጫወትብህ?» አለኝ

«በቀን በቀን እየመጣህ ያፈቀድህን ውሸት ብታስቀዳኝስ? በጓደኝነት ስም አደራ የተቀበልኳትን የጓደኛዬን ሚስት ለባዶ ቃላት ሸጥኩልህ ማለት'ኮ ነው»

ተንኮልና ሳቁ ከፊቱ ጠፉ:: እንደሚመዝነኝ ያህል ትኩር ብሎ አየኝ

«I respect you immensely» አለኝ:: ድምፁ ውስጥ እንደማክበርና ማድነቅ ዜማ የሰማሁ መሰለኝ:: አልገባኝም::

«Indeed» አልኩት

«እውነቴን ነው:: እንዲያውም ከራሴ በስተቀር አንተን ብቻ ሳይሆን አይቀርም የማከብረው»

«ምክንያቱስ?»

«ምክንያቱም ከሀሊናህ ጋር ሁልጊዜ አይን ለአይን እንደተያየህ ነው:: ራስህን አታታልልም:: አሁን ለምሳሌ እርግጥ ነው፡ ትርሲትን ሸጥልኝ ነው 'ምልህ:: ግን ባንተ ቦታ ሌላ ማንም ሰው ቢሆን ትርሲትን ሸጥልኝ እንደምለው አይገባውም ነበር:: ምክንያቱም እምቢ ማለት ግድ ስለማይሆንበት፣ ሆን ብሎ እንዳይገባው ያደርግና፣ ሳይገባው ይሸጥልኝ ነበር:: ገባህ 'ምልህ?»

የማከብረውን ያህል እንደሚያከብረኝ ላይ ጊዜ ትልቅ ፍንዘ

ተስማን። እንደ ክንፌ ያለ ብዝሀተ ካከበረኝ፣ በሆነ ውንሥለት ታስረው የሚኖሩ የሰው ልጆች የሚባሉት ብሮች በሙሉ ቢንቁኝ እኳን ያህል ግድ የለኝም።

ግን ክንፌ እያከበረኝም ቢሆን ሊያታልለኝ ይችላል። እንዲያውስ አክብሮኝ ሲለኝ ማታለሉ እንዳልሆነ ምን ማረጋገጫ አለኝ? «እሱን እንተወውና፤ እንደሚያታልለኝ እንዴት አውቃለሁ?» አልኳት

ሲጋራ አቀጣጠለና «ለመሆኑ አታልዬህ አውቃለሁ 'ንዴ? እኔ ላስታውስ በጭራሽ አታልዬህ አላውቅም። አንድ ነገር ልንገርህ? ብቻ አትንገራቸው 'ንዴ! ሌሎች ሰዎችንም ቢሆን የሚሉትን ያህል የማማሹን ግማሽ 'ንኳ አታልያቸው አላውቅም። በህይወቴ ውስጥ ቢበዛ ሀያ ሰው መቶ በመቶ አታልዬ ይሆናል። የቀሩትን ሰዎች ግን ግማሽ በግማሽ ነው። ግማሽ በእውነቴ ተታለው፣ ግማሽ ደሞ እያወቁ እንዳታልላቸው ፈልገው ነው። በኋላ ሲያወሩ «ክንፌ የሰራኝን ጉድ ንገራችኋለሁ?» ብለው የፈተኗቸውን ያህል ለመጨመር ለማስፋፋት፣ ለመተኮስ፣ ለመታወቅ እንዲያፈዳቸው ብለው ነው። Center of attention ለመሆን። ገባህ? ለምሳሌ ሲያወሩ «እኔ ለራሴ ምንም አልጠረጠርኩም፣ ክንፌ ብሎ ሎኬ ያሰበችውን አሰባ ኖሯል!» ወይም «እገር ጤና ብዬ እገባለሁ፣ ክንፌ ሆዬ ለኬ ... ወይም «ደሞ 'ሚገርምኽ፣ እንደምታታልለኝ አውቄ ነበር። ታዲያ እያልኩ እያየ ተታልልኩ። እያ ክንፌ! ጉደኛ ነው'ኮ» ይሉ የለ?»

እዚህ ላይ ክንፌ እውነቱን ነው። ብቻ

«አንድ ነገር ልጠይቅህ 'ስቲ?» አልኳት

«ጠይቀን»

«እኛ አሁን በመጨረሻ ያበረከትከልኝ ጊሰኩር ፕላንህ ውስጥ ተዘጋጅታ የተቀመጠች ነበረች ወይስ አሁን ነው የመጣችልህ?»

ኩት ብሎ ሳቀ «ቼዝ ጨዋታ ትችላለህ?» አለኝ

«አልችልም»

«ተማር። ትምህርቱን ይመጣበል። ወይም ፖለቲካ ውስጥ ግባ»

«ለምን?»

«እንግልህ ወጣት ነህ። ራሱን እያንቀሳቀሰ «አቤት ሽበት ባይኖርህ 'ንዴት ጥሩ ነበር!»

«ምክንያቱስ?»

«ምክንያቱም፣ አንደኛ፣ ማሚት ልብ ውስጥ በጥላሁን ፋንታ አንተን እተክልህ ነበር። ሁለተኛ፣ ብርሃኑ እስኪመለስ ድረስ ማሚትና ትርሲትን እያተለዋወጥን እንጫወታቸው ነበር። ያኔ አሰናቶችንና



አይናለምን እንደምናናፍቀው ታስታውስ የለ? ሶስተኛ፣ ብርሃኑ ሲመለስ ትርሲትን መልሰንለት ስናበቃ፣ እኔና'ንተ በቼዝ ወይም በፖለቲካ fascinating የሆነ ውድድር እንይዝ ነበር»

«እንዴት ያለ ውድድር?»

«ከማሚት ልብ ውስጥ አንተን ለማስወጣት ስንት ወር እንደሚፈጅብኝ። አቤት 'ንዴት ያለ ግሩም ጨዋታ ይሆን ነበር! ብቻ ምን ይደረግ፣ ሽበታም ሆንክ» ብሎ ትንሽ አካለበኝ

«ታዲያ ሽበታም ብሆን ምን አለበት?»

«የደረቀ ችግኝ ብትተክለው ይፀድቃል? ማሚት ልብ ውስጥም ሽበት ያለው ሰው በጭራሽ ስር ሊሰድ አይችልም»

«ምክንያቱስ?»

«ማሚት እርጅና በጣም ትፈራለች»

ሁለታችንም ዝም አልን። ክንፌ የጭስ ቀለበቶች አከታትሎ አወጣና ፍፁም እስኪሰወሩ ተመለከታቸው። ፊቱ ላይ እንደ ጥላ በጥተኛ የሆነ ሀዘን አረፈል። ለራሱ እንደሚያወራ ያህል ዝግ ባለ ድምፅ

«ትኩሳት ይሁት ወይም በሌላ ምክንያት መጥፎ ህልም ስታይ የሚመጣባት ያው ህልም ነው። እርጅታ ጭርጭስ ብላ መንገድ ዳር ቁጭ ብላለች። ብቻዋን ናት። ከሰው ጋር ማውራት ትፈልጋለች። ግን ማንም ሰው አይፈልጋትም። ንግግር እንደውሀ ይጠማታል። እሷን የሚመስል ወጣት ልጅ በአጠገቧ ሲያልፍ «የክንፌ ወንድም ነህ? ክንፌ'ኮ የኔ ፍቅር ነው» ልትለው እጇን ትከፍታለች። ግን ኩኩኩ ብቻ ነው ልትል 'ምትችለው «ቀይ!» ብላ ሙሃ ትነቃለች። ጩኸቷ ጩኸት አይደለም፣ የታላቅ ፍርሃት ቁራጭ ነው። ትጠመጠምብኛለች። «ክንፌ! ክንፌ! ክንፌ!» ትለኛለች። ግንባሯ ላይና ጡቶቿ መሀል ላብ ይንቆረቆራል። ትንፋሿ ይቆራረጣል። እቅፌ አባብላታለሁ። ህልሙ ትቷት ሲበር በግድ እየተነፈሰች «ክንፍዬ! ልክ ነገ ላረጅ ዛሬ ልትገድለኝ አትችልም?» ትለኛለች። ፍርሀቱ እንዲጎዳ እያቃጎቀች፣ ለጥቂት ደቂቃ እንደ እብድ ትሆናለች «ክንፍዬ! የተማርከ ነህ፣ ንገረኝ 'ስቲ። 'ራሴን ለመግደል ብፈልግ ከሁሉ ቀላል መንገድ የቱ ነው?» ትላለች። ሳያን ጊዜ ጠረማምሁላት እየሳምኳት «እንደሱ አትበይ» ስላት «አሁን ራሴን አልገልም'ኮ። በኋላ። አንተ ስትተወኝ። ወጣቶቹ ሁሉ ሲተውኝ። ነገ ሳረጅ ዛሬ» ትላለች። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ፍርሀቷን አብረን እናባርረዋለን። እንቅልፏ ጤናውን መልሶ ያገኛል»

ክንፌ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደኔ እየተመለከተ፣ ለመሳቅ እየሞከረ «እና ሽበትህ እርጅናን ስለሚያሳስባት በፍፁም ልትወድህ አትችልም» አለኝ

«ለዚህ ነዋ ከወጣቶች ጋር ብቻ 'ምትተኛው?» አልኩት:: በጭንቅላቱ አዎን አለኝ:: ከዚህ በፊት በጭራሽ ያላስብኩት ነገር አሁን ተገልጾልኝ፣ ግማሽ ለራሴ ግማሽ ለከንፈ መናገር ጀመርኩ

«እና ብዙ ወጣት 'ምትቀያይረው ከእርጅናው ለመሸሽ ነዋ! ባንድ በኩል ከወጣትነታቸው የሚያጋሯት እንደሚመስላት አይነት ነው:: ወጣትነቱ እንደ ሉሚ ሽታ ወደሷ የሚተላለፍ እንደሚመስላት ያህል:: በሌላ በኩል ደሞ ወጣቶቹ ከተሻሙዋት ከተንገበገቡላት እሷ ራሷ ወጣት መሆኗን ያረጋግጥላታል:: ስለዚህ ብርሃኑ. . .»

ትኩር ብሎ ከንፈን 'ያየሁት፣ ከበፊት ይበልጥ እንዲያዳምጠኝና ጥያቄዬን እንዲመልስልኝ እየፈለግኩ

«እንግዲያው አንተ ብርሀኑን ከልቧ ለማስወጣት የምትፈልገው ቅናት ስለያዘህ አይደለማ?» አልኩት

ዝም ብሎ አየኝ

«እሱ በጭራሽ እንደማይፈልጋት ስላወቅክ ነው:: ማሚት እስካሁን የፈለገችውን ወንድ ሁሉ ታገኝ ስለነበረ፣ እሱ ሲያቅታት «ማርጀት ጀመርኩ» ብላ መጥፎ ሀልሟን ሳትተኛም በውን ልታየው ትጀምራለች:: ተስ ኢያለች ጨርሳ ታብዳለች:: ወይም በሁለት ሶስት አመት ውስጥ አንድ ሁለት ኢያለ ሌሎች ወጣቶች እምቢ ያሏት 'ንደሆነ፣ ደንግጣ ራሷን ትገድላለች:: ወይም. . .»

«እንደሱ አትበል!» አለኝ ፊቱን እያጠቆረ

«ይቅርታ!» አልኩት

«እንለፈው» አለኝና አሁንም ትንሽ ለመሳቅ እየሞከረ «መቼስ ደራሲ መሆንህ አይቀርም፣ አንድ ነገር ልንገርህ:: ማሚትን «ብርሃኑ ከመሄዱ በፊት የመሰናበቻ እሱንና ትርሲትን ቅዳሜ ማታ እኔና 'ንቺ ናይት ክለብ ብንጋብዛቸው ምን ይመስልሻል?» አልኳት:: ቢያስደንባት አንድ ነገር ነው ብዬ ነው:: ታውቃለህ፣ ቤቷ ሲመጣ አሽሽሙቿን ሁሉ ያስደንባል፣ ያሜውታል:: ያሳስቃል:: ግን ከሷ ጋር ደንሶ አያውቅም:: ተነጋግሮም አያውቅም::

«ትርሲትን ነገርኳት:: በደስታ ዘለለች:: በኋላ ብርሃኑን አገኘሁትና ነገርኩት:: ምን አለኝ መሰለህ?»

«ምን አለህ?»

«በጣም አመሰግናለሁ:: ግን ከማሚት ጋር አንድነት ለመሄድና ለመደሰት my principles won't allow. አንተ ብቻህን ከጋበዝከኝ ግን በደስታ እመጣለሁ with or without ትርሲት» አለኝ እልህለሁ

«ተቀየምከው?»



«ምን እቀየመዋለሁ? ማሚትን እንደ'ኔ አያውቃት:: እንዴ! እንዴ! እንዴ!»

«ምነው?»

«እስረሳኸኝ 'ኮ! ታዲያስ፣ ውላችን ይርጋ ወይስ ትሸሩዋለህ?» ሀዘኑ ከፊቱ መሸሽ ጀምሯል

«ይርጋ!» አልኩት

«Shake on it» አለኝ:: ተጨባበጥን::

ተንኮሉና ቀልዱ ፊቱ ላይ መታየት እየጀመረ «እንመለስ ወደ በረሀችን» አለና፣ ባንድ እጁ ቢራውን እየጨለጠ በሌላው ቦዩን ጠራው:: እኔ ልከፍል ቦርሳዬን ሳወጣ በጁ ከለከለኝና የራሱን ቦርሳ አወጣ:: በእንግሊዝኛ

«እኔን ልትጋብዘኝ?» አልኩት እየሳኩ

«ታዲያ ማነው 'ሚከፍለው? እኔ መሰልኩህ? ሀብቴ'ኮ ነው» አለኝ

«ሀብቴ?»

«አዎን ሀብቴ:: ከካሳ ወልደአማኑኤል ጭፍራዎች አንዱ»

«እንዴት?» ስለው፣ ሀብቴ ቢሮ ሄዶ እንዴት ስለ ብርሃኑ ሽጉጥ እንዳስጠነቀቀውና እንዴት መቶ ሃያ ብር እንደተበደረው እየነገረኝ እየሳቅን ወደ ደጃች ውቤ ሰፈር አመራን::

ጎርጊስ ሀውልት ስንደርስ፣ እዛ አቶብስ ማቆሚያው ሥፈር ቆመው ወንድ 'ሚጠብቁትን ትንንሽ የአሥራ አራት፣ የአስራ ሶስት አመት ሽርሙጦች እየሁና የጥላሁንና የነሱን ዝምድና እያስታወስኩ፣ ከንፈ ስለዚህ ጉዳይ ያውቅ እንደሆን ለማወቅ

«አንድ ብር ካለህ እንዷን ሀፃን ሞልተህ ና» አልኩት

«ሀፃን ጠፋና ጨብጦ ልመና እነኩን ልሂድ?» አለኝ

ስለ ጥላሁንና ስለነሱ ቢያውቅ ኖሮ «አ ልጄ! አባባ ጥላሁን ልጆቼን በጳህብኝ ብለው ይገድሉኛል» ወይም እንዲህ ዓይነት ነገር ይለኝ ነበር:: መንገዳችንን ቀጠልን::

«By the way, አዲስ አበባ ከርከር ገብቷል እሱ:: እየተጠነቀቅክ ብዳ» አልኩት

«እንዴት ነው 'ምጠነቀቀው?»

«ፈረንጆች ናቸው እሱ ያመጡት:: ስለዚህ ፈረንጅ 'ሚበዳትን ሴት አለመብዳት ነዋ»

«ኢድ ባክህ! ምን ፈረንጅ ነው? ክርክር የመጣው ከጎንደር። የጎንደር ሀኪም ክርክር ማከም ስልችት አለው። ስለዚህ አንድ ሰው ክርክር ያዘኝ ሲለው፣ ልብሱን በሙሉ ያስወልቅና፣ ጠረጴዛ ላይ አውጥቶ

«ዝለል» ይለዋል። ሰውየው ይዘላል። ሐኪሙ «በሀይል ዝለል» ይለዋል። በሀይል ሲዘል የተከረከረው የቁላው ጫፍ እንደሾላ ይረግፍና መሬት ላይ ይንከባለላል

ሐኪሙ «ልብስህን ልበስ» ይልና፣ የረገፈውን የቁላውን ጫፍ አንስቶ በማይክሮስኮፕ ከመረመረው በኋላ እንዲህ ይላል

«እውነትህን ነው ክርክር ነው የያዘህ። ይህን ጫፍህን በወረቀት ልጠቅልልህ ወይስ በገንዘብ ቦርሳህ ይዘኸው ትሄዳለህ?»

ባለ ክርክሩ «ምነው ድክተር? ያድኑይ ዘንድ ነበር'ኮ እርሶ ዘንድ የመጣሁ?» ሲለው

«ታዲያ አሁን በሙጫ ላጣብቅልህ?» ይለዋል

ሰውየው ይናደድና «እምቢዮ! ቁላዬን ስጠይ!» ብሎ ጫፉን መንጭቆ ይወስድና

«ባይሆን ለጠንቋይ እሸጠዋለሁ» እያለ እያጉረመረመ ይሄዳል

እንዱ ወታደር ታዲያ ይኸ ክርክር ያዘውና ሀኪም ቤት መሄድ ፈርቶ ይሁን ገንዘብ አጥሮት፣ አልሄደም

አንድ ቀን ወታደሮች ተሰልፈው ጅምናስቲክ ሲሰሩ ሲዘሉ፣ የዚህ ወቴ የቁላው ጫፍ ተበጥሶ መሬት ተንከባሏል

«እግ! ጫፌ ወደቀች!» አለና ብድግ አርጎ ኪሱ ክቶ ጅምናስቲኩን ቀጠለ

ግን አስተማሪው ጎንበስ ሲል አይቶት ኖሮ

«በቃ አሳርፍ» አለና ወታደሮቹ ቆሙ። እዚህ ወታደር ጋ መጥቶ

«ለምን ነበር ጎንበስ ያልከው?» አለው

«የቁላዬ ጫፍ ወድቆብይ»

«በቃ? ለቁላህ ጫፍ ነበር?»

«አዎን» አስተማሪው ተናደደ «ስሙ ሁላችሁም!» አሉ «ምንም ነገር ቢሆን በጅምናስቲክ ሰዓት እቃ ለማንሳት ጎንበስ ማለት ክልክል ነው። ገባችሁ? ምንም ቢወድቅባችሁ!»

«የቁላዬ ጫፍ 'ኮ ነው እያ!» አለ ወታደሩ

«ዝም በል! በጂምናስቲክ ጊዜ እንኳን የቁላችሁ ጫፍ ይቅርና፣ ክርክር ስሙኒ ራሷ ከኪሳችሁ ብትወድቅ ጎምበስ ብሎ ማንሳት ክልክል



ነው። ልብ አድርጉ!» ብሏቸው ጂምናስቲካቸውን ቀጠሉ።

እንዲህ እየተጫወትን ማሚት እሸሩሩ ቤት ደረስን። መዝናቀው አይዘፍንም። ሰአት ብናይ ገና አምስት ሰዓት ነው። መጋረጃውን ገልጠን እንገባለን፣ ለካ ቤቱ ደረበሻል። ባንድ በኩል ጥላሁን በስስት ሰው ተይዞ «ልተቁን እጨፈልቃቸዋለሁ» እያለ ይጋበዛል። በሌላ በኩል አንድ ረጃርም ቀዬን ሰውዬ እንደዚሁ ተይዞ ይፍጨረጨራል። ከንፈ.

«እንግዲህ ጥላሁንን 'ምትችለው አንተ ነህ። ሂድና አስታግሰው ብርሃኑ 'ስኪሄድ ድረስ እዚህ ቤት ረብሻ አልፈልግም» አለኝ። እየሁት። ምላሱን አጠጣብኝ።

ሳቄን እንደምንም ያዝኩት።

ሄጄ ጥላሁን ፊት ቆምኩ። ስካር ባቀላቸው ትልልቅ አይኖቹ አየኝ። መፍጨርጨሩን ተወ። የያዙትን ሰዎች «ልቀቁት» አልኳቸው። አመኑቱ።

«ልቀቁት» አልኳቸው። ለቀቁት። እጁን ከንዱ ጋ ያዝኩ ወደ ውጭ ወሰድኩት። በቁጣ

«መቼ ነው 'ንግዲህ አንተ 'ምታድገው?» አልኩት

«እሱ'ኮ ነው ነገር የፈለገኝ» አለ

«ቢፈልግህስ ለምን አትታገሰውም? ጎበዝ መሆንህን ለማሳየት ነው? ትብዝናህን ሁሉ ሰው ያውቅልሀል። ታዲያ ለምን በሄድክበት ሰዎችን ሰላም ትነሳቸዋለህ? እነሱ እዚህ 'ሚመጡት ችግራቸውን ለመርሳት ነው 'ንጂ አንተን እያዩ ለመደንገጥ አይደለም»

ዝም አለኝ። በልቤ አሮጌ አልኩ። ካሁን ካሁን በአንድ ቡክስ እንከባለሉን ወደ ረብሻው ይመለሳል እያልኩ ስፈራ ነበር

«አሁን በጥንቃቄ ስማኝ» አልኩት

«እንኳን ከአንድ ሰውና ከአምስት ሰውም ቡክስና ቴስታ ብትማታ ምንም ፍርሀት እንደማይሰማህ አውቃለሁ። ስለዚህ ይህን ሰውዬ ዝብተህ ብትደበድበው ትብዝና እንዳልሆነ እኔና አንተ እናውቃለን። እውነት ጎበዝ ከሆንክ፣ እስቲ አሁን ግባና ቤቱቹ ሁሉ እያዩህ ሰውየውን ይቅርታ ለምነው! በላ!» እየገፋፋሁ ወደ መጠጥ ቤቱ አስገባሁት። ሰተት ብሎ ሄዶ ሰውየውን ጨብጠውና ጮክ ብሎ

«የኔ ጥፋት ነበር ይመስለኛል ይቅርታ» አለው

ሰውየው «እረ ጥፋቱስ የኔ ነው» አለ

ታረቁ። ከንፈ ይህንን እያየ «አንተ ጠማማ» አለኝ። ጥላሁን ሰውየውን ቢራ ጋበዘው። ሰውየው በተራው ጥላሁንን ጋበዘውና ሄስበጎ

ክፍሉ ደህና'ደር ብሎ ጨብጦት ወጣ፡፡

ክፍሉ ደህና'ደር ብሎ ጨብጦት ወጣ፡፡ ብርሃኑና ትርሲት እንደተቃቀፉ፣

ጥላሁንና ክንፈ፣ እኔ፣ ብርሃኑና ትርሲት እንደተቃቀፉ፣ ጥላሁንና ክንፈ ባንኮኒው ጋ ቆመን ስናወራ፣ እንደ እምስታችንም እንደልማዳችን ባንኮኒው ጋ ቆመን ስናወራ፣ እንደ በጣም ግዙፍ የሆነ ባለመነፅር አሜሪካዊ ከውስጠኛው ክፍል ወጣና ብርሃኑና ክንፈን

«Hello there » አላቸው

«Hello, Mr Hutchins» አሉት

ትንሽ አወሩትና «See you» ብሏቸው ወጥቶ ሄደ

ክንፈ «ታውቁት የለ?» አለን፡፡ እናውቀውም ስንለው

«እንዴት አታውቁትም? Mr Jim Hutchins!»

ጥላሁን «እናውቅም አልንህ!» አለው

«ሀሙስ ሀሙስ ማታ ወደ አምስት ሰዓት ላይ ወደ ቸርቺል ጎዳና ብቅ በሉ፡፡ ታገኙታላችሁ፡፡ የቸርቺል ጎዳና ሸርሙጦች ስሙን ማን መሰላችሁ 'ማሉት? «ግማችን» ጂም ሀቺንስ ለማለት ነው 'ንግዲህ፡፡ እንዲት ጂፕ መኪና አለችው፡፡ ሀሙስ ሀሙስ ማታ ልክ አምስት ሰዓት ሲሆን ጂፑን ዜሮ ማርሽ ያስገባና ቸርቺል ጎዳናን መውረድ ይጀምራል፡፡ ሸርሙጦቹ በር ጋ ቆሞ «ግማችን መጡ» ተባብለው ወደየበራቸው ይንጋጋሉ፡፡ ይመለከቱታል፡፡ እሱ መኪና ውስጥ ቁጭ እንዳለ ሎሆ

«እምስ አለ?» ይላቸዋል

ታውቃላችሁ 'ንግዲህ፣ ማንም ሰው እንዲህ ቢል ወይ ይስቁበታል ወይ ዝም ይሉታል፡፡ እሱን ግን «አዎን አለ» ይሉታል

«ይገማል?» ብሎ ይጠይቃቸዋል

«ሌላ ሰው እንዲህ ቢላቸው፣ አንተ ቡሽቲ! የ'ናትህ እምስ ነው 'ንጂ የኛ እምስ ይገማል?» ወይም «አንተ ለከታፍ ቡሽቲ! በየሰአቱ እየተበዳህ ጣልያኑና አረቡ እያንቆረቆሩብህ ቂጥህን ሳትታጠበው እንደወንድ ሱሪ እየታጠክ ትገማለህ 'ንጂ እኛ ነን 'ምንገማው?» ይሉታል፡፡ መፈጠሩን ያስጠሉታል

Mr Jim Hutchinsን ግን «ይገማል?» ሲላቸው

«አይገማም ታጥቧል፣ ሽቶ ተርከፍክፎበታል» ይሉታል

«ኢቹ! አልፈልግም እንግዲያው!» ይላቸውና መኪናውን አስነስቶ ቁልቁል ይቀጥላል «ቀጥሎ 'ሚገኘው የሸርሙጦች ተርታ ሲደርስ እንደዚሁ ይጠይቃል

«እምስ አለ?»



«አዎን አለ»

«ይገማል?»

«አይገማም ኧረ! ታጥቧል»

«ኢቹ! አልፈልግም እንግዲያው!»

ግን ከ'ነሱ አንዷ ይገማል ወይ ብሎ ሲጠይቅ

«ትንሽ ትንሽ» ትለውና ከመኪናው ዘሎ ቤቷ ይገባል፡፡ ወይም «ይገማል?» ሲል «መጥተው ያሸቱት» ትለዋለች፡፡ በቃ ይገባና በድቶ አስር ብር ከፍሎ ይሄዳል

ታዲያ ሸርሙጦች በቡና ሰአት ሲቀልዱ

«ባሬስ ማንቲም ጠፋ፣ ሚስተር ግማችንን ገምቼ ልጠብቃቸው መሰለኝ ይላሉ

ክንፈ ይህን ሁሉ ሲነግረን፣ የወንድና የሴት ድምፅ እየቀያየረ፣ ልክ እነሱ ሲነጋገሩ የምንሰማ እየመሰለን በሳቅ እንንከተከታለን፡፡ እሱ ግን ሳቅ የሚሏት ነገር ፊቱም ላይ አትታይ፣ ድምጹም ውስጥ አትሰማ፡፡ ልክ ትልቅ ቁም ነገር እንደሚነግረን ያህል ነበር፡፡ ይሄ የሱ አለመሳቅ የባሰውን ያስቀናል፡፡ ብዙ ከሳቅን በኋላ ብርሃኑ

«አንተ ውሸታም! አማርኛ የት ያውቅና ነው?» አለው

«ባያውቅስ!» አለ ክንፈ፡፡ የባሰውን በሳቅ ፈረስን

ሳቃችን ቀዝቀዝ ሲል ክንፈ ቀጠለ

«ሚስቱ ቆንጆ ብጤ ነች፡፡ Blonde ነች፡፡ አበሰልኳትና፣ እሱ ልክ በአምስት ሰዓት የሚገማ እምስ ፍለጋ እንደሚሄድ አውቄ ሃሙስ ማታ በአራት ሰአት ቤቷ ሄድኩ፡፡ ስስማት ሳሻሻት ቆየሁና፣ ልብሳችንን አውልቀን ልንጀምር ስንል

'By the way, what is your opinion about bodily odor?' አለችኝ»

እኛ ስንስቅ ክንፈ ለትርሲት ተረጎመላትና አብረን መሳቅ ቀጠልን፡፡ አሁንም ብዙ ከሳቅን በኋላ ብርሃኑ


«አንተ ውሸታም! ሚስት መች አገባና ነው?» አለው

ክንፈ «ባያገባስ! አንተ ምን አገባህ?» አለውና ገና ሳቃችንን ነንጨርስ

«ይልቅ ቆንጆ ሙዚቃ ጀመረልህ፡፡ የሰው ወሬ ከምታበላሽ ትርሲትን አስደንሳት» ብሎ ሁለቱን ወደ ወለሉ መሀል በኩል ገፋቸው፡፡

ማማት ከየት እንደመጣች 'ንጃ፣ አጠገባችን ቆማ አየሁዋት፡፡ የሀበሻ ልብስ ለብሳ፣ ነጭ ጉትቻ አንጠልጥላ፣ ቀይ ሽጋ ፊቷ ሳቅ እያለ፣ ትልልቅ አይኖቿን ወደ ጥላሁን እያነሳች

Meysor Bro
t.me/BooksandYou



ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር በ1950ዎቹ

እገሩ ማንም የለበት
እልቦው ላይ እልቦ ተቆልሉበት
ባዶ ላይ ባዶ ተደራርቦበት
ነይ'ኮ ነይ'ኮ ልበልሽ እንኮኮ
ተይ'ኮ ተይ'ኮ እትሁኚ ችኮ

ወደ ምዕራብ ፀሃይ
ወደ ምስራቅ ጥላ
በመካከላቸው
ተደብቋል እምና

እነ ማቱሳላ
እነ አብርሃም
ጠጡ ሁቲሁላ
እድሜ የሚያረዝም
ምስጢሩን ለማንም
አልተናገሩም
ጠጥተው ዝም ዝም
ሞተው ዝም ዝም

22 ብር